የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ለምክር አገልግሎት ግዥ

(የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ)

የሚውል መደበኛ የጨረታ ሰነድ

ብሔራዊ ግልፅ ጨረታ

የግዥው ዓይነት፡- (የማማከር አገልግሎቶች አጠቃላይ መግለጫ ይግባ)

የግዥው መለያ ቁጥር፡- (የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ)

የፕሮጀክቱ ስም፡- (የፕሮጀክት ስም ይግባ)

የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው የወጣበት ቀን:- (ቀን ይግባ)

ባህር ዳር፣____ወር_____ዓ.ም.

የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ

ማውጫ

ምዕራፍ 1: የጨረታ ሥነ-ሥርዓቶች I

ክፍል 1: የአማካሪዎች መመሪያ I

ክፍል 2፡ የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠነድ XL

ክፍል 3፡ የግምገማ ዘዴና መስፈርቶች III

ክፍል 4: የጨረታ ቅጾች IX

ክፍል 5: በጨረታ መሳተፍ የሚችሉ ሀገራት (ብቁ ሀገሮች) V

ምዕራፍ 2: የፍላጎት መግለጫ VI

ክፍል 6: ቢ.ጋር VI

ምዕራፍ 3: ውል 2

ክፍል 7: አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች VII

ክፍል 8: የውሉ ልዩ ሁኔታዎች VIII

ክፍል 9: የውል ቅጾች 5

ምዕራፍ 1: የጨረታ ሥነ-ሥርዓቶች

ክፍል 1: የአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ

ማውጫ

ሀ. ጠቅላላ II

1. መግቢያ II
2. የገንዘብ ምንጭ III
3. ማጭበርበር፣ ሙስናና አቤቱታ የሚታይበት ሥርዓት IV
4. ሀጋዊ (ብቁ) አማካሪዎች VI
5. የጥቅም ግጭት VII

ለ. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ይዘት IX

6. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ IX
7. በመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ የሚቀርቡ የጽሁፍ ጥያቄዎች/ ማብራሪያዎች X
8. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነዶችን ስለማሻሻል XI
9. የቅድመ መወዳደሪያ ሀሳብ ኮንፈረንስ/ስብሰባ/ XI

ሐ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አዘገጃጀት XII

10. በጨረታ የመሳተፍ ወጪ XII
11. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ቋንቋ XII
12. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ዝግጅት XIII
13. ሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበር XIII
14. የአማካሪ ሙያዊ ብቃትና አቅም XIV
15. የአማካሪው የፋይናንስ አቋም XV
16. የአማካሪው የቴክኒክ ብቃት፤ ክህሎትና የሥራ ልምድ XV
17. ባለሙያ ሰራተኞች XVI
18. የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ቅፅ እና ይዘት XVII
19. የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ ቅጽ እና ይዘት XX
20. የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ የገንዘብ አይነት እና ክፍያ XXII
21. የጨረታ የመወዳደሪ ሀሳብ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ XXII
22. የጨረታ ዋስትና XXII
23. የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ ቅፅና አቀራረብ XXIV

መ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አቀራረብና አከፋፈት XXIV

24. የጨረታ መወዳደሪ ሀሳብ አቀራረብ ..... Error! Bookmark not defined.
25. የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ የማስረከቢያ ቀነ-ገደብ XXIV
26. ዘግይተው የሚቀርቡ የመወዳደሪያ ሀሳቦች XXIV

27. ከጨረታው መውጣት፣ መተካትና የጨረታ የመወዳሪያ ሀሳብ ማሻሻል XXIV
28. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አከፋፈት XXV

ሠ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ መገምገምና ማነጻፀር XXVI

29. ምስጢራዊነት XXVI
30. በጨረታው መወዳደሪያ ሀሳብ ላይ ማብራሪያ ስለመጠየቅ XXVI
31. የጨረታው መወዳደሪያ ሀሳብ ምሉዕነት (ብቁነት) XXVII
32. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ያለመጣጣምና ግድፈቶች XXVII
33. አጠራጣሪ የጨረታ ዋጋዎችና የስሌት ስህተቶች XXVIII
34. ልዩ አስተያየት (MARGIN OF PREFERENCE) XXIX
35. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ XXIX
36. የመወዳደሪያ ሀሳብ ህጋዊነት፣ የሙያ፣ የቴክኒክና የፋይናንስ ተቀባይነት XXX
37. የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ XXXII
38. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ አከፋፈት XXXIII
39. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ XXXIV
40. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ንጽጽር XXXV
41. ድርድሮች XXXV
42. የድህረ ብቃት ግምገማ XXXVI
43. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ መቀበል ወይም አለመቀበል XXXVII
44. በድጋሚ የጨረታ ማስታወቂያ ስለማውጣት XXXVII

ረ. ውል ስለመፈፀም XXXVII

45. አሸናፊ አማካሪን የመምረጫ መስፈርቶች XXXVII
46. ከውል በፊት የግሹውን መጠን ስለመለወጥ XXXVIII
47. የጨረታ ውጤትና አሸናፊ አማካሪን ስለማሳወቅ XXXVIII
48. የውል አፈራረም XXXIX
49. የውል ማስከበሪያ ዋስትና XXXIX

ክፍል አንደ የአማካሪዎች መመሪያ

ሀ. ጠቅላላ

1. መግቢያ

1.1 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ (ዝ.ጨ.መ.ሰ) የተመለከተው የግዥ ፈጻሚ መ/ቤትመ/ቤት ለዚህ የግዥ ሂደት ተገቢውን የውል ተግባራት የሚያከናውን ባለሥልጣን ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት ግዥዎች ላይ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው በወጡት ህጐች ተገዢ ይሆናል፡፡ ይህ ግዥ ፈጻሚ መ/ቤት የምክር አገልገሎት ከሚሰጡ ተቋማት (አማካሪዎች) ውል የመዋዋል ሥልጣን እና ኃላፊነት አለው፡፡ በዚህ መሠረት ይህ የግዥ ሂደት በቅርቡ በወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠነዱ በተመለከተው የግዥ ዘዴ መሠረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

1.2 ይህን የማወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ በማውጣት ግዥ ፈሚው መ/ቤት የተመረጡ አማካሪ ተቋማት/ድርጅቶች (ከዚህ በኋላ “አማካሪ” ተብለው የሚጠሩት) በዝ.ጨ.መ.ሰ. ውስጥ በተጠቀሱት አጠቃላይ መግለጫዎች መሠረት የማማከር አገልግሎት እንዲሰጡ የቴክኒክ እና የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳቦች ለየብቻ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል፡፡ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ለሚካሄዱ የውል ድርድሮችና በመጨረመሻም ከተመረጡ አማካሪዎች ጋር ውል ለመፈራረም መሠረት ይሆናል፡፡ በዚህ የግዥ ሂደት የሚሰጡት የማማከር አገልግሎቶች በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ውስጥ በቀረቡት መረጃዎች መሠረት በክፍል 6 ቢ.ጋር ላይ በተለይ ተጠቅሷል፡፡

1.3 ለጨረታው የተጋበዙ አማካሪዎች ማቅረብ የሚችሉት የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አንድ ብቻ ነው፡፡ አማካሪዎች ከአንድ በላይ የመወደሪያ ሀሳብ ካቀረቡ ወይም ከተሳተፉ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ ውድቅ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በንዑስ አማካሪነት፣ በግል ባለሙያነት ጨምሮ ከአንድ በላይ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ላይ ከመሳተፍ አያግድም፡፡

1.4 የዚህ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ሰነድ የግዥ መለያና የሎት (lot) ብዛት በጨረታው ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ ተመልክቷል፡፡ ለእያንዳንዱ ሎት (lot) የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲቀርብ በሚጠየቅበት ጊዜ አማካሪዎች የመወዳደሪያ ሀሳብ ሰነዳቸውን ለአንድ ሎት (lot)፣ ለበርካታ ሎቶች (lots) ወይም ለሁሉም ሎቶች (lots) ማቅረብ ይችላሉ፡፡ እያንዳንዱ ሎት (lot) የራሱ የሆነ ውል የሚኖረው ሲሆን በአንድ ሎት (lot) ውስጥ የተጠቀሰውን ቁጥር መከፋፈል ግን አይቻልም፡፡ አማካሪዎች ለሁሉም ሎቶች (lots) ወይም

በእያንዳንዱ ሎት (lot) ውስጥ የተጠቀሰውን ቁጥር በሙሉ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

1.5 ክፍል 1 የአማካሪዎች መመሪያ አማካሪዎች የመወዳደሪያ ሀሳብ ሰነዳቸውን ሲያዘጋጁ እንዲያግዝ ታስቦ የተዘጋጀ እንጂ የውል መ/ቤት አይደለም፡፡

1.6 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማንኛውንም የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የመቀበል ግዴታ የለበትም፡፡ እንዲሁም የመምረጥ ሂደቱ ተጠናቆ ጨረታው ለአሸናፊ ከመሰጠቱ ወይም ከመገለፁ በፊት በማናቸውም ጊዜ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ በዚህ ምክንያት ምንም አይነት ከአማካሪዎች የይገባኛል ጥያቄ አይነሳበትም፡፡

1.7 የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ያቀረበውን የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ ጥያቄ ተከትሎ ለሚቀርቡት የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቦች ባለቤት ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት አማካሪዎች ለግዥ ፈፃሚ መ/ቤትያቀረቡት የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ዘግይተው ከቀረቡ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቦች በስተቀር አይመለስላቸውም፡፡

1.8 አማካሪዎች በግል የሚያካሂዳቸው የሽያጭ ሁኔታዎች እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ይህ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ሲያቀርቡ ግን ይህን የግዥ ሂደት ሙሉ በሙሉ እና ያለምንም ገደብ የሚፈፅሙት የቀረበውን የመወዳደሪያ ሀሳብ ጥያቄ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አማካሪዎች የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን ከማቅረባቸው በፊት በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተመለከቱትን መመሪያዎች፣ ቅፆች፣ የውል ሁኔታዎችና የፍላጐት ዝርዝሮች በጥንቃቄ ሊመረምሩዋቸው ይገባል፡፡ በጨረታ ሰነዱ ላይ የተጠየቁት መረጃዎችና ሰነዶች ተሟልተው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ካልቀረቡ የመወዳደሪያ ሀሳባቸው ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል፡፡ የጨረታ ሰነዱን አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም ቅሬታ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

1.9 በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እና በአማካሪዎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን ወይም ኤሌክትሮኒክ ያልሆነ የተከተለ ይሆናል፡፡

2. የግንዘብ ምንጭ

2.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በክፍል 6 ለተመለከቱት የአገልግሎት ፍላጐቶች ግዥ የሚውል የፀደቀ (የተፈቀደ) በጀት አለው፡፡ በዚሁ የመወዳደሪያ ሀሳብ በተመለከተው መሰረት ከአማካሪው ጋር ውል በማሰር የአገልግሎት ግዥውን ለመፈፀም አስቧል፡፡

2.2 ክፍያ የሚፈፀመው በቀጥታ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤትሲሆን፣ አማካሪው ክፍያውን የሚያገኘው ከግዥ ፈፃሚ መ/ቤትጋር በገባው የውል ቃልኮችንና ሁኔታዎች መሠረት ይሆናል፡፡

3. **ማጭበርበር፣ ሙስናና አቤቱታና ይግባኝ የሚታይበት ሥርዓት**

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት (ካሁን በኋላ "መንግሥት" እየተባለ የሚጠራው) በአብክመ ገንዘብ ቢሮ (ካሁን በኋላ "ቢሮ" እየተባለ የሚጠራው) የሚወክል ሲሆን፣ ግዥ ፈፃሚ አካላትና አማካሪዎች በግዥ ሂደት ወቅትና በውሎች አፈፃፀም ወቅት የሥነ-ምግባር ደንቦችን በከፍተኛ ደረጃ እንዲያከብሩ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በዚሁ ፖሊሲ መሠረት መንግሥት፡-

(ሀ) ከላይ በአንቀፅ 3 ላይ ለተመለከተው አፈፃፀም ሲባል ለሚከተሉት ቃላት ቀጥሎ የተመለከተውን ፍች ይሰጣል፡፡

(i) **"የሙስና ድርጊት"** ማለት የአንድን መንግሥት ባለሥልጣን በግዥ ሂደት ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለማባበል (ለማማለል) በማሰብ ማንኛውም ዋጋ ያለው ነገር መስጠት፣ ወይንም ለመስጠት ማግባባት ማለት ነው፡፡

(ii) **"የማጭበርበር ድርጊት"** ማለት ያልተገባን የገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ግዴታን ላለመወጣት በማሰብ የግዥ ሂደቱንና የውል አፈፃፀሙን በሚጐዳ መልኩ ሀቁን በመለወጥና አዛብቶ በማቅረብ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የሚፈፀም ድርጊት ነው፡፡

(iii) **"የመመሳጠር ድርጊት"** ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ አማካሪዎች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እያወቀም ሆነ ሳያውቀው በመመሳጠር ውድድር አልባና ተገቢ ያልሆነ ዋጋን መፍጠር ማለት ነው፡፡

(iv) **"የማስገደድ ድርጊት"** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሰዎችን መ/ቤት ና ንብረት በመጉዳትና ለመጉዳት በማስፈራራት በግዥ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ወይም የውል አፈፃፀም ማዛባት ማለት ነው፡፡

(v) "የመግታት (የማደናቀፍ) ድርጊት" ማለት

- ለምርመራ ጉዳይ በፌዴራል ስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ በፌዴራል ዋና ኦዲተር በገንዘብ ቢሮ ወይም በኦዲተሮች የሚፈለጉ መረጃዎችን ሆን ተብሎ በማጥፋት፣ በማስፈራራትና ጉዳት በማድረስ መረጃዎችን እንዳይታወቁ በማድረግ፣ የምርመራ ሂደቶችን መግታት ወይም ማደናቀፍ ማለት ነው፡፡

- የዚህ መደበኛ የጨረታ ሰነድ መ/ቤት የሆነው የአማካሪዎች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 3.5 ላይ የተመለከቱትን የቁጥጥርና የኦዲት ሥራዎች ማደናቀፍ ከመግታት ድርጊት ጋር አብሮ የሚታይ ይሆናል፡፡

(ለ) በአሸናፊነት የተመረጡ አማካሪዎች በራሳቸው ወይም በተወካያቸው አማካኝነት የሙስናና የማጭበርበር፣ የማሴር፣የማስገደድና የመግታት/ማደናቀፍ ድርጊት በጨረታው ሂደት ወቅት ከፊፀሙ ከጨረታው ይሰረዛሉ፡፡

(ሐ) አማካሪዎች በማንኛውም በውድድሩ ጊዜ ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በሙስና፣ በማጭበርበር፣ በመመሳጠር፣ በማስገደድና በማደናቀፍ ተግባር ተካፋይ መሆናቸው ከተረጋገጠ ለተወሰነ የጊዜ ገደብ በመንግሥት ግዥ ተካፋይ እንዳይሆኑ ይታገዳሉ፡፡ የታገዱ አማካሪዎች ስም ዝርዝር ከባለስልጣኑ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት http://www.egp.ppa.gov.et ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3.1 ላይ ከተጠቀሰው ጋር በተያያዘ የግዥ ፈፃሚ አካሉ ወይም አማካሪው ወይም የአማካሪው ተወካይ በማማከር አገልግሎት ግዥ ሂደት ወይም በውል አፈፃፀም ወቅት በሙስና ወይም በማጭበርበር ወይም በመሳሰሉት ድርጊቶች መሳተፋቸው ከተረጋገጠ/ከታወቀ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የማማከር አገልግሎት ግዥ ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

የጨረታውን ውጤት ባልተገባ ሁኔታ ለማስቀየር በማሰብ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ባለሥልጣን ወይም ለግዥ ሠራተኛ ማማለያ የሰጠ ወይም ለመስጠት ጥያቄ ያቀረበ አማካሪ ከጨረታው እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡ በሌሎች የመንግሥት ግዥዎችም እንዳይሳተፍ ይደረጋል፡፡ ያስያዘው የጨረታ ዋስትናም ይወረሳል፡፡
አማካሪዎች በሙስናና በማጭበርበር ጉዳይ ላይ በዚሁ የጨረታ ሰነድ የተመለከቱትን ሁኔታዎች መቀበላቸውን በጨረታው ማቅረቢያ ሰንጠረዥ ላይ ማመልከት ይኖርባቸዋል፡፡

ከውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የአቅራቢዎች በኦዲተሮች እንዲመረመሩና ኦዲት እንዲደረጉ ቢሮው የመጠየቅ መብት አለው፡፡
በመንግሥት የግዥ አዋጅና መመሪያ መሠረት አንድ አማካሪ ከጨረታ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አዋጁንና መመሪያውን የጣሰ ከመሰለውና ቅር ከተሰኘ አፈፃፀሙ እንደገና እንዲታይለት ወይም እንዲጣራለት ለግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የበላይ ሀላፊ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ አማካሪው ቅሬታ ያስከተለበትን ድርጊት ባወቀ ወይም ሊያውቅ ይገባ ከነበረበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት

ሀላፊ አቤቱታውን በፅሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የበላይ ኃላፊ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም አማካሪው በተሰጠው ውሳኔ ካልረካ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አምስት የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ይግባኙን ማቅረብ ይችላል፡፡ ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ በሁለቱም ወገኖች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4. ህጋዊ (ብቁ) አማካሪዎች

4.1 አማካሪ ማለት በተፈጥሮ ሰውነት ያለው ወይም በሕግ ሰውነት የተሰጠው የግል፣ የሕዝብ ወይም መንግስታዊ ተቋምን የሚያመለክት ሲሆን በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.5 ወይም የሁለም ድምር ሆኖ፤ የውል ስምምነት በመግባት ሕጋዊ ችሎታ ያለው የግል ተቋም ወይም የሽርክና ማህበር ሊሆን ይችላል፡፡ የሽርክና የጥምረት ወይም እሽሙር ማህበር በሚሆንበት ወቅት፡-

(ሀ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰነዱ ውስጥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የሽርክና፣የጥምረት ወይም እሽሙር ማህበርአባላት በሙሉ በጋራ እና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

(ለ) የሽርክና፣ የጥምረት ወይም እሽሙር ማህበር ማህበሮቻቸውን በሙሉ ወይም በከፊል ወክሎ በእነሱ ምትክ በጨረታው ሂደት እና በውል አፈፃፀም ወቅት አስፈላጊውን ሁሉ የሚያከናውንላቸው ተወካይ ይመርጣሉ፡፡

4.2 ይህ የአማካሪዎች የመጨረሻው ጥሪ (የሽርክና፡ የጥምረት ወይም እሽሙር ማህበርእንዲሁም ሌሎች ማህበራትን ጨምሮ) በክፍል 5 ስለ ብቁ አገሮች በተዘረዘረው መሠረት የብቁ አገሮች ዜግነት ላላቸው አማካሪዎች ሁሉም ክፍት ነው፡፡ በጨረታው የሚሳተፍ አማካሪ የአንድ የተወሰነ አገር ዜጋ ተደርጎ የሚወሰደው አማካሪው የአገሪቷ ዜጋ ከሆነ ወይም በአገሪቷ ሕግ መሠረት ተመዝግቦ ሥራዎችን የሚያከናውን መሆኑን ከተረጋገጠ ነው፡፡ ይህ የዜግነት መመዘኛ መስፈርት በማንኛውም የውል ክፍል በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ለሚቀርቡ ንዑስ አማካሪዎች ጭምር ያገለግላል፡፡

4.3 አንድ ተጫራች በጨረታ ማስረከቢያ ቀነ-ገደብ ወይም ከዚያ በኋላም ቢሆን በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 3.1(ሐ) መሠረት ዕገዳ የተጣለበት ከሆነ ይህንን ጨረታ ለመካፈል ብቁ አይሆንም፡፡

4.4 በመንግስት ሥር የሚተዳደሩ ድርጅቶች በጨረታው ለመሳተፍ ሕጋዊ (ብቁ) የሚሆኑት በሕግ እና በፋይናንስ ደረጃ እራሳቸው የቻሉ ከሆነ እንዲሁም በንግድ ሕግ መሠረት ሥራዎቻቸውን የሚያከናውኑ እና ከግዥ ፈፃሚ አካላት ጥገኝነት ነጻ ከሆኑ ብቻ ነው፡፡

4.5 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር አማካሪዎች በጨረታው ለመሳተፍ ሕጋዊ መሆናቸው ግዥ ፈፃሚው በአስተማማኝነት ለማረጋገጥ ያስችለው ዘንድ የሚከተሉትን መረጃዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

(ሀ) በመክሰር ላይ ያለ ወይም በመክሰር ምክንያት በሂደት የሚዘጋ፣ ሥራዎቻቸው በማናቸውም ምክንያት የታገደ ወይም በፍርድ ቤት በክስ ሂደት ላይ አለመሆናቸው የሚያሳይ መረጃ ወይም ሰነድ፤

(ለ) ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አግባብነት ያላቸው የሰነድ ማስረጃዎች፡-

I. አማካሪው የተሰማራበትን የሥራ ዘርፍ የሚገልፅ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ፤

II. በታክስ ባለስልጣን የተሰጠ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት (ስለ ውል ዋጋ በሚመለከት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተገለፀው መሰረት

III. በታክስ ባለስልጣን የተሰጠ የወቅቱ ግብር የተከፈለበት የምስክር ወረቀት

IV. በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተዛማጅነት ያለው የሙያ ትግበራ ማረጋገጫ፡-

4.6 በዚህ የመንግሥት የግዥ ሂደት ለመሳተፍ በአቅራቢዎች ዝርዝር ላይ መመዝገብ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡

4.7 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ በተጠየቀው መሠረት አማካሪዎች አጥጋቢ በሆነ መልኩ በተከታታይ ብቁ የነበሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

4.8 ተጫራቹ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር በመንግስት ግዥ ላይ የሚሳተፉ ማናቸውም የሕግ ሰውነት ያላቸው ተቋማት፣ የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበራት እንደ አንድ የቅድመ ብቃት መስፈርት በነዚሁ ተቋማት ላይ የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ያላቸውን ሰዎች የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

4.9 የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ያለው ተጫራች የሚባለው ከሚከተሉት አንዱን ማሟላት ሲችል ብቻ ነው፡፡

ሀ/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቢያንስ አስር በመቶ [10%] የሚሆነውን የድርጅቱን አክሲዮኖች ወይም የመምረጥ መብቶችን በባለቤትነት የያዙ ወይም የተቆጣጠሩ ሰዎች፤

ለ/ በሌሎች መንገዶች በድርጅቱ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ወይም የሚቆጣጠሩ ሰዎችን ወይም

ሐ/ በባለቤትነት የተመዘገቡም ሆነ ያልተመዘገቡ ሆነው በድርጅቱ ላይ የመጨረሻ እና ውጤታማ ቁጥጥር ያላቸው ሰዎች፡፡

4.10 በተጫራቾች የሚቀርቡ የተጠቃሚ ባለቤትነት መብትን የሚገልጹ መረጃዎች ሀሰተኛ ያልተሟሉና ትክክለኛነት የሚጎላቸው መሆናቸው በመንግስት መ/ቤቶች ከተረጋገጠ፣ የቀረበውን የመጫረቻ ሰነድ በቅድሚያ ውድቅ በማድረግ በተጫራቹ ላይ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርቡ ይችላል፡፡

5. የጥቅም ግጭት

5.1 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት (ከዚህ በኋላ ‹‹መንግስት›› ተብሎ የሚጠቀሰው) አማካሪዎች በማናቸውም ወቅት የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ጥቅም በከፍተኛ ደረጃ በሚያረጋግጥ መልኩ ሙያውን የጠበቀ፤ ተጨባጭ የሆነ እና ከአድሎ የፀዳ ምክር እንዲያቀርቡ ይፈልጋል፡፡ እንዲሁም ከተመሳሳይ ድርጅቶች ሊከሰት ከሚችል ማንኛውም የጥቅም ግጭት ወይም ለጥቅም ግጭት የሚዳርግ ተግባር ራሳቸውን ማራቅና ወደፊት ሥራ

የማግኘት ዕድልን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ አማካሪዎች እና ማንኛውም ሽሪክቻቸው በማንኛውም ሁኔታ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ተግባራት መሳተፍ የጥቅም ግጭት ውስጥ እንደገቡ ታሳቢ ይደረጋል፡፡

(ሀ) በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለማማከር አገልግሎት ሳይሆን የአንድ ፕሮጀክትን እቃዎች፣ ስራዎች፣ ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች እንዲያቀርብ የተደረገ ድርጅት ወይም አጋሮች ከነዚህ እቃዎች፣ ሥራዎች ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች ጋር ግኑኝነት ያለው የማማከር አገልግሎት እንዳይሰጥ ውድቅ ይደረጋል፡፡ በአንፃሩ ለአንድ ፕሮጀክት ዝግጅት ወይም አፈፃፀም የተቀጠረ አማካሪ ወይም አጋሮቹ ከማማከር አገልግሎቱ በስተቀር ከፕሮጀክቱ ዝግጅት ወይም አፈፃፀም ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ዕቃዎች፣ ስራዎች ወይም አገልግሎቶች እንዳያቀርብ ይታገዳል፡፡ ለዚህ አረፍተ ነገር ሲባል ከማማከር አገልግሎት የተለየ ሌሎች አገልግሎቶች ማለት ወደተጨባጭ ቁሳዊ ውጤት የሚያመሩ ለምሳሌ፣ እንደ ቅየሳ፣ የፍለጋ ቁፋሮ፣ የአየር ላይ ፎቶግራፎችና የሳትላይት ምስሎች ማለት ነው፡፡

(ለ) አማካሪው (ሰራተኞቹ እና ንዑስ አማካሪዎችን ጨምሮ) ወይም ማናቸውም አጋሮቹ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም ሌላው የመንግስት አካላት ከሚያከናውናቸው የግዥ ተግባራት ጋር በማንኛውም መልኩ የጥቅም ግጭት ውስጥ የሚያስገባ ተግባር ውስጥ መሠማራት የለባቸውም። ለምሳሌ፤ ለመሰረተ ልማት ግንባታ ፕሮጀክት የምህንድስና ዲዛይን ለመስራት የተቀጠረ አማካሪ ለዚሁ ፕሮጀክት ገለልተኛ የሆነ የአካባቢ ተፅዕኖ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ መሰማራት የለበትም፡፡ እንዲሁም የመንግስት ንብረቶችን ወደ ግል ለማዘዋወር የተሰማራ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤትእንዲያግዝ የተቀጠረ አማካሪ እነዚህን ንብረቶች መግዛት ወይም ገዢዎችን ማማከር የለበትም። በተመሳሳይ ሁኔታ ለአንድ ተግባር ቢጋር እንዲያዘጋጅ የተቀጠረ አማካሪ ይህን ተግባር ለመስራት ሊቀጠር አይችልም፡፡

(ሐ) ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሰራተኞች ጋር የንግድ ወይም ቤተሰባዊ ግንኙነት ኖሮት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ተግባራት አንዱ፡

i. ቢጋር በማዘጋጀት
ii. አማካሪን በመምረጥ
iii. በውሉ የቁጥጥር ስራ ላይ የሚሳተፍ አማካሪ (ሰራተኞች እና ንዑስ አማካሪዎችን ጨምሮ ከዚህ ግንኙነት የሚመነጩት የጥቅም ግጭቶችን ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚያሳምን መልኩ በግዥ ወይም በውል አፈፃፀም ሂደት ውስጥ ካልተፈቱ በስተቀር ኮንትራት አይሰጠውም፡፡

5.2 አማካሪዎች ለግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት በውሉ መሰረት በሚሰጡት አገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ የግዥ ፈፃሚ መንግስታዊ መ/ቤት ጥቅም ለማስጠበቅ ተጨባጭ ወይም ታሳቢ የጥቅም ግጭት ሊፈጥርባቸው የሚችሉ ማንኛውም ሁኔታ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ እንደዚህ አይነቶቹን የጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን አለማሳወቅ ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት አማካሪውን ውድቅ እንዲያደርገው ወይም ውሉ እንዲቋረጥ ሊያደርገው ይችላል፡፡

5.3 ማንኛውም የባለስልጣን ወይም የግዥ ፈፃሚው ቅጥር ሰራተኞች በራሳቸው ሚኒስትር መስሪያ ቤት፣ መምሪያ ወይም ኤጀንሲዎች በአማካሪነት ማገልገል የለባቸውም፡፡ የግዥ ፈፃሚውን መስሪያ ቤት የለቀቁ ሰራተኞች ከዚህ በፊት ለሚሰሩበት መስሪያ ቤት፣ መምሪያ ወይም ተቋም ከለቀቁበት ቀን አንስቶ ባሉት አንድ ዓመት በኋላ መስራት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ምንም አይነት የጥቅም ግጭት እንደማያስከትል ሲረጋገጥ ነው፡፡ አማካሪው ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ በራሳቸው ስር በሰራተኝነት ከቀጠሩ በቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳቡ ላይ እንደዚህ አይነቶቹ ሰራተኞች ከሚሰሩበት መንግስታዊ ተቋም ያለደመወዝ ክፍያ በእረፍት ላይ መሆናቸው እንዲሁም ከሚሰሩበት መስሪያ ቤት ውጪ በሌላ ስራ በሙሉ ጊዜ መስራት እንደሚችሉ ማረጋገጫ መቅረብ አለበት፡፡ እንዲህ አይነቱ ማረጋገጫ በአማካሪው ቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ጋር ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

5.4 የተመረጠው አማካሪ ከተጠቀሰው ተግባር ጋር ግኑኝነት ያለው የማማከር አገልግሎት በመስጠት ተነፃፃሪ ጥቅም የሚያስገኝለት ከሆነ ከቀረቡት ሌሎች አማካሪዎች ሲነፃፀር ይህ አማካሪ የተሻለ ዕድል ያለው መሆኑን የሚገልፁ ማስረጃዎች ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከመወዳደሪያ ሃሳብ መጠየቂያው ጋር አብሮ ለተወዳዳሪ አማካሪዎች ሁሉ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

ለ. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ይዘት

6. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ

6.1 የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ከዚህ በታች የተገለፁት ክፍሎችን ማለትም ምዕራፍ 1፣ 2 እና 3ን የያዘ ነው፡፡ እንዲሁም በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 8 መሰረት የሚደረጉ ማሻሻያዎች ወይም ተጨማሪዎች በጋራ መነበብ ይኖርባቸዋል፡፡

ምዕራፍ 1፡ የጨረታ ሥርዓቶች

ክፍል 1፡ የአማካሪዎች መመሪያ
ክፍል 2፡ የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠነድ
ክፍል 3፡ የግምገማ ዘዴ እና መስፈርት
ክፍል 4፡ የጨረታ ቅጾች
ክፍል 5፡ ብቁ ሀገሮች

ምዕራፍ 2፡ የፍላጎቶች መግለጫ

ክፍል 6፡ ቢ.ጋር (Terms of Reference)

ምዕራፍ 3፡ ውል
ክፍል 7፡ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች (አ.ው.ሁ)
ክፍል 8፡ ልዩ የውል ሁኔታዎች (ል.ው.ሁ)
ክፍል 9፡ የውሉ ቅጾች

6.2 በጨረታው ለመሳተፍ ፍላጐት ላላቸው ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሚዘጋጀው ጥሪ የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ መ/ቤትመሆን ይገባዋል፡፡ በጨረታ ጥሪ እና በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 6.1 የተጠቀሱት የጨረታ ሰነዶቹ መካከል አለመግባባት ከተነሳ የጨረታ ሰነዱ ክፍሎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

6.3 አማካሪዎች የጨረታ ሰነዶችን በቀጥታ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ካለመውሰዳቸው ጋር ተያይዞ ለሚከሰት ማናቸውም ጉድለት ወይም አለመሟላት የግዥ ፈፃሚ መስሪያ ቤት ተጠያቂነት የለበትም፡፡ አማካሪዎች የጨረታ ሰነዱን በቀጥታ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ያልተቀበሉ ከሆነ በማምገማ ወቅት ውድቅ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ የጨረታ ሰነዶቹ በውክልና በሽያጭ የተወሰዱ ከሆነ የጨረታ ሰነዶቹን በሚወሰዱበት ጊዜ የተጫራቾች ስም በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ዘንድ መመዝገብ አለበት።

6.4 አማካሪዎች በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው ውስጥ የተዘረዘሩትን ሁሉንም መመሪያዎች፣ ቅጾች፣ ስምምነቶች እና ልዩ ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ እንዲመረምሩ ይጠበቃል፡፡ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የተጠየቁትን ሁሉንም መረጃዎች ወይም ሰነዶች አለማቅረብ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ ውድቅ እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡

7. የመንግስት የኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት በመጠቀም በመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ የሚቀርቡ የጽሁፍ ጥያቄዎች/ ማብራሪያዎች

7.1 በጨረታ ሰነዶቹ ላይ ማብራሪያ የሚፈልግ አማካሪ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሰውን የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት አድራሻ ተጠቅሞ የሚፈልገውን ማብራሪያ በፅሑፍ መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተጫራቾች ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ ላይ በተገለጸው መሰረት ከጨረታ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን በፊት ለደረሱት የማብራሪያ ጥያቄዎች በሙሉ በፅሑፍ መልስ ይሰጣል፡፡ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የመልሱን ቅጂዎች የጠያቂውን ማንነት ሳይገልፅ የጨረታ ሰነድ በቀጥታ ከተቋሙ ለገዙት አማካሪዎች በሙሉ ይልካል፡፡ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በማብራሪያው

ውጤት መሠረት የጨረታ ሰነዶቹን የሚያሻሽል ከሆነም ይህንኑ የሚያደርገው በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 8 እና ንዑስ አንቀጽ 27.2 የተመለከተውን ሥነ-ሥርዓት ተከትሎ ነው።

7.2 በጨረታ ሂደትም ሆነ በጨረታ ግምገማ ወቅት ተቀባይነት የሚኖረው በቀጥታ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በፅሑፍ የተሰጠ የማብራሪያ ጥያቄ መልስ ብቻ ነው። በሌላ አኳኋን ማለትም በቃል፣ በፅሑፍ፣ ወይም በግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ሠራተኛ ወይም በሌላ ተወካይ ወይም በሌላ ሦስተኛ መ/ቤት የተሰጡ መልሶች ወይም ማብራሪያዎች ከግዥ ፈፃሚ መ/ቤትየተሰጡ ማብራሪያዎች ተደርገው አይቆጠሩም።

8. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነዶችን ስለማሻሻል

8.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአማካሪዎች በቀረበለት የማብራሪያ ጥያቄ ወይም በራሱ ተነሳሽነት መሰረት በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው ላይ ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማሻሻያውን ማሳወቅ ይኖርበታል። ግዥ ፈፃሚው መ/ቤቱ ጨረታውን ከመክፈቱ በፊት በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሹን የጨረታ ሰነዱ ተደራሽ በተደረገበት ሥርዓት መስጠት አለበት።

8.2 በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ይዘት ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ለውጦች ወይም ማሻሻያዎች በተመሳሳይ ጊዜ ለአማካሪዎች ስለተደረገው ለውጥ ወይም የተሻሻለውን የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ እንዲያውቁት ይደረጋል። አማካሪዎች እንደዚህ ዓይነቶቹን የተሻሻለ የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያዎች መቀበላቸውን ወዲያውኑ ያረጋግጣሉ። በተሻሻለው የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የተካተቱ መረጃዎች አማካሪዎቹ ለጨረታ በሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ እንዲካተት እንደሚያደርጉት ታሳቢ ይደረጋል።

8.3 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትበራሱ ነፃ ምርጫ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የማስረከቢያ መዝጊያ ቀኑን ሊያራዝመው ይችላል። ይህም የመወዳደሪያ ሀሳቡ መጠየቂያ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 8.1 እንደተጠቀሰው ከተሻሻለ እና በዚህም በተሻሻለው ሀሳብ ምክንያት አማካሪዎች በሚያደርጉት ማሻሻያ ላይ በቂ ጊዜ የላቸውም ተብሎ ሲያምን እንዲሁም መ/ቤቱ በሰጠው ማብራሪያና ማሻሻያ ላይ ቅሬታ ካላቸው ይግባኝ ማቅረብ እንዲችሉ የጨረታ ማቅረቢያ ቀነ-ገደቡን ቢያንስ ለተጨማሪ አምስት የሥራ ቀናት ሊያራዝም ይችላል።

9. የቅድመ መወዳደሪያ ሀሳብ ኮንፈረንስ/ስብሰባ/

9.1 ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘውና ማብራሪያ ለማድረግ ጨረታው ውስብስብ መሆኑን ሲያምንበት በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው ላይ ለአማካሪዎች ተገቢውን ማብራሪያ ለመስጠትና ውይይት ለማድረግ የቅድመ መወዳደሪያ ሀሳብ ኮንፈረንስ ሊያከናውን ይችላል።

9.2 ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የተረከቡት ሁሉም አማካሪዎች በቅድመ መወዳደሪያ ሀሳብ ኮንፈረንስ ይሳተፉ ዘንድ የኮንፈረንሱ ሰዓት፣ ቀን እና አድራሻ በመጥቀስ ያስታውቃል፡፡

9.3 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትሁሉንም አማካሪዎች በቅድመ መወዳደሪያ ሀሳብ ኮንፈረንስ እንዲሳተፉ ይጋብዛል፡፡ ሁሉንም አማካሪዎች በቅድመ መወዳደሪያ ሀሳብ ኮንፈረንስ እንዲሳተፉ እድሉን መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በዚህ ኮንፈረንስ ለመሳተፍ የሚደረግ ወጪ በሙሉ በአማካሪዎች ይሸፈናል፡፡

9.4 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሁሉንም አማካሪዎች የሚኖራቸው ማብራሪያ/ጥያቄ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ አንቀጽ 7.1 እና 7.2 በተጠቀሰው አድራሻ እና በተጠቀሰው ቀን እና ሰአት እንዲያቀርቡ ይጋብዛቸዋል፡፡

9.5 የቅድመ መወዳደሪያ ሀሳብ ኮንፈረንስ በቃለ-ጉባኤ ይያዛል፡፡ የኮንፈረንሱ ቃለ-ጉባኤ የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ለተቀበሉ አማካሪዎች በሙሉ የተደረገውን ማብራሪያ እና ማሻሻያዎች በማካተት የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳባቸውን ያቀርቡ ዘንድ ይሰጣቸዋል፡፡

ሐ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አዘገጃጀት

10. በጨረታ የመሳተፍ ወጪ

አማካሪው ከጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ዝግጅት፣ ርክክብ፣ እና የውል ድርድር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጪዎችን ይሸፍናል፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጨረታ ውጤት ወይም ሂደት ምንም ይሁን ምን ከነዚህ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ወጪዎች ተጠያቂ አይሆንም፡፡

11. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ቋንቋ

11.1 የጨረታው መወዳደሪያ ሀሳብ እንዲሁም ከጨረታው መወዳደሪያ ሀሳቦች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ልውውጦች እና ሰነዶች እንዲሁም ግንኙነቶች በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ በተጠቀሰው ቋንቋ መፃፍ ይኖርባቸዋል፡፡

11.2 ከጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ ቋንቋ ውጪ የተዘጋጁ የአማካሪው የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ እና አጋዥ ሰነዶች ህጋዊ እውቅና እና ክህሎት ባለው ተርጓሚ ተተርጉሞ ከዋና ሰነዶቹ ጋር መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይ የሚተረጐሙ ሰነዶች የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ መሰረታዊ ይዘትን የያዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

11.3 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በዋና ሰነድ እና በተተረጐመው ሰነድ ላይ የይዘት ልዩነት ወይም ግጭት መኖሩን ከተገነዘበ፣ እንደዚህ አይነቶቹ ግጭቶች ጥቃቅን ስህተቶች የያዙ ካልሆኑ በስተቀር ሰነዶቹን ሙሉ ለሙሉ ውድቅ ያደርጋል፡፡

12. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ዝግጅት

12.1 አማካሪዎች የቴክኒክ እና የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦቻቸውን ለየብቻቸው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

12.2 የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ በሚያዘጋጁበት ወቅት አማካሪዎች የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ሰነዶችን በዝርዝር እንዲመረምሩ ይጠበቃል፡፡ የተጠየቀው መረጃ በበቂ ሁኔታ ያለማቅረብ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

12.3 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትበክፍል 6፣ በቢጋር የተገለፁት ፍላጎቶች እንዲሁም አስፈላጊው እና ተዛማጅነት ያላቸው የፕሮጀክት ዳታ እና ሪፖርቶችን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

12.4 የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ለማስረከብ የሚደረግ ጥሪ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ለተጠቀሱ አማካሪዎች ይላካል፡፡

13. የሽርክና፣ የጥምረት ወይም እሽሙር ማህበር

13.1 አማካሪዎች ከሌሎች አማካሪዎች ጋር በሽርክና ወይም በንዑስ አማካሪነት አገልግሎቱን መስጠት ጠቃሚ ነው ብለው ካሰቡ እንደአግባብነቱ ሌሎች ተቋማት ወይም ድርጅቶች በንዑስ አማካሪነት ሊቀጥሩ ይችላሉ፡፡ አማካሪው ለዚህ ስራ ጥሪ ካልተደረገላቸው ሌሎች ድርጅቶች ወይም የሽርክና ማህበር ጋራ ለመስራት ካሰበ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በቅድሚያ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማረጋገጫ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ቀድሞ ጥሪ ካልተደረገላቸው አማካሪዎች ጋር አብሮ የሚሠራ ሲሆን አማካሪው የማህበሩ መሪ በመሆን ያገለግላል፡፡

13.2 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር አማካሪዎቹ በጨረታው ለሚሰጣቸው የውል ግዴታ ከሌሎች አማካሪዎች ጋር በጣምራ መስራት የለባቸውም፡፡

13.3 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ ማንኛውም ክፍተት እየታየ ተመሳሳይ ንዑስ አማካሪዎች በተለያየ የመወዳደሪያ ሀሳብ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ በንዑስ ውል ለሚሰጥ ስራ አጠቃላይ የሚቀርብ የውል ዋጋ ጣርያ በመቶኛ ሂሳብ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ይገለፃል፡፡

13.4 አማካሪው የሁለት ወይም ከዛ በላይ ተቋማት የሽርክና ወይም ጊዜያዊ ህብረት ማህበር ከሆነ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርበው አንድ ነጠላ ውል መፈፀምን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በማህበሩ ስልጣን የተሰጠው ግለሰብም በጨረታ ሰነዱ ላይ መፈረም ይኖርበታል፡፡ በዚህም የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ እና በማንኛውም የውል ሂደት ማህበሩ በጋራ እና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ እነዚህ ተቋማት ከግዥ ፈፃሚው አካሉ ጋር በሚኖር የጨረታ ወይም የውል ግንኙነት ማህበሩ የውል ግዴታ በሚያስርበት ጊዜ መሪ ሆኖ

እንዲያገለግል አንድ አባል ይወክላሉ፡፡ ጊዜያዊ ህብረት ወይም የሽርክና ማህበር ያለ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጽሁፍ ቅድመ እውቅና አይቀየርም፡፡

13.5 የጨረታው መወዳደሪያ ሀሳብ በሽርክና ወይም እሽሙር ማህበሩ ተወካይ ይፈረማል፡፡ ነገር ግን የማህበሩ ተወካይ መሆኑን እንዲሁም በእንደዚህ አይነቶቹ የጨረታ ወይም የውል ስምምነቶች ለመፈረም ስልጣን እንዳለው በአባላቱ በጽሁፍ የተሰጠ የውክልና ስልጣን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ የሽርክና ወይም እሽሙር ማህበርን በመወከል ፊርማውን እንዲያኖር ስልጣን የተሰጠው ተወካይ ውክልናውን ለግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ የተፈቀደለት የውክልና ስልጣን ላይ ያሉት ፊርማዎች በሽርክና ወይም እሽሙር ማህበሩ አሰራር ደንብ እንዲሁም በሀገሪቷ ተዛማጅነት ባላቸው ህጐች መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ላይ ፊርማቸውን ያኖሩ በሽርክና ወይም ጊዜያዊ ማህበሩ ምትክ ውል እንዲዋዋሉ ወይም ማህበሩን ወክለው ሂደቱን እንዲፈጽሙ ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡ የእንደዚህ አይነቶቹ ማህበራት እያንዳንዱ አባል ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚጠይቃቸው አስፈላጊ የህግ፣ የቴክኒክ እና የፋይናንስ መመዘኛ መስፈርቶች እንደሚያሟሉ እንዲሁም የሚገባውን ውል በአግባቡ ለመወጣት ብቁ መሆናቸው መረጋገጥ ይኖርታል፡፡

14. የአማካሪ ሙያዊ ብቃትና አቅም

14.1 አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የአማካሪዎች ሙያዊ ማረጋገጫ እና ብቃት ለማረጋገጥ አማካሪዎቹ የቡድን ክህሎት ማትሪክስ እንዲሁም የሰራተኞቻቸው ስታትስቲክስ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ለተጠቀሰው ጊዜ በክፍል 4 የተጠቀሰው የአማካሪዎች የማረጋገጫ ቅጽ እና የጨረታ ቅጾችን በመሙላት ያረጋግጣሉ፡፡

14.2 በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ላይ የተጠቀሱትን ስራዎች የሚያከናውኑ ቁልፍ ሰራተኞችየስራ ልምድ፣ ተዛማጅነት ያላቸው የፕሮጀክት ትግበራ ልምድ እንዲሁም የትምህርት እና ስልጠና ማረጋገጫዎችን አማካሪዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

14.3 አማካሪዎች ለሚያቀርቧቸው ሥራተኞች ምስክርነት የሚሰጡ (reference) ሰዎችን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም ሰዎች የመወዳደሪያ ሀሳቡ በሚገመገምበት ጊዜ መገኘት የሚችሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም ሁሉም ካልተገኙ በስተቀር አንድ ወይም ሁለት ምስክርነትን የሚሰጡ ሰዎችን ባለማግኘት ብቻ ተወዳዳሪውን መጣል አይቻልም፡፡

15. የአማካሪው የፋይናንስ አቋም

15.1 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የተጠየቀ ከሆነ፤ አማካሪው የሚገባውን ውል በአግባቡ ለማከናወን እና ለማስተዳደር በቂ የፋይናንስ ሀብት እንዳለው ለማረጋገጥ እና ለማጣራት በክፍል 4 የጨረታ ቅጾች ላይ የአማካሪዎች ማረጋገጫ ተብለው በተጠቀሱት ሰንጠረገሮች አግባብነት ያላቸውን የፋይናንስ ዳታዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

15.2 ንዑስ አንቀጽ 15.1 ከተጠቀሱት ማረጋገጫዎች በተጨማሪ የአማካሪው የፋይናንስ አቋም ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ሰነዶች የሚከተሉት ናቸው፡-

(ሀ) በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ የፋይናንስ መግለጫ
(ለ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የተጠቀሱት ሌሎች ሰነዶች

16. የአማካሪው የቴክኒክ ብቃት፤ ክህሎትና የሥራ ልምድ

16.1 አማካሪው የኩባንያውን እና የድርጅቱን ወቅታዊ ሁኔታ አግባብነት ካላቸው ዋናው ኩባንያና እህት ኩባንያዎችን ጨምሮ ዝርዝር መግለጫ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ አማካሪው በክፍል 6 ቢ.ጋር የተዘረዘሩትን የማማከር አገልግሎቶችና የስራ ልምድ እና ብቃት ዝርዝር መግለጫ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም አማካሪው በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የተጠቀሱትን ጨምሮ ሌሎች በሂደት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን ተግባራት በምን መልኩ ወይም እንዴት ለማከናወን እንዳቀደ ዝርዝር መግለጫ ያቀርባል፡፡

16.2 ይህ መረጃ ራሱን በቻለ ቅጽ ያማካሪዎች ማረጋገጫ መመዘኛ መስፈርት በሚል በክፍል 4 የጨረታው ሰነድ ላይ የተጠቀሰውን መረጃ ማካተት ይኖርበታል፡፡

16.3 ውሉን አጥጋቢ በሆነ መልኩ አማካሪው እንደሚያከናውን ወይም የውሉን ግዴታ በአግባቡ እንደሚወጣ ለማረጋገጥ ከዚህ በፊት ከሌሎች ድርጅቶች ከአገልግሎቱ ጋር ተመሳሳይነት ባለው መልኩ ያከናወናቸውን መልካም የስራ አፈፃፀም ብቃት የሚመሰክሩለት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተጠቀሰው ሁኔታ አስፈላጊውን የመልካም አፈፃፀም ማረጋገጫ በተፈቀደው ብዛት እና ወቅት ጨምሮ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ማረጋገጫ ትክክለኛ ስለመሆኑ ለማጣራት የመልካም አፈፃፀም ብቃት ምስክር ወረቀት የሰጡትን ድርጅቶች መረጃ ጭምር ማያያዝ የሚኖርበት ሲሆን ቢያንስ የግንኙነት መመስረቻው መረጃ፤ የመልካም አፈፃፀም ምስክር ወረቀት ሰጪው ስም፣ የስራ ተግባር፣ አድራሻ፣ ኢ-ሜይል እና ስልክ ቁጥር ይጨምራል፡፡ እያንዳንዱ

የቀረበው ማጣቀሻ የአማካሪውን የአፈፃፀም ብቃት እና የአማካሪውን አሰራር አቅም በሚያውቅ የደንበኛው የፕሮጀክት አስተዳደር ወይም የበላይ ኃላፊ መቅረብ ያለበት ሲሆን ይህም ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግምገማ በሚያካሂድበት ጊዜ ሊያገኘው የሚችል ግለሰብ መሆን ይኖርበታል፡፡

16.4 የውሎች የመልካም አፈፃፀም ማረጋገጫ የሚከተሉትን ዳታዎች መያዝ ይኖርበታል፡-

(ሀ) የተዋዋይ ወገኖች ስም እና የተቋቋሙበት ቦታ
(ለ) የውሉ አርዕስት (ይዘት)
(ሐ) የውሉ መጠን ዋጋ
(መ) የውሉ የስራ አፈፃፀም ጊዜ እና ቦታ
(ሠ) ውሉ አጥጋቢ በሆነ መልኩ መፈፀሙን የሚያረጋግጥ መግለጫ

16.5 አማካሪው የሽርክና ጥያቄ ካቀረበ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መረጃዎች ለሽርክና ማህበሩ አባላት በሙሉ መድረስ ይኖርበታል፡፡ ይህን መረጃ በተለያዩ ክፍሎች የሚቀርብ ሲሆን ለእያንዳንዱ የሽርክና ማህበር አባል ይቀርብለታል፡፡ በተጨማሪም የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ በሽርክና ማህበር አባላት መካከል ስላለው ግንኙነት ይዘረዝራል፡፡

16.6 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት የአማካሪው የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርት እንዲሁም ብቃት ለማረጋገጥ በመ/ቤት ተገኝቶ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህም አማካሪው ውሉን ለማስተዳደር ወይም ለመፈፀም በቂ ብቃት እንዳለው ለማረጋገጥ ነው፡፡

17. ባለሙያ ሰራተኞች

17.1 የተመደበውን ስራ የሚያከናውኑ ሙያተኞች ቁጥር (ብዛት) ወይም የሚያስፈልገው በጀት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ይቀርባል፡፡ ነገር ግን ሁለቱም አንድ ላይ መታየት የለባቸውም፡፡ እንዲሁም የመወዳደሪያ ሀሳቡ የሚዘጋጀው ባሉት ሙያተኞች ቁጥር ወይም አማካሪው በሚያቀርበው በጀት መሠረት ይሆናል፡፡

17.2 በአንድ የተወሰነ በጀት ለሚከናወኑ ስራዎች እንደዚህ ዓይነቱ ቋሚ በጀት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ይገለፃል፡፡ የሚቀርበውም የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ ከበጀቱ በላይ መሆን/መብለጥ አይኖርበትም፡፡ ሆኖም በዚህ በጀት ለሚከናወን ሥራ አገልግሎት የሚሰጡት ሰራተኞች ቁጥር መግለፅ የለበትም፡፡

17.3 የሚቀርቡት ሙያተኞች ለሥራው የሚመጥኑ እና የብቃት የምስክር ወረቀት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

17.4 የሚቀርቡት ሰራተኞች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ ባሉት ሁኔታዎች አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ቢኖራቸው ይመረጣል፡፡

17.5 አማራጭ ሙያተኞች (ሠራተኞች) መቅረብ የለባቸውም፤ እንዲሁም ለእያንዳንዱ የሥራ ምድብ አንድ ካሪክሉም ቪቴ (CV) ብቻ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

18. የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ቅፅ እና ይዘት

18.1 የሚቀርቡት የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳቦች በሙሉ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው የተዘረዘሩትን መመዘኛ መስፈርቶች ሚሟላት እና የሚከተሉትን መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

18.2 የሥራ ምድቡን ባህሪ መሠረት በማድረግ አማካሪዎች ሙሉ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ /Full Technical Proposal/ ወይም ጠቅለል ያለ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ /Simplified Technical Proposal/ ማስረከብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቡ የሚቀርብበት ፎርማቶች በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ተገልፀዋል፡፡ የተሳሳተ የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረብ የመወዳደሪያ ሀሳቡን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ የሚቀርበው የቴክኒካል የመወዳደሪያ ሀሳብ በዚህ አንቀፅ ስር የተካተቱትን መረጃዎች አባሪ የተደረጉ የመመዘኛ መስፈርትና ቅፆችን በመጠቀም መቅረብ አለበት (በክፍል 4 መሠረት)፡፡

የአማካሪውን ብቃት የሚያረጋግጡ የግድ መቅረብ ያለባቸው አስፈላጊ ሠነዶች የሚከተሉት ናቸው፡-

(ሀ) የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ማስረከቢያ ሠንጠረዥ (ክፍል 4፣ ቅጽ ቁ 1) እና የሚከተሉትን አስፈላጊ አባሪዎች ጨምሮ፡-

(i) ከታክስ ባለስልጣን የተሰጠ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ሰርቲፊኬት ስልጣን በተሰጠው ግብር ሰብሳቢ ተቋም (በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ አንቀጽ 4.5 (ለ) (ii) በተገለጸው የዋጋ መጠን በላይ ሲሆን፡፡

(ii) ከታክስ ባለስልጣን የተሰጠ ጊዜው ያላበቃ የግብር ክፍያ የምስክር ወረቀት በዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የተፈቀደ ከሆነ የንግድ ምዝገባ ወይም በዘመኑ የታደሰ ንግድ ፍቃድ

(iii) እንደአግባብነቱ ተዘማጅነት ያለው የሙያ ትግበራ የምስክር ወረቀት

(ለ) የአማካሪው አግባብነት ማረጋገጫ (ክፍል 4፣ ቅፅ ቁ 2) የሚከተሉትን የግዴታ መቅረብ ያለባቸውን ሰነዶችና አባሪዎች ጨምሮ፤

I. የአማካሪው ድርጅት አጭር ድርጅታዊ መግለጫ (ቅጽ ቁ 2፣ንኡስ አንቀጽ (ለ))
- **ለሙሉ መወዳደሪያ ሀሳብ ብቻ፡** የአማካሪ ድርጅት አጭር መግለጫ እንዲሁም አማካሪዎቹ ስላላቸው የቅርብ ጊዜ የስራ ልምድ መግለጫ እና ድርጅቱ የሽርክና ማህበር ከሆነ የሁለቱም ሽሪኮች ድርጅታዊ መግለጫ እንዲሁም ተመሳሳይ የስራ ልምድ ማለትም በንኡስ አንቀጽ (ሀ) እና (ሐ) ቅጽ ቁ 2 መሠረት መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለእያንዳንዱ የስራ ምድብ መግለጫው በስራ መደቡ የሚሳተፉ ንዑስ አማካሪዎች/ሙያተኛ ሰራተኞች ስም፣ የስራ መደቡ ላይ የሚቆዩበት ጊዜ፣ የውሉ መጠን እንዲሁም አማካሪው የሚኖረውን የስራ ሚና ማሳየት ይኖርበታል፡፡ የሚቀርበው መረጃ አማካሪው ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጋር የፈፀማቸውን በህጋዊ መልኩ በድርጅትነት ወይም በተቋምነት ወይም ሽርክና ስራ ምድቦች ተግባር ብቻ የተመለከተ መሆን አለበት፡፡ በግል በሚሰሩ የሙያ ሰራተኞች ወይም ከሌሎች የአማካሪ ተቋማት ጋር የተከናወኑ የማማከር ስራዎች የአማካሪው የራስ ልምድ ተደርገው አይቀርብም፡፡ ሆኖም በግል በእንደዚህ አይነቶቹ ተግባራት የተሰማሩ የሙያ ሰራተኞች በሚያቀርቡት ካሪኩለም ቪቴ ላይ የስራ ልምዳቸውን ሊጠቅሱት ይችላሉ፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጥያቄ ካቀረበ የስራ ልምድ ተብሎ ስለቀረበው ማስረጃ አማካሪዎች ማረጋገጫ ለማቅረብ ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡
- **ጠቅለል ላለ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ**: ከዚህ በላይ የተጠቀሰው መረጃ አያስፈልግም፡፡ እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ሐ) ቅጽ ቁ 2 ጥቅም ላይ አይውሉም፡፡

II. በቢ.ጋሩ (ቅጽ ቁ 2 እና ንዑስ አንቀጽ (ሠ)) የሚኖሩ አስተያየቶች እና ሃሳቦች
- **ለሙሉ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ብቻ፡-** በቢ.ጋሩ የሚኖሩ አስተያየቶች እና ሃሳቦች ማለትም የስራ ምድቡ ጥራት እና ውጤታማነትን ለማሻሻል የሚቀርቡ የአስተዳዳር ድጋፍ፣ የጽ/ቤት ቦታ፣ የአካባቢ ትራንስፖርት፣ መሳሪያ፣ ዳታ ወዘተ በግዥ ፈፃሚው የሚቀርቡት (ቅጽ ቁ 3 ክፍል 4)
- **ጠቅለል ላለ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ**: ንዑስ አንቀጽ (ሠ) እና (ረ) ቅጽ ቁ 2 ጥቅም ላይ አይውልም፡፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አስተያየቶች እና ሃሳቦች ካሉ በአሰራር ዘዴ እና ሁኔታ መካተት ይኖርባቸዋል፡፡ (የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ 18.2 (ሐ) እና (2) ይመልከቱ)

III. በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ /ITC/ አንቀጽ 23.2 በተጠቀሰው ሁኔታ መሰረት ኩባንያው/የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበር፣ የጊዜያዊ ህብረትን በመወከል በጨረታ ሰነዱ የሚፈርም ግለሰብ ተገቢ እና የተረጋገጠ የውክልና ስልጣን በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

IV. የአማካሪውን የፋይናንስ አቋም ለማረጋገጥ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ አንቀጽ 15.2 የተጠቀሱትን ሰነዶች፤

V. በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ መሰረት አማካሪው ከዚህ በፊት በተሰጠው ውል መሰረት ስራዎቹን በአግባቡ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እና በተመደበው በጀት ማጠናቀቁን የሚገልጽ የስራ አፈፃፀም ምስክር ወረቀት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ አንቀጽ 16.3 በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር

VI. በሙያተኛ (ሰራተኞች) ወይም በወኪሎቻቸው የተፈረመ ካሪኩለም ቪቴ (በቅጽ ቴ4 ክፍል 4 መሰረት)

(ሐ) የቴክኒክ መወዳዳሪያ ሀሳብ (ክፍል 4፣ ቅጽ ቴ 3) የአሰራር ዘዴ እና የስራ እቅድ እንዲሁም መቅረብ ያለባቸው አባሪዎች እንደሚከተለው ይሆናል፡-

i. **ለሙሉ ቴክኒካዊ መወዳደሪያ ሀሳብ እና ጠቅለል ላሉ ቴክኒካዊ መወዳደሪያ ሀሳብ**፡ በውሉ መሰረት ለሚከናወኑ ስራዎች የአሰራር ዘዴ እና የስራ እቅድ የሚከተሉት ፍሬ ሃሳቦችን ጨምሮ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህም ቴክኒካዊ የስራ አቀራረብ እና ዘዴ፣ የስራ እቅድ እንዲሁም ድርጅታዊ እና የሰራተኞች መርሃ ግብር ለቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ይዘት በቅጽ ቴ 3 ክፍል 4 በቀረበው መሰረት መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የስራው እቅድ በሰንጠረዡ ከተጠቀሰው የስራ ጊዜ ሰሌዳ ጋር አብሮ የሚሄድ መሆን ይኖርበታል፡፡ (ንዑስ አንቀጽ መ የቅጽ ቴ 3) በዚህ ሰንጠረዥ ለእያንዳንዱ የስራ ተግባር የሚፈጀው ጊዜ በባርቻርት ይቀርባል፡፡

ii. ጠቅለል ላለ ቴክኒካዊ መወዳደሪያ ብቻ የስራውን አቀራረብ መግለጫና ዘዴ እንዲሁም አሰራር የሚገልጽ የፅሁፍ መረጃ 10 ገጽ ያልበለጠ መሆን ይኖርበታል፡፡ሆኖም ጠቃሚ መረጃዎችን አያይዞ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይህም ቻርቶችን ስዕሎችን እንዲሁም አስተያየት እና ሃሳቦችን ያጠቃለለ መሆን ይኖርበታል፡፡

iii. የቀረቡት የሙያተኛ (ሰራተኞች) ቡድን ዝርዝር፣ የእያንዳንዱ ሰራተኛ የሙያ አይነት፣ የሚሰጠው የስራ ኃላፊነት እና የስራ ተግባሮቻቸው (በንዑስ አንቀጽ ሠ ቅጽ ቴ 3) መሰረት ይቀርባል፡፡

iv. ለሚኖር የስራ ምድብ ያለው የሰራተኞች የማማከር አገልግሎት ግምት (የውጭ ሀገር እና የሃገር ውስጥ ሙያተኞች) (በንዑስ አንቀጽ ረ ቅጽ ቴ 3 መሰረት) የሚቀርበው ሰራተኞች ዝርዝር በጽ/ቤቱ አካባቢ እና ለመስክ ስራ የሚሰማሩ፣ የውጭ እና የሃገር ውስጥ ሰራተኞች ተብሎ ተለይቶ መቅረብ አለበት፡፡

v. ለሙሉ ቴክኒካዊ መወዳደሪያ ሀሳብ ብቻ የቀረበው የአሰራር ዘዴ እንዲሁም የሚያስፈልገው የሰራተኞች ስልጠና ዝርዝር፣ ቢጋሩ ስልጠናን የሚያመላክት ከሆነ የስልጠናው አይነት ቁምር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

(መ) በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያአንቀጽ 22 መሰረት የጨረታ ዋስትና፤

(ሠ) በሽክርክና፣ በጥምረት ወይም በእሽሙር ማህበር የሚቀርብ ጨረታ ከሆነ በሽርክና ማህበሩ የሚኖር የዳታ ቅጽ፣ ሽርክና ማህበሩ የሚተዳደርበት ወይም ተግባር የሚሆንበት የውል ስምምነት፣ ወይም የሽርክና ማህበሩን ለመመስረት የተፈፀመው እቅድ፣ ረቂቅ ስምምነትን ጨምሮ በተጫራቾች መመሪያ /ተ.መ. / አንቀጽ 4.1 መሠረት መቅረብ ይኖርበታል።

(ረ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ በተጠቀሰው መሰረት በአማካሪው መሞላት እና መቅረብ ያለባቸው ሌሎች ሰነዶች ወይም መረጃዎች

18.3 በሁለት ኢንቨሎፕ የሚቀርብ የመወዳደሪያ ሀሳብ ከሆነ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቡ ማንኛውንም ፋይናንስ ነክ መረጃ መጨመር የለበትም። የፋይናንስ መረጃ የያዘ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ መስፈርቱን ባለማሟላት ተብሎ ውድቅ ሊደረግ ይችላል።

19. የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ ቅጽ እና ይዘት

19.1 የቀረቡት የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳቦች በሙሉ የመወዳደሪያ ሀሳቡ መጠየቂያ ውስጥ ያሉትን መስፈርቶች ሟሟላት ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ከሥራው ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ወጪዎች በሙሉ በዝርዝር ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን በክፍል 4 ውስጥ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን የአማካሪውን ችሎታ የሚያሳዩ የሰነድ መረጃ እና መደበኛ ቅጽ የግድ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

(ሀ) የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማስረከቢያ ሠንጠረዥ (ክፍል 4፣ ቅጽ 1)

(ለ) የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳቡ (ክፍል 4፣ ቅጽ ፋ 2) ከዚህ የሚከተሉትንአስገዳጅ መረጃና እና አባሪዎችን ያካትታል።

I. የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳቡ ጠቅላላ ዋጋ (ንኡስ-አንቀፅ (ሀ) ቅጽ ፋ 2)

II. የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳቡን በሥራ ዝርዝር በመከፋፈል (ቅጽ ኤፍ 2 ንዑስ አንቀጽ (ለ))

III. ክፍያዎቹን መከፋፈል (በጊዜ ላይ ተመስርቶ)፣ (ቅጽ ፋ 2 ንዑስ አንቀጽ (ሐ))

IV. ክፍያዎቹን መከፋፈል (ጥቅል ክፍያ) (ቅጽ ኤፍ 2 ንዑስ አንቀጽ(መ))

V. በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ እንደተገለፀው የሚተኩ ወጪዎችን መከፋፈል (በጊዜ ላይ ተመስርቶ)፣ (ቅጽ ፋ 2 ንዑስ አንቀጽ (ሠ)

VI. የሚተኩ ወጪዎችን መከፋፈል (ጥቅል ክፍያ) (ቅጽ ፋ 2 ንዑስ አንቀጽ (ረ))

19.2 አጠቃላይ የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳቡ ዋጋ ተገቢውን ሁኔታ በመጠቀም በሚከተለው የዋጋ ክፍሎች/ዝርዝሮች ይከፋፈላሉ።

(ሀ) የሠራተኞች ክፍያ እንደአስፈላጊነቱ በስራ ቦታው ውስጥ እና የመስክ ሥራ የክፍያውን መጠን በሚያሳይ መልክ እና

(ለ) የሚተካ ወጪ ለምሳሌ፣ ለዕለት ወጪ (ምግብና መኝታ) ፣ ለትራንስፖርት (በሀገር ውስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ለማንቀሳቀስ እና ለመመለስ)፣ የአገልግሎት እና መሳሪያዎች (ተሽከርካሪዎች፣ የቢሮ ዕቃዎች፣ የቤት

እቃዎች እና አቅርቦት)፣ የሰነዶች ህትመት፣ ትርጉም እና በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ አንቀጽ 19.1 (ለ) (5) ውስጥ የተመለከቱት ሌሎች ወጪዎች

19.3 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ እንደተገለፀው ጠቅላላው የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳቡ ዋጋ በተለያዩ ዝርዝር ስራዎች ይከፋፈላሉ። እንዲሁም በፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳቡ (ቅጽ ፋ 2) ውስጥ ያሉት ተጓዳኝ ሰንጠረገሮች ውስጥ ተካትተው እያንዳንዱ ዝርዝር ስራ ዋጋ መሞላት ይኖርበታል፡፡

19.4 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በግልጽ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳቡ መከፈል ያለባቸውን አጠቃላይ የታክስ ክፍያዎችን በግልጽ ነጣጥሎ ግምት መስጠት ይኖርበታል፡፡ እነዚህም (ለምሳሌ ተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የሽያጭ ታክስ፣ ማህበራዊ ክፍያዎች ወይም የገቢ ግብር በተለይ በአገር ውስጥ በማይኖር የውጪ ሠራተኛ ቀረጦች፣ ክፍያዎች የገቢ ቀረጦች) እና ሌሎች ክፍያዎች በአማካሪው እና በሠራተኞቻቸው ላይ የተጣለውን ክፍያ ያጠቃልላል

19.5 ተስተካክሎ የተሞላው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ቅፅ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በግምገማው ወይም በድርድር ወቅት የተሻሻለውን ጨምሮ፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ለማቀነባበር በሚከተሉት ስምምነቶች ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ እነዚህም፤

(ሀ) የውሉን ዋጋ ከፋፍሎ ማቅረብ የሚቻለው ጠቅላላው የውል ዋጋ ሲሆን ጠቃሚታ ላይ የሚውሉው የማንኛውንም ተጨማሪ አገልግሎት ወይም ወጪ ዋጋ ለመወሰን ሲታሰብና፤

(ለ) ጊዜን መሰረት በማድረግ ስለሚፈፀም ውል የወጪ ግምቱን በቀረቡት ግብአቶች መሰረት ለማስላት ሲያስፈልግ፤ ነው፡፡

19.6 አማካሪው ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ የሚያቀርበውን የዋጋ ቅናሽ በፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማስረከቢያ ሰንጠረዥ ላይ የመተግበሪያ ዘዴው ማመላከት ይኖርበታል፡፡

19.7 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ንዑስ አንቀጽ 1.4 በልዩ ሁኔታ ከተገለፀ የመወዳደሪያ ሀሳቦች በእያንዳንዱ የውል ሰነዶች ወይም ሎቶች (lots) ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የዋጋ ተመን በእያንዳንዱ ሎት በተገለፀው ዝርዝር መሠረት 100 % (አንድ መቶ ፐርሰንት) መሆን ይኖርበታል፡፡ ከአንድ ውል በላይ ማንኛውም የዋጋ ቅነሳ ለማቅረብ የሚፈልጉ አማካሪዎች በፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳባቸው መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡ የሚደረግ የዋጋ ቅነሳ በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 19.6 መሠረት የሚቀርብ ሲሆን ለሁሉም ሎቶች የሚቀርብ የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ በተመሳሳይ ሰዓት መቅረብና መከፈት ይኖርበታል፡፡

19.8 የውሉ አይነት በልዩ የውል ሁኔታዎች (ል.የው.ሁ) ይገለጻል፡፡

20. የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ የገንዘብ አይነት እና ክፍያ

20.1 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በልዩ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር አማካሪው ለማማከር አገልግሎት ለሚያቀርባቸው የማማከር አገልግሎቶች ዋጋው በኢትዮጵያ ብር መቅረብ ይኖርበታል፡፡

21. የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

21.1 የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከጠቀሰው የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ማስረከቢያ ቀነ-ገደብ በኋላ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ውስጥ ለተገለጸው ጊዜ ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡ ለአጭር ጊዜ የሚያገለግል የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ መስፈርት የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ ግዥ ፈጻሚው የመንግስት መ/ቤት ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡ በዚህ ወቅት አማካሪዎች በጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ የጠቀሷቸው ሙያተኞች (ሠራተኞች) መኖራቸውን ያረጋግጣል፡፡ ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት በዚህ የጊዜ ገደብ ውሰጥ ድርድሮች እልባት እንዲያገኙ የተቻለውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል፡፡

21.2 በተለየ ሁኔታ ወይም በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ የአገልግሎት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ግዥ ፈጻሚው የመንግስት መ/ቤት አማካሪዎች የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ እንዲያራዝሙለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የሚቀርቡት ጥያቄዎች እና መልሶች በጽሑፍ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

21.3 የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ በማንኛውም ምክንያት ማራዘም የማይፈልጉ አማካሪዎች ያስረከቡት የጨረታ ዋስትና ሳይወረስ ወዲያውኑ ከጨረታው ውድቅ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

21.4 ግዥ ፈጻሚ አካሉ የሚያደርገውን የጨረታ ጊዜ ማራዘም ተግባር የተቀበሉ አማካሪዎች ስምምነታቸውን በጽሑፍ መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ አማካሪዎች የአገልግሎት ዘመኑ እንዲራዘም ሲጠይቁ በጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ የጠቀሷቸው ሠራተኞች መኖራቸው እንዲሁም ለተራዘመ ጊዜ ከአማካሪው ጋር ሥራቸውን እንደሚቀጥሉ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ያለውን የአገልግሎት ዘመን እንዲሁም ያስረከቡትን የጨረታ ዋስትና ማራዘም ይኖርባቸዋል፡፡

21.5 የአገልግሎት ዘመኑን ማራዘም የማይፈልግ አማካሪ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ያቀረበውን የማራዘሚያ ጥያቄ እንዳልተቀበለ ታሳቢ ተደርጐ ከጨረታው ሂደት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

22. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና

22.1 መ/ቤት በተለያዩ ምክንያቶች አስፈላጊነቱን መ/ቤቱ አምኖበት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ የጨረታ ማስከበሪያ እንደሚያስፈልግ ካልተለገለጸ በስተቀር የጨረታ ማስከበሪያ ላይጠየቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የመንግስት መ/ቤቱ የጨረታ ማስከበሪያ መጠየቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ በኤሌክትሮኒክ ወይም ኤሌክትሮኒክ ባልሆነ ግዥ ሥርዓቱ ይሆናል፡፡

22.2 የጨረታ ዋስትና በአማካሪው ምርጫ በሚከተሉት መልክ ሊቀርብ ይችላል፡-

(ሀ) በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና

(ለ) የማይሻር ሌተር ኦፍ ክሬዲት

(ሐ) እውቅና ካለው ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም የተሰጠ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ፡ ሁሉም ህጋዊ ከሆኑ ሀገራት ወይም ሀገር ታማኝነት ወይም እውቅና ካላቸው ምንጮች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡የጨረታ ዋስትናው በክፍል 4 በተገለፀው የጨረታ ዋስትና ቅጽ ወይም በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተረጋገጡት ሌሎች ተመሳሳይ ቅጾች መቅረብ ይችላል፡፡ በማንኛውም መልኩ የሚቀርበው ቅጽ የአማካሪውን ሙሉ ስም መያዝ ይኖርበታል፡፡ የጨረታው ዋስትና ከጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ማስረከቢያ ጊዜ በኃላ ለ28 ቀናት ያገለግላል፡፡ ይህ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አገልግሎት ማብቂያ ጊዜ የሚራዘም ከሆነ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

22.3 በሽክርክና ማህበር በኩል የሚቀርብ የጨረታ ዋስትና በሽርክና ማህበሩ ስም የሚቀርብ ይሆናል። ሽርክና ማህበሩ በህጋዊ መልኩ የተቋቋመ እስከሆነ ድረስ፡፡ ካልሆነ ግን የሽርክና ማህበሩ አባላት ከሆኑት ወገኖች በእያንዳንዳቸው ስም መቅረብ ይኖርበታል፡፡በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀፅ 22.7 መሠረት የሚፈፀሙ የጨረታ ዋስትና ጥሰቶች በሁሉም የሽርክና ማህበር አባላት ላይ ማዕቀብ በመጣል ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

22.4 የጨረታ ዋስትና ያልቀረበለት ማንኛውም የጨረታ መወዳደሪ ሀሳብ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እንዳልተሟላ ታሳቢ በማድረግ ውድቅ ያደርገዋል፡፡

22.5 ጨረታውን ያላሸነፉ አማካሪዎች የሚያቀርቡት የጨረታ ዋስትና ለአማካሪዎች በተቻለ ፍጥነት ሊመለስላቸው ይገባል፡፡

(ሀ) ጨረታውን ያሸነፉ አማካሪዎች ያስያዙት የጨረታ ዋስትና ውሉን ሲፈራረሙ እና አስፈላጊውን የውል ማስከበሪያ ዋስትና ሲያቀርቡ በተቻለው ፍጥነት ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡

22.6 የጨረታ ዋስናት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊወረስ ይችላል፡-

(ሀ) ተጫራቹ በጨረታ ማቅረቢያ ሰነድ ውስጥ በተጠቀሰውና ጨረታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ከጨረታው ከወጣ፣ ወይም በመመሪያው የተጠቀሱ ሌሎች የጨረታ ዋስትናን የሚያስወርሱ ጉዳዮች ሲፈጸሙ ወይም

(ለ) አሸናፊው ተጫራች ቀጥለው የተመለከቱትን ሳይፈፅም ከቀረ፡-

I. ጨረታው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ አሸናፊ ተጫራች መሆኑ በፅሑፍ ተገልጸለት ውል ለመዉሰድ ወይም የውል ማስከበሪያ ለማስያዝ ፈቃደኛ ካልሆነ፣

II. ተጫራቹ የሂሳብ እርማት ተደርጎ ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆነ፤

23. የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ ቅፅና አቀራረብ

23.1 በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ ላይ በሚጠየቀው መሰረት ተጫራቾች የቴክኒክና የፋይናንስ የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን ለይተው ለየብቻ ማቅረብ ይኖባቸዋል፡፡

መ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አቀራረብና አከፋፈት

24. የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ የማስረከቢያ ቀነ-ገደብ

24.1 የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ከማለፉ በፊት መቅረብ አለበት፡፡

24.2 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በራሱ ምርጫ የጨረታ ማስረከቢያ ቀነ-ገደብን ሊያራዝመው ይችላል፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጨረታውን የመወዳደሪያ ሀሳብ የማስረከቢያውን ቀን ሲያራዝም በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 8 መሰረት ያሻሽላል፡፡ የማስረከቢያ ቀነ-ገደብ ከመራዘሙ በፊት የነበሩት የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት እና የአማካሪ ግዴታዎች የማስረከቢያ ቀን ሲራዘም የሚኖራቸው መብት እና ግዴታ በተራዘመው የጊዜ ገደብ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

25. ዘግይተው የሚቀርቡ የመወዳደሪያ ሀሳቦች

25.1 ግዥ ፈጻሚው የመንግስት መ/ቤት በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 24 መሰረት ከጨረታው ማቅረቢያ ቀነ-ገደብ በኋላ የሚቀርቡ ማናቸውም የጨረታ ሰነዶች ተቀባይነት የላቸውም፡፡

26. ከጨረታው መውጣት፣ መተካትና የጨረታ የመወዳሪያ ሀሳብ ማሻሻል

26.1 አማካሪው የሚያቀርባቸውን የመወዳደሪያ ሀሳቦች የጨረታ መዝጊያ የጊዜ ገደብ ከመደረሱ በፊት መውጣት፣ መተካትና የጨረታ የመወዳሪያ ሀሳብ ማሻሻል ይችላል።

26.2 ተጫራቹ የመጫረቻ የመወዳደሪያ ሀሳብ ካስገባ በኋላ ጨረታው በአየር ላይ በሚቆይበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ከጨረታው ሊወጣ፣ የመጫረቻ ሰነዱን ሊተካ ወይም ሊያሻሽል ይችላል፡፡

26.3 በአማካሪው የጨረታ ማስረከቢያ ሠንጠረዥ ወይም የተደረጉት ማናቸውም ማሻሻያዎች ላይ የጨረታው የመወዳደሪያ ሀሳብ የማስረከቢያው የመጨረሻ ቀን እንዲሁም የጨረታው የመወዳደሪያ ሀሳብ የአገልግሎት ማብቂያ ቀን ተብሎ በተጠቀሰው ጊዜ መካከል ምንም አይነት የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ ከጨረታው ሂደት መውጣት፣ መተካት ወይም ማሻሻል አይደረግበትም፡፡

27. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አከፋፈት

27.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚከተሉትን የጨረታ አከፋፈት ሥነ ሥርዓት መከተል አለባቸው፡፡

ሀ) በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የሚደረግ ማንኛውም የጨረታ አከፋፈት ተጫራቾች በአካል መገኘት ሳያስፈልግ የኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ዘዴ በመጠቀም መከናወን አለበት፡፡

ለ) የህዝብ ቁልፍ መጠበቂያ ሥርዓት ተግባራዊ እንከሚሆን ድረስ ለጨረታ አከፋፈት ዓላማ ማንኛውም ተጫራች በኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱ የተሰጠውን የግል የሚስጥር ቁልፍ በጨረታ ሰነዱ ላይ በሚገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለመንግስት መ/ቤቱ ማጋራት አለበት፡፡ የግል የሚስጥር ቁልፉን ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ለመ/ቤቱ ያላሳወቀ ተጫራች የመጫረቻ ሰነድ ሳይከፈት ከጨረታ ውጪ ይደረጋል፡፡

ሐ) የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የግል የሚስጥር ቁልፍ በወቅቱ ያሳወቁ ተጫራቾችን የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ አከፋፈት ወቅት መክፈት አለባቸው፡፡

መ) በፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) የተደነገገው ቢኖርም የግል የሚስጥር ቁልፋቸውን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት የተጫራቾች ነው፡፡

ሠ) የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጨረታውን አከፋፈት ሁኔታ እና ሂደት የሚያሳይ ቃለ ጉባኤ መያዝና ኤሌክትሮኒክ ሥርዓቱን ተጠቅመው ይፋ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

27.2 የግዥ ፈፃሚው አካል የጨረታ መክፈቻውን ሂደት ቢያንስ የሚከተሉትን አካቶ ይመዘግባል፡፡ የተጫራቹን ስም፣ ከጨረታ የመውጫ፣ የመተኪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄዎችን፣ የጨረታ ዋጋውን ከተቻለ በየጥቅሉ (ካለ)፣ ማንኛቸውንም ቅናሾችና አማራጭ የዋጋ ሀሳቦች፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና መኖርና ያለመኖር፣

27.3 ማንኛውም በጨረታ መክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ወቅት ያልተከፈተና ያልተነበበ የጨረታ ሰነድ ለቀጣይ ግምገማ ሊቀርብ አይችልም፡፡

27.4 የተጫራቾች በገዛ በራሳቸው ፈቃድ መቅረት ጨረታውን ከመክፈት አያስተጓጉለውም፡፡

27.5 የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳብ ተከፍተው የአማካሪው ስም፣ የጨረታ ዋስትና እንዲሁም ሌሎች የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳቦች ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚፈልገው መልኩ እንዲነበቡ ይደረጋል፡፡

27.6 በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 26.1 መሰረት ዘግይተው ከደረሱ የመወዳደሪያ ሀሳቦች በስተቀር በመክፈቻው ቀን ምንም አይነት የጨረታው የመወዳደሪያ ሀሳብ ውድቅ አይደረግም፡፡

27.7 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓት ተጠቅሞ የሚከፍታቸውን የማማከር ጨረታዎች ቃለ-ጉባኤ የሚይዝና ለተወዳዳሪዎች የሚደርስ ይሆናል፡፡

27.8 በጨረታው የመወዳደሪያ ሀሳብ መክፈቻ ዕለት ተከፍቶ ያልተነበበ የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ ለቀጣይ ግምገማ አይቀርብም፡፡

27.9 በንዑስ አንቀጽ 27.8 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጫራቾች ከጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ውጪ ያሉ በተለያዩ ምክንያቶች የተጠየቁትን የህጋዊነት ሰነዶች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር አካተው ባያቀርቡም ተፈላጊ ሰነዶችን ጨረታው በተከፈተበት ዕለት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ካሟሉ የተፈለገው ሰነድ ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት በሚመለከተው ተቋም የተሰጡ መሆናቸውን በማረጋገጥ በጨረታው እንዲቀጥሉ መደረግ አለበት፡፡

ሠ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ መገምገምና ማነጻፀር

28. ምስጢራዊነት

28.1 የጨረታው ምርመራ፣ ግምገማ ማብራሪያ እና ንጽጽርን የሚመለከቱ መረጃዎች ለአማካሪው ወይም ከጨረታውን ሂደት ጋር ተዛማጅነት ለሌላቸው ግለሰቦች አይገለጽም፡፡ መረጃው በምስጢር ይያዛል፡፡

28.2 ማንኛውም አማካሪ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጨረታውን የመወዳደሪያ ሀሳብ ለመገምገም፣ ለመመርመር እንዲሁም ለማነፃፀር በሚያደርገው ሂደት ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር ከሞከረ ግዥ ፈፃሚው የጨረታውን የመወዳደሪያ ሀሳብ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

28.3 የአማካሪዎች መመሪያ ንዑስ አንቀፅ 29.2 እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከጨረታ መክፈት እስከ ውል መፈራረም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ማንኛውም አማካሪ ከጨረታ ሂደት ጋር በተገናኘ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ማግኘት የሚፈልግ ከሆነ ፍላጎቱን በፅሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

29. በጨረታው መወዳደሪያ ሀሳብ ላይ ማብራሪያ ስለመጠየቅ

29.1 የጨረታው የመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ በሚደረግ ምርመራ፣ ግምገማ እና ንጽጽር ለማገዝ ሲባል ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በራሱ ውሳኔ ማንኛውንም አማካሪ የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳቡን እንዲያብራራለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከቀረበው ጥያቄ ጋር ተያያዥነት የሌለው በአማካሪው የቀረበ ማብራሪያ ተቀባይነት የለውም፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚያቀርበውን የማብራሪያ ጥያቄ ተከትሎ የሚሰጥ መልስ የመንግስት የኤልክትሮኒክ ሥርዓቱን በመጠቀም መሆን አለበት፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፋይናንስ የመወዳደሪ ሀሳቦች ግምገማ በሚያከናውንበት ወቅት በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 32 መሰረት ከታዩት የስሌት ስህተቶች ማስተካከያ ውጪ ማንኛውም በመወዳደሪያ ሀሳቡ የሚቀርብ የዋጋ ወይም የይዘት ለውጥ ወይም ማሻሻያ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

29.2 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ላቀረበው የማብራሪያ ጥያቄ አማካሪው ተገቢውን ማብራሪያ በተፈለገው ቀንና ሰዓት ካልሰጠ በአማካሪው የቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ ውድቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

30. የጨረታው መወዳደሪያ ሀሳብ ምሉዕነት (ብቁነት)

30.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የመወዳደሪያ ሀሳቡን ምሉእነት የሚወስነው በራሱ በጨረታው የመወዳደሪያ ሀሳብ ይዘት መሰረት ነው።

30.2 በከፍተኛ ደረጃ የቀረበውን መመዘኛ መስፈርት የሚያሟላ የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማለትም የውሉ ስምምነቶች፣ ሁኔታዎች እና ዝርዝሮች ጋር የሚጣጣም እንዲሁም ምንም አይነት ጉልህ የሆኑ ልዩነቶችና ግድፈቶች የሌለ ሆኖ ሲቀርብ ነው። ቁሳዊ የሆነ ልዩነት ወይም ግድፈት ማለት፤

(ሀ) ተቀባይነት ካገኘ

I. በሚሰጠው የምክር አገልግሎት ላይ በማንኛውም መልኩ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥር ሲሆን፤

II. ከቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ጋር በማንኛውም መንገድ በማይጣጣም መልኩ በውሉ የተቀመጡትን የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ወይም አማካሪ መብት እና ግዴታዎች የሚገድቡ ሲሆን፤

(ለ) ከፀደቀ የሌሎች አማካሪዎችን የተወዳዳሪነት ባህሪ ሀ.ጋዊ ባልሆነ መልኩ የሚጥስ እና ሚዛናዊ ያልሆነ ተፅዕኖ የሚኖረው ከሆነ

30.3 የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ የጨረታው መጠየቂያ ላይ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች በአግባቡ የማያሟላ ከሆነ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወዲያውኑ ውድቅ ያደርገዋል። በዚህም ሁኔታ አማካሪዎች ማስተካከያ በማድረግ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡን ብቃት ማሻሻል አይችሉም።

30.4 የቀረበውን መመዘኛ መስፈርት በአግባቡ አያሟላም ተብሎ የተወሰነበት የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ምክንያቱ ተገልፆ በማመልከቻ ቃለ-ጉባኤ ላይ በግልፅ መስፈር አለበት።

30.5 ከቀረቡት የመወዳደሪያ ሀሳቦች አንድ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ብቻ መስፈርቱን የሚያሟላ ሆኖ ከተገኘ ወይም ውድቅ ካልተደረገ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ ሙሉ ግምገማ ሊያጠናቅቅና ከአማካሪው ጋር ውል ሊፈራረም ይችላል። ይህ የሚሆነው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አማካሪው ያቀረበውን የውል ዋጋ ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ተቀራራቢ ወይምያነሰ ሆኖ ካገኘው እንዲሁም ቀደም ሲል ግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ያዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ውስጥ ውድድርን የሚገድቡ መስፈርቶች አለመኖሩ እርግጠኛ መሆን ሲቻል ብቻ ነው።

31. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ያለመጣጣምና ግድፈቶች

31.1 የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ በከፍተኛ ደረጃ የጨረታውን መመዘኛ መስፈርት የሚያሟላ ሆኖ ከተገኘ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከፍተኛ ልዩነት የማይፈጥሩ ያለመጣጣሞችና ግድፈቶችን ሊያልፋቸው ይችላል።

31.2 የጨረታው መወዳደሪያ ሀሳቡ በከፍተኛ ደረጃ የመመዘኛ መስፈርት የሚያሟላ ሆኖ ከተገኘ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የታዩ ግድፈቶችንና አለመጣጣሞችን ለማስተካከል የሚያስፈልጉት መረጃዎች እና ሰነዶችን ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ ገደብ ውስጥ አማካሪውን እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል። አማካሪው እንደዚህ አይነቶቹን መረጃዎች እና ሰነዶች በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ ተጠይቆ በወቅቱ ካላቀረበ ጨረታው ውድቅ ሊደረግበት ይችላል።

32. አጠራጣሪ የጨረታ ዋጋዎችና የስሌት ስህተቶች

32.1 ግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት የሚታዩትን የስሌት ስህተቶች በሚከተሉት መሰረት ማስተካከል ይኖርበታል፡

(ሀ) የአንዱ ዋጋ እና ብዛት ተባዝቶ የሚገኝ አጠቃላይ ዋጋ እንዲሁም ከአንድ ነጠላ ዋጋ መካከል ልዩነት ካለ የነጠላ ዋጋ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ተደርጐ አጠቃላይ ዋጋ ይስተካከላል፡፡ ይህም ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በነጠላ ዋጋ ላይ ዴሲማል ነጥብ ያረፈበት ቦታ ግልጽ የሆነ ስህተት እንዳለበት ሃሳብ ከሠጠ ነው፡፡ በእንደዚህ አይነቶች ሁኔታዎች የዋጋ ተመን የተሰጣቸው ጠቅላላ ዋጋ ተፈፃሚነት እንዲኖረው ተደርጐ የአንድ ነጠላ ዋጋ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

(ለ) ንዑስ ድምሮች ተደምረው ወይም ተቀንሰው የሚመጣው ጠቅላላ ድምር ስህተት ካለው ንዑስ ድምሮቹ የበላይነት ያላቸው ሲሆን ጠቅላላው ድምር በዚሁ መሠረት እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

(ሐ) በአጋዝ እና በፊደል መካከል ልዩነት ካለ በፊደል የተፃፈው ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ ይህም በአጋዝ የተፃፈው የስሌት ስህተት ከሌለው ነው፡፡ በእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ በአጋዝ የተፃፈ በ (ሀ) እና (ለ) መሰረት እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

32.2 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በስሌት ላይ የታዩ ስህተቶችን ያስተካክላል፡፡ የተስተካከሉትንም ወዲያውኑ ሳይዘገይ ለአማካሪው ያሳውቃል፡፡ አማካሪው የተደረጉ ማስተካከያዎችን በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተጠቀሰው መሠረት ማስታወቂያው ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ መቀበሉን ያረጋግጣል፡፡ የተደረጉ ማስተካከያዎች በግልጽ በፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ ይገለፃሉ፡፡

32.3 አማካሪው የተደረጉ ማስተካከያዎችን ካልተቀበለ ወይም በሒሳብ ማስተካከያው የማይስማማ ከሆነ የጨረታ ማስከበሪያው ተወርሶ ከጨረታው እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ የተደረገው የሂሳብ ስሌት አማካሪው በመክፈቻ ወቅት ካቀረበው የንባብ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ ወደ ላይም ሆነ ወደ ታች ከ3% (ሶስት በመቶ) ከበለጠ ከውድድር ውጭ ይሆናል፡፡

33. የተሰበረ ወይም የተጋነነ የጨረታ ዋጋ

33.1 የምክር ግዥን በተመለከተ ከመሥሪያ ቤቶች በሚቀርብለት ጥያቄ መነሻ ባለስልጣኑ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በማዕከል በሚከናወን የገበያ ዋጋ ጥናት መሰረት በሚገኘ የገበያ ዋጋ ጋር በአንጻራዊነት ሲታይ የቀረበው ዋጋ ከ10% (አስር በመቶ) የበለጠ ሲሆን እንደተጋነነ የጨረታ ዋጋ እንዲሁም የቀረበው ዋጋ ከ20% (ሃያ በመቶ) ያነሰ ሲሆን እንደተሰበረ የጨረታ ዋጋ ይቆጠራል፡፡

34. ልዩ አስተያየት (Margin of preference)

34.1 ልዩ አስተያየት ለሀገር ውስጥ (ለኢትዮጵያውያን) አማካሪ ኩባንያዎች ይሰጣል፡፡

34.2 የሀገር ውስጥ (ኢትዮጵያውያን) አማካሪ ኩባንያዎች በፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ ላይ የዋጋ ንጽጽር ሲደረግ የሚሰጥ ልዩ አስተያየት መጠን 7.5 በመቶ ነው፡፡

34.3 ለምክር አገልግሎት የሚሳተፉ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ተመራጭ እንዲሆኑ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

(ሀ) ኩባንያው በኢትዮጵያ የተቋቋመ መሆን ይኖርበታል፡፡

(ለ) ከኩባንያው ካፒታል 50 በመቶ በላይ በኢትዮጵያ ተፈጥሯዊ ወይም የህግ ሰውነት በተሰጠው መ/ቤትየተያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

(ሐ) ከኩባንያው የቦርድ አባላት ከ50 በመቶ በላይ የኢትዮጵያ ዜግነት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

(መ) ከኩባንያው ቁልፍ ሰራተኞች መካከል ቢያንስ 40 በመቶ የኢትዮጵያ ዜግነት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

34.4 የጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት ተዛማጅነት ባላቸው ህጐች የተቋቋሙ ከሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚወዳደሩ የሀገር ውስጥ አማካሪዎች ጋር ለሚደረግ ውድድር 5% (አምስት በመቶ) ልዩ አስተያየት እድል ይሰጣቸዋል፡፡

35. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ

35.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአማካሪው የቀረበው የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 18 መሰረት የተጠቀሱትን በሙሉ ማቅረቡን በማረጋገጥ ምርመራ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በአማካሪው የቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ በመጠየቂያ ውስጥ ከተጠቀሰው አስተዳደራዊ ፍላጎቶች ጋር እንደሚጣጣም ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

35.2 የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳቡ ከተከፈተበት ጊዜ ጀምሮ ጨረታው ለአሸናፊ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ አማካሪዎች የቴክኒክ እና/ወይም የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብን በሚመለከት ጉዳይ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጋር መገናኘት የለባቸውም፡፡ አማካሪዎች ግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት በሚያደርገው የምርመራ ተግባር ያልተገባ ተጽእኖ ለማድረግ ሙከራ የሚያደርጉ ከሆነ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የመወዳደሪያ ሀሳባቸውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

35.3 ግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤቱ የሚቀርብለት የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ መስፈርቱን አላሟላም በማለት ውድቅ የሚያደርገው፡-

(ሀ) አማካሪዎች በጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ በኩባንያው/ሽርክና ማህበር/ ጊዜያዊ ህብረት ወክሎ የፈረመው ግለሰብ የተረጋገጠ የውክልና ስልጣን ካላቀረቡ (በተጫራቾች መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 13.5 መሰረት)

(ለ) የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳቡ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ አንቀጽ 11.1 በተገለፀው ቋንቋ ካልተፃፈ

(ሐ) አማካሪዎች የተፈረመበት እና በግልጽ ቀን የተፃፈበት የጨረታ ዋስትና ካላቀረቡ

(መ) የጨረታ ዋስትና በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያአንቀጽ 22 መሰረት ካልቀረበ

36. የመወዳደሪያ ሀሳብ ህጋዊነት፣ የሙያ፣ የቴክኒክና የፋይናንስ ተቀባይነት

36.1 የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ ሁሉንም የግድ መቅረብ ያለባቸው ሰነዶች መቅረባቸው ከተረጋገጠ በኋላ አማካሪው መስፈርቶችን ማሟላቱን በማረጋገጥ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እያንዳንዱን የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ ህጋዊነት፣ የቴክኒክ፣ የሙያ እንዲሁም የፋይናንስ ተቀባይነት ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ውሳኔውን ተከትሎ የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳቡ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ላይ በቀረቡት መስፈርቶች መሠረት የሚያሟላ ወይም የማያሟላ በማለት ይመድባል፡፡

37. ህጋዊ ተቀባይነት

37.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የቀረበለት የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ መስፈርቱን አላሟላም በማለት ውድቅ የሚያደርገው፡-

(ሀ) አማካሪው በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያንዑስ አንቀጽ 4.2 የተጠቀሰው ዜግነት ከሌለው

(ለ) አማካሪው በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያአንቀጽ 5 በተጠቀሰው መሠረት የጥቅም ግጭት እንዳለበት ከተረጋገጠ

(ሐ) አማካሪው በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያአንቀጽ 4.5 (ለ) (1) መሰረት አገልግሎቱ ያላበቃ ህጋዊ ንግድ ፈቃድ እንዲሁም የተሰማራበት የንግድ ዝርዝር አይነት ካላቀረበ

(መ) አማካሪው በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 4.6 መሰረት የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ካልተመዘገበ

(ሠ) የሀገር ውስጥ አማካሪዎች ከታክስ ባለስልጣን የተሰጣቸው የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ካላቀረቡ (በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ አንቀጽ 4.5) (ለ) (2) በተጠቀሰው የውል ዋጋ በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 4.5 (ለ) (2) መሠረት

(ረ) የሀገር ውስጥ አማካሪዎች በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 4.5 (ለ)(3) መሰረት በታክስ ባለስልጣን የተሰጣቸውን የወቅቱን ግብር የተከፈለበት የምስክር ወረቀት ካላቀረቡ

(ሰ) የውጭ አማካሪዎች በተመሰረቱበት ሀገር የተሰጣቸው የድርጅታቸው የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የንግድ ፈቃድ በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያአንቀጽ 4.6 (ሐ) መሰረት ካላቀረቡ

(ሸ) አማካሪዎች በማንኛውም የመንግስት የግዥ ተግባራት እንዳይሳተፉ የእገዳ ውሳኔ ከተጣለባቸው ማለትም በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያአንቀጽ 4.3 መሰረት የውል ጥሰት በመፈፀማቸው ውሳኔ ከተላለፈባቸው

(ቀ) በሽርክና ማህበር ለሚቀርቡ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቦች አማካሪዎች በሽርክና ማህበር ያለውን ዳታ፣ ሽርክና ማህበሩ የሚተዳደርበት ደንብ ወይም ሽርክና ማህበር ለማቋቋም ስላለው እቅድ የሚገልጽ ደብዳቤ፣ የስምምነት ረቂቅ በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 4.1 መሰረት ካላቀረቡ

(በ) የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ያላቸውን ሰዎች የማሳወቂያ ፎርም በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 4.8 መሰረት ሞልቶ ካላቀረቡ

(ተ) በተጫራቾች መመሪያ አንቀጽ 4.9 ላይ ከተጠቀሱት የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ያላቸው ተጫራቾች ሊያሟሉ ከሚችሉት ቅድመ ሁኔታዎች አንዱን ማሟላት ካልቻሉ፣

(ቸ) የሚቀርቡ የተጠቃሚ ባለቤትነት መብትን የሚገልጹ መረጃዎች ሀሰተኛ ያልተሟሉና ትክክለኛነት የሚጎላቸው መሆናቸው በመ/ቤቱ ከተረጋገጠ፣

38. ፕሮፌሽናል ተቀባይነት

ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚቀርብለት የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ መመዘኛ መስፈርትን አላሟላም በማለት ውድቅ የሚያደርገው፡-

(ሀ) አማካሪው በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠዥ አንቀጽ 4.5 (ለ) (4) መሰረት ተዛማጅነት ያላቸው የሙያ ትግበራ ማረጋገጫ ካላቀረበ

(ለ) አማካሪው በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ አንቀጽ 14.1 መሠረት ከሙያ መመዘኛ መስፈርት እና ብቃት ተያዥነት ያላቸው ጉዳዮች በአንቀጹ ለተጠቀሰው ጊዜ የማረጋገጫ ቅጽ ካላቀረበ

(ሐ) አማካሪው የአማካሪው ማረጋገጫ ቅጽ በሚጠይቀው መሠረት ሙያተኞቹ የተሰጠውን ውል በአስተማማኝ ሁኔታ ለመፈፀም የሚያስችል ብቃት እንዲሁም የቡድን ሥራ ክህሎት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ መረጃ ካላቀረበ

(መ) አማካሪው ስላሉት ሙያተኞች (ሠራተኞች) ተፈላጊ መረጃ (CV) በሠራተኞቹ ወይም በወኪሎቻቸው አማካኝነት አስፈርሞ ካላቀረበ

39. የቴክኒክ ተቀባይነት

ግዥ ፈጻሚ መንግስታዊ መ/ቤት የሚቀርብለት የጨረታ የመወዳደሪያ ሀሳብ መመዘኛ መስፈርቱን አላሟላም በማለት ውድቅ የሚያደርገው፤

(ሀ) አማካሪው በቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳብ ማስረከቢያ ቅጽ ላይ የሚሠጠውን የምክር አገልግሎት በተመለከተ የሚገልጽ ማረጋገጫ ለማቅረብ ካልቻለ

(ለ) አማካሪው በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ የተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ ያከናወቸው አግባብነት ያላቸው የማማከር አገልግሎቶችበጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተጠቀሰው ብዛትና ወቅት ማከናወኑን ማረጋገጫ ካላቀረበ፡፡

(ሐ) አማካሪው ከዚህ በፊት በአጥጋቢ መልኩ ስላከናወናቸው የውል ተግባራት በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ አንቀጽ 16.3 መሠረት በተጠቀሰው በጀት እና ጊዜ አንፃር የሚገልጽ ማረጋገጫ ካላቀረበ

(መ) አማካሪው የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳብ ቅፅ ቁ 3 በክፍል 6 በተጠቀሱት ሁኔታዎች ሞልቶ ካላቀረበ

40. የፋይናንስ ተቀባይነት

ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት በሚከተሉት ምክንያቶች የሚቀርብለትን የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

(ሀ) አማካሪው በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 15.2 ለተጠቀሰው ጊዜ እንዲሁም በክፍል 3 በተጠቀሰው የምርመራ ዘዴ እና መስፈርት መሠረት የኩባንያው የፋይናንስ መግለጫ በተመሰከረለት ኦዲተር አስመርምሮ ካላቀረበ

(ለ) በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ አንቀጽ 15.2 (ለ) በሚያስፈልገው መሠረት ያለውን የፋይናንስ አቅም የሚያረጋግጡ ተጨማሪ ሌሎች ሰነዶች ካላቀረበ

(ሐ) በክፍል ሶስት በተጠቀሰው አመታዊ አማካይ የገንዘብ ዝውውር (የምርመራ ዘዴ እና መስፈርት በጨ.ዝ.መ.ሰ. በልዩ ሁኔታ ከተገለጸው መጠን ዋጋ ከፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳቡ የሚልቅ ሆኖ ካልተገኘ)

መ. አማካሪው በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 19 መሠረት የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ ዋጋ ማስላት ካልቻለ

ሠ. አማካሪው በጨ.ዝ.መ.ሰ የአማካሪዎች መመሪያ አንቀጽ 20 መሠረት የጨረታ ዋጋውን በተገለጸው የገንዘብ አይነት መሠረት ካላቀረበ

41. የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ

41.1 ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት እስከዚህ የምርመራ ሂደት ድረስ ብቁ ናቸው ተብለው የተገመገሙትን እያንዳንዱን የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳብ ይገመግማል፡፡

41.2 ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የቀረቡት የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳቦች የውሉ ስምምነቶች እና ሁኔታዎች፣ የግምግማ መመዘኛ መስፈርቶች፣ ንዑስ መመዘኛ መስፈርቶች እንዲሁም በክፍል ሶስት የተጠቀሱትን ነጥቦች የሚያሟሉ መሆናቸውን ይገመግማል፡፡ የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳቡ ከተጠቀሱት መመዘኛ መስፈርቶች ውጪ በሌላ መመዘኛ መስፈርት አይገመገምም፡፡ መስፈርቱን በተገቢው ሁኔታ ያሟሉ እያንዳንዳቸው የመወዳደሪያ ሀሳቦች የቴክኒክ ውጤት ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ የግምገማ ደረጃ የሚቀርቡት የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳቦች በየመወዳደሪያ ሀሳቡ መጠየቂያ የተጠቀሱት ጠቃሚ የተባሉ ዋና ዋና ነጥቦች በተለይ በቢጋር የተጠቀሱትን መስፈርቶች ወይም

በክፍል ሶስት የተጠቀሰውን ዝቅተኛ የቴክኒክ ውጤት ካላገኙ ውድቅ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

41.3 ለፋይናንስ ግምገማ የሚደርሱ የመወዳደሪያ ሀሳቦች የሚወሰኑት በክፍል ሶስት በተገለጸው የአሰራር ዘዴ እና መስፈርት መሠረት ይሆናል፡፡

41.4 የቴክኒካል ግምገማ ውጤት በጨረታው ሂደት ለተሳተፉ አማካሪዎች በሙሉ በጽሁፍ ይገለጽላቸዋል፡፡

41.5 የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ ከተጠናቀቀ በኋላ የቴክኒክ መመዘኛ መስፈርቱን ባለሟሟላታቸው ምክንያት ከጨረታ ውጪ እንዲሆኑ ለተደረጉ አማካሪዎች ውድቅ የተደረጉበትን ምክንያት መግለጽ እንዲሁም ያስያዙት የጨረታ ዋስትና ተመላሽ ተደርጎ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ የያዘ ኢንቨሎፕ አይከፈትም፡፡

41.6 ተሸንፈው ከጨረታ ውጪ የሆኑት አማካሪዎች በግምገማው ሂደት ላይ ወይም በግምገማ ውጤት ላይ ያላቸውን ቅሬታ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

41.7 በቴክኒክ ግምገማው ላይ አማካሪው ቅሬታ ካቀረበ ቅሬታው የመጨረሻ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ የጨረታ ዋስትና አይመለስላቸውም፡፡

41.8 የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቡን የሚገመግሙት ባለሙያዎች የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቡ ግምገማ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ አይቀርብላቸውም፡፡

42. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ አከፋፈት

42.1 በቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ተቀባይነት ያገኙ አማካሪዎች የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦቹ የሚከፈቱበትን ሰዓት እና ቦታ በመግለጽ ግዥ ፈጻሚው የመንግስት መ/ቤት የኤሌክትሮኒክ የመንግስት የግዥ ሥርዓትን ወይም ኤሌክትሮኒክ ያልሆነ ዘዴን በመጠቀም ያሳውቃቸዋል፡፡ የፋይናንስ ኢንቨሎፕ አከፋፈት ሂደቱን መከታተል ለሚፈልጉ ሁሉም አማካሪዎች የፅሁፍ ማስታወቂያ በተመሳሳይ ጊዜ ሊላክላቸው እና በቂ ጊዜም ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

42.2 በቴክኒክ ግምገማ ላይ ቅሬታ ከተነሳ ቅሬታው የመጨረሻ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ መከፈት የለበትም፡፡

42.3 የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ የሚከፈተው የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቦች ተቀባይነት ባገኙት አማካሪዎች ሲሆን የመወዳደሪያ ሀሳብ አከፋፈት ሥርዓት እንዲከታተሉ ወይም እንዲገኙ በጽሁፍ ለተገለጸላቸው አማካሪዎች ባለበት ነው፡፡

42.4 የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቦቹ ተገምግመው ተቀባይነት ያገኙት አማካሪዎች የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦቹ ተከፍተው የአማካሪው ስም፣ አማካሪው በቴክኒክ ደረጃ ያገኘውን ውጤት፣ ለጨረታ ያቀረበው አጠቃላይ ዋጋ እና አማካሪው ያቀረበው የዋጋ ቅናሽ እንዲሁም ለዋጋ ቅናሽ ምክንያት የሆኑ የተገለፁ ሁኔታዎች እና ሌሎች ከዋጋ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መረጃዎች

ለአማካሪዎች ይነበብላቸዋል በተጨማሪም የመክፈቻ ቃለ-ጉባኤ እንዲደርሳቸው ይደረጋል

42.5 ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ አከፋፈት ሂደት ቃለ ጉባኤን ይይዛል። ቃለ-ጉባኤው ቢያንስ የአማካሪውን ስም፣ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ላይ የቀረበ ዋጋ እንዲሁም በፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ አከፋፈት ሂደት የተነሱ ነጥቦችን ይይዛል። ቃለ ጉባኤው የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ሥርዓትን በመጠቀም ለሁሉም አማካሪዎች እንዲደርስ ይደረጋል።

43. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ

43.1 ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት እያንዳንዱ የተከፈተውን የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ይገመግማል።

43.2 እያንዳንዱን የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ለመገምገም ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የሚከተሉትን ታሳቢ ማድረግ ይኖርበታል።

(ሀ) የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ ጠቅላላ ዋጋ

(ለ) በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 32 መሠረት ለታዩ የስሌት ስህተቶች የተደረገ የዋጋ ማስተካከያ

(ሐ) የዋጋ ተቀናሽ በመቅረቡ ምክንያት የተደረገው የዋጋ ማስተካከያ

(መ) ከዚህ በላይ በ (ሀ) እና (ለ) በተጠቀሱት ምክንያቶች የቀረበውን መጠን ወደ አንድ ነጠላ ምንዛሬ መቀየር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ

(ሠ) በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያንዑስ አንቀጽ 32 መሠረት በአለመጣጣሞችና ግድፈቶች የተደረጉ ማስተካከያዎች

(ረ) በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 34 መሠረት ለአማካሪዎች ልዩ አስተያየት መስጠት በማስፈለጉ የሚደረጉ ማስተካከያዎች

43.3 በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 32 መሠረት ለተፈፀሙ ስህተቶች ከተደረጉ ማስተካከያዎች በተጨማሪ በቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርቡት ሌሎች ሥራዎች እንዲሁም ዝርዝሮች ውስጥ ዋጋ ካልተሰጣቸው በሌሎች ሥራዎች ዝርዝሮች ዋጋቸው እንደተካተተ ተደርጎ ይታሰባል። አንድ የሥራ ዝርዝር ወይም መደብ በፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ላይ የተሰጠው ዋጋ ከቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ የሚለይ ሆኖ ከተገኘ፣

(ሀ) በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው መሰረት ስራው በአንድ የተወሰነ የጊዜ ሂደት በሚከናወን ውል የሚፈጸም ከሆነ ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት በፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ እና በቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቡ መካከል ያለው የመጠን ልዩነት ለፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ ባለው የዋጋ መለኪያ መሠረት አጠቃላይ መጠን በማስላት አጠቃላይ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ወጪ ማስተካከያ ያደርግበታል።

(ለ) በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው መሰረት የውሉ አጠቃላይ ዋጋ ተገልጾ የሚከናወን ከሆነ ከዚህ አንፃር በፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ ላይ ምንም ዓይነት ማስተካከያ አይደረግበትም። የሚጠቀሱ ዋጋዎች በአማካሪዎች በመጫረቻ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ላይ ከተፈቀደ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 43.2 (መ) መሠረት ወደ አንድ የገንዘብ አይነት ይቀየራሉ።

43.4 የቀረበው ዋጋ ለግምገማ ዓላማ ሲባል በዋጋው ላይ ግብር፣ ቀረጥ፣ ክፍያዎች ወይም ተዘማጅነት ባላቸው ሕጐች የሚከፈሉ ክፍያዎችን (እና በውሉ ምክንያት መከፈል ያለባቸው ሂሳቦች) ይጨምራል፡፡ በአማካሪዎች የሚቀርብ ዋጋ የትርጉም፣ የጉዞ፣ የጽሁፍ መሳሪያዎች እና ሌሎች ወጪዎችን ሊጨምር ይችላል፡፡

43.5 የመወዳደሪያ ሀሳቡ መጠየቂያዎች አማካሪዎች ለተለያዩ ሎቶች (lots) የተናጠል (የተለያየ) ዋጋ እንዲያቀርቡ ከፈቀደ እንዲሁም የተለያዩ ሎቶች ለአንድ አማካሪ ከተሰጠ፣ የግምገማው ዘዴ አጠቃላይ ሎቶች ላይ ዝቅተኛ ዋጋ እንዲሁም በፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ማስረከቢያ ሠንጠረዥ የቀረበ የዋጋ ቅናሽ ካለ ታሳቢ ተደርጐ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ እንዲሁም በክፍል ሶስት የግምገማ ዘዴ እና መስፈርት መሠረት ይገመግማል፡፡

44. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ንጽጽር

44.1 የግዥ ፈጻሚውን መ/ቤት መመዘኛ መስፈርት በሚሟላት ከቀረቡት የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦች ይበልጥ ተመራጭ የሆነውን ለመለየት በክፍል ሶስት የመመዘኛ መስፈርትን እና ዘዴ መሠረት ያነጻጽራል፡፡

44.2 ጥራት እና ዋጋን መሠረት በማድረግ የሚደረጉ ንጽጽሮች ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የሚከተሉት የመምረጫ አሰራሮችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

(ሀ) የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቦቹ ተቀባይነት ካገኙት መካከል የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦቹ ከፍተኛ ነጥብ ዝቅተኛ ዋጋ ላቀረበ እንዲሁም ዝቅተኛው ነጥብ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበ ይሰጣል፡፡

(ለ) ለሌሎች አማካሪዎች የሚሰጡ ነጥቦች ባቀረቡት ዋጋ መሠረት ይወሰናል፡፡

(ሐ) የምክር አገልግሎት ግዥ ለመፈጸም በአማካይ ከሚቀርቡ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቦች አጠቃላይ ውጤት የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ 80 በመቶ እንዲሁም ቀሪው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ 20 በመቶ ነጥብ ይኖራቸዋል፡፡

(መ) በቴክኒክ እና በፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ ላይ አጠቃላይ ድምር የላቀ ውጤት ያገኘ አማካሪ የጨረታው አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

44.3 ጥራትን መሰረት በሚያደርግ ምርጫ በቴክኒክ ግምገማው ላይ የላቀ ነጥብ ያገኘው አማካሪ ውጤታማ አማካሪ ተደርጐ ይመረጣል፡፡

44.4 በቋሚ (በተወሰነ) በጀት ላይ በሚደረግ ምርጫ ለግዥው በተመደበ በጀት እርከን ውስጥ ዋጋ ያቀረቡት አማካሪዎች በቴክኒክ እና በፋይናንስ ግምገማ አጠቃላይ ከፍተኛ ነጥብ ያገኙት በአሸናፊነት ይመረጣሉ፡፡

44.5 ዝቅተኛ ወጪን መሰረት በማድረግ በሚከናወን ምርጫ በዝቅተኛነት የተገመገመውን ዋጋ የሚያቀርብ አማካሪ ከቀረቡት አማካሪዎች ውስጥ ዝቅተኛውን ተፈላጊ የቴክኒክ ብቃት በሚሟላት ከተመረጡት አማካሪዎች ውስጥ አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

45. ድርድሮች

45.1 የመወዳደሪያ ሀሳቡ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጽሁፍ አሸናፊውን አማካሪ ያስታውቃል፡፡ እንዲሁም በጨረታ

ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ በተጠቀሰው ቦታ አሸናፊው አማካሪ በውሉ ላይ እንዲደራደር ጥሪ ያስተላልፉለታል፡፡

45.2 ከተመረጡ አማካሪዎች ጋር የሚደረግ ድርድር ይዘት በሚከናወነው የማማከር ሥራ ይዘት፣ ስራውን ለማከናወን ተግባር ላይ የሚውል አሰራር ዘዴ፣ አማካሪው የሚጠቀምባቸው ሙያተኞች አይነት፣ የስራው መርሃ ግብር እና የጊዜ ሰሌዳ፣ የሚከናወኑ ስራዎች፣ ሰራተኞች፣ በመስክ እና መስሪያ ቤት የሚያገለግሉበት ጊዜ፣ አማካሪው ለሚሰጠው አገልግሎት የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎች፤ አማካሪው የሚያቀርባቸው የሪፖርት ይዘት እና የአቀራረብ ሁኔታ እንዲሁም ከአገልግሎቱ አፈፃፀም ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ጉዳዮች በማንሳት ይደራደራሉ፡፡

45.3 የመወዳደሪያ ሀሳቡ መጠየቂያ አስፈላጊነት እንዲሁም አማካሪው ማቅረብ የሚገባው የስራ ጥራት ለድርድር አይቀርብም፡፡

45.4 በአማካሪው ስለቀረበው ዋጋ በግዢ ፈፃሚው መ/ቤት እና በአማካሪው መካከል ምንም አይነት ድርድር አይደረግም፡፡

45.5 ከሌሎች መስፈርቶች ሌላ በቀረቡት ቁልፍ ሙያተኛ ሰራተኞች መሰረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አማካሪዎቹን ከመረጠ በመወዳደሪያ ሀሳቡ በቀረቡት ሠራተኞች መሰረት ውሉን እንዲደራደር ይጠበቃል፡፡ ከውል ድርድሩ በፊት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በመወዳደሪያ ሀሳቡ የቀረቡት የስራ ባልደረቦች በትክክል መኖራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልገዋል፡፡ያልተጠበቀ የስራ መጀመሪያ ቀን ሚጓተት ወይም በቁልፍ ባለሙያ ሰራተኞች የጤና እክል ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በውል ድርድር ጊዜ በመወዳደሪያ ሀሳቡ የተጠቀሱትን ሠራተኞች በሌላ እንዲተኩ አይደራደርም፡፡

45.6 ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ንዑስ አንቀጽ መሰረት ከአማካሪው ጋር የሚደረግ ስምምነት የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ጥቅም የሚጎዳ ወይም ለአንድ ለተወሰነ አማካሪ በመወገን የሌሎችን አማካሪዎች ጥቅም በሚፃረር መልኩ መሆን የለበትም፡፡

46. የድህረ ብቃት ግምገማ

46.1 የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ሰነዶች በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያው በተሰጡት መመዘኛ መስፈርቶች መሠረት በመገምገም አሸናፊው አማካሪ ከተለየ በኋላ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የአማካሪውን ወቅታዊ የብቃት ሁኔታ ለማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የድህረ ብቃት ግምገማ ሊያከናውን ይችላል፡፡

46.2 የአሸናፊው አማካሪ የድህረ ብቃት ማረጋገጫ ግምገማ በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 36 የተዘረዘሩትን መረጃዎች ሊያካትት ይችላል፡፡ ይህም አማካሪው ያቀረባቸው ሰነዶች ስላለው ወቅታዊ የህግ፣ ሙያ ነክ፣ የቴክኒክ እና የፋይናንስ አቋም በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠይቁ ከተገለፁት መመዘኛ መስፈርቶች ጋር ሲነፃፀሩ አጥጋቢ ሆኖ ካልተገኘ ነው፡፡

46.3 ጨረታውን ያሸነፈ አማካሪ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጥያቄ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ማረጋገጫ ሰነዶች ካላቀረበ ወይም አማካሪው ያቀረበው መረጃ እውነተኛ ሆኖ ካልተገኘ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ ውድቅ ይሆናል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሌሎች መመዘኛ

መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጫራቾችን ለመለየት ቀጥሎ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን አማካሪ የመወዳደሪያ ሀሳብ ብቃት በመገምገም ይወስናል፡፡

47. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ መቀበል ወይም አለመቀበል

47.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጨረታው ውጤት ለአሸናፊው ከመግለፁ በፊት ማንኛውም የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የመቀበል ወይም ያለመቀበል፣ እና የጨረታ ሂደቱን ውድቅ የማድረግ እንዲሁም ሁሉንም የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቦች በማንኛውም ወቅት በአማካሪዎች ምንም ዓይነት የኃላፊነት ወይም ተጠያቂነት ተግባር ሳያስከትልበት ውድቅ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

48. በድጋሚ የጨረታ ማስታወቂያ ስለማውጣት

48.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለ2ኛ ጊዜ በሚከተሉት ምክንያቶች በድጋሚ የጨረታ ጥሪ ሊያወጣ ይችላል፡፡

ሀ) የበፊቱ የጨረታ ጥሪ ውጤታማ ካልሆነ ማለትም በአይነት ወይም በፋይናንስ መመዘኛ መስፈርቱን የሚያሟላ ተጫራች ካልተገኘ፤

(ለ) በክልሉ የግዥ አፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 123 መሠረት የቀረበው የጨረታ ዋጋ ከወቅታዊ የገበያ ዋጋ አንጻር ከ10% (አስር በመቶ) የበለጠ ሲሆን እንደተጋነነ በመቁጠር ወይም ከ20% (ሃያ በመቶ) ያነሰ ሲሆን እንደተሰበረ በመቁጠር፣

(ሐ) የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡን በማስመልከት በወጡ አዋጆች እና የግዥ መመሪያዎች መሰረት አማካሪዎች ህጋዊ መመዘኛ መስፈርት ሳያሟሉ ሲቀሩ ወይም የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያውን በማሻሻል ተጨማሪ አማካሪዎችን በጨረታው እንዲሳተፉ ሊያደርጋቸው ይችላል ተብሎ ከታመነበት

(መ) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ውሉን ተፈፃሚ ለማድረግ አዳጋች ሆኖ ከተገኘ

(ሠ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 48.1 (ለ) የተገለፀው ቢኖርም በግምገማ የሚመረጡ አሸናፊዎች የሞሉት ዋጋ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤቱ በትክክለኛና ወቅታዊ የገበያ መረጃ በተዘጋጀ የዋጋ ግምት በጨረታዉ የተሰበረ ዋጋ ያቀረበዉ ድርጅት ወይም ተቋራጭ ባቀረበዉ የተሰበረ ዋጋ መስራት የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ (Conformation Letter) አሸናፊነቱ በተገለጸ በ3 የሥራ ቀናት ዉስጥ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህን ማድረግ ካልቻለ ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ተወርሶ ከዉድድር ዉጭ ይደረጋል፡፡

(ረ) የቀረበው ዋጋ የተሰበረ ከሆነ የሚያስይዙት ከ10 በመቶ የዉል ማስከበሪያ ዋስትና በተጨማሪነት በተሰበረው በእያንዳንዱ ፐርሰንት ልዩነት ላይ 2 በመቶ እየተሰላ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ዋስትና የሚያስይዝ ይሆናል፡፡

(ሰ) የቀረበው ዋጋ የተሰበረ ከሆነ ቅድመ ክፍያ አይፈቀድም፡፡

ረ. ውል ስለመፈፀም

49. አሸናፊ አማካሪን የመምረጫ መስፈርቶች

49.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ ተገቢውን መመዘኛ መስፈርት ካሟሉት አማካሪዎች ውስጥ አሸናፊ አድርጎ ይመርጣል፡፡ ነገር

ግን አማካሪው ውሉን አጥጋቢ በሆነ መልኩ ለማከናወን ብቃቱ እንዳለው ከተረጋገጠ ብቻ ነው።

49.2 የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ ለእያንዳንዱ ሎት(lot) እንዲቀርብ ጥሪ ከተደረገ ውሎቹ ከአሸናፊው ጋር የሚደረጉት በእያንዳንዱ ሎት ነው። ነገር ግን በቀረበው የዋጋ ቅናሽ መሰረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአጠቃላይ የተሻለውን አማራጭ መፍትሄ ሊወስድ ይችላል።

49.3 አማካሪው ከአንድ በላይ ሎቶች እንዲያሸንፍ ከተደረገ ሁሉንም ሎቶች የሚሸፍን አንድ ነጠላ ውል እንዲዋዋል ሊደረግ ይችላል።

50. ከውል በፊት የግዥውን መጠን ስለመለወጥ

50.1 ጨረታው ለአሸናፊ በሚሰጥበት ወቅት ግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት በክፍል 6 የተጠቀሱትን የምክር አገልግሎቶች መጠን የመቀነስ ወይም የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው። ነገር ግን በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ከተጠቀሰው መቶኛ ሂሳብ መብለጥ የለበትም። እንዲሁም በጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ እና የመወዳደሪያ ሀሳቡ መጠየቂያ የቀረቡት ነጠላ ዋጋዎች እና ሌሎች ስምምነቶች እና ሁኔታዎች ላይ ለውጥ ማድረግ የለበትም።

51. የጨረታ ውጤትና አሸናፊ አማካሪን ስለማሳወቅ

51.1 የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የአገልግሎት ጊዜ ከማለቁ በፊት ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ለሁሉም አማካሪዎች በተመሳሳይ ጊዜ በጽሁፍ የጨረታውን ውጤት ያሳውቃል።

51.2 በጨረታው ሂደት ያልተሳካላቸው አማካሪዎች በጨረታው መውደቃቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ሲደርሳቸው የወደቁበትን ምክንያት እንዲሁም ጨረታውን ያሸነፈው አማካሪ ማንነት በመግለጽ ይሰጣቸዋል።

51.3 ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ለአሸናፊ አማካሪዎች የሚሰጣቸው አሸናፊነትን የሚገልጽ ደብዳቤ በአሸናፊ እና በግዢ ፈጻሚ መ/ቤት መካከል የተፈፀመ ውል ተደርጎ መወሰድ የለበትም። በግዥ ፈጻሚው መ/ቤት እና በአሸናፊ አማካሪው መካከል ውል እንደተፈጸመ ታሳቢ የሚደረገው ለግዥ ሂደቱ ግዥ ደንቦች እና ስምምነቶችን የያዘ ውል ሁለቱ ወገኖች ተዋውለው ሲፈራረሙበት ብቻ ነው።

51.4 ለአሸናፊው አማካሪ የሚሰጥ አሸናፊነቱን የሚገልፅ ደብዳቤ የሚከተሉትን መረጃዎች ማካተት ይኖርበታል።

(ሀ) ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡን መቀበሉን፤
(ለ) አጠቃላይ የውሉን ዋጋ፤
(ሐ) አሸናፊው አማካሪ ማቅረብ የሚኖርበት የውል ማስከበሪያ ዋስትና እንዲሁም የውል ማስከበሪያ ዋስትናውን ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን (ቀነ ገደብ)

52. የውል አፈራረም

52.1 ግዥ ፈጻሚውን የመንግስት መ/ቤት የጨረታውን አሸናፊ ከገለጸ በኋላ ለአሸናፊው አማካሪ ውሉን በተቻለ ፍጥነት ይልክለታል፡፡

52.2 አሸናፊው ተጫራች የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ሌላ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር አሸናፊው ተጫራች ማሸነፉ ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ ከ5 የስራ ቀናት በኃላ ባሉት 10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ውሉን መፈረም ይኖርበታል ፡፡

52.3 ግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡን ውጤት ለአማካሪዎች ከገለፀበት ጊዜ ጀምሮ ከ5 የስራ ቀናት በፊት ወይም በጨረታ ሂደቱ አቤቱታ ከቀረበ ውሉን መፈረም የለበትም፡፡

53. የውል ማስከበሪያ ዋስትና

53.1 አሸናፊው ተጫራች በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች /አ.ው.ሁ/ በተፈቀዱት መሰረት አማካሪው የውል ማስከበሪያ ዋስትና በማቅረብ መፈረም ይኖርበታል፡፡ በክፍል 9 የውል ቅጾች የተጠቀሱትን የውል ማስከበሪያ ዋስትና ቅፆች ወይም በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተቀባይነት ባላቸው ሌሎች ቅጾች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

53.2 አማካሪው ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የውል ማስከበሪያ ዋስትና አለማቅረብ ወይም ውሉን አለመፈረም የጨረታ ዋስትናውን ወይም የውል ማስከበሪያ ዋስትናውን ለመውረስ በቂ ምክንያቶች ይሆናሉ፡፡

53.3 ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በሚያደራጇቸው ወይም በሚቆጣጠሯቸው አግባብነት ባላቸው ድርጅቶች በመ/ቤቱ የበላይ የገንዘብ መጠን ተጠቅሶና ተፈርሞ የተሰጣቸው የጨረታ ዋስትና የሥራ አፈፃፀም ዋስትና ወይም የቅድመ ክፍያ ዋስትና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

53.4 አሸናፊው አማካሪ ውሉን ለመፈረም ካልቻለ ወይም ፍላጐቱ ከሌለው ወይም ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የውል ማስከበሪያ ዋስትና ማቅረብ የማይችል ከሆነ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በ2ኛ ደረጃ ውጤታማ ለሆነው አማካሪ ወይም ሌሎች አማካሪዎች ጥሪ በማድረግ እንዲፈርሙ ያደርጋል፡፡ አሸናፊው ተጫራች ውሉን ሳይፈርም ሲቀር ወይም የውል ማስከበሪያ ዋስትና ሳያቀርብ ሲቀር፣ የግዥ ፈፃማው መ/ቤት በጨረታ ውድድሩ ሁለተኛ የወጣውን ተጫራች በመጋበዝ ውል እንዲፈርም ያደርጋል፡፡ይህ ካልሆነ ሦስተኛው የወጣው ተጫራች ያቀረበው ዋጋ የተጋነነ ካልሆነ አሸናፊ ማድረግ ወይም አዲስ ጨረታ ማውጣት ይችላል፡፡

ክፍል 2፡ የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ

ማውጫ

ሀ. መግቢያ 1

ለ. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ 1

ሐ. የጨረታ መወዳደሪ ሀሳብ አዘገጃጀት 2

መ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አቀራረብና አከፋፈት 3

ሠ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ መገምገምና ማነፃፀር 4

ረ. ውል ስለመፈፀም 5

ክፍል 2

የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠነድ /ጨ.ዝ.መ.ሠ/

የአማካሪዎች መመሪያ መለያ	ከአማካሪዎች መመሪያ ጋር የተያያዘ
ሀ. መግቢያ	
አ.መ. 1.1	ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ፡- [የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ስም ይግባ] አድራሻ፡- [የተመዘገበ አድራሻ ይግባ]
አ.መ.1.1	የጨረታው ሰነድ የወጣበት የግዥ ዘዴ፡- [የግዥ ዘዴ ይግባ]
አ.መ.1.2	የፕሮጀክቱ ስም፡- [የፕሮጀክቱ ስም ይግባ] የምክር አገልግሎት ግዥ አይነት፡- [አጠቃላይ የምክር የአገልግሎቶች ግዥ መግለጫ ይግባ]
አ.መ.1.4 እና	የግዥ መለያ ቁጥር .....
አ.መ.1.4	በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ያሉት የሎቶች (lots) ቁጥርና መለያ [የ lot መለያ ቁጥር ይግባ]
አ.መ.4.1 (ሀ)	ግለሰቦች፣ የጋራ ማህበራት፣ ጊዜያዊ ማህበራት ወይም ማህበራት በጋራና በተናጠል ተጠያቂ መሆን አለመሆናቸው ይገለፅ። [ግለሰቦች ወይም የጋራ ማህበራት በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ካልሆኑ " በምትኩ፣የሚከተሉት ልዩ ተጠያቂነቶችና ሀላፊነቶች ለያንዳንዱ ግለሰብ ወይም የጋራ ማህበራት ተግባራዊ እንደሚሆን ይግባ " (በዝርዝር ይብራራ)] በሽርክና፣ በጥምረት ወይም በእሽሙር ማህበር ወይም በማኅበር ያሉ ግለሰቦች ወይም ተቋማት በተናጠልና በጋራ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡
አ.መ.4.5 (ለ) (ii)	ለውሉ ዋጋ እና ከዛ በለይ (መጠኑ ይጠቀስ) ለሚጫረቱ ለአገር ውስጥ ተጫራቾች በግብር ባለስልጣኑ የተሰጠ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይገባቸዋል፡፡
አ.መ.4.5 (ለ)(iv)	አግባብ ያለው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አስፈላጊነት [የሙያ ብቃት ይገለፅ]
አ.መ.4.7	አማካሪ ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ ያለውን ሕጋዊነት በሚከተሉት ማስረጃዎች ማረጋገጥ አለበት ሀ.--------- ለ.--------- ሐ.---------
ለ. የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ	
አ.መ.7.1 እና 9.4	ለጥያቄ ወይም ለማብራሪያ ዓላማዎች ብቻ የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት አድራሻ፡-

የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት	[ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ስም ይግባ]
ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም	[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም ይግባ]
የቢሮ ቁጥር	[ቢሮ ቁጥር ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ]
የመንገዱ ስም	[የመንገድ ስም ይግባ]
ከተማ	[የከተማ ስም ይግባ]
አገር	ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር	[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር

		ይግባ]
	የኢሜል አድራሻ	[የኢሜል አድራሻ ይግባ
አ.መ.7.1 እና 9.4	ለጥያቄና ማብራሪያ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን፡- [ቀን፣ወር፣ እና አ.ም. ይግባ] ሰዓት፡- [ሰዓት ይግባ]	

ሐ. የጨረታ መወዳደሪ ሀሳብ አዘገጃጀት	
አ.መ.11.1	የጨረታ መወዳደሪ ሀሳብ ቋንቋ [የጨረታው ቋንቋ ይገለፅ] _____ ነው።
አ.መ.12.4	ለሚከተሉት አማካሪዎች የጨረታ መወዳደሪ ሀሳብ ማቅረቢያ ጥሪ ተልኳል፡- ……
አ.መ.13.1	አማካሪው ከሌሎች ለዚህ ጨረታ ካልተጋበዙት ጋር በሽርክና ለመስራት የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ፈቃድ ማግኘት ማስፈለግ አለማስፈለጉ ይጠቀስ _____
አ.መ.13.2	አማካሪው ከሌሎች በዚህ ሥራ እንዲሳተፉ ከተጋበዙት ጋር መተባበር መፈቀድ አለመፈቀዱ ይጠቀስ _____
አ.መ.13.3	የንዑስ አማካሪነት ወሰን እንደሚከተለው ነው_____
አ.መ.14.1	አማካሪው የአማካሪዎች ማረጋገጫ ላይ ስለ ሙያዊ ብቃት እንዲሁም ወቅታዊ እና ላለፉት ዓመታት ያሳያቸው የአፈጻጸም ብቃቶች ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህም የሚሰጠው ያለውን ሙያዊ ብቃት ለማረጋገጥ ነው፡፡
አ.መ.15.2 (ለ)	አማካሪው ስላለው ወቅታዊ የፋይናንስ አቅም ማሳያ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ ይኖርበታል። ሀ. __ ለ. __ ሐ. ___
አ.መ.16.3	አማካሪው ቢያንስ ባለፉት ___አመታት ከዚህ በፊት በተዋዋይ ወገኖች የተሰጠ አጥጋቢ የውል አፈፃፀም ብቃት ማረጋገጫ እና የተከናወነውን የገንዘብ መጠን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ------
አ.መ.16.6	ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የአማካሪውን ወቅታዊ የቴክኒክ መስፈርቶች አጥጋቢነት እንዲሁም ብቃት ለማረጋገጥ በመ/ቤት በመገኘት ምርመራ ሊያደርግ ይችላል፡፡
አ.መ.17.2	የቁልፍ ሙያተኛ ሠራተኞች ወርሀዊ ተሳትፎ ግምት፡- ----------
አ.መ.17.1	በቋሚ በጀት መሰረት ለሚከናውን ስራ የተዘጋጀው በጀት ---------- ነው፡-
አ.መ.18.2	የሚቀርበው የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ቅርፅ (format) የሚከተለው ነው □ ሙሉ የቴክኒክ መወዳደሪ ሀሳብ □ ጠቅለል ያለ የቴክኒክ መወዳደሪ ሀሳብ
አ.መ 19.1 (ለ) (V)	የአማካሪው ሰራተኞች ከመደበኛ የስራ ቦታቸው ወይም እንደአግባብነቱ ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ክልል ውጪ አገልግሎት ለመስጠት በሚሄዱበት ጊዜ የሚከፈል የውሎ አበል አግባብነት ባለው የመጓጓዣ ዘዴ ወይም እጅግ ቀጥታ ወይም አጭር ከሆነ የመጓጓዣ ዘዴ በመጠቀም ሠራተኞች የሚያደርጉትን የሥራ ነክ ጉዞ ተከትሎ የሚኖር አስፈላጊ የጉዞ ወጪ ለመስሪያ ቤት እቃዎች የጥናት እና የቅየሳ ወጪ አግባብነት ያላቸው አለም አቀፍ እና አገር አቀፍ የመገናኛ ወጪዎች ለምሳሌ፤ በአግልግሎት ወቅት ለስልክ ወይም ሌሎች

	የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚወጣ ወጪ አማካሪው ለሚቀርበው አገልግሎት ዓላማ የሚያስፈልገው ማንኛውም መሳሪያዎች ወይም ዕቃዎች የኪራይ እና የጭነት ወጪ በአማካሪው መቅረብ ለሚኖርባቸው ሪፖርቶች የህትመት እና የስርጭት ወጪ ሌሎች ክፍያዎች እንደአግባብነቱ ጊዜያዊ እና ቋሚ ወጪዎች (ካለ) እና በውሉ ላይ ላልተሸፈኑ ተጨማሪ ዕቃዎች ወጪ
አ.መ 19.3	በየሥራ ዘርፉ የተከፋፈለ አጠቃላይ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ዋጋ ስለማቅረብ
አ.መ19.4	የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ የግብር መጠኑን ለብቻው በግልፅ ማሳየት አለበት፡፡ እንደአመቺነቱ የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት (ሀ) አማካሪው የከፈለውን ማንኛውም እንደዚህ ዓይነት ግብር ለአማካሪው ተመላሽ ያደርጋል፡፡ ወይም (ለ) አማካሪውን ወክሎ እነዚህን የግብር ዓይነቶችን ይከፍላል
አ.መ 19.7	ለእያንዳንዱ ሎት (lot) የቀረበለት የዋጋ ተመን በእያንዳንዱ በተዘረዘረው የሎት (lot) ላይ ካለው መቶኛ ቢያንስ ___% መመሳሰል አለበት፡፡ በእያንዳንዱ ሎት (lot) ውስጥ ላለ አገልግሎት የሚቀርብለት የዋጋ ተመን ቢያንስ ለእያንዳንዱ የተዘረዘረ የሎት (lot) መጠን ከተሰጠው መቶኛ ጋር___% መመሳሰል አለበት፡፡
አ.መ 22.1	የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ዋስትና ማስፈለግ አለማስፈለጉ ይጠቀስ፡፡ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ዋስትና የሚያስፈልግ ከሆነ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ዋስትና መጠን .....ይሆናል
አ.መ 22.3	የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ .....ቀናት ይሆናል፡፡
መ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አቀራረብና አከፋፈት	
አ.መ 23.1	ከዋናው የጨረታው መወዳደሪያ ሀሳብ በተጨማሪ የቅጂ ብዛት ..... ያስፈልጋል፡፡

	ለጨረታው መወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ ብቻ የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት አድራሻ እንደሚከተለው ነው፡፡ [የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ስም ይግባ] [ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም ይግባ] [ቢሮ ቁጥር ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ] [ፖ.ሳ.ቁ.ይግባ] [የመንገድ ስም ይግባ] [የከተማ ስም ይግባ] [ፖ.ሳ ኮ ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ] አገር ኢትዮጵያ የመወዳደሪያ ሀሳብ የማቅረቢያ ቀነ-ገደብ ቀን፡- [ቀን፣ወር፣ እና አመት ይግባ ምሳሌ፡-15 ግንቦት 2019 ዓ.ም ፣ወሩ በፊደል ይፃፍ] ሰዓት፡- [ሰዓት፣ከጠዋቱ ወይም ከሰአት በኋላ ተብሎ ይግባ]
አ.መ 42.1	የመወዳደሪያ ሀሳብ መክፈቻ ቦታ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ የግዥ ፈፃሚ አካል ስም ይግባ የቢሮ ቁጥር [ቢሮ ቁጥር ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ] የመንገድ ስም [የመንገድ ስም ይግባ] ከተማ [የከተማ ስም ይግባ] አገር ኢትዮጵያ ቀን [ቀን፣ወር፣ እና አመት ይግባ] ሰዓት [ሰዓት፣ከጠዋቱ ወይም ከሰአት በኋላ ተብሎ ይግባ]
ሠ. የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ መግምገምና ማነፃፀር	
አ.መ 32.2	አማካሪው ስለተፈፀመው የስሌት ስህተት ማስተካከያ መቀበሉን በ3 ቀናት ጊዜ ውስጥ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
አ.መ 36.4 (ለ)	አማካሪው ከሚያቀርበው የአግባብነት ማረጋገጫ ዝርዝር ጋር ባለፉት ------ አመታት ውጤታማ በሆነ መልኩ ስላከናወናቸው ------ ስራዎች የሚያረጋግጥ የስራ አፈፃፀም ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
አ.መ 36.5 (ሐ)	የአማካሪው ያለፉት አመታት አማካኝ አመታዊ ገቢ (ተርን ኦቨር) ከፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ መጠን በ ---- ጊዜ የሚበልጥ መሆን ይኖርበታል፡፡
አ.መ 43.2 (መ)	ለመወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማና ማነፃፀሪያ ሲባል በተለያዩ የገንዘብ አይነቶች የተጠቀሱ የመወዳደሪያ ሀሳብ ዋጋዎች ሁሉ ወደ አንድ ምንዛሬ ለመቀየር ጥቅም ላይ የዋለው የገንዘብ አይነት ----------ነው፡፡

<table>
<tr><td>አ.መ 43.4</td><td>ግምገማው ሁሉንም ግብር፣ ቀረጥ፣ ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎችን ይጨምራል፡፡</td></tr>
<tr><td>አ.መ 49.3</td><td>ለአንድ አማካሪ ከአንድ በላይ የሆነ የአሸናፊነት ውሳኔ መፈቀድ አለመፈቀዱ ይገለፅ፡፡ በዝቅተኛነት የሎቶች (lots) የግምገማ ዘዴ በግምገማ ዘዴ እና መስፈርት ክፍል 3 እንደተጠቀሰው ይሆናል፡፡</td></tr>
<tr><td>አ.መ 45</td><td>ድርድር የሚካሄደው በሚከተለው አድራሻ ይሆናል፡-
<table>
<tr><td>ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት</td><td>[ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>የቢሮ ቁጥር</td><td>[ቢሮ ቁጥር ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ]</td></tr>
<tr><td>የመንገድ /ስም/</td><td>[የመንገድ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ከተማ</td><td>[የከተማ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>አገር</td><td>ኢትዮጵያ</td></tr>
</table></td></tr>
<tr><td colspan="2">ረ. ውል ስለመፈፀም</td></tr>
<tr><td>አ.መ 49</td><td>የሚጨምረው የምክር አገልግሎት የግዥ መጠን በመቶኛ [የተፈቀደ ትልቁ መቶኛ ይግባ]
የሚቀንሰው የምክር አገልግሎት የግዥ መጠን በመቶኛ [የተፈቀደ ትንሹ መቶኛ ይግባ]</td></tr>
</table>

ክፍል 3፡ የግምገማ ዘዴና መስፈርቶች

ማውጫ

1. የሙያ፣ የቴክኒክ እና የፋይናንስ ብቃት መስፈርት IV
2. የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ IV
3. የፋይናንስ መወዳደሪ ሀሳቦች መገምገምና ማነጻጸር VII
4. ለሀገር ውስጥ አማካሪዎች የሚደረግ ልዩ አስተያየት .....Error! Bookmark not defined.
5. የብዙ ግዥዎች ግምገማ .....Error! Bookmark not defined.

[ማስታወሻ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መስፈርቶች ለብቻቸው ተጫራቾችን ለመምረጥ እንደመጨረሻ ተደርገው መቆጠር የለባቸውም]

የግምገማ ዘዴና መስፈርቶች

ይህ ክፍል በክፍል 1 የአማካሪዎች መመሪያ እና ክፍል 2 የጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ ከተመለከቱት አሰራሮች እና መመዘኛዎች ጋር በጥምረት የሚነበብ ሲሆን፣ ይህም የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ጨረታውን ለመገምገም የሚጠቀምበትና አማካሪው አስፈላጊው ችሎታ እንዳለው የሚወስንበት ይሆናል።ማንኛውም ሌላ አሰራር ወይም መመዘኛ መስፈርት ጥቅም ላይ አይውልም።

1. የሙያ፣ የቴክኒክ እና የፋይናንስ ብቃት መስፈርት

ከዚህ ቀጥሎ ያሉት የችሎታ መመዘኛዎች ለምክር አገልግሎት ግዥው ተግባራዊ ይሆናሉ። በጊዚያዊ ህብረት የቀረቡ ጨረታዎችን በተመለከተ ይህ የችሎታ መመዘኛ ለጊዚያዊ ህብረቱ አባላት በአንድ ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

1.1 የአማካሪው ሙያዊ ችሎታና አቅም (አ.መ. አንቀጽ 14)

ሀ. ለአማካሪው በአሁኑ ወቅት የሚሰራው ሥራተኛ በጥቂቱ (የሚያስፈልገው ብዛት ይግባ)
ለ. በንኡስ አንቀጽ (ሀ) ከተጠቀሱት ሰራተኞች መሐከል ቢያንስ_____ (ቁጥር ይግባ)
ሐ. ሌላ ተጨማሪ መስፈርት ካለ ይጠቀስ (ተጨማሪ መመዘኛ ካለ ይግባ)

1.2 የአማካሪው የቴክኒክ ችሎታ፣ ብቃት እና ልምድ (አ.መ. አንቀጽ 16)

ሀ. አማካሪው ባለፉት አመታት ከዚህ ውል ያላነሰ በጀት ያላቸው፣ ኮንትራቶች በብቃት አጠናቀዋል (ተፈላጊ የውሎች ብዛት ይግባ)
ለ. ሌላ ተጨማሪ መስፈርት ካለ ይጠቀስ (ተጨማሪ መመዘኛ ካለ ይግባ)

1.3 የአማካሪው የፋይናንስ አቋም (አ.መ. አንቀጽ 15)

ሀ. ተጫራቹ ባለፉት ---- ዓመታት የነበረው አማካይ የተረጋገጠ ዓመታዊ ገቢ ቢያንስ ለዚህ ጨረታ ከቀረበው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ በ_____ ጊዜ የሚበልጥ መሆን አለበት። (ተፈላጊ የአመት ብዛት ይግባ)
ለ. ሌላ ተጨማሪ መስፈርት ካለ ይጠቀስ (ተጨማሪ መመዘኛ ካለ ይግባ)

2. የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ

2.1የቴክኒካል የመወዳደሪያ ሀሳብ የሚገመገመው በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 18 ውስጥ የተጠየቀው የአማካሪው ችሎታ የሚያሳየው የሰነድ ማስረጃ በሙሉ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ነው።

2.2 የቴክኒካል መወዳደሪያ ሀሳቡ ሁሉንም አስገዳጅ የአማካሪውን ችሎታ ማረጋገጫ የሰነድ ማስረጃዎች መያዛቸው ከተረጋገጠ በኋላ ግዢ ፈፃሚው መ/ቤት በእያንዳንዱ ጨረታ ሕጋዊ፣ ቴክኒካዊ፣ ሙያዊ እና የፋይናንስ ትክክለኛነት በማረጋገጥ፣ በመወዳደሪያ ሀሳቡ ውስጥ የተጠየቀውን የችሎታ መስፈርት የማያሟላ ወይም የሚያሟላ መሆኑን ይለያል፡፡

2.3 ከዚያም በኋላ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ካቀረበው ቢጋር አንፀባር የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቡን መጣጣሙን በማረጋገጥ ከተነተነ በኋላ በቴክኒክ በኩል የሚያሟላ ወይም የማያሟላ በማለት ይለያያል፡፡

2.4 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የቴክኒክ የመወዳደሪያ ሀሳቡን ምርመራ የሚቀጥለው በመወዳደሪያ ሀሳቡ ውስጥ ያለመጣጣሞችና ግድፈቶችን በማስተካከል በተገቢው መንገድ ምላሽ መስጠቱን ለመወሰን ነው፡፡

2.5 ሁሉም ዋና ዋና ሕጋዊ፣ ሙያዊ፣ ቴክኒካዊ እና የፋይናንስ መስፈርቶች ከተሟሉ የቴክኒክ ሀሳቦቹ በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 37 መሠረት ተገምግመው ነጥብ የሚሰጣቸው ሲሆን ይህም የሚከናወነው ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን የቴክኒክ መገምገሚያ መስፈርቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት እና ከዚህ በአጠቃላዩ የግምገማ ሂደት ውስጥ የሚኖራቸውን አንፃራዊ ክብደት ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

ሀ. የቴክኒክ ምርመራው መስፈርት እና የነርሱ የክብደት ደረጃ ነጥቦች የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ መሠረት ይሆናል፡፡

ቅድ ሚያ	የመመዘኛው ስም		የተመጣጣኝ ደረጃ በ%
1	በአማካሪነት አገልግሎት የተሰማራ ቁልፍ ሙያተኛ ችሎታ እና ብቃት ሀ. የቡድን መሪ ለ. እንደአስፈላጊነቱ ሀላፊነትና ሙያ አስገባ ሐ. እንደአስፈላጊነቱ ሀላፊነትና ሙያ አስገባ መ. እንደአስፈላጊነቱ ሀላፊነትና ሙያ አስገባ		ነጥብ ይግባ ነጥብ ይግባ ንጥብ ይግባ
	ለመመዘኛው የሚሰጠው አጠቃላይ ነጥብ (1)		30-60%
	ከዚህ በላይ ለተገለጹት ለእያንዳንዱ ምድብ ቦታ ወይም ትምህርት የሚሰጡት ነጥቦች የሚወሰኑት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ሶስት ንዑስ መስፈርቶች እና ተዛማጅ የመቶኛ (%) ክብደት ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡		
	ሀ. አጠቃላይ ችሎታ	(20 - 30%)	ነጥብ ይግባ
	ለ. ለሥራው ያለው ብቃት	(50 - 60%	ነጥብ ይግባ
	ሐ. እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ እና በቋንቋው ያለው ልምድ	(10-20%)	ነጥብ ይግባ
	ጠቅላላ ክብደት	100%	

2.	በሥራ ላይ እንዲውል የቀረበው የምክር ዘዴ ሀ. የቴክኒክ አቀራረብ እና የጥናት ዘዴ ለ. የሥራ እቅድ ሐ. አደረጃጀት እና የሠራተኛ አመዳደብ	ነጥብ ይግባ ነጥብ ይግባ አነጥብ ይግባ
	ለመስፈርቱ የተሰጠው አጠቃላይ ነጥብ (2)	20-50%
3	የአማካሪው ልዩ ልምድ (በተለምዶ ንዑስ መመዘኛዎች አይሰጡም)	5-10%
4	ዕውቀት የማሸጋገር ችሎታ.... የፕሮግራሙ (የሥልጠናው) የእውቀት ሽግግር አመቺነት ሀ. የሥልጠና ፕሮግራሙ ተገቢነት ለ. የሥልጠናው አቀራረብ እና ሥርዓት ሐ. የኤክስፐርቶቹ እና አሰልጣኞቹ ችሎታ (ብቃት)	ነጥብ ይግባ ነጥብ ይግባ ነጥብ ይግባ
	ለመስፈርቱ የተሰጠው አጠቃላይ ነጥብ (4)	5-10%
5	ከቀረቡት ቁልፍ ሠራተኞች መካከል የኢትዮጵያውያን ተሳትፎ (በተለምዶ ንዑስ መመዘኛዎች አይሰጡም)	5-10%
6	ለአምስቱ መመዘኛዎች የተሰጠው አጠቃላይ ነጥብ (1+2+3+4+5)	100

ለ. የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የነጥብ ስኬል በመጠቀም ማንኛውንም የቴክኒክ ምርመራ መመዘኛ ይገመግማል፡-

ውጤት		መግለጫ
10	እጅግ በጣም ጥሩ	የመመዘኛውን መስፈርት በከፍተኛ ሁኔታ ከሚሟላቱም በላይ በብዙ መንገድ በጣም ተፈላጊ ነው፡፡
9	በጣም ጥሩ	የኛን ፍላጐትና ጥቅም በሚያስጠብቅ መንገድ የመመዘኛውን መስፈርት በይበልጥ አሟልቷል፡፡
7-8	ጥሩ	የመመዘኛውን መስፈርት ሙሉ በሙሉ አሟልቷል
5-6	አጥጋቢ	አብዛኛውን የመመዘኛ መስፈርት በበቂ ሁኔታ ያሟላል ምናልባት በጣም አስፈላጊ ያልሆኑትን ነገሮች ሟሟላት አልቻለም፡፡
3-4	ደካማ	ሁሉንም የመመዘኛ መስፈርቶች አነስተኛ ተቀባይነት ባለው ደረጃ አሟልቷል
1-2	በጣም ደካማ	በጣም አነስተኛ በሆነ ደረጃ መስፈርቱን ቢያሟላም ሁሉንም በጣም ወሳኝ የሆኑ አንዳንድ ነገሮችን አላሟላም፡፡
0	የማያሟላ	በማንኛውም መንገድ የመመዘኛውን መስፈርት አላሟላም

2.6 ለሁሉም የቴክኒክ ምርመራ መስፈርት በግል የተሰጡት ነጥቦች የሚመዘኑት በተቀመጡት ተመጣጣኝ የክብደት ነጥቦች መሠረት ነው፡፡ ውጤቱም የሚሰላው የእያንዳንዱ መስፈርት ተመጣጣኝ ነጥብ ከውጤቱ ጋር በማባዛት ይሆናል፡፡

2.7 በምርመራው ውስጥ ካለው ነጥብ ያነሰ ውጤት ያገኙ አማካሪዎች ተቀባይነት አያገኙም፡፡ ነገር ግን ጥሩ ነጥብ እና ከዚህ በላይ ውጤት ያገኙት አማካሪዎች

የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ኢንቨሎፕ ይከፍታል፡፡ (የቴክኒካዊ ብቃቶች ዝቅተኛ ነጥቦች ወሰን ይቀመጥ)

3. የፋይናንስ መወዳደሪ ሀሳቦች መገምገምና ማነጻጸር

በመንግስት የግዥ አዋጅ እና መመሪያ ውስጥ በተገለፀው አሰራር መሠረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ሥርዓት በመከተል ስኬታማ የሆነውን አማካሪ ይመርጣል፡፡

3.1 ጥራት እና ወጪ ላይ ተመስርቶ የሚደረግ መረጣ (Quality and cost based selection)

(ሀ) በፋይናንስ ግምገማው ሂደት ከፍተኛው ነጥብ የሚሰጠው በጣም ዝቅተኛ የሆነ ዋጋ ላቀረበው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ሲሆን እንዲሁም በአንፃሩ ዝቅተኛው ነጥብ ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ይሆናል፡፡ለሌሎች አማካሪዎች የተሰጡት ነጥቦች የሚሰጡት በሚያቀርቡት ዋጋ መሠረት ይሆናል፡፡

(ለ) በአማካሪዎች ለቀረቡት መወዳደሪያ ሀሳቦች ከሚሰጡት አጠቃላይ ነጥቦች ውስጥ የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቡ 80% የሚይዝ ሲሆን ቀሪው 20% የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ ድርሻ ይሆናል፡፡

(ሐ) ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከዚያ በኋላ የቴክኒክ ነጥቡ በፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ ዋጋ ላይ ደምሮ ጠቅላላ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ ነጥብ ጋር ይደምረውና የመወዳደሪያ ሀሳቡን የመጨረሻ ደረጃ ይወስናል፡፡

(መ) ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሥራ ውሉን የሚሰጠው በቴክኒክ እና ፋይናንስ አጠቃላይ ድምር ውጤት ከፍተኛውን ውጤት ላገኘው መወዳደሪያ ሀሳብ ይሆናል፡፡

(ሠ) ሁለት አማካሪዎች እኩል ውጤት ካመጡ የአገር ውስጥ አማካሪዎች ቅድሚያውን ያገኛሉ፡፡

(ረ) ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በግምግማው እኩል ነጥብ ያመጡ አማካሪዎች በተጠየቀው መወዳደሪያ ሀሳብ አቅጣጫ ተጨማሪ ሁኔታዎችን እንዲያስገቡ ሊጠይቃቸው ይችላል፡፡ ይህም ስኬታማውን አማካሪ ለማየት የሚጠቅም ይሆናል፡፡

(ሰ) ሆኖም ግን እኩል ነጥብ ያመጡ አማካሪዎች እንዲያስገቡ የተጠየቁትን የመጨረሻ መወዳደሪያ ሀሳብ ሳያስገቡ ከቀሩ ወይም እንደገና ያስገቡት መወዳደሪያ ሀሳብ ሲመረመር ነጥባቸው እኩል ከሆነ እና አሸናፊው ካልታወቀ ስኬታማው አማካሪ በተቻለ መጠን ሁሉም አማካሪዎች በተገኙበት ዕጣ በመጣል ይመረጣል፡፡

3.2 ጥራትን መሠረት ያደረገ መረጣ (Quality based selection)

(ሀ) በቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቡ ግምግማ ከፍተኛውን ነጥብ ያገኘው አማካሪ እንደ ስኬታማ አማካሪ ሆኖ ይመረጣል፡፡

(ለ) ከላይ በተጠቀሰው ንዑስ አንቀጽ ውስጥ ያለው ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ በተመረጠው አማካሪ የተሰጠው ዋጋ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አቅም በላይ ከሆነ፤ ግዥ ፈፃሚው አካሉ ምናልባት በቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ ውስጥ ሁለተኛውን ከፍተኛ ነጥብ ካመጣው አማካሪ ጋር ውል ሊገባ ይችላል፡፡

3.3 የተወሰነ የበጀት መረጣ (Fixed budget selection)

(ሀ) በፋይናንስ ግምግማው ሂደት ከፍተኛው ነጥብ የሚሰጠው ዝቅተኛ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ላቀረበው ሲሆን ባንጻሩ ዝቅተኛው ነጥብ የሚሰጠው ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ይሆናል፡፡ ለሌሎች አማካሪዎች የተሰጡት ነጥቦች ባቀረቡት የዋጋ መጠን ይወስናል፡፡

(ለ) በአማካሪዎች ለቀረቡት መወዳደሪያ ሀሳቦች ከተሰጡት አጠቃላይ ነጥቦች የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳቡ ድርሻ እና ቀሪው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ ድርሻ ይሆናል፡፡ (ለቴክኒካዊ ፕሮፖዛሉ ተፈላጊ መቶኛ ነጥቦች አስገባ)

(ሐ)ለግዥው በተመደበው የበጀት ገደብ ውስጥ ዋጋውን ያቀረበው አማካሪ ሆኖ በቴክኒክ እና ፋይናንስ ግምገማው አጠቃላይ ድምር ውጤት ከፍተኛውን ነጥብ ያገኘው እንደ ስኬታማ አማካሪ ተደርጎ ይመርጣል፡፡

(መ) አስፈላጊ ከሆነ ዋጋውን ሳይጨምር በአንዳንድ ጉዳዩች ላይ ከተመረጠው አማካሪ ጋር ድርድር ሊደረግ ይችላል፡፡

(ሠ) ለግዥው ከተያዘው/ከተገኘው በጀት በላይ ዋጋ ያቀረቡ አማካሪዎች ከፈጠረታው እንዲወጡ ይደረጋሉ፡፡

3.4 ዝቅተኛ ዋጋን መሠረት ያደረገ ምርጫ (least cost based selection)

(ሀ) ዝቅተኛውን ዋጋ ያቀረበው አማካሪ እንደስኬታማ አማካሪ ሆኖ የሚመረጥ ሲሆን የሚመረጠውም ለቴክኒካዊ መስፈርቱ የተቀመጡትን ተፈላጊ ዝቅተኛ ነጥቦች በሚሟላት በቴክኒካዊ መንግድ ካለፉ አማካሪዎች መካከል የተመረጠው ይሆናል፡፡

4. ለሀገር ውስጥ አማካሪዎች የሚደረግ ልዩ አስተያየት

4.1 በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 34 እንደተገለፀው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለሀገር ውስጥ አማካሪ ኩባንያዎች ልዩ አስተያየት የሚሰጣቸው በሚከተሉት አንቀጾች ውስጥ በተገለፁት አሰራር መሠረት ይሆናል፡-

(ሀ) ብቃት ያላቸው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦች ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ቡድኖች ውስጥ ይከፋፈላሉ፡፡

i ቡድን ሀ፡- በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያንዑስ አንቀፅ 34.3 የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ በሀገር ውስጥ አማካሪ ኩባንያዎች የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦች፡፡

ii ቡድን ለ፡- ሌሎች የፋይናንስ መወዳደሪ ሀሳቦች በሙሉ ናቸው፡፡

4.2 የፋይናንስ መወዳደሪ ሀሳቦችን ለመመርመር እና ለመወዳደር ሲባል ብቻ በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 34.3 መሠረት ከተወሰነው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦች ዋጋ 7.5% በቡድን "ለ" ውስጥ ከተመደቡት ሁሉም የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦች ጋር አብሮ ይደመራል፡፡

5. የብዙ ግዥዎች ግምገማ

በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ መሠረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከአንድ በላይ አማካሪ ለአንድ ወይም የብዙ ምድብ ውል ለመስጠት ስለሚፈቅድለት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት አሰራሮች ብዙ ውሎችን ለመፈፀም ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ (የብዙ ምድብ ውል መፈቀድ አለመፈቀዱ ይገለፅ)

በዝቅተኛነት የተገመገሙትን የሎት ጥርቅሞች ለመወሰን ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ፡-

(ሀ) በብዙ ምድቦች ወይም ውሎች የተካተቱትን ቢያንስ በየመደቡ የሚገኙ ጉዳዮች በመቶኛ ወይም በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ 19.7 ውስጥ የዘረዘሩትን ብዛት በመቶኛ ብቻ ይገመግማል፡፡

(ለ) ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ግምት ውስጥ ያስገባል

(i) የግምገማውን መመዘኛ መስፈርት ለሚያሟላው እያንዳንዱ የብዙ መደብ የቀረበው ዝቅተኛ ግምገማ የተደረገበት መወዳደሪያ ሀሳብ

(ii) በብዙ መደቡ የተደረገ የዋጋ ቅናሽ እና ለአተገባበራቸው የተዘረጋው ሥርዓት በፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ ውስጥ በአማካሪው በቀረበው መሠረት እና

(iii) የአቅርቦት ውስንነትና የአፈፃፀም አቅምን ግምት ውስጥ ያስገባና ተስማሚ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የሚያስገኝ የውል አሰጣጥ ቅደም ተከተል፡፡

ክፍል 4: የጨረታ ቅጾች

ማውጫ

ሀ. የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ - መደበኛ ቅጾች.....1

1. የቴክኒክ መወዳደሪ ሀሳብ ማቅረቢያ ሰነድ - ቅጽ ቴ1.....1
2. የአማካሪው የአግባብነት ማረጋገጫ ሰነድ - ቅጽ ቴ2.....4
3. የቴክኒክ መወዳደሪ ሀሳብ - ቅጽ ቴ3.....9
4. የሽርክና/ጊዚያዊ ማህበር መረጃ ቅጽ.....11
5. የባለሙያዎች ተፈላጊ መረጃ (CV) - ቅጽ ቴ4.....13
6. የጨረታ ዋስትና.....14
7. የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ማሳወቂያ ፎርም.....19

ለ. ፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ - መደበኛ ቅጾች.....18

1. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ማስረከቢያ ሠንጠረዥ - ቅጽ ፋ1.....18
2. የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ - ቅጽ ፋ2.....21

ሀ. የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ - መደበኛ ቅጾች

የቴክኒክ መወዳደሪ ሀሳብ ማቅረቢያ ሰነድ - ቅጽ ቁ1

ቦታና ቀን ፡- [ጨረታው የቀረበበት ቦታ እና ቀን(ቀን፣ወር እና አመተ ምህረት)ይግባ]

የግዥ መለያ ቁጥር ፡- [የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]

ለ፡

[የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ስም ይግባ]

[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስም ይግባ]

[ሥ.ማ.ቁ.ይግባ]

[አድራሻ ይግባ]

ኢትዮጵያ

በ .....የቀረበ

	የአማካሪው መቀመጫ ሙሉ ስም እና አድራሻ	ዜግነት
የቡድን መሪ		
አባል		
ወዘተ		

እኛ ከዚህ በታች ስምምነታችንን ያረጋገጥነው በግዥ መለያ ቁጥር --- ለቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ምላሽ ለመስጠት ቀጥሎ የተመለከተውን እንገልፃለን፡-

ሀ. በግዥ መለያ ቁጥር፡ (መለያ ቁጥር ይግባ) የቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ውስጥ ያለውን ይዘት መርምረን ሙሉ በሙሉ ተቀብለነዋል፡፡ በመሆኑም ደንቦቹን በሙሉ ያለምንም ገደብ ወይም ወሰን ተቀብለናል፡፡

ለ. ከዚህ በታች ስምምነታችንን ያረጋገጥነው በእናንተ የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ጊዜ እና ሀሳብ መሠረት የማማከር አገልግሎት ለመስጠት እንስማማለን፡፡

ሐ. ይህን የቴክኒክ መወዳደሪያ ሀሳብ እና የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ አቅርበናል፡፡

መ. ይህን የመወዳደሪያ ሀሳብ የምናቀርበው በኢጋርነት ከ .....ጋር ነው።
(የእያንዳንዱ ተባባሪ አማካሪ ሙሉ ስምና አድራሻ ይግባ)

ሠ. በዚህ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ውስጥ ያሉት መረጃዎችና መግለጫዎች በሙሉ ትክክለኛ መሆናቸውንና በውስጡ ማንኛውም የተሳሳተ ትርጉም ከያዙ ከውድድሩ እንደምንወጣ ተቀብለናል፡፡

ረ.የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳባችን ፀንቶ የሚቆየው በጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ ሠነድ ከተወሰነው የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ለ ..... ቀናት መሆኑን እና ለርሱም ተገዥ እንደምንሆን፤ እንዲሁም ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት በማንኛውም ጊዜ ተቀባይነት እንዳለው ነው፡፡

ሰ. የጨረታው መወዳደሪያ ሀሳብ ሕጋዊ በሆነበት ወቅት ድርድር የሚካሄድ ከሆነ በቀረበው ሠራተኛ መሠረት ለመደራደር ተስማምተናል፡፡ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳቡ ለኛ ገዢ ሲሆን ከውሉ ድርድር ውጤት በኋላ ለሚኖረውም ማሻሻያ እንገዛለን፡፡

ሸ. እኛ እና በዚህ የግዥ ሂደት የሚሳተፉ ማናቸውም ንዑስ አማካሪዎች በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀፅ 4.1 መሠረት በመንግስት ግዥ ለመሳተፍ ብቁ መሆናችንና ከዚህ ቀደም በነበረን የሥራ ውል ግዴታችንን ባለመወጣታችን በቢሮው እና/ወይም በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በመንግሥት ግዥ እንዳንሳተፍ አልታገድንም፡፡

ቀ. በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 5 ውስጥ ስለማጭበርበር እና ወደፊት በሚገኝ ሙስና የተደነገጉትን ደንቦች አንብበን ተረድተናል፡፡ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የምናረጋግጠው በግዥው ሂደት እና በማንኛውም የውል አፈፃፀም ወቅት እራሳችንን በዚህ መጥፎ ተግባር ላይ የማንገኝ መሆኑን ነው፡፡

በ. ከሌሎች አማካሪዎች ጋር የምዝበራና የማጭበርበር ስምምነት አልፈፀምንም፡፡

ተ. ለባለስልጣን ወይም ለኃላፊ ጉቦ ለመስጠት ወይም ለማማለል አልሞክርንም ወይም የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ለማሸነፍ እና ውጤቱን ለመቀየር ለግዥ ፈፃሚ አካሉ ወይም ለገዢው ሠራተኞች ጉቦ አልሰጠንም፡፡

ቸ. እንደአማካሪነታችን በዚህ የጨረታ ሂደት ከአንድ በላይ በሆነ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ላይ አልተሳተፍንም፡፡

ነ. ምንም ዓይነት የጥቅም ግጭት የለብንም፡፡ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ኦርጅናል የቢ.ጋር ዝግጅት ላይ አልተሳተፍንም፡፡

ኘ.የኛ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ተቀባይነት ካገኘ በመወዳደሪያ ሀሳብ ጥያቄው አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 55 መሠረት የውል ማስከበሪያ ዋስትና ለመስጠት እና በውሉ መሠረት ለመተግበር ቃል እንገባለን፡፡

አ. እኛና ማንኛውም ንዑስ አማካሪዎች ወይም አቅራቢዎች በዚህ ውል ማንኛውም ክፍል የምንሳተፍ ሁሉ ከታወቁ ሐገሮች ዜግነት ያለን ነን፡፡ (የእንዳንዱ አማካሪ ተባባሪዎች ንዑስ አማካሪዎች ዜግነት አስገባ)

ከ. ይህ ውል ተግባራዊ በሚሆንበት ወቅት በማንኛውም ደረጃ ቢሆን ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ላይ ለውጥ ቢኖር ግዥ ፈጻሚውን መ/ቤት ወዲያውኑ እናሳውቃለን፡፡ በዚህ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ውስጥ አውቆ የተሰጠ ያልተሟላ ወይም ትክክል ያልሆነ መረጃ ቢኖር የምናውቅና የምንቀበል መሆኑን እንገልጻለን፡፡ ከዚህም ሆነ ከሌላ ውሎች በተለይ በክልሉ እና/ወይም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት የገንዘብ እርዳታ ከሚካሄድ ፕሮጀክት ልንታገድ እንደምንችል እንገነዘባለን፡፡

ኸ. ይህ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ እና ከናንተ የደረሰን የአሸናፊነት ውጤት የፅሁፍ ማስታወቂያ በመኻከላችን ግዥ ውል እንዳልሆነም እናውቃለን፡፡ ይህ የሚሆነው በመሐከላችን ሕጋዊ የሆነ ውል ከተዘጋጀ እና ተፈጻሚ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

ወ. ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብት እንዳላችሁ እንረዳለን፡፡

ስም፤ (በጨረታ ፕሮፖዛል ላይ የሚፈርም ግለሰብ ሙሉ ስም ይግባ)

ሀላፊነት፤ (በጨረታ ፕሮፖዛል ላይ የሚፈርም ግለሰብ ህጋዊ ሀላፊነት ይግባ)

ፊርማ፤ (ከላይ ስሙና ሃላፊነቱ የተጠቀሰው ግለሰብ ፊርማ አስገባ)
(የአማካሪ ሙሉ ስም አስገባ)

ቀን፤ (ቀን አስገባ (ወር አስገባ) (የተፈረመበት ዓ.ም አስገባ)

አባሪዎች፡ (ዕዝሎች)

1. አማካሪው የሚሰራውን የንግድ አይነት የሚያሳይ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ
2. ከታክስ ባለስልጣን የተሰጠ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ሰርተፍኬት
3. ከታክስ ባለስልጣን የተሰጠ ታክስ የተከፈለበት ሕጋዊ የምስክር ወረቀት
4. አግባብነት ያለው የሙያ ብቃት ሰርተፍኬት
5. የጨረታ ዋስትና እና
6. በግዥ ፈፃሚው የሚጠየቁ ሌሎች ሰነዶች

(የተጠየቀው መረጃ የሚቀርበው ከዚህ በታች በተመለከተው ፎርማት መሰረት ሲሆን ከቴክኒካል ፕሮፖዛሉ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት። አማካሪው ፎርማቱን ማሻሻል ይችላል። ለሚፈጠረው የጥራት ጉድለት ሀላፊነቱን ይወስዳል።)

2. የአማካሪው የአግባብነት ማረጋገጫ ሰነድ - ቅጽ ቴ2

ቦታ እና ቀን፡ (ጨረታ ፕሮፖዛል የሚገባበት ቀን፣ ወርና ዓ.ም ይግባ)

የግዥ መለያ ቁጥር፡ (መለያ ቁጥር ይግባ)

ለ፡ (የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሙሉ ስም ይግባ)
(ስልጣን የተሰጠው ግለሰብ ስም ይግባ)
(የመልዕክት ሳጥን ቁጥር ይግባ)
(አድራሻ ይግባ)

ኢትዮጵያ

ሀ. ስለ አማካሪው የሚገልጽ አጠቃላይ መረጃ (ተገቢው ሳጥን ላይ ምልክት አድርግ)

የአማካሪው ሕጋዊ ስም	(ሙሉ ስም ይግባ)
የጋራ የንግድ ሥራ ከሆነ የእያንዳንዱ ወገን ሕጋዊ ስም	(ሙሉ ስም ይግባ)
የተመዘገበበት ቦታ	(የተመዘገበበት ቦታ ይግባ)
የተመዘገበበት ሀገር ሕጋዊ አድራሻ	(ትክክለው አድራሻ ይግባ)
ስልጣን ያለው ተወካይ መረጃ	ስም፡ (ሙሉ ስም ይግባ) ማዕረግ፡ (ማዕረጉ ይግባ) አድራሻ፡(አድራሻው ይግባ) ስልክ/ፋክስ፡(የስልክና ፋክስ ቁጥር ይግባ) የኢ-ሜይል አድራሻ፡ (አድራሻው ይግባ)
የተያያዙ ኦርጅናል/ዋና ሠነዶች	☐ የሽርክና ማህበር ከሆነ ረቂቅ ስምምነቱን ጨምሮ ሽርክና ለመመስረት የተጻፈ ደብዳቤ ወይም ሽርክና ምስረታን የሚያሳይ ስምምነት በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 4.1 መሠረት
	☐ የሽርክና ማህበር ዳታ ቅጽ
	☐በግዥ ፈፃሚው ሀገር ውስጥ በመንግሥት ይዞታ ስር የሚገኝ ድርጅት ከሆነ በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀፅ 4.4 መሠረት የህጋዊ እና የፋይናንስ ነፃነት ያለውና በአገሪቱ የንግድ ህግ የሚተዳደር መሆኑን የሚገልፅ ማስረጃ

የህን የጨረታ መወዳዳሪያ ሀሳብ ኩባንያውን/የሽርክና ማህበሩን/ጊዜያዊ ህብረቱን ወክሎ የፈረመው ግለሰብ ለመፈረም ሙሉ ስልጣን የተሰጠው መሆኑን እያረጋገጥን ሕጋዊ ውክልናውን አብረን አያይዘናል።

ለ. የፋይናንስ አቋም

በኛ (የአማካሪው ስም ይግባ) የፋይናንስ መግለጫ ላይ እንደተጠቀሰው በተመሰከረለት ኦዲተር እንደተመረመረው እና በዚህ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ውስጥ እንደቀረበው ይህንን ውል ለመተግበር በቂ የሆነ የፋይናንስ ሀብት አለን፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ የኛን የፋይናንስ መረጃ ይዟል፡፡ እነዚህ መረጃዎች በኛ አመታዊ የኦዲት ሂሳቦች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ በሁሉም አምዶች ውስጥ ያሉት አሐዞች የተሰጡት በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ተመስርተው ሲሆን ይኸውም የየአመቱን ቀጥተኛ ንፅፅር ለማድረግ በሚያመች መልኩ ነው፡፡

የፋይናንስ መረጃ	በቀድሞ አመታት የተገኙ ታሪካዊ መረጃ				
	2ኛ ዓመት	1ኛ ዓመት	ያለፈው ዓመት	በዚህ ዓመት	ማዕከላዊ
ሀ. ከገቢና ወጪ ዝርዝር መረጃ (ከባላንስ ሺት መረጃ)					
1. ጠቅለላ ሀብት					
2. ጠቅላላ ዕዳ					
i. የተጣራ ልዩነት (1-2)					
3. በአሁኑ ጊዜ ያለው ሀብት					
4. የአጭር ጊዜ እዳ					
ii. የሥራ ማስኬጃ (3-4)					
ለ. ከትርፍና ኪሳራ ዝርዝር መረጃ (ከኢንካም ስቴትመንት መረጃ)					
1. ጠቅላላ ሀብት					
2. ከታክስ በፊት ትርፍ					
3. ኪሳራ					

.

በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሰንጠረዥ በተጠየቀውና ከላይ ከሰጠነው የፋይናንስ መረጃ በተጨማሪ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ሰነዶች አያይዘናል፡፡

(ሀ)

(ለ)

የተያያዙት ሰነዶች ቀጥሎ ካሉት ሁኔታዎች ጋር ይስማማሉ፡፡

- ሰነዶቹ የአማካሪውን ወይም የሽርክ፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ህብረቱን የፋይናንስ ሁኔታ የሚያሳዩ ቢሆኑም የእህት ወይም የአጋር ኩባንያን ሁኔታ ግን አያሳይም፡፡
- ታሪካዊ የፋይናንስ መግለጫው በታወቀ የሂሳብ ሠራተኛ ተመርምሯል፡፡

- ታሪካዊው የፋይናንስ መግለጫ የተሟላ ሲሆን ከፋይናንስ መግለጫው በተጨማሪ ሁሉንም ማስታወሻዎች ያካትታል፡፡
- ታሪካዊው የፋይናንስ መግለጫው ከተጠናቀቀው እና ከተመረመረው የሂሳብ ጊዜ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

ዓመታዊው የተርንኦቨር መረጃ	
ዓመት	የገንዘቡ መጠን እና ምንዛሪው
አማካይ አመታዊ ተርንኦቨር	

ሐ. የአማካሪው አደረጃጀት

(አማካሪው የተቋሙ እና የተባባሪዎቹ አጭር መግለጫ እንዴት እንደተዋቀረ ጭምር አካቶ ማቅረብ አለበት። ስራውን አሁን እጁ ላይ ከሚገኙ ስራዎች እንዴት አቀናጅቶ ለመስራት እንዳሰበ ማብራራት አለበት።)

መ. የቴክኒክ ችሎታ፣ ብቃት እና ያለው ልምድ

ከዚህ ስራ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የማማከር አገልግሎቶችን ለመስጠት ቴክኒካዊ እና ሙያዊ ችሎታው ያለን (የአማካሪው ስም ይግባ) መሆኑን ለማረጋገጥ ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥ ባለፉት አመታት (የአመታት ብዛት ይግባ) ውስጥ ከዚህ የጨረታ ማወዳደሪያ ሀሳብ ውስጥ ከተጠቀሰው ጋር ተቀራራቢ በሆነ በጀት በስኬት የተጠናቀቁ ውሎችን (የውሎች ብዛት ይግባ) በአጭሩ ያስቀምጣል፡፡

እያንዳንዱ የሽርክ፣የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበር አባል የራሱን አግባብነት ያላቸው የውል ዝርዝሮችን በተናጠል ያቀርባል፡፡

የሥራው ስም፡- (ሙሉ ስም ይግባ)	የውል ግምታዊ ዋጋ በብር (በአሁን የዶላር ዋጋ)፡- (ግምቱ ይግባ)
ሀገር፡- (የሀገሩ ስም ይግባ) በሀገር ውስጥ የሚገኝበት ቦታ፡- (ይግባ)	ሥራው የፈጀው ጊዜ (ወራት)፡- (ይግባ)
የደንበኛው ስም፡- (ሙሉ ስም ይግባ)	የሠራተኛው ጠቅላላ ተሳትፎ በወራት፡-
የደንበኛው አድራሻ፡- (አድራሻው ይግባ)	በድርጅቱ የተሰጠው አገልግሎት ግምታዊ ዋጋ (በአሁኑ የአሜሪካን ዶላር)፡- (ግምታዊ ዋጋ ይግባ)
የስልክ ቁጥር፡- (የስልክ ቁጥሩ ይግባ)	ኢ-ሜይል አድራሻ፡- (አድራሻው ይግባ)
የተጀመረበት ቀን (ወር/አመት)፡- (ወርና ዓ.ም ይግባ)	የተጠናቀቀበት ቀን (ወር/ዓመት)፡-(ወርና ዓ.ም ይግባ)

የተባባሪ አማካሪዎች ስም (ካለ)፡-(ሙሉ ስም ይግባ)	በተባባሪ አማካሪዎች የተሰጡ ወራት- የባለሙያ ሠራተኞች ቁጥር፡-
በሥራው ላይ የተሳፈሉ ከፍተኛ ማዕረግ ያላቸው ሠራተኞች ስም (ፕሮጀክት ዳይሬክተር/አስተባባሪ፣ የቡድን መሪ) እና የተሰሩት ሥራዎች፡-	
የፕሮጀክቱ ታሪካዊ መግለጫ፡- (መግለጫው ይግባ)	
በእርስዎ ሠራተኛ የተሰጠው ትክክለኛ አገልግሎት ዝርዝር መግለጫ፡-	

የውሉን አጥጋቢ አፈፃፀም በተመለከተ የደንበኛው የምስክር ወረቀት ከዚህ ሰነድ ጋር ተያይዟል፡፡

ሠ. ሙያዊ ችሎታ እና ብቃት

የኛን (የአማካው ስም ይግባ) ሙያዊ ብቃት እና ችሎታ ለማረጋገጥ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ሰንጠረዥ የአሁኑን እና ከሁለት አመት በፊት የነበረውን የሠራተኞች ስታትስቲክስ ይዟል፡፡

አማካይ የሰው ኃይል	ካለፈው አመት በፊት		ያለፈው አመት		በዚህ አመት	
	አጠቃላይ	የዘርፉ ባለሙያዎች	አጠቃላይ	የዘርፉ ባለሙያዎች	አጠቃላይ	የዘርፉ ባለሙያዎች
ቋሚ						
ጊዜያዊ						
ድምር						

የሚከተሉት የቡድን ክህሎት ማትሪክስ ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክህሎቶች እና ለስራው ውጤታማ የሆነ መጠናቀቅ የሚያስፈልጉትን ክህሎቶች ይለያል፡፡

የባለሙያው ስም			
ሚና፡-	(ለምሳሌ፣የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ፣የቴክኒክ ስፔሻሊስት ወዘተ)		
እውቀት	የእውቀት ደረጃ	የህይወት ታሪክ ገጽ ማጣቀሻ	አስተያየት
ልምድ	የእውቀት ደረጃ	የህይወት ታሪክ ገጽ ማጣቀሻ	አስተያየት
ተጨማሪ እውቀት እና ልምድ	የእውቀት ደረጃ	የህይወት ታሪክ ገጽ ማጣቀሻ	አስተያየት

በሠንጠረዡ የሚታዩ የስራ ልምዶች በግለሰቡ ህይወት ታሪክ (C.V.)ገጾች ይደገፋሉ፡፡ ለቡድን የተሰጡ የክህሎት ደረጃዎችን ለማሳየት የሚከተሉትን ደረጃ አወጣጥ መስፈርት ተጠቅመናል፡-

መ	መግባባት	በተመሳሳይ መስክ የትምህርት አጋጣሚ ነበረው፤ ነገር ግን በተግባር ላይ የዋሉትን ክህሎቶች አልተጠቀመም፡፡
ሠ	ሥራ	በወጣው የክህሎት ደረጃ የተወሰነ የስራ ልምድ አለው፡፡
በ	ብቃት	የተለያየ አድማስ/ውስብስብ ባህሪ ያላቸውን ከ2-5 ፕሮጀክቶች ለመተግበር ይህንን ክህሎት ተጠቅሟል፡፡
መ	ሙያ	ያለውን ክህሎት በመጠቀም ከ5 በላይ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡

ረ. በቢጋሩ ላይ አስተያየቶች እና ሃሳቦች

(አማካሪው የስራውን ሁኔታ በተሻለ ለማከናወን በቢጋሩ ላይ መሻሻል አለበት ወይም መታየት አለበት ብሎ የሚያምንበትን ሁሉ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ከፕሮፖዛሉ ጋር አያይዞ ማቅረብ ይችላል።)

ሰ. በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚቀርቡ ሰራተኞች እና መገልገያዎች አስተያየት እና ሃሳብ

(አማካሪው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሠራተኞች፣ መረጃ፣ አገልግሎቶችና አቅርቦቶች ላይ ትችቶች/አስተያየቶች መስጠት አለበት፡፡)

ሸ. የሥራ አመራር እና የቁጥጥር ስርአት

(አማካሪው ውሉን ለማሰተዳደር የተመደቡት ክፍሎች በመግለፅ በቁጥጥር ስርዓት አይነቶች ወዘተ ዝርዝር መስጠት አለበት፡፡)

ቀ. የአማካሪ ኦዲት

(አማካሪ የኦዲተሮቹን ስም አድራሻ፣ እና ስልክ ቁጥር መስጠት አለበት፡፡)

በ. የባንክ ሂሳብ ቁጥር እና የባንክ አድራሻ

ክፍያው መፈፀም ያለበት የባንክ ሂሳብ የሚከተለው ነው፡-
(የባንክ አድራሻ በዝርዝር ይግባ)

ስም፤ (ጨረታ ፕሮፖዛሉ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ሙሉ ስም ይግባ)

ኃላፊነት፤ (ጨረታ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ህጋዊ ሀላፊነት ይግባ)

ፊርማ፤ (ከላይ ስሙና ሃላፊነቱ የተጠቀሰው ግለሰብ ፊርማ ይግባ)
(የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ)

በ እና ስለ ድርጅቱ በጨረታው ሰነድ ለመፈረም ስልጣኑ የተሰጠው መ/ቤት በዛሬው .....ቀን ..... ፤ (ቀን ይግባ) (ወር ይግባ) (የተፈረመበት ዓ.ም ይግባ)

አባሪዎች: /ዕዝሎች/

1. በጨረታው ሰነድ ላይ ለመፈረም ስልጣኑ የተሰጠው መ/ቤት የውክልና ስልጣን መግለጫ
2. አማካሪው ባለፉት አመታት ውጤታማ በሆነ መልኩ ያጠናቀቃቸውን ስራዎች የሚያሳይ ከሌሎች ተዋዋይ ወገኖች የተሰጠ ማረጋገጫ። (ተፈላጊ የሰርተፊኬቶች ቁጥር አስገባ)
   (ተፈላጊ የአመታት ብዛት አስገባ)
3. ለቀረቡት ሙያተኛ ሰራተኞች የግለሰቦች ህይወት ታሪክ (cv) መግለጫ ቅጽ ቴ4 (የቅጅዎች ብዛት አስገባ)
4. አዲት የተደረጉ የፋይናንስ መግለጫዎች
5. በጨረታው ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ መስፈርት መሰረት የአማካሪውን የፋይናንስ አቋም የሚያሳዩ ሰነዶች

ማስታወሻ፡-
ለአማካሪዎች፤ አማካሪው እንደሚከተለው ለሦስት ክፍሎች የተከፈለውን ቴክኒካዊ ፕሮፖዛል (50 ገፆች) ማቅረብ አለበት፡፡

i. የቴክኒካዊ አቀራረብ ዘዴ
ii. የሥራ እቅድ
iii. አወቃቀር በሠራተኛ በማደራጀት

3. የቴክኒክ መወዳደሪ ሀሳብ - ቅጽ ቴ3

ቦታ እና ቀን፤(ጨረታ የገባበትን ቀን ወርና ዓ.ም እንዲሁም ቦታ አስገባ)
የግዥ መለያ ቁጥር፤ (የግዥ መለያ ቁጥር አስገባ)
አማራጭ ቁጥር፤ (በአማራጭ የቀረበ ጨረታ ከሆነ መለያ ቁጥር አስገባ)

ለ፡ (የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስም ይግባ)
(የመልዕክት ሳጥን ቁጥር ይግባ)
(አድራሻ ይግባ)

ኢትዮጵያ

ሀ. የቴክኒክ አቀራረብ እና ዘዴ ፤

(በዚህ ምዕራፍ አማካሪው የስራው ዓላማዎች፣ የአገልግሎቶች አሠጣጥ፣ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ዘዴዎችን እና የሚጠበቀውን ውጤት ለማግኘት በተመለከተ መግለጫ መስጠት አለበት)

ለ. የስራ እቅድ

(በዚህ ምዕራፍ አማካሪው ዋና ክንውኖች ይዘታቸውና የሚፈጀው ጊዜ እና የሪፖርት ማቅረቢያ ቀኖችን በተመለከተ ሃሳብ ማቅረብ አለበት፡፡)

ሐ. አደረጃጀትና የሰራተኞች አመዳደብ

(በዚህ ምዕራፍ አማካሪው የቡድኑን አወቃቀርና ይዘት ሃሳብ መስጠት አለበት)

መ. የስራ የግዜ ሠሌዳ ፤ (ሳምንታት፤ ወራት፤ ይጠቀስ) ፣

ተ.ቁ	ተግባር	የጊዜ ሠሌዳ											
		1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ	5ኛ	6ኛ	7ኛ	8ኛ	9ኛ	10ኛ	11ኛ	12ኛ

(የስራውን ዋናዋና ክፍሎች ይጠቀስ)

ሠ. የቡድን ስብጥር እና የስራ ምደባ

ሙያተኛ ሰራተኞች				
ስም	ተቋም	የሙያ አይነት	የስራ ኃላፊነት	የተመደቡበት ስራ

ረ. የሰራተኞች የጊዜ ሰሌዳ (በቻርት መልክ ይቅረብ)

ተ.ቁ	የሰራተኛው ስም		የሠራተኞች ግብአት												አጠቃላይ የሠራተኞች ግብአት		
			1	2	3	4	5	6	7	8	9	10	11	12	በመስሪያ ቤትውስጥ	በመስክ	ጠቅላላ
የውጭ																	
1																	
2																	
3																	
ንዑስ ድምር 1																	
1																	
2																	

	ንዐስ ድምር															
	ድምር															

	የሙሉ ጊዜ ግብአት
	የትርፍ ግዜ ግብአት

(የሠራተኛ ግብአት ስራው ከተጀመረበት ጀምሮ መቆጠር አለበት ወይም እንደአስገላጊነቱ በሳምንትና በወራት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ለሙያተኞች የሠራተኛ ግብአት በስም መመልከት ሲኖርበት፤ለደጋፊ ሰራተኞች ደግሞ በስራ መደብ ብቻ መጠቀስ ይኖርበታል፡፡)

ስም፤ (በውል ፕሮፖዛሉ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ሙሉ ስም ይግባ)
ኃላፊነት፤(በውል ፕሮፖዛሉ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ህጋዊ አግባብነት ይግባ)
ፊርማ፤ (ከላይ ስሙና ሃላፊነቱ የተጠቀሰው ግለሰብ ፊርማ ይግባ)
(የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ)
በመወዳደሪያ ሀሳቡ በ..... እና ስለ ድርጅቱ የመፈረም ስልጣን ያለው
በዛሬው _____ቀን ..... (ቀን አስገባ) (ወር ይግባ) (የተፈረመበት ዓ.ም ይግባ)

አባሪዎች:
(ተያያዥ ሰነዶች ካሉ ዘርዝር)

4. የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበር መረጃ ቅጽ

ቀን፡- (ጨረታ ፕሮፖዛሉ የገባበት ቀን፣ ወርና ዓ.ም ይግባ)
የግዥ መለያ ቁጥር፡- (መለያ ቁጥር ይግባ)
አማራጭ ቁጥር፡- (ጨረታ ፕሮፖዛሉ እንደአማራጭ የቀረበ ከሆነ የመለያ ቁጥር ይግባ)

1.	ሽርክና ማህበር/ጊዜያዊ ማህበር ስም	(የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ማህበሩ ሙሉ ህጋዊ ስም ይግባ)
2	የስራ አመራር ቦርድ አድራሻ	
	ፖ.ሳ.ቁ	(የመልዕክት ሳጥን ቁጥር ይግባ)
	የመንገድ ስም	(የመንገድ አድራሻና ቁጥር ይግባ)
	ከተማ	(የከተማ ስም ይግባ)
	የፖስታ ኮድ	(ተገቢ ከሆነም የፖስታ ኮድ ይግባ)
	ሀገር	(የሀገር ስም ይግባ)
	ስልክ	(የሀገርና የከተማ ኮዶችን ባካተተ መልኩ የስልክ ቁጥር ይግባ)
	የኢ-ሜይል አድራሻ	(የኤመይል አድራሻ ይግባ)
3	በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና/ወይም በክልሉ የሚገኝ ኤጀንሲ ካለ (የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር ህብረት መሪው ከውጭ ሀገር ሲሆን)	
	ፖ.ሳ.ቁ	(የመልዕክት ሳጥን ቁጥር ይግባ)
	የመንገድ ስም	(የመንገድ አድራሻና ቁጥር ይግባ)
	ከተማ	(የከተማ ስም ይግባ)
	የፖስታ ኮድ	(ተገቢ ከሆነም የፖስታ ኮድ ይግባ)
	ሀገር	(የሀገር ስም ይግባ)
	ስልክ	(የሀገርና የከተማ ኮዶችን ባካተተ መልኩ የስልክ ቁጥር ይግባ)
	ፋክስ ቁጥር	(የሀገርና የከተማ ኮዶችን ባካተተ መልኩ የፋክስ ቁጥር ይግባ)
	የኢ-ሜይል አድራሻ	(የኤመይል አድራሻ ይግባ)
4	የአባላቱ ስም	
	አባል 1	(የመቀመጫ ህጋዊ ስምና አድራሻ ይግባ)
	አባል 2	(የመቀመጫ ህጋዊ ስምና አድራሻ ይግባ)
	ወዘተ	
5	የመሪው አባል ስም	(የመቀመጫ ህጋዊ ስምና አድራሻ ይግባ)
6	የሽርክና፣ የጥምረት ወይም የእሽሙር / ህብረት ስምምነት ገዢ ህግ	
	የተፈረመበት ቀን	(ቀን ይግባ፣ ቦታ ይግባ)
	ቦታ	
7	በአባላት መካከል ስላለው የኃላፊነት ክፍፍል (በመቶኛ) ስለሚሰጠው አገልግሎት አይነት እና ዝርዝር ጭምር	(በአባላት መሐከል ያለው የሃላፊነት ክፍፍል ይግባ) (ጨረታው ላይ የሚፈርም ግለሰብ ሙሉ ስም ይግባ) (ጨረታው ላይ የሚፈርም ግለሰብ ህጋዊ አግባብነት ይግባ) (ከላይ ስሙና ሃላፊነቱ የተጠቀሰው ግለሰብ ፊርማ ይግባ) (የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ) (ቀን አስገባ)፣ (ወር አስገባ)፣ (የተፈረመበት ዓ.ም ይግባ)

ስም፡ (በጨረታ ፕሮፖዛሉ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ሙሉ ስም ይግባ)

ኃላፊነት፡ (በጨረታ ፕሮፖዛሉ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ህጋዊ ሀላፊነት ይግባ)

ፊርማ፡ (ከላይ ስሙና ሃላፊነቱ የተጠቀሰው ግለሰብ ፊርማ ይግባ)
(የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ)
ቀን፡ (ቀን አስገባ) (ወር አስገባ) (የተፈረመበት ዓ.ም ይግባ)

(ማስታወሻ ለአማካሪዎች፣ ለእያንዳንዱ ስራ የተመደበው ባለሙያ ሠራተኛ ከዚህ በታች በተሰጠው ቅፅ መረጃ እንዲሰጥ ይፈለጋል። ይህም አማካሪው በቴክኒካዊ ፕሮፖዛሉ ላይ ማካተት አለበት።)

5. የባለሙያዎች ተፈላጊ መረጃ (CV) - ቅጽ ቴ4

1. የቀረበው የስራ ኃላፊነት (ለአንዱ ሃላፊነት አንድ ዕጩ ብቻ)_____
2. የተቋሙ ስም _____
3. የሰራተኛው ስም _____
4. የትውልድ ቀን _____ዜግነት_____
5. ትምህርት (የተቋሞች ስም በማመልከት ኮሌጅ/ዩኒቨርሲቲ እና ሌሎች የትምህርት ተቋሞች ይመልከት)_____
6. የሙያ ማህበራት አባልነት _____
7. ሌሎች ስልጠናዎች (በትምህርት ላይ ያልተካተቱ ሌሎች ወሳኝ ስልጠናዎች ይጠቀስ)_____
8. የስራው ልምድ የተገኘባቸው ሀገሮች (ባለፉት 10 ዓመታት የስራ ልምድ የተገኘባቸው ሀገሮች ይዘርዝር)_____
9. ቋንቋዎች (ለእያንዳንዱ ቋንቋ ያለው ችሎታ ጥሩ አጥጋቢና ደካማ በማለት ለንግግር፣ ለንባብና ለመፃፍ ይመልከት)_____
10. የስራ ቅጥር ማህደር (ከምረቃ ጀምሮ እስከ አሁን ያለው የስራ ልምድ ዝርዝር፣ ሃላፊነቶችም እንዲሁ ይጠቀስ) _____

ከ__ዓ.ም_____እስከ__(ዓ.ም)_____
አሰሪ_____
የስራ ኃላፊነት _____

11. የተመደቡት ስራዎች ዝርዝር (በዚሁ ስራ (task) ስር የሚከናወኑትን ሁሉ ዘርዝር)	12. የተመደበለትን ተግባር ለማከናወን ያለውን ችሎታ በይበልጥ የተሠሩ ስራዎች (በነጥብ 11 ስር የተዘረዘሩት የአባሉን ችሎታ ይበልጥ የሚገልፁ መረጃዎችን ከታች በተሰጠው መሠረት አመልክት) የተመደበበት ፕሮጀክት ስም _____ ዓመት፡_____ ቦታ፡_____ ደንበኛ፡_____ ዋና የፕሮጀክቱ ገጽታዎች፡ _____ የስራ ኃላፊነት፡ _____ የተከናወኑ ስራዎች፡ _____

ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ፊርማዬ የተመለከተው እስከማውቀው ድረስ የቀረበውን ካሪኩለም ቪቴ (cv) የእኔን፣ የትምህርት ደረጃ እና የስራ ልምዴን በትክክል እንደሚገልፅ አረጋግጣለሁ። በዚህ መግለጫ ላይ ሆን ተብሎ የሚደረግ ማሳሳት ከስራዬ ሊያባርረኝ ወይም ውድቅ ሊያደርገኝ እንደሚችል እገነዘባለሁ።

ቀን፡
ሀጋዊ/ስልጣን የተሰጠው ተወካይ ስም

(ማስታወሻ፡- ለአማካሪዎች፤ የጨረታ ዋስትናው በሚሰጠው የፋይናንስ ተቋም አርማ ባለው ወረቀት መዋፍ ያለበት ሲሆን በጨረታ ዋስትው ላይ እንዲፈር ተገቢው ስልጣን በተሰጠው ግለሰብ መፈረም አለበት፡፡ ይህም ጨረታው ላይ በተጫራቹ መካተት አለበት)

6. የጨረታ ዋስትና

ቀን፤ (ፕሮፖዛሉ የሚገባበት ቦታ፣ ቀን፣ ወርና፣ ዓ.ም ይግባ)
የግዥ መለያ ቁ. (የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ)
አማራጭ ቁ. (የማማከር አገልግሎቶቹ አጭር መግለጫ ይግባ)

ለ፡ *(የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሙሉ ስም ይግባ)*

የአማካሪ ሙሉ ስም_____ከዚህ በኋላ ‹አማካሪ› ተብሎ የሚጠቀሰው በግዥ መለያ ቁጥር_____በተደረገው ጥሪ መሠረት የማማከር አገልግሎት የመወዳደሪያ ሀሳብ ‹‹ከዚህ በኋላ የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ›› ተብሎ የሚጠቀሰውን አቅርቧል፡፡

ይህ ሰነድ ለሚደርሳችሁ በሙሉ እኛ የተመዘገበ ጽ/ቤታችን በ_____ የሆነው (ከዚህ በኋላ ‹‹ዋስትና ሰጪዎች››) ተብለን የምንጠቀሰው መጠን ብር _____ _____ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጨረታ ማስረከቢያ ዋስትና ለማቅረብ እንዲሁም ዋስትና ሰጪው በራሱ፣ በወራሾቹ ወይም ወኪሎቹ በጨረታው ደንብ ተገዢ ለመሆን የጨረታ ዋስትና አቅርበዋል፡፡ ይህንን የጨረታ ዋስትና በዋስትና ሰጪዎቹ የተለመደ ማህተም በዛሬው _____ቀን እንዲያርፍበት ሆኗል፡፡

የዚህ የውል ግዴታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ ንዑስ አንቀጽ 21.2 ካልተጠቀሰ በስተቀር አማካሪው በጨረታ መወዳደሪ ሀሳቡ መሠረት የጨረታ የአገልግሎት ጊዜ ሳያበቃ በጨረታው ከወጣ ወይም
2. አማካሪው በግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት የጨረታው መወዳደሪያ ሀሳብ መቀበሉን ከተገለፀለት እንዲሁም በጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ አገልግሎት ዘመን የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን ወይም ለማቅረብ ካልቻለ

    ሀ/ ውሉን ካልፈፀመ ወይም
    ለ/ የውል ማስከበሪያ ዋስትና በአማካሪዎች የጨረታ መመሪያ አንቀጽ 49 መሰረት ካላቀረበ

ግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት በመጀመሪያው የጽሁፍ ጥያቄ ሲያቀርብ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን መጠን ለመክፈል ተስማምተናል፡፡ ይህም ግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የክፍያ ጥያቄ ያቀረበው ተገቢ እና ትክክለኛ መሆኑን፤ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች አንዱ ወይም ከአንዱ በላይ በመከሰቱ ምክንያት የቀረቡ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ነው፡፡

ይህ ዋስትና የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የአገልግሎት ጊዜ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካለቀበት ቀን ጀምሮ ለ28 ተጨማሪ ቀናት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚቀርብ የክፍያ ጥያቄ ለዋስትና ሰጪው ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ መቆየት የለበትም፡፡

ስም፡ *(በጨረታ ፕሮፖዛሉ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ሙሉ ስም ይግባ)*

ኃላፊነት፡ *(በጨረታ ፕሮፖዛሉ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ህጋዊ ሀላፊነት ይግባ)*

ፊርማ፡ *(ከላይ ስሙና ሃላፊነቱ የተጠቀሰው ግለሰብ ፊርማ አስገባ)*
(የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ)

ቀን፡ *(ቀን አስገባ) (ወር አስገባ) (የተፈረመበት ዓ.ም ይግባ)*

7. የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ማሳወቂያ ፎርም፣

የግዥ መለያ ቁጥር ....[መለያ ቁጥር ያስገቡ]

የጨረታው ርዕስ/መግለጫ ስም፡ .....[የስራውን ስም ያስገቡ]

ለ፡-..... [ሙሉ የግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ ስም ያስገቡ)

እኛ ከታች ስማችን የተጠቀሰው ድርጅት/ድርጅቶች የሚከተሉትን የተጠቃሚ የባለቤትነት መብት መረጃዎችን እናቀርባለን።

ጠቃሚ የባለቤትነት ዝርዝሮች፡-

የተጠቃሚ ባለቤትነት መብት ማንነት		በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ 10% ወይም ከዚያ በላይ የሆኑትን አክሲዮኖች ይዘዋል? (አዎ/አይ)	በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ 10% ወይም ከዚያ በላይ የመምረጥ መብቶችን አለዎት? (አዎ/አይ)	በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አብላጫውን የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ተመጣጣኝ የአስተዳደር አካል የመሾም መብት አለዎት? (አዎ/አይ)	በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኩባንያው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ወይም ቁጥጥር የማድረግ አቅም አለዎት? (አዎ/አይ)
1. ሙሉ ስም		--------% በኩባንያው ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የአክሲዮን ድርሻ አለኝ፡፡	.... % በኩባንያው ውስጥ የመምረጥ መብት አለኝ፡፡	የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ተመጣጣኝ የአስተዳደር አካል ነኝ፡- አዎ ----- ይህ መብት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተያዘ ነው?: ቀጥታ	በድርጅቱ ውስጥ ተጽዕኖ ወይም ቁጥጥር የማድረግ አቅም አለኝ፡፡ አዎ --- አይደለም --- ይህ ተጽእኖ ወይም ቁጥጥር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ነው? ቀጥታ .....
ዲጂታል መታወቂያ ካርድ					
ፖስታ ሳ. ቁጥር					
ስልክ					
ኢሜይል					
ሥራ ወይም ሙያ					
2. ሙሉ ስም		--------% በኩባንያው ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የአክሲዮን ድርሻ አለኝ፡፡	..... % በኩባንያው ውስጥ የመምረጥ መብት አለኝ፡፡	የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም ተመጣጣኝ የአስተዳደር አካል ነኝ፡- አዎ ----- ይህ መብት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተያዘ ነው?: ቀጥታ	በድርጅቱ ውስጥ ተጽዕኖ ወይም ቁጥጥር የማድረግ አቅም አለኝ፡፡ አዎ --- አይደለም --- ይህ ተጽእኖ ወይም ቁጥጥር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ነው? ቀጥታ .....
ዲጂታል መታወቂያ ካርድ					
ፖስታ ሳ. ቁጥር					
ስልክ					
ኢሜይል					
ሥራ ወይም ሙያ....					

የአማካሪው ስም፡ [የአማካሪውን ሙሉ ስም አስገባ]
በአማካሪው ስም ጨረታውን ለመፈረም የተፈቀደለት ሰው ስም [በጨረታው ለመፈረም የተፈቀደለት ሰው ሙሉ ስም ያስገቡ]_____

ጨረታውን የፈረመው ሰው ኃላፊነት፡- [ጨረታውን የፈረመው ሰው ሙሉ ኃላፊነት አስገባ)

ከላይ የተጠቀሰው ሰው ፊርማ፡ [ስም፣ ኃላፊነት እና ፊርማ አስገባ]

የተፈረመበት ቀን [የተፈረመበት ቀን አስገባ] [ወር አስገባ]፣ [ዓመት አስገባ]

ለ. ፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ - መደበኛ ቅጾች

1. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ማስረከቢያ ሠንጠረዥ - ቅጽ ፋ1

ቦታ እና ቀን፤ *(ጨረታ የገባበትን ቀን ወርና ዓ.ም እንዲሁም ቦታ ይግባ)*

የግዥ መለያ ቁጥር፤ *(የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ)*

አማራጭ ቁጥር፤ *(በአማራጭ የቀረበ ጨረታ ከሆነ መለያ ቁጥር ይግባ)*

ለ፡ (የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስም ይግባ)
(የመልዕክት ሳጥን ቁጥር ይግባ)
(አድራሻ ይግባ)

ኢትዮጵያ

የቀረበው በ፡

	የአማካሪው ሙሉ ስም እና የመቀመጫ አድራሻ	ዜግነት
መሪ		
አባል		
ወዘተ....		

ከዚህ በላይ በተገለፀው የግዥ መለያ ቁጥር ..... በቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ መሠረት እኛ ከዚህ በታች ስምምነታችንን በመግለፅ የሚከተለውን እናረጋግጣለን፡-

(ሀ) የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ በግዥ መለያ ቁጥር (መላያ ቁጥር አስገባ) መርምረን ሙሉ ይዘቱን ተቀብለነዋል፡፡ በመሆኑም ደንቦቹ ያለምንም ተቃውሞ ተቀብለናቸዋል፡፡

(ለ) በቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ መጠይቅ መሰረት ለምናቀርበው የምክር አገልግሎት ማረጋገጫ የቴክኒክ እና የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦች አቅርበናል፡፡ *(የአገልግሎቶች አጭር መግለጫ ይግባ)*

(ሐ)በፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ የተጠቀሰው አጠቃላይ ዋጋ ሁሉንም ግብር ጨምሮ እንዲሁም ሌሎች ከታች በ‹መ› ውስጥ የተጠቀሱትን ተቀናሾችን ሳይጨምር ከዚህ በታች እንደተጠቀሰው ይሆናል፡፡ *(የሀገር ውል ታክስ ማስገባት አስፈላጊ ካልሆነ መስተካከያ ይደረግ)፣ (የገንዘብ አይነት ይግባ)*

(መ)የቀረቡት የዋጋ ቅናሾች እንዲሁም የአተገባበር ዘዴዎች እንደሚከተሉት ናቸው፡- *(ቅናሽ ይግባ)*

በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ቅናሽ፡ የእኛ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ ተቀባይነት ካገኘ የሚከተሉት የዋጋ ቅናሾች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ (እያንዳንዱ ቅናሽ የተደረገበት አይነት በዝርዝር ይገለፅ)

- **በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ ቅናሽ፡** የእኛ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቡ ተቀባይነት ካገኘ የሚከተሉት የዋጋ ቅናሾች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ *(እያንዳንዱ ቅናሽ የተደረገበት አይነት በዝርዝር ይገለፅ)*

- **የዋጋ ቅናሽ የአተገባበር ዘዴ፡** የዋጋ ቅናሹ የሚከተሉት የአሰራር ዘዴዎችን በመከተል ተግባራዊ ይሆናል፡፡ *(ቅናሽ ለማድረግ በጥቅም ላይ የዋለው ዘዴ ይገለፅ)*

- **በሁኔታዎች የሚደረግ ቅናሽ፡** የእኛ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ተቀባይነት ካገኘ የሚከተሉት የዋጋ ቅናሾች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ *(ቅናሽ የተደረገበት እያንዳንዱ አይነት በዝርዝር ይገለፅ)*

- **የዋጋ ቅናሽ አተገባበር ዘዴ፤** የዋጋ ቅናሾች የሚከተሉት አሰራር ዘዴዎችን ይከተላል፡፡ *(ቅናሹ ተግባራዊ ለማድረግ ስራ ላይ የዋለው ዘዴ ይገለፅ)*

(ሠ)በዚህ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርቡት ዋጋዎች የተዘጋጁት በገለልተኛ እና የማንኛውንም አማካሪ ወይም ተወዳዳሪ ምክር፣ ግንኙነት ወይም ስምምነት በሚገድብ መልኩ ነው፡፡ እነዚህም፤ *(የአማካሪው ስም ይግባ)*

i. እነዚህ ዋጋዎች

ii. መወዳደሪያ ሀሳብ ለማቅረብ ያለውን እቅድ ወይም

iii. እነዚህ ዋጋዎችን ለማስላት ተግባር ላይ የዋለ አሰራር ዘዴ ወይም ሁኔታዎች

(ረ) በዚህ የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ የሚቀርብ ዋጋ ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ለማንኛውም አማካሪ ወይም ተወዳዳሪ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አይቀርብም፡፡

(ሰ) የአቀረብነው የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠይቁ በቀረበው የማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ለ_____ቀናት ያገለግላል፡፡ እንዲሁም በእኛ ላይ በህግ ፊት ተፈፃሚነት ያለው ሲሆን የአገልግሎት ዘመኑ ከማብቃቱ በፊት ለሚደረጉ ማሻሻያዎች ተግባራዊ ይሆናል፡፡ *(የቀናት ብዛት ይገለፅ)*

(ሸ) ድርጅታችን የሚከስር ወይም የሚዘጋ ወይም ስራዎቻችን የታገዱ በፍ/ቤት ሂደት ውስጥ ያለን አለመሆናችን እናረጋግጣለን፡፡

(ቀ) በኢትዮጵያ የግብር ህግ መሰረት የታክስ ክፍያ ግዴታችንን አሟልተናል፡፡

(በ) ያቀረብነውን ማንኛውም የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ የመቀበል ግዴታ እንደሌለባችሁ ተገንዝበናል፡፡

ስም፤ *(በውል ፕሮፖዛሉ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ሙሉ ስም ይግባ)*

ኃላፊነት፤ *(በውል ፕሮፖዛሉ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ህጋዊ አግባብነት ይግባ)*

ፊርማ፤ *(ከላይ ስሙና ሃላፊነቱ የተጠቀሰው ግለሰብ ፊርማ ይግባ)*

(የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ)

ቀን፤ በዛሬው _____ቀን 2018……(ቀን አስገባ) (ወር አስገባ) *(የተፈረመበት ዓ.ም ይግባ)*

አባሪዎች:

1. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ (ቅጽ ፋ 2) እና
2. በግዥ ፈፃሚው የሚጠየቁ ሌሎች ሰነዶች

(ማስታወሻ ለአማካሪው፤ ይህ የፋይናንስ ፕሮፖዛል በአማካሪው ስም እንዲፈርም ስልጣን በተሰጠው ግለሰብ መፈረም አለበት)

2. የፋይናንስ የመወዳደሪያ ሀሳብ - ቅጽ ፋ2

ቦታ እና ቀን፤(ጨረታ የገባበትን ቀን ወርና ዓ.ም እንዲሁም ቦታ ይግባ)

የግዥ መለያ ቁጥር፤ (የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ)

አማራጭ ቁጥር፤ (በአማራጭ የቀረበ ጨረታ ከሆነ መለያ ቁጥር ይግባ)

ለ፡ (የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስም ይግባ)
(የመልዕክት ሳጥን ቁጥር ይግባ)
(አድራሻ ይግባ)

ኢትዮጵያ

ሀ. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ አጠቃላይ ዋጋ

የዋጋ ዝርዝር	ዋጋ	ዋጋ በኢት. ብር
የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ አጠቃላይ ዋጋ		

(በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚከፈል የሀገር ውስጥ ታክስ ጨምሮ አጠቃላይ ዋጋ ይገለፅ)

ለ. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ከዝርዝር ስራዎች አንጻር

የስራዎች ስብስብ (ምዕራፍ)፡-	መግለጫ፡-	
የዋጋ ዝርዝር	ዋጋ	ዋጋ በኢት. ብር
ክፍያዎች		
ተመላሽ ወጪ		
የአገር ውስጥ ግብር		
ድምር		

(ይህ ሰንጠረዥ 2.2 ቢያንስ ለአጠቃላይ ስራውን ለማከናወን የሚሸፍን መሆን አለበት። ዝርዝር ዋጋውን በተመለከተ አጭር መግለጫ መስጠት ያስፈልጋል፡፡)

ሐ. ዝርዝር ወጪ (ጊዜን መሰረት ያደረገ)

(ይህ ሰንጠረዥ የሚሞላው ጊዜን መሠረት ያደረገ የውል ቅፅ በፕሮፖዛል ጥያቄ የተካተተ እንደሆነ ነው።)

ተ.ቁ	የሰራተኛው ስም	ኃላፊነት	ሰራተኛ-ወር-ተመን	ግብአት-ሰራተኛ-ወር	ተመን	ተመን በኢ.ብር
የውጭ ሰራተኛ						
1						
2						
3						

ድምር 1						
የሀገር ውስጥ ሰራተኛ						
1						
2						
ድምር 2						
				አጠቃላይ ድምር		

(እያንዳንዱ ሰንጠረዥ ከስራ ከፍፍል አንፃር የተጠቀሰ የፋይናንስ ፕሮፖዛል ዝርዝር መሞላት አለበት። ለባለሙያዎች በየስማቸው፣ ለድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ደግሞ በስራ መደብ መቅረብ አለበት።)

መ. ዝርዝር ወጪ (በጥቅል)

(ይህ ሰንጠረዥ የሚሚላው የውል ቅፅ ንዑስ ድምር በፕሮፖዛል ጥያቄ የተካተተ እንደሆነ ነው።)

ተ.ቁ.	የሰራተኛው ስም	ኃላፊነት	ሰራተኛ-ወር-ተመን
የውጭ ሰራተኛ			
1			
2			
የሀገር ውስጥ ሰራተኛ			
1			
2			

(ይህ ሰንጠረዥ የሰው ሃይል ማሟላት እቅድ ሠንጠረዥ ላይ የተዘረዘሩ ሙያተኞችና አጋዥ ሠራተኞች በተመሳሳይ መልኩ መሟላት አለበት።)

ሠ. ተመላሽ የሚሆን ወጪ ዝርዝር (ጊዜን መሰረት ያደረገ)

(ይህ ሰንጠረዥ የሚሞላው ጊዜን መሠረት ያደረገ የውል ቅፅ በፕሮፖዛል ጥያቄ የተካተተ እንደሆነ ነው፡፡)

የስራዎች ስብስብ (ምዕራፍ)						
ተ.ቁ	መግለጫ	መለኪያ	መጠን	ብዛት	ዋጋ	ዋጋ በኢት. ብር
	የውሎ አበል	ቀን				
	አለም አቀፍ በረራዎች	ጉዞ				
	ልዩ ልዩ የጉዞ ወጪዎች	ጉዞ				
	የመገናኛ ወጪዎች					
	ማርቀቂያ፣ የሪፖርት ማባዣ					
	የመሳሪያ፣ ዕቃ፣ አቅርቦት ወዘተ					
	የግል እቃዎች ማጓጓዣ	በጉዞ				
	የኮምፒውተር፣ ሶፍትዌር					
	የላብራቶሪ ምርመራ					
	ንዑስ ውሎች					
	የአካባቢ የማጓጓዣ ወጪዎች					
	የመስሪያ ቤት ኪራይ፣ የጽህፈት ስራ					
	የግዥ ፈፃሚ መንግስት መ/ቤት ሰራተኞች ስልጠና					
	ጠቅላላ ወጪ					

ይህ ሰንጠረዥ ለእያንዳንዱ ሰንጠረዥ (በስራ አንፃር የተጠቀሰ የፋይናንስ ፕሮፖዛል ዝርዝር መሞላት አለበት)

ረ. ተመላሽ የሚደረግ ወጪ ዝርዝር (በጥቅል)

(ይህ ሰንጠረዥ የሚሞላው የውል ቅፅ ንዑስ ድምር በፕሮፖዛል ጥያቄ ያካተተ እንደሆነ ነው)

ተ.ቁ	ዝርዝር	መለኪያ	የአንዱ መለኪያ
	የውሎ አበል	ቀን	
	አለም አቀፍ በረራዎች	ጉዞ	
	ልዩ ልዩ የጉዞ ወጪዎች	ጉዞ	
	የመገናኛ ወጪዎች		
	ማረቀቂያ፣ የሪፖርት ማባዣ		
	የመሳሪያ፣ ዕቃ፣ አቅርቦት ወዘተ		
	የግል እቃዎች ማጓጓዣ	በጉዞ	
	የኮምፒውተር፣ ሶፍትዌር		
	የላብራቶሪ ምርመራ		
	ንዑስ ውሎች		

	የአካባቢ የማጓጓዣ ወጪዎች		
	የመስሪያ ቤት ኪራይ፣ የጽህፈት ስራ ድጋፍ		
	የግዥ ፈፃሚ መንግስት መ/ቤት ሰራተኞች ስልጠና		
	ጠቅላላ ወጪ		

(አግባብነት የሌላቸውን ሰርዝ፣ ወይም ሌሎች አይነቶች ጨምር፤ እያንዳንዱ ዋጋና የገንዘብ አይት ጥቀስ፤ የበረረ መስመሩ ይጠቀስ)

ስም፡ (በፋይናንስ ፕሮፖዛል ላይ የሚፈርም ግለሰብ ሙሉ ስም ይግባ)

የስራ ኃላፊነት፤ (በፕሮፖዛሉ ላይ የሚፈርም ግለሰብ ህጋዊ ሀላፊነት ይግባ)

ፊርማ፤ (ከላይ ስሙና ሃላፊነቱ የተጠቀሰው ግለሰብ ፊርማ ይግባ)
(የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ)

ቀን፤ (ቀን አስገባ) (ወር አስገባ) (የተፈረመበት ዓ.ም ይግባ)

አባሪዎች:

የአማካሪውን የፋይናንስ አቅም ለማወቅ በጨረታ ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ መቅረብ የሚጠበቅባቸው ሰነዶች፤

ክፍል 5: በጨረታ መሳተፍ የሚችሉ ሀገራት (ብቁ ሀገሮች)

ሀ. ለጨረታው ህጋዊ የሚሆኑ ሀገራት(ብቁ ሀገሮች)

የግዥ መለያ ቁጥር፡.....

በውሉ መሰረት የሚቀርቡ እቃዎች ወይም የምክር አገልግሎቶች ከማንኛውም አገር ሊቀርቡ ይችላሉ ነገር ግን የሚከተሉትን አያካትቱም፡፡

ሀ. ተፈላጊ የሆነውን አገልግሎት ለመስጠት የሚደረገውን ወድድር የሚያስተጓጉል በመሆኑ በኢትዮጵያ ፌ.ዲ.ሪ መንግስት እስከታመነበት ድረስ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት በህግ ወይም በደንብ ከአንድ የተወሰነ ሀገር የንግድ ግኑኝነት እንዳይደረግ የከለከለ

ለ. የተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት በምዕራፍ 7 የወጡትን ደንቦች እና ህጎች መሰረት በማድረግ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ከአንድ የተወሰነ ሀገር እቃዎች እንዳይገቡ ወይም በዛ ሀገር ለሚገኝ ሰው ወይም ድርጅት ክፍያ እንዳይፈጸም ያገደ ከሆነ፡፡

ምዕራፍ 2: የፍላጎት መግለጫ

ክፍል 6: ቢጋር

ማውጫ

1. የስራው ዳራ.....1
2. የሚፈለገው የምክር አገልግሎት ተፈፃሚነት ወሰን.....1
3. የፍላጎቶች መግለጫ.....1
4. የሰነድ አያያዝ ፍላጎቶች.....1

ክፍል 6፡ ቢጋር (Terms of reference)

ሀ. የስራው ዳራ

የተፈለገው አገልግሎት በህሪይና መጠን በአጭሩ ይገለፅ፤ የአገልግሎቱ ፍላጎት እንዴትና ለምን እንደመነጨ፤ አጠቃላይ የአገልግሎቱ አላማ እንዲሁም የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች አመጣጥ ይጠቀስ። ለምሳሌ፤ አገልግሎቱ የነበረ ነው ወይስ አዲስ፤ ከመጀመሪያው ጀምሮ የአገልግሎቱ ዝርዝር ፍላጎት ብሄራዊ ስታንዳርድ ወይም ሌላ አላማ መሰረት ማድረጉ ይገለፅ።

ለ.የሚፈለገው የምክር አገልግሎት ተፈፃሚነት ወሰን

ዝርዝር ፍላጎቱ ረጅም ከሆነ ይህ ክፍል እንደ ማጠቃለያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። በረጅሙ እንዲካተት ከተፈለገ ግን ከዚህ በታች በዝርዝር መግለጫው ላይ የሚካተት ይሆናል። የአገልግሎቱ ወሰን የሚከተሉትን ይጨምራል። በነዚህ ብቻ የተወሰነ ግን አይደለም።

- የአገልግሎቱ አጭር መግለጫና ተፈላጊ ውጤቶች
- ለአገልግሎቱ ታሳቢ የተደረገ ፍላጎት
- ተጫራቹ ስልጠና የሚሰጥ ወይም ሰነዶች የሚያቀርብ ስለመሆኑ
- ሌላ ተጫራቹ ማድረግ የሌለበት ወይም ያለበት ሁኔታ

ሐ. የፍላጎቶች መግለጫ

1. የሚቀርቡ የስኬትና ውጤት ዒላማዎች ዝርዝር

   (ግድ በሚሉ መመዘኛዎችና ለአማካሪው የተወሰነ ነፃነት በሚሰጡ መመዘኛዎች መሃከል ያውን ልዩነት ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል)

2. የሚያስፈልገው የስራ አፈፃፀም ደረጃ

   (ተፈላጊው ውጤት ለማምጣት የሚያስችል ተፈላጊው የአፈፃፀም ደረጀ (ከብዛት ጥራትና ጊዜ አንፃር) ይዘርዝር)

3. ዝርዝር የምክር አገልግሎት የመመዘኛ መስፈርቶች እና ዒላማዎች

   (የሚፈለጉት የማማከር፣ አገልግሎ ውጤቶች ከተወሰኑ በኋላ ሌሎች ተፈላጊ የጥራት ጉዳዮች በአግባቡ መለየት አስገላጊ ይሆናል።)

4. የጥራት ማረጋገጫ መስፈርቶች

   (ለሚፈለገ የጥራት መመዘኛዎች አማካሪው ተገዢ መሆኑን ለመገምገም የሚያስችሉ የአፈፃፀም መለኪያዎች ይዘርዝር)

5. የስራ አፈፃፀም መለኪያዎች እና ዒላማዎች

(መመዘኛዎቹ በአግባቡ ማሟላታቸውን እንዲሁም የተጠቀሱት የአፈፃፀም ደረጃዎች ማሟላታቸውን ለመገምገም የሚያስችሉ የአፈፃፀም መለኪያዎች ይዘርዝር)

6. የቦታ እጥረቶች እና ውስንነቶ

   (የተፈለገው የማማከር አገልግሎት የሚሰጥት ቦታ በማማከር አገልግሎቱ ላይ ያልተፈለገ ተፅዕኖ የሚያሳድር ከሆነ ችግሩ በዝርዝር ይጠቀስ)

7. የወጪ ዝርዝር
8. ለስልጠና አስፈላጊ ሁኔታዎች

   (የሚያስፈልገው ስልጠና አይነት፣ ደረጃ፣ የስጠናው ጊዜና ቦታ ይገለፅ)

9. የውል አስተዳደር መስፈርቶች

   (የሪፖርት አቀራረብ መመዘኛዎች ይቀመጥ)

10. የስራ ኃለፊነት መግለጫ

    (የአማካሪው የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተጠያቂነቶች በግልፅ ይቀመጥ)

11. የሽግግር ስርዓት

    (የሽግግር ስርዓቶች የውሉ መጀመሪያ መጠናቀቂያ ታሳቢ በማድረግ በግልፅ ይቀመጥ)

መ. የሰነድ አያያዝ ፍላጎቶች

ቢጋሩ ሌሎች ሰነዶችን ሊጠቅስ ይችላል። እነዚህ ሰነዶች የቢጋሩ መ/ቤት ሆነው ይቆጠራሉ። እያንዳንዱ ሰነድ የት እንደሚገኝ ተገልፆ በዝርዝር መቀመጥ አለበት። ቢጋሩ የሚጠቅሰው ከሰነዱ የተወሰነውን ክፍል ብቻ ከሆነ ይህንኑ ክፍል ብቻ መጠቀስ አለበት። ለምሳሌ፤

- ናሽናል ወይም እንተርናሽናል ስታንዳርድ
- ህጋዊነት
- ሌላ የመንግስት አዋጅ ወይም መመሪያ

ምዕራፍ 3: ውል

ክፍል 7: አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች

ማውጫ

ሀ. አጠቃላይ ድንጋጌዎች 1

1. ፍቺዎች 1
2. ሀላፊነት ስለመስጠት 4
3. የተዋዋይ ወገኖች ግንኙነት 4
4. ተገቢ ጥንቃቄ (DUE DELIGENCE) 4
5. ማጭበርበርና ሙስና 5
6. ትርጓሜ 6

ለ. ውል 7

7. የውሉ ሠነዶች 7
8. ውሉ የሚመራበት/የሚገዛበት ሕግ 8
9. የውል ቋንቋ 8
10. ማስታወቂያዎችና የጽሁፍ ግንኙነቶች 8
11. ኃላፊነት ላይ ያለው አባል ስልጣን 9
12. ስልጣን ያላቸው ኃላፊዎች 9
13. ሀላፊነትን ለሌላ ማስተላለፍ 9
14. ንዑስ የስራ ተቋራጭነት 10
15. የውል ማሻሻያዎችና ለውጦች 10
16. በሕጎችና ደንቦች ላይ የሚደረግ ለውጥ 11
17. ግብሮችና ቀረጦች 11
18. አስገዳጅ ሁኔታዎች 12
19. ውል ማፍረስ 13
20. ሀላፊነት ለሌላ ማስተላለፍን ስለማገድ 13
21. ውል ማቋረጥ 13
22. የውል መቋረጥ ሁኔታዎች 16
23. የመብቶችና ግዴታዎች መቋረጥ 16
24. የምክር አገልግሎትን ማቋረጥ 17
25. የአለመግባባቶች አፈታት 17
26. የታወቁ ጉዳቶች ካሳ 18
27. የማማከር አገልግሎት መጀመር 18
28. የማጠናቀቂያ ቀን 19
29. ምስጢራዊነት 19
30. ልዩ ልዩ 20

ሐ. የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግዴታዎች 21

31. የድጋፍና የነፃ መብት ድንጋጌ 21
32. የመሬት አቅርቦት 22
33. አገልግሎቶችና መገልገያ ዕቃዎች (FACILITIES) 23
34. ክፍያ 23

35. አቻ ሠራተኛ (የሰው ኃይል) 23
መ. ለአማካሪው የሚፈፀሙ ክፍያዎች 24
36. የውል ዋጋና የገንዘብ አይነት 24
37. የውል አይነት ..... ERROR! BOOKMARK NOT DEFINED.
38. አማራጭ 1- በጥቅል ዋጋ ውል መሰረት የሚፈፀሙ ክፍያዎች 24
39. አማራጭ 2- ጊዜን መሠረት ያደረጉ የውል ክፍያዎች ..... ERROR! BOOKMARK NOT DEFINED.
40. የክፍያ ጊዜ ሰሌዳና ቅድሚያ ክፍያ 24
41. የደረሰኝ አቀራረብና የአከፋፈል ሁኔታ 26
42. የዋጋ ማስተካከያ 28
ሠ. የአማካሪው ግዴታዎች 28
43. የአማካሪው ኃላፊነቶች 28
44. ብቁ መሆን (ውል ለመፈፀም) 29
45. የስነ ምግባር ደንቦች 30
46. የጥቅም ግጭቶች 31
47. የካሣ ክፍያና የተጠያቂነት ገደብ 32
48. በአማካሪው ሊሟሉ የሚገባቸው የመድን ዋስትናዎች 33
49. ጤና እና ደህንነት 34
50. የአዕምሯዊና የኢንዱስትሪ ንብረት ባለቤትነት መብቶች 35
51. ሪፖርት የማቅረብ ግዴታዎች 36
52. የሂሳብ አያያዝ፤ ኢንስፔክሽንና አዲት 36
53. የመረጃ (ዳታ) አጠባበቅ 36
54. ክለሳ (REVIEW) 37
55. የውል ማስከበሪያ ዋስትና 37
ረ. ውል ስለመፈፀም 38
56. የምክር አገልግሎቶች ተፈፃሚነት ወሰን 38
57. የሚጠበቁ ውጤቶች - DELIVERABLES 38
58. የምክር አገልግሎት አፈፃፀም 39
59. የአፈፃፀም መለኪያ 40
60. ቦታ (LOCATION) 42
61. የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ቦታዎችን (SITE) ስለመጠቀም 42
62. መገልገያ መሳሪያዎችና ዕቃዎች 43
63. ቁልፍ የሰው ኃይል 45
64. የሰው ኃይል ስለማፀደቅ 46
65. የሰው ሃይል ቁጥጥር እና ኢንስፔክሽን (ክትትል) 46
66. የሠራተኛው የሥራ ሠዓት 47
67. ሰራተኛ ማስወገድ እና/ወይም መተካት 48
68. ጊዜን ስለማራዘም 49
ሰ. ፍትሃዊነትና ታማኝነት (GOOD FAITH) 49
69. ቅን ልቦና (ታማኝነት) 49
70. የውል አፈፃፀም 49

ክፍል 7

አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች

ሀ. አጠቃላይ ድንጋጌዎች

1. ፍቺዎች

1.1 በዚህ አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ውስጥ ያሉት አርእስቶች በውሉና ትርጓሜ ላይ ምንም አይነት ገደብ፣ ለውጥ ወይም ተጽእኖ አያሳድሩም።

1.2 ከዚህ ቀጥሎ የሚገኙት ቃላትና ሐረጐች ከዚህ በታች የተሰጣቸውን ፍቺ ይይዛሉ።

ሀ "ሥልጣን ያለው ኃላፊ"	ማለት በየጊዜው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተሰየመ ግለሰብ ሲሆን ለአማካሪው በጽሑፍ የተገለፀለት እና ከውሉ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ነገሮች በሙሉ ግዥ ፈፃሚ አካሉን ወክሎ የሚሰራና ይህ ግለሰብ ማንኛውንም ሥልጣን የተሰጠው ተወካይም ጭምር ነው።
(ለ) "የከሰረ" "	ማለት የሚያመለክተው ማንኛውንም መ/ቤት ሲሆን ይኸውም ይህ መ/ቤት (i) ማንኛውም ኪሳራ ሲደርስ፣ ዕዳውን መክፈል የማይችል ሰው ሲኖር፣ እንደገና ሕጉን ለማውጣትና ለማደራጀት ወይም ተመሳሳይ ተግባር ለማከናወን እርምጃ ለመውሰድ ወይም የሕግ አሰራሩ ሲጀመር የሚስማማ ወይም የሚፈቅድ፣ የሚጀምር ወይም የክስ አቤቱታ የሚያስገባ ወይም በተቃራኒው ለክሱ አቤቱታ የሚያቀርብ ወይም የሚያሰማ ሲሆን (ii) ለአበዳሪዎቹ ጥቅም ሲል የሚሰራ ወይም ማንኛውንም አጠቃላይ ዝግጅት የሚያደርግ (iii) አለበለዚያም የከሰረ ወይም ዕዳውን ለመክፈል የማይችል (ነገር ግን በማስረጃ መሆን አለበት) (iv) ማንኛውንም ንብረት በተመለከተ ከፋይ አስተዳዳሪ፣ ተቀባይ፣ ባለአደራ፣ ጠባቂ ወይም ተመሳሳይ ሥልጣን ያለው ወይም (v) በአጠቃላይ መከፈል ያለባቸውን ዕዳዎች ለመክፈል የማይችል ሰው ማለት ነው።
(ሐ) "ማጠናቀቅ"	ማለት በውሉ ውስጥ በተቀመጡት ሕጐችና ደንቦች መሠረት አማካሪው የውሉን ሕጐች አክብሮ ሥራውን ሲያጠናቅቅ ነው።
(መ) "አማካሪ"	ማለት በውሉ መሠረት ሕጋዊ ወይም ተገቢ የሆነው ሰው ሲሆን ከሚመለከተው የመንግስት መ/ቤት የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የተፈቀደለት ሰው ማለት ነው።
(ሠ) "የውሉ ሰነዶች"	አጠቃላይ ሁኔታዎች ውስጥ የተዘረዘሩት ሰነዶች ሲሆኑ የሚያካትቱትም ተያያዦችን፣ አባሪዎችን እና በማጣቀሻው ውስጥ አብረው ያሉትን ሰነዶች በሙሉ ሲሆን ማንኛውንም ማሻሻያዎች ይጨምራል።
(ረ) "የውሉ ሥራ መሪ"	ማለት በአማካሪው የተሰየመና ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በየጊዜው በጽሑፍ የተገለፀለት ሲሆን ከውሉ ጋር ለተያያዙ ጉዳዬች የአማካሪው ተወካይ ሆኖ እንዲሰራ ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን ይህ ግለሠብ ሥልጣን የተሰጠው ሌላ ተወካይንም ያካትታል።
(ሰ) "የውሉ ዋጋ"	በዚህ ውል መሠረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአማካሪው የሚከፍለው ክፍያ ሲሆን ይህም ለባለመብት የሚከፈሉ ክፍያዎች (royalties) የፈቃድ ክፍያዎች እንዲሁም የዕምሯዊ ባለቤትነት መብትን ለመጠቀም ወይም ለማስከበር የሚያደርጋቸው ክፍያዎችን

	ይጨምራል
(ሸ) “ውል”	ማለት በመንግስታዊ መ/ቤት እና በአማካሪው መካከል የተደረገ የውል ስምምነት ሲሆን በውል ሰነድ የተጠቀሱ ሰነዶችን እና አባሪዎች፣ ተያያዥ ሰነዶችን እና በማጣቀሻው ውስጥ የተጠቀሱትን ሰነዶች በሙሉ ያካተተ ነው፡፡
(ቀ) “ቀን”	ማለት በተከታታይ ያሉ ቀናት ማለት ነው
(በ) “ማስረከብ”	ማለት አገልግሎትን ከአማካሪው ወደ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማስተላለፍ ሲሆን አገልግሎቱንም በውሉ ውስጥ በተጠቀሰው ሕግና ደንቦች መሠረት መፈፀም ማለት ነው፡፡
(ተ) “ውሉ” የሚፀናበት ቀን”	ማለት በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 27.1 መሠረትይህ ውል ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን ማለት ነው፡፡
(ቸ) “ብቁ ሀገሮች”	ማለት በጨረታ መወዳደሪ ሀሳብ በክፍል 5 ውስጥ በተዘረዘረው መሠረት ብቃት ያላቸው ሕገሮች እና ግዛቶች ማለት ነው፡፡
(ኀ) “አጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች”	ከአሁን በኋላ “አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች” ማለት ውሉ የሚገዙ በዚህ ውል ክፍል ውስጥ ያሉት ሕጐችና ደንቦች ናቸው፡፡ነገር ግን በልዩ የውል ሁኔታዎች ወይም በውል ስምምነቱ የተሻሻሉትን አይጨምርም፡፡
(ነ). “መልካም የኢንዱስትሪ ልምድ”(ተባባሪ)	ማለት የክህሎት፣ትጋት እና የአርቆ አስተዋይነት በተሞላበት ሁኔታ መተግበር ሲሆን ይኸውም ከዚህ ውል ጋር ተመሳሳይ የሆነ የማማከር አገልግሎቶችን ከሚሰጥ ችሎታና እና ልምድ ካለው አማካሪ የሚጠበቅ ነው፡፡ውሉንም ተዛማጅ በሆኑ የንግድ ማህበራት ባወጡት የሥነ ምግባር ሕጐች መሠረት ሥራውን ማካሄድ ማለት ነው፡፡
(ኘ) “መንግስት”	ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነው፡፡
(አ) “በጽሑፍ”	ማለት በእጅ ጽሁፍ ወይም በታይፕ የተመዘገበ (የተጻፈ) ሰነድ ማለት ነው፡፡
(ከ) “ኢንሹራንስ”	ማለት አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 48 በውሉ ውስጥ እንደተቀመጠው በአማካሪው መፈፀም ያለባቸው አስፈላጊ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎችን በሙሉ ማለት ነው፡፡
(ኸ) “የታወቁ ጉዳቶች”	ማለት በውሉ ውስጥ የተገለፀው ካሳ ሲሆን በአማካሪው የሚከፈል ነው። አማካሪው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ካሳ የሚከፍለው ውሉን ሳይፈጽም ከቀረ ወይም በውሉ መሠረት በጊዜ ካልጨረሰ ወይም በውሉ ውስጥ ያሉትን ሕጐች ሳያከብር ከቀረ ይሆናል፡፡
(ወ) “ቦታ”	ማለት በአባሪ“ሀ” የተገለፀውን እና የማማከር አገልግሎት የሚከናወንበትን ቦታ ወይም በሌላ በኩል ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትና አማካሪው በፅሁፍ የተስማሙበት ቦታ ማለት ነው፡፡
(ዘ) “ጠቅላላ የውል ዋጋ”	ማለት በውሉ መሠረት አገልግሎት የሚሰጥበትን ዋጋ ሲሆን የሚያካትተው ሁሉም የተወሰኑ አጠቃላይ ዋጋዎች ነው፡፡
(ዠ) “አባል””	ማለት የሽርክና ማህበር/ጊዜያዊ ህብረት ከመሠረቱት አካላት አንዱ ማለት ሲሆን አባላት ማለት ሁሉንም አካላት ያካትታል፡፡
(የ) “ወገን”	ማለት ግዥ ፈፃሚው ወይም አማካሪውን እና የተፈቀደላቸውን ወራሾችን እና “ወገኖችን” ያካትታል፡፡
(ደ) “የግል መረጃ”	ማለት ከማንኛውም መረጃ የሚለይ(የሚታወቅ) በሕይወት ያለ ግለሰብ እና /ወይም ከዚህ መረጃ እና ሌላ መረጃ ከአማካሪው ጋር የተያያዘ እና የግለሰቡን ኃሳብ የሚገልጽ እንዲሁም የአማካሪውን ዕቅድ የሚያሳይ ነው፡፡
(ጀ) “ሠራተኞች”	ማለት በአማካሪው ወይም በንዑስ አማካሪው የተቀጠሩ ሠራተኞች

	ሆነው አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን “የውጭ ሠራተኛ” ማለት ግን ከኢትዮጵያ ውጭ የመጣ ባለሙያ እና ደጋፊ ሠራተኛ ሲሆን አገልግሎት በሚሰናበት ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር እና በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 63 ውስጥ የተጠቀሰው “ቁልፍ ሠራተኛ” ማለት ነው፡፡
(ገ) “የመንግሥት መሥሪያ ቤት”	ማለት በሙሉ ወይም በከፊል በፌደራል መንግሥት በጀት የሚተዳደር ወይም በተቋቋመበት ሕግ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ተቋም ተብሎ የተሰየመ የፌደራል መንግሥት አካል ሲሆን በፌደራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶችን ይጨምራል፤
(ጠ) “የሚተኩ ወጪዎች””	ማለት ከሥራው ጋር ለተያያዙ ወጪዎች የሚከፈል ሲሆን የአማካሪውን ክፍያ አያጠቃልልም
(ሀሀ) “የአገልግሎት የግዥ ትእዛዝ”	በአጽህሮት “አ.ግ.ት.” የማማከር አገልግሎት ለመግዛት በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚቀርብ የግዥ ስምምነቶች እና የዋጋ ዝርዝር የያዘ አንድ መጠየቂያ ሰነድ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዱ የአገልግሎት የግዥ ትዕዛዝ የሚሰጠው የማማከር አገልግሎት ርክክብ የሚፈፀምበትን የዋጋ ዝርዝር የያዘ እና ገዢ የሆነ የውል መሳሪያ ነው፡፡
(ለለ) “አገልግሎቶች”	ማለት በአባሪ -ሀ ውስጥ በተገለፀው መሠረት በአማካሪው የሚሰጡ አገልግሎቶች ማለት ነው፡፡
(ሐሐ) “ልዩ የውል ሁኔታዎች”	ከዚህ በታላ ል.የው.ሁ በሚል የሚጠሩት ከስምምነቱ ጋር የተያያዙ የውል ሁኔታዎች ሲሆኑ ይህም ውሉን የሚገዛና ከአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች የበላይነት ያለው ማለት ነው፡፡
(መመ) “ንዑስ አማካሪ”	ማለት ማንኛውም ሰው የግል ወይም በመንግስት መ/ቤት ወይም ሁለቱም ሆኖ ሕጋዊ ወራሾች ወይም የተፈቀደላቸውን ወኪሎችን ጨምሮ ከፊል የማማከር አገለግሎትን ለመስጠት በአማካሪው የተቀጠሩ ማለት ነው፡፡
(ሠሠ) “ንዑስ ውል”	ማለት ማንኛውም ውል ወይም ስምምነት ወይም የቀረበ ውል ወይም ስምምነት ሲሆን የተፈጸመውም በአማካሪው (ወይም ወኪል ሠራተኛ ወይም ንዑስ አማካሪው) እና ማንኛውም ሶስተኛ ወገን ሲሆን ሶስተኛው ወገንም የተሰማማውም ለአማካሪው አገልግሎት ለመስጠት ወይም ለአመራሩ አስፈላጊ የሆነ መመሪያ ወይም ቁጥር ለማድረግ ነው፡፡ ነገር ግን የአማካሪውን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ለማገዝ አገልግሎቱን ለመስጠት ከሶስተኛ ወገን ጋር የተደረጉ ስምምነቶችን አይጨምርም፡፡
(ረረ) “ሶስተኛ ወገን”	ማለት ከግዥ ፈጻሚው ወኪል፣ ከአማካሪው ወይም ከንዑስ አማካሪው ውጪ የሆነ ሰው ወይም መ/ቤት ነው፡፡
(ሰሰ) “በጊዜ ላይ የተመሰረተ ውል”	ማለት ውል ሆኖ አገልግሎቱ የሚሰጠው በተወሰነ ክፍያ እና መጠን ሆኖ ሥራ በተሰራበት ጊዜ መሠረት ክፍያው ይፈጸማል፡፡
(ሸሸ) "የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ ስርዓት"	ማለትከህዝብ ግዥ ጋር የተያያዙ ተግባራት በኤሌክትሮኒክስ ስርዓት የሚከናወኑበት ስርዓት ነው.
(ቀቀ) የመፈጸሚያ ጊዜ	ማለት በውሉ ውስጥ ያሉት ተግባራት ወይም ግዴታዎች የሚጀምሩበት/ውሉን መፈጸም የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡
(በበ) የግዥ መለያ ቁጥር	ማለት የጨረታው መለያ ቁጥር ነው።

2. ሀላፊነት ስለመስጠት

2.1 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አቅራቢው አገልግሎቶችን እንዲያቀርብ ኃላፊነት ሲሰጠው፤

(ሀ) አቅራቢው በውሉ አፈጻጸም በማንኛውም ወቅት ሙያዊና ትህትና በተሞላበት ሁኔታ የግዥ ፈጻሚውን መ/ቤት ምስል ማሳየትና ማስተዋወቅ አለበት፡፡

(ለ) አቅራቢው ልዩ የውል ሁኔታዎችና የፍላጎት መግለጫዎችን በጥንቃቄና በትክክል ይፈጽማል፡፡

(ሐ) አቅራቢው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የወጡትን ህጎችና ደንቦች እንዲሁም መልካም የኢንዱስትሪ ተግባር የሚፈቅደውን ሁሉ ይፈጽማል፡፡

(መ) አቅራቢው በየጊዜው በሚመለከተው ባለስልጣን እየተሻሻሉ የሚወጡትን ፖሊሲዎች፣ ህጎችና ስነስርአቶች ያከብራል፡፡

(ሠ) አቅራቢው በአለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን የሚወጡትን የጥራት ደረጃዎች ያከብራል፡፡

(ረ) አቅራቢው በውሉ ዋጋና በዚሁ አንቀጽ የተጠቀሱትን የሀላፊነት አሰጣጥ ቃሎችና ሁኔታዎች ያከብራል፡፡

3. የተዋዋይ ወገኖች ግንኙነት

3.1 በዚህ ውል ውስጥ ያሉት ማናቸውም የግዥ ፈፃሚው እና የአማካሪው ግኑኝነት ልክ እንደ ጌታ እና አሽከር ወይም እንደ ወካይና ተወካይ ተደርገው መወሰድ የለባቸውም፡፡ አማካሪው በውሉ መሠረት ሠራተኞችንና ሥራውን የሚያከናውኑ ንዑስ አማካሪዎች የመቅጠር ኃላፊነት አለበት። እነሱ ለሚሰጡት አገልግሎት አማካሪው ኃላፊነቱን ይወስዳል፡፡

4. ተገቢ ጥንቃቄ (Due Deligence)

4.1 አቅራቢው ሊገነዘባቸው የሚገቡ ጉዳዮች፤

(ሀ) በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም ተወካይ የሚሰጠውን መረጃ ትክክለኛነት በተመለከተ ራሱን ለማርካት ተገቢ የሆነ ማጣራት ስራ ማከናወን ይገባዋል፡፡

(ለ) ውሉ ተግባራዊ ከሚሆንበት ቀን በፊት ሁሉንም ተገቢነት ያላቸው ጥያቄዎች ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማቅረቡን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(ሐ) ውሉ ውስጥ የገባው ራሱ ባደረጋቸው ተገቢ የሆኑ ጥንቃቄዎች በመተማመን ብቻ መሆን አለበት፡፡

4.2 አማካሪው የሥራውን አከባቢ በመመርመር ለግዥ ፈፃሚ መ/ቤት አገልግሎቱን ለመስጠት አመቺ አለመሆኑን በማረጋገጥ መግለጽ አለበት፡፡ ከዚያም የሥራውን አካባቢ ለማሻሻል መፍትሔ በማቅረብ፤የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀትና ተያያዥ ወጪውን በማውጣት በውሉ መሠረት ሥራው ከመካሄዱ በፊት ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት፡፡

4.3 አማካሪው የሥራውን ቦታ ለመመርመር ካልቻለ ወይም አስፈላጊውን የመፍትሔ እርምጃ በማዘጋጀት በአንቀጽ 4.2 መሠረት ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አስቀድሞ ካላሳወቀ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማንኛውንም ተጨማሪ ወጪ ወይም ክፍያ የመጠየቅ መብት የለውም፡፡እንዲሁም ኃላፊነቱ የሚወድቀው በአማካሪው ላይ ይሆናል፡፡ያለ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድአማካሪው ተጨማሪ ወጪ ወይም ክፍያ ማውጣት የለበትም፡፡

4.4 ከተገቢ ጥንቃቄ ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶች ለመፍታት አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን መጠቀም ይችላለ፡፡አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን የሚጠቀሙ ከሆነ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በተቋቋሙ እና በተገቢው መ/ቤት ዕውቅና በተሰጣቸው አካላት በኩል መሆን አለበት፡፡ከላይ በተዘረዘሩት አማራጮች መፍታት ካልተቻለ በክልሉ ህግ መሰረት የሚፈቱ ይሆናል፡፡

5. ማጭበርበርና ሙስና

5.1 የግዥ ፈጻሚ አካላት፤ተጫራቾችና አማካሪዎች በግዥ ሂደትና በውል አፈጻጸም ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የግዥ ስነምግባር እንዲከተሉ የሚጠይቅ ነው፡፡ የግዥ ፈፃሚ አካላት የማጭበርበርና የሙስና ድርጊት እንዳይፈፀም የሚከለክል አሠራር በጨረታ ሰነዶቻቸው ውስጥ እንዲያካትቱ ይደረጋል፡፡

5.2 አማካሪው እና/ወይም ሠራተኞቹ፣ንዑስ የሥራ ተቋራጮቹ፣ንዑስ አማካሪዎቹ፣አገልግሎት ሰጪዎቹ እና አቅራቢዎቹ በሙስና፣ በማታለል ተግባር፤በማሴር፣በማስገደድ ወይም በመመሳጠር ተግባሮች ላይ ተሰማርተዋል ብሎ ካመነ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአማካሪው የ14 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት በውሉ መሠረት የአማካሪውን የሥራ ቅጥር ይሰርዛል (ያቋርጣል)። በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 21.2(i) የማባረር ሁኔታው እንደተከናወነ የአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 21 ተግባራዊ ይሆናል፡፡

5.3 ውሉ በሚተገበርበት ወቅት የአማካሪው ሠራተኛ በሙስና፣በማታለል፣ በሴራ፣በማስገደድ ወይም በጉጂ ተግባር ላይ መሳተፉ ከተረጋገጠ ሠራተኛው በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 67 መሠረት ይባረራል፡፡

5.4 ቢሮው ለዚህ ደንብ ሲባል ከዚህ በታች ያሉትን ሕጐች በሚቀጥለው አኳኋን ተርጉሞታል፡-

(ሀ) “የሙስና ተግባር” ማለት በውሉ አፈፃፀም ወይም በግዢው ሂደት ውስጥ የመንግስት ባለስልጣን የሆነውን ሰው አስተሳሰብ ለመቀየር በቀጥታም ሆነ

በተዘዋዋሪ መንገድ ማንኛውም ዋጋ ያለውን ነገር ማቅረብ፣ መስጠት፣ መቀበል ወይም ማስማማት ነው።

(ለ) "የማጭበርበር ተግባር" ማለት የገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም ለማግኘት በግድየለሽነት እና ከግዴታ ለመሸሽ አንድን መ/ቤት አውቆ ማሳሳት ወይም መምከር፣ ወይም መጥፎ ሁኔታ ውስጥ መግባት ነው።

(ሐ) "የመመሳጠር ተግባር" ማለት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አማካሪዎች መካከል ግዢ ፈፃሚው መ/ቤት እያወቀ ይሁን ወይም ሳያውቅ ዋጋውን በሐሰት እና ነፃ ውድድር በሌለበት ሁኔታ ማቅረብ።

(መ) "አስገዳጅ ተግባር መፈፀም" በግዢው ሂደት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ በሰዎች ወይም በንብረታቸው ላይ ጉዳት በማድረስ ወይም ለማድረስ በማስፈራራት የውሉን አተገባበር ወይም ውሉ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ማዛባት ማለት ነው።

(ሠ) "የማሰናከል"(ማደናቀፍ)ተግባር ማለት

(i) አውቆ ማጥፋት፣ ማሳሳት፣ መለወጥ ወይም ማስረጃ መደበቅ ወይም የሐሰት ምስክርነት መስጠት በተለይ የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽንን፣ የፌዴራል ኦዲተሩን፣ የመንግስት ግዢና ንብረት ባለስልጣን ወይም የኦዲተሮችን ምርመራ ማሰናከል በሙስና በሐሰት፣ በማስገደድ ወይም በመመሳጠር እና /ወይም በማስፈራራት፣ በመጉዳት፣ በማስቆጣት ለምርመራው የሚያስፈልጉትን ነገሮች እንዳያጋልጡ በማድረግ የምርመራ ሂደቱን ማሰናከል ማለት ነው።

(ረ) የምርመራ ተግባሩን እና በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 52.2 የተሰጠው የኦዲት መብት ለማሰናከል የሚፈፀመው ድርጊትም የዘሁ መ/ቤት ተደርጎ ይወሰዳል።

5.5 አማካሪው በሙስና፣ በማጭበርበር፣ በማሰናከል፣ ወይም በማስገደድ ተግባር ላይ መሰማራቱን ቢሮው ካረጋገጠ አማካሪውን ለተወሰነ ጊዜ በመንግስት ግዢ እንዳይሳተፍ ሊያግደው ይችላል።

5.6 አማካሪው በሀገር አቀፍ ወይም አለም አቀፍ መ/ቤት በሙስና ወይም በማታለል ተግባር ላይ መሰማራቱ ከተገለፀ ባለስልጣን አማካሪውን የመወዳደር ብቃት እንደሌለው በመፈረጅ የመንግስት ውልን እንዳያገኝ የማድረግ መብት አለው።

5.7 አማካሪው በሙስና ተግባር የተሰማራ ከሆነ በኢትዮጵያ መንግስት ፈንድ ለሚከናወኑ ውሎች ቢሮው በሚቀጥራቸው ኦዲተሮች አማካኝነት የአማካሪዎችን ሂሳብ ለመመርመርና ኦዲት እንዲደረጉ የሚገልፅ አንቀጽ በተለይ ከውሉ ውስጥ እንዲካተት የመጠየቅ መብት ይኖረዋል።

5.8 በአማካሪውና በግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ወይም ከባለስልጣን ጋር የሚደረግ ማናቸውም ግንኙነት በተለይ ከማጭበርበር ወይም ሙስና ጋር የተገናኘ ከሆነ በጽሑፍ መሆን ይኖርበታል።

6. ትርጓሜ

6.1 እንደየአገባቡ ነጠላ ማለት ብዙ በአንፃሩም ብዙ ማለት ነጠላ ሊሆን ይችላል።

6.2 በነዚህ ሕጐችና ደንቦች ማንኛውንም ጸታ የሚጠቅሱ ቃላቶች የሚያካትቱት ሁለንም ፆታዎች ነው፡፡

6.3 ሙሉ ስምምነት

ይህ ውል ሁለንም ቃል ኪዳኖች፣ ደንቦች እና ሕጐች የያዘ ነው፡፡ የተዋዋይ ወገኖች ማንኛውም ኤጀንት ሆነ ወኪል እዚህ ውስጥ ያልተካተቱትን መግለጫዎች፣ ውክልና፣ ቃል መግባት ወይም ስምምነት ሊያደርግ አይችልም፡፡ በመሆኑም ተዋዋይ ወገኖች በዚህ ምክንያት በሕግ ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

6.4 ማሻሻያ

ማንኛውም በፅሁፍ ያልተደረገ፣ ቀን ያልተፃፈበት፣ በግል ውሉን የማይጠቅስና ተዋዋይ ወገኖች ስልጣን በሰጧቸው ተወካዮች ያልተፈረመ ማሻሻያ ወይም ለውጥ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

6.5 የተተወ ሆኖ አለመቆጠር

(ሀ) ከዚህ በታች ባሉት አጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 6.5 (ለ) መሠረት በማናቸውም ወገን የሚደረጉ መዘግየቶች መታገስ ወይም ቸልተኝነት በተለይ ሕጐቹንና ደንቦችን ማስፈፀም በዚህ ውል መሠረት የሌላውን ወገን መብት አይጐዳውም፣ አያግደውም፣ አያጎድለውም ወይም በአንዱ ወገን የሚደረግ የውሉን ደንብ ጥሰት እንደ ቀጣይ የውል ጥሰት ተደርጐ አይቆጠርም፡፡

(ለ) በዚህ ኮንትራት የአንዱን ወገን መብት፣ ሥልጣን ወይም መፍትሔ እንዲተው/እንዳይተገበር ከፈለገ በጽሑፍ ሆኖ ቀን የተፃፈበት የውክልና ሥልጣን ባለው ሃላፊ የተፈረመ እና እስከ ምንያህል ደረስ እንደማይተገበር መጥቀስ ይኖረበታል፡፡

6.6 ከፋፋይነት (Severability)

በዚህ ውል ውስጥ የማንኛውም ድንጋጌ ወይም ሁኔታ መከልከል ወይም ዋጋ ማጣት ወይም ያለመከበር (እገዳ) በውሉ ውስጥ ያሉ ሌሎች ድንጋጌዎች ወይም ሁኔታዎች ዋጋ አያሳጣም ወይም መፈፀምን አያስቀርም።

ለ. ውል

7. የውሉ ሠነዶች

7.1 ውሉን የሚያዋቅሩት ሰነዶች በሚከተለው አኳኋን በቅደም ተከተላቸው መሰረት ይተረጐማሉ፡፡፡

(ሀ) ስምምነቱ እና ሁሉም አባሪዎች

(ለ) ልዩ የውል ሁኔታዎች (ል.የው.ሁ)

(ሐ) አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች(አ.የው.ሁ)

(መ) በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በዝርዝር የተቀመጡት የውሉ መ/ቤት ተደርገው የሚቆጠሩት ማንኛውም ሰነዶች

7.2 ውሉን የሚያዋቅሩት ሰነዶች በሙሉ ተያያዥነት ያላቸው፣ ተደጋጋፊ እና አንዱ ሌላውን የሚያብራራ እንዲሆኑ ይጠበቃል።

7.3 በዚህ ውል መሰረት በግዢ ፈፃሚው መ/ቤት ወይም በአማካሪው እንዲወሰድ የተፈለገ ወይም የተፈቀደ ድርጊት፤ እንዲሰጥ የተፈለገ ወይም የተፈቀደ ማናቸውም ሰነድ፤ ሊወስድ ወይም ሊሰጥ የሚችለው በልዩ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 12.1 ውስጥ እንደተገለፀው ስልጣን ባለው ተወካይ ይሆናል፡፡

7.4 ውሉ የያዘው በግዢ ፈፃሚው መ/ቤት እና በአማካሪው መካከል የተደረገውን ስምምነት ሲሆን ከዚህ ውል በፊት የተደረጉ ሁሉንም ግንኙነቶች፣ ድርድሮች እና ስምምነቶች (የቃል ሆነ የጽሁፍ) የሚተካ ነው፡፡ የተዋዋይ ወገኖች ማንኛውም ኤጀንት ወይም ተወካይ በዚህ ስምምነት ውስጥ ያልተገለፀውን ማንኛውንም አይነት መግለጫ፣ ውክልና፣ ቃልኪዳን ወይም ስምምነት ለማድረግ አይችልም። ተዋዋይ ወገኖች በዚህ ምክንያት በህግ ተጠያቂ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

8. ውሉ የሚመራበት/የሚገዛበት ሕግ

8.1 በልዩ የውል ሁኔታዎች በተለየ ሁኔታ ካልተገለ በስተቀር ውሉ ትርጉሙ እና ፍቺው እንዲሁም በሁለቱ ወገኖች መካከል ያለው ግንኙነት የሚገዛውና የሚፈታው በክልሉ ወይም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕጐች መሰረት ይሆናል፡፡

9. የውል ቋንቋ

9.1 ከውሉ ጋር የተያያዙ ሰነዶች እና በጽሁፍ ሆነ በቃል የተደረገ ግንኙነት የሚደረገው በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በተገለፀው ቋንቋ ይሆናል፡፡ የውሉ ክፍል የሆኑ ደጋፊ ሰነዶች እና የታተሙ ጽሁፎች በሌላ ቋንቋ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በሌላ ቋንቋ የተሰጡ ሰነዶች በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በተገለፀው ቋንቋ ሊተረጎሙ ይገባል፡፡ ለውሉ ፍቺ ሲባል ይህ ትርጉም ገዢ ይሆናል፡፡

9.2 አማካሪው የትርጉሙን ዋጋ ይሸፍናል፡፡ በትርጉም መዛባት ምክንያት ለሚፈጠር ችግርም አማካሪው ተጠያቂ ይሆናል፡፡

10. ማስታወቂያዎችና የጽሁፍ ግንኙነቶች

10.1 በዚህ ውል መሰረት የሚሰጡ ማሳሰቢያዎች፣ ጥያቄዎች ወይም ስምምነቶች በጽሁፍ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ‹‹በጽሁፍ›› ማለት ግንኙነቱ በጽሁፍ ሆኖ ለተቀባዩ መድረሱ ሲረጋገጥ ነው፡፡

10.2 ማናቸውም ማስታወቂያዎች፣ ጥያቄዎች ወይም ስምምነቶች ለተቀባዩ ተሰጥቷል ወይም ደርሷል ተብሎ የሚወሰደው ባለጉዳዩ ስልጣን ለሰጠው ወገን በመ/ቤት ሲሰጥ ወይም በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በተገለፀው አድራሻ መላኩ ሲረጋገጥ ነው፡፡

10.3 በውሉ መሰረት አንዱ ወገን አድራሻውን ለመቀየር ከፈለገ ሌላውን ወገን በጽሁፍ በማሳወቅ የአድራሻ ለውጥ ማድረግ ይችላል፡፡

11. ኃላፊነት ላይ ያለው አባል ስልጣን

11.1 አማካሪው የሽርክና ማህበር/ጊዜያዊ ህብረት/ ከአንድ መ/ቤት በላይ ያያዘ ማህበር ከሆነ አባላቱ በውል ሁኔታዎች የተጠቀሰውን መ/ቤት ስልጣን በመስጠት እነሱን ወክሎ በዚህ ኮንትራት የተቀመጡትን የውል መብቶችና ግዴታዎች እንዲፈፀም ያደርጋል። ይህም ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ያለምንም ገደብ መመሪያ እና ክፍያ መቀበልን ይጨምራል።

12. ስልጣን ያላቸው ኃላፊዎች

12.1 ስልጣን ባለው ኃላፊ የተሰጠ ማንኛውም ማስታወቂያ፣ መረጃ ወይም የተደረገ ግንኙነት በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተሰጠ ወይም የተደረገ ሆኖ ይቆጠራል።

12.2 አማካሪው ስልጣን ለሌላቸው የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሰራተኞች የማማከር አገልግሎት አይሰጥም።

13. ሀላፊነትን ለሌላ ማስተላለፍ

13.1 ኃላፊነትን ለሌላ ማስተላለፍ ማለት በጽሁፍ የተደረገ ስምምነት ሆኖ አማካሪው ውሉን ወይም የውሉን መ/ቤት ለሶስተኛ ወገን ሲየስተላለፍ ነው።

13.2 ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በቅድሚያ የጽሁፍ ፈቃድ ሳይሰጠው አማካሪው ውሉን በሙሉ ይሁን በከፊል ወይም ከዚህ ውል በተያያዘ የሚገኙ ጥቅሞችንና ትርፎችን ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይችልም።

ሀ. ለአማካሪው ባንኮች ጥቅም ሲባል በውሉ መከፈል ያለባቸው ወይም ሊከፈል የሚገባው ገንዘብ ሲኖሩ፤

ለ. የአማካሪውን መብት ለአማካሪው ዋስትና ሰጪዎች መስጠት በተለይ ሌላ ሰው ካለበት ተጠያቂነት እንዲድን ከሆነ እና ዋስትና ሰጪዎቹ የአማካሪውን ኪሳራ ወይም ተጠያቂነት ካለፉት ሊሆን ይችላል።

13.3 በልዩ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 13.2 መሰረት የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አማካሪው ኃላፊነቱን እንዲያስተላልፍ መፍቀድ አማካሪው እስከአሁን ለፈፀማቸውና ሳያስተላልፋቸው ከቀሩት ከፊል የውል ስራዎች ጋር በተያያዘ ከሚኖሩት ግዴታዎች ነፃ አያደርገውም።

13.4 አማካሪው ያለፈቃድ ውሉን ለሌላ ሰው ከሰጠ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ያለምንም ማስጠንቀቂያ በውሉ ልዩ ሁኔታዎች አንቀጽ 19 እና 21 መሰረት በመብቱ ላይ ገደብ ይጥልበታል።

13.5 ውሉ የተላለፈላቸው አካላት ውሉ የሚጠይቀውን የብቃት መመዘኛ መስፈርቱን ማሟላት አለባቸው። በምንም አይነት መልኩ በውሉ ከመሳተፍም ሊታገዱ አይገባም።

13.6 ሁሉም ኃላፊነት የማስተላለፍ ተግባር ለዚህ ውል ደንብ ተገዢ ይሆናሉ። በውሉ ያሉ ሕጎችና ደንቦችንም ማካተት ይኖርባቸዋል ።

14. ንዑስ የስራ አማካሪነት

14.1 አንድ ንዑስአማካሪ ሕጋዊ የሚሆነው አማካሪው የውሉን ከፊል ስራ እንዲሰራለት ከሶስተኛ ወገን ጋር የፅሁፍ ስምምነት ሲያደርግ ብቻ ነው።

14.2 አማካሪው በውል ውስጥ ካልተካተቱ ንዑስ አማካሪዎች የማማከር አገልግሎት ማግኘት ከፈለገ አስቀድሞ ከግዥ ፈፃሚ መ/ቤት የፅሁፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት። ስለንዑስ አማካሪዎች ስለሚሰጡት የማማከር አገልግሎት እና ማንነት ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መገለፅ አለበት። በዚህም በውሉ አጠቃላይ ሁኔታዎች አንቀጽ 10 መሰረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በ15 ቀናት ውስጥ ማስታወቂያው እንደደረሰው ለአማካሪው ውሳኔውን ይሰጣል፤ ውሳኔውን የሚያዘገየው ከሆነም ምክንያቱን ይገልፃል።

14.3 የማንኛውም ንዑስአማካሪነት ደንብ የውሉ ደንብ ተገዥ እና ከውሉ አንቀፆች ጋር የሚጣጣም ይሆናል።

14.4 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትከንዑስ ስራአማካሪዎቹ ጋር ምንም አይነት የውል ግንኙነት አይኖረውም።

14.5 ንዑስ አማካሪዎቹ የውሉን መስፈርት አማልተው እስከተገኙ ድረስ በውሉ ላይ ከመሳተፍ ሊታገዱ አይችሉም።

14.6 አማካሪው በንዑስ አማካሪዎች፣ በወኪሎቻቸውና ሠራተተኞቻቸው የሚፈፀሙ ድርጊቶች በራሱ የተፈፀሙ ስህተቶችና ግዴለሽነቶች እንደሆኑ በመቁጠር ኃላፊነቱን ይወስዳል። የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከፊል የውሉ ስራ በንዑስ አማካሪዎች እንዲሰራ መፍቀድ አማካሪውን በዚህ ውል ከገባቸው ግዴታዎች ነፃ አያደርጉትም።

14.7 አማካሪው ያለ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ፈቃድ ከንዑስ አማካሪው ጋር ውል ከገባ ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት አማካሪውን በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀፅ 19 እና 21 መሰረት ያለምንም ማስጠንቀቂያ ማዕቀብ ይጥልበታል።

14.8 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትንዑስ አማካሪው ብቃት የሌለው መሆኑ ካረጋገጠ አማካሪው ብቃትና በቂ ልምድ ያለው ሌላ ንዑስ አማካሪ እንዲተካ ወይም ስራውን ራሱ እንዲያካሂድ ሊያደርግ ይችላል።

15. የውል ማሻሻያዎችና ለውጦች

15.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በማንኛውም ወቅት አማካሪውን በጽሁፍ ማስታወቂያ በአጠቃላይ የውል ሁኔታ አንቀፅ 10 መሠረት የውሉን አድማስ (ወሰን) ሳይለቅ ማሻሻያዎችን እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል።

15.2 የሚደረጉት ለውጦች በውሉ መሠረት የሥራውን ማጠናቀቂያ ጊዜ የሚያሳጥሩና የሚያስረዝሙ ሲሆን ተመጣጣኝ የሆነ የማስረከቢያ ወይም የማጠናቀቂያ ጊዜ ወይም ሁለቱም ተሰጥቶ ውሉ በዚሁ መሠረት መስተካከል አለበት። በዚህ አንቀጽ ስር በአማካሪው የሚጠየቅ ማስተካከያ አማካሪው ከግዥ ፈፃሚ አካሉ የለውጥ ትዕዛዝ ከደረሰው በሀያ ስምንት (28) ቀናት ውስጥ ማስታወቅ ይኖርበታል።

15.3 በአማካሪው የሚደረጉ የክፍያና የዋጋ ሁኔታዎች ቀደም ብለው በውሉ ውስጥ ካልተካተቱ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት በቅድሚያ ይስተካከላሉ፡፡

15.4 ማንኛውም በውሉ ደንብ ላይ የሚደረግ ለውጥ መመዝገብ አለበት፡፡ እንዲሁም አማካሪው ስልጣን በሰጠው ፊርማ እና በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መተግበር ይኖርበታል፡፡ የተደረጉት ለውጦች ለውጡ በመካሄዱ ምክንያት በውሉ ላይ ሊመጡ የሚችሉ ቀጣይ ማሻሻያዎችንም ከግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን አለባቸው፡፡

15.5 የተደረገው ለውጥ በፊርማ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን በማሻሻያው ካልተጠቀሰ በስተቀር ወደኃላ ተመልሶ ተግባራዊ አይሆንም፡፡

15.6 እያንዳንዱ የተመዘገበው ለውጥ መፈረምና የቅደም ተከተል ቁጥርና ቀን ሊፃፍበት ይገባል፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትና አማካሪው የለውጡን የስምምነት ውል እያንዳንዳቸው ኦርጅናሉን (ዋናውን) የመያዝ መብት አላቸው፡፡

15.7 ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ልዩነት ከሌላቸው ውሉ ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

16. በሕጎችና ደንቦች ላይ የሚደረግ ለውጥ

16.1 በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የመወዳደሪያ ሀሳብ በመጠየቂያ ከወጣ በኃላ ማንኛውም ህግ፣ ደንብ፣ ትዕዛዝ፣ ወይም የህግ አቅም ያለው ውስጠ ደንብ ታትሞ ቢወጣ ቢጣስ ወይም የውል ቦታ ቢለወጥ (ስልጣን ባለው መ/ቤት የሚደርግ የትርጉም የአፈፃፀም ሁኔታን ጨምሮ) እና ይህም በቀጣይነት የማስረከቢያውን ቀንና ወይም የውሉን ዋጋ ሲያስቀይር በአማካሪው ላይ በደረሰው ችግር መጠን ይህ የማስረከቢያ ቀን ወይም የውል ዋጋ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ አይችልም፡፡

17. ግብሮችና ቀረጦች

17.1 በውሉ በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር አማካሪው በመንግስት፣ ማዘጋጃ ቤት፣ በክልሉ፣ በኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ውጪ ከምክር አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁሉንም አይነት የግብር፣ ቀረጥ እና ሌሎች ክፍያዎች የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

18. አስገዳጅ ሁኔታዎች

18.1 ለዚህ ውል ሲባል ‹‹አስገዳጅ ሁኔታዎች›› ማለት ከአማካሪው ቁጥጥር ውጪ የሆኑ እና የተከሰቱ ነገሮች ሲሆኑ እነዚህም ነገሮች አማካሪው ግዴታውን እንዳይወጣ የሚያግዱት ሆነው ከዚህ በታች የተመለከቱትን ያካትታል፡-

(ሀ) ውሉን እንዳይፈፀም በመንግስት የሚደረግ ክልከላ

(ለ) የተፈጥሮ አደጋዎች ለምሳሌ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ እሳት፣ ፍንዳታ፣ ማዕበል፣ ጐርፍ ወይም ሌሎች መጥፎ የአየር ሁኔታዎች ወይም

(ሐ) አለም አቀፍ ወይም የእርስ በርስ ጦርነት
(መ) ሞት ወይም ከባድ አደጋ ወይም ባልተጠበቀ ሁኔታ አማካሪው ከታመመ ወይም
(ሠ) የፍትሐብሔር ህግ ላይ የተጠቀሱ ሌሎች ከአቅም በላይ የሆኑ ነገሮች

18.2 ከዚህ በታች ያሉት ነገሮች ከአቅም በላይ የሆኑ ነገሮች ተደርገው አይቆጠሩም፡-

(ሀ) ስራውን እያካሄደ እያለ አድማ ወይም አመጽ ማካሄድ አንዱን ወገን ወይም የንግዱን ቅርንጫፍ የሚጐዳ ከሆነ
(ለ) ውሉን ለመፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ጥሬ እቃዎች ዋጋን መጨመር ወይም መቀነስ
(ሐ) አዲስ ሕግ ወጥቶ ተበዳሪው ግዴታውን ለመወጣት የበለጠ ሲያስቸግረው
(መ) በአማካሪው፣ በንዑስ አማካሪው ወይም በወኪሉ ወይም በሰራተኛው በቸልተኝነት ወይም ሆን ተብሎ የተፈፀመ ጥፋት ከሆነ
(ሠ) አማካሪውበሚከተሉት ላይ በቅድሚያ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግና መገመት የነበረበት ሲሆን፤

(i) ውሉ ስራ ላይ የሚውልበትን ጊዜ፣
(ii) ግዴታን በመወጣት ሂደት ሊያስወግዳቸው ወይም ሊቋቋማቸው የሚችሉትን ሁኔታዎች

(ረ) የገንዘብ አቅም ውሱንነት ወይም ተገቢ ክፍያ አለመፈፀም

18.3 ግዴታዎቹን ለመወጣት ያልቻለ አማካሪ ግዴታውን ያልተወጣው ከአቅም በላይ በሆኑ ክስተቶች ከሆነ እና አማካሪው ሁሉንም አስፈላጊ ቅድመ ጥንቃቄ እና ምክንያታዊ የሆኑ አማራጭ እርምጃዎችን ከወሰደ ግዴታውን እንዳልተወጣ እና ውሉን እንዳቋረጠ ተደርጎ መቆጠር የለበትም፡፡

18.4 አስገዳጅ ሁኔታዎች ያጋጠሙት አማካሪ ችግሮቹን ለመወጣት ምክንያታዊ በሆነ መንገድ

(ሀ) በአጭር ጊዜ ውስጥ ግዴታውን እንዳይወጣ ያደረጉትን ሁኔታዎች ማስወገድ
(ለ) በአስገዳጅ ሁኔታው ምክንያት የሚፈጠሩ ጉዳቶችን መቀነስ አለበት።

18.5 በአስገዳጅ ሁኔታዎች የተጐዳ አማካሪ በተቻለ መጠን ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤትስለሁኔታው መከሰት፤ የችግሩ አይነትና ምክንያት ድርጊቱ ከተፈፀመ ከአስራ አራት (14) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መግለጽ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም ችግሮች ተወግደው ሁኔታዎች ወደ ነበሩበት የተመለሱ መሆናቸው በተቻለ ፍጥነት ማሳወቅ አለበት፡፡

18.6 በዚህ ውል መሰረት አንደኛው ወገን አንድን ስራ በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ካላጠናቀቀ በጠፋው ጊዜ ልክ የመጠናቀቂያው ጊዜ ሊራዘምለት ይገባል፡፡

18.7 አስገዳጅ ሁኔታዎች ተከስተው አገልግሎት ለመስጠት በማይችልበት ወቅት አማካሪው ግዢ ፈፃሚ መ/ቤት በሚሰጠው መመሪያ የሚከተሉትን ተግባራት ይፈጽማል፡-

(ሀ) ሰራተኞቹን እና መሳሪያዎቹን ያነሳል፡፡ ወጪውም በገዥው መ/ቤት ይፈፀማል፡፡

(ለ) አማካሪው በተቻለ መጠን አገልግሎት መስጠቱን ይቀጥላል፡፡ ሆኖም ግን በውሉ መሰረት ለአማካሪው ይከፈላል፡፡ አስፈላጊ ከሆነም ተጨማሪ ክፍያ ካለ ይፈፀማል፡፡

18.8 በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት አማካሪው ውሉን ለመፈፀም ካልቻለ 30 (ሰላሳ) ቀናት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሁለቱ ወገኖች ተወያይተው በተቻለ መጠን ስራው እንዲቀጥል ስምምነት ላይ ሊደርሱ ይገባል፡፡

18.9 ነገር ግን የአስገዳጅ ሁኔታው መከሰት ወይም መጠን እነዚህ ወገኖች ካላስማማቸው ጉዳዩ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 25 መሰረት ይፈታል፡፡

19. ውል ማፍረስ

19.1 አንደኛው ወገን ውል አፈረሰ የሚባው በውሉ ላይ በተገለፀው መሰረት ግዴታውን ሳይወጣ ሲቀር ነው፡፡

19.2 የውል ጥሰት ሲኖር ለተጐዳው ወገን የሚከተሉትን ነገሮች ይፈፀማሉ፡-

(ሀ) በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 26 ውስጥ እንደተገለፀው ለጉዳቱ ካሳ የመጠየቅ እና/ወይም

(ለ) የውል መቋረጥ

19.3 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የካሣ ክፍያ ተጠቃሚ ሲሆን ለአማካሪው ሊከፍል ከሚገባው የውል ዋጋ ተቀናሽ ያደርጋል ወይም የሚመለከተውን ዋስትና ሰጪ መ/ቤት ይጠይቃል፡፡

20. ሀላፊነት ስለማገድ

20.1 አማካሪው በዚህ ውል የገባውን ግዴታ ካልፈፀመ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በፅሁፍ በማሳወቅ ያስተላለፈለትን ኃላፊነት ሊያግድና የአማካሪውንም ክፍያዎች ሊያዘገይ ይችላል፡፡ የፅሁፍ ማስታወቂያውም የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

ሀ. የድክመቱን ሁኔታዎች መግለጽ

ለ. ማስታወቂያው ከደረሰው በሰላሳ /30/ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተበላሸውን ስራ እንዲያስተካክል አማካሪውን መጠየቅ

21. ውል ማቋረጥ

በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውል ማቋረጥ

21.1 ውል የሚቋረጠው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እና አማካሪው በውሉ መሰረት ያላቸው መብት ወይም ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ነው፡፡

21.2 በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ውስጥ ለስራ መቋረጥ ከተገለፀው በተጨማሪ ለአማካሪው ከሰላሳ ባላነሱ ቀናት ውስጥ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የስራው መቋረጥ ምክንያት እና ውሉ የሚቋረጥበት ቀን በመግለጽ ውሉ ይቋረጣል፡፡ (በአንቀጽ (በ) ከተጠቀሰው ከስድሳ (60) ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ የሚሰጥ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በስተቀር) ማስጠንቀቂያው የሚሰጠው በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 21.2 (ሀ) እስከ (ሐ) ውስጥ የተገለፁት ድርጊቶች ማናቸውም ከተፈፀሙ ይሆናል፡፡

(ሀ) አማካሪው በውሉ ውስጥ የተገለፀውን የማማከር አገልግሎቱን በሙሉ ወይም በከፊል ለመስጠት ካልቻለ ወይም በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 68 መሰረት ግዥ ፈፃሚው የሰጠውን የማራዘሚያ ጊዜ ሳይጠቀም ከቀረ ወይም የማማከር አገልግሎቱ በውሉ ውስጥ የተገለፁትን የፍላጎቶች መግለጫ ካላሟላ ይሆናል፡፡

(ለ) በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀፅ 20 መሠረት አማካሪው የእገዳ ማስጠንቀቂያ በተሰጠው በሰላሳ ቀናት ውስጥ ወይም ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጽሁፍ በፈቀደለት ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ጉድለቱን ሳያስተካክል ሲቀር

(ሐ) አማካሪው (ወይም አማካሪው ከአንድ መ/ቤት በላይ ከሆነ፣ አባላቱ) ከከሰረ ወይም ከአበዳሪዎቹ ጋር ከእዳ ነፃ ለመሆን ከተስማማ ወይም ለአበዳሪዎቹ ጥቅም ሲል የሕግ ከለላ ተጠቃሚ ሲሆን ወይም እንደገና ለማዋቀር ወይም ውህደት ለመፍጠር ካልሆነ በስተቀር በአስገዳጅ ሁኔታ ወይም በፈቃደኝነት ጉዳቱን ከተቀበለ

(መ) በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 25.2 መሰረት መደበኛ ያልሆነ ቀጥተኛ ድርድር ተደርጎ የተደረሰበት የመጨረሻ ውሳኔ አማካሪው ሳያሟላ ከቀረ

(ሠ) በአስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት አማካሪው ከስድሳ (60) ላላነሱ ቀናት የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ካልቻለ

(ረ) አማካሪው ያለግዥ ፈፃሚ አካሉ ፈቃድ ውል ወይም ንዑስ ውል ከሰጠ

(ሰ) ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት አማካሪው ሙያዊ የስነ ምግባር ጥሰት መፈፀሙን በማስረጃ ሲያረጋግጥ

(ሸ) አማካሪው በመንግስት በጀት የመደበለትን ፕሮጀክት የውል ግዴታን ባለመወጣጡ ምክንያት የውል ጥሰት መፈፀሙ ሲረጋጥ፡፡

(ቀ) አማካሪው በጨረታ ውድድር ወይም በውል አፈፃፀም ሂደት በሙስናና በማታለል ተግባር ከተሠማራ

(በ) በውሉ ማሻሻያ ሰነድ ተመዝግቦ ካልቀረበ በስተቀር በአማካሪ ህጋዊ ሰውነት ወይም ባለቤትነት ላይ ልዩነት የሚያስከትል ድርጅታዊ መዋቅር ለውጥ ሲደረግ

(ተ) የውሉን አፈፃፀም የሚያሰናክል ማንኛውም ሌላ ህጋዊ እግድ

(ቸ) አማካሪው ተገቢውን ዋስትና ወይም የመድን ሽፋን ካልሰጠ ወይም ዋስትናውን ወይም የመድን ሽፋኑን የሚያቀርበው መ/ቤት ግዴታውን ካልተወጣ

(ነ) የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የግዥ ፍላጎት ግልፅ በሆነ ምክንያት ከተለወጠ

(ኘ) በውሉ ዋጋ እና በገበያ ዋጋው መካከል ከፍተኛ ልዩነት ካለ እና ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውሉን ለመተግበር የማያዋጣው ሲሆን

(ኛ) ግዥ ፈፃሚው በራሱ ስልጣንና በማንኛውም ምክንያት ውሉን ለማቋረጥ ከወሰነ

(አ) በአጠቃላይ ውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 26.1(ለ) ውስጥ በተጠቀሰው መሰረት የተከማቸው የታወቀ የጉዳት ካሳ ከፍተኛ ደረጃ ሲደርስ

በአማካሪው የሚደረግ የውል ማቋረጥ

21.3 አማካሪው ከሰላሳ (30) ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት የጽሁፍ የማስጠንቀቂያ በመስጠት ከዚሁ በታች የተዘረዘሩት ድርጊቶች ከተፈፀሙ በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 21.3 /ሀ/ እስከ /መ/ መሰረት የስራ ውሉን የሚያቋርጠው፡-

(ሀ) በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 25 ከተጠቀሱት በአማራጭ የአለመግባባት አፈታት ሁኔታዎች በስተቀር ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአማካሪው መክፈል የነበረበት ክፍያ አማካሪው ክፍያው የዘገየበት መሆኑን በመግለጽ በጽሁፍ ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 45 ቀናት ውስጥ ሳይከፍል ሲቀር

(ለ) የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት በውሉ መሰረት ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት የውል ጥሰት ሲፈጽምና አማካሪው የውል ጥሰት መፈጸሙን በጽሁፍ ካሳወቀው ከ45 ቀናት በኋላ (ወይም አማካሪው በፈቀደው የግዜ ገደብ) ጉድለቱን ሳያስተካክል ሲቀር

(ሐ) በአስገዳጅ ሁኔታዎች ከስልሳ /60/ ቀናት ውስጥ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ካልቻለ

(መ) ግዥ ፈፃሚው በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 25 መሰረት አለመግባባቱን ለመፍታት የተሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ ሳይቀበል ሲቀር

ውሉ ሲቋረጥ ስለሚኖሩ አለመግባባቶች

21.4 በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 21.2 (ሀ) እስከ (ነ) ወይም በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 21.3 ከተጠቀሱት ሁኔታዎች አንዱ መከሰቱ ላይ በተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት ከተነሳ ውሉ እንዲቀረጥ ማስታወቂያ የደረሰው ወገን ማስታወቂያ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት በአርባ አምስት (45) ቀናት ውስጥ ጉዳዩን በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 25 መሰረት በአማራጭ የአለመግባባት አፈታት እንዲፈታ ይጠይቃል፡፡እንዲሁም ውሉ በአማራጭ የአለመግባባት አፈታት ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አለመግባባት ምክንያት እንዲቋረጥ አይደረግም፡፡

21.5 ግዥ ፈፃሚው በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 21.2 (ሀ) እስከ (ነ) በተጠቀሱት ምክንያቶች ውሉን የሚያቋርጠው ከሆነ አማካሪው በውሉ መቋረጥ ምክንያት ለግዥ ፈፃሚው ሳይሰጥ የቀራቸውን አገልግሎቶች ከሌላ ተመሳሳይ አማካሪ ዘንድ ግዥ ሊፈጽም ይችላል፡፡በዚህ ምክንያት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለሚደርስበት ተጨማሪ ወጪዎች አማካሪው ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ ነገር ግን አማካሪው ያልተቋረጠውን የውል ግዴታ ማከናወኑን ይቀጥላል፡፡

21.6 ግዥ ፈፃሚው በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 21.2 (ኘ) መሰረት ውሉ ከተቋረጠ በውሉ ማቋረጫ ማስታወቂያ ላይ ውሉ የተቋረጠው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አመቺነት ስለመሆኑና በአማካሪው የውሉን ምን ያህል ስራ እንደሚያከናውን እና የውሉ መቋረጥ ተግባራዊ የሚሆንበት ቀን መግለጽ አለበት፡፡

ውሉ ሲቋረጥ የሚኖር ክፍያ

21.7 ግዥ ፈፃሚው በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 21.2 (ኘ) በተጠቀሰው ሁኔታ ውሉን ካቋረጠው ውሉ ከመቋረጡ በፊት አማካሪው ያወጣቸውን ወጪዎች በሙሉግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ይመልስለታል (ይተካለታል)፡፡

21.8 ግዥ ፈፃሚው በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ንዑስ አንቀጽ 21.2 (ሐ) የሚያቋርጠው ከሆነ ለአማካሪው የሚከፍለው ካሳ አይኖርም፡፡ይህም የሚሆነው በውሉ መቋረጥ ምክንያት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሊያነሳቸው የሚችሉ የይገባኛል የክፍያ ጥያቄዎች አንደተጠበቀ ሆኖ ነው፡፡

21.9 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በዚህ አንቀጽ መሰረት ውሉን ሲያቋርጥ ጥርጣሬዎችን ለማስቀረት ቀሪ የውሉ ዋጋ እና ተከፋይ መጠን በሚመለከት አማካሪው በሚያነሳቸው ይገባኛል የክፍያ ጥያቄዎች ምንም አይነት ገደብ አይጣልበትም፡፡

22. የውል መቋረጥ ሁኔታዎች

22.1 ግዥ ፈፃሚው እና አማካሪው የውሉን መቋረጥ ወይም ጊዜ ማለፍ በውሉ መሰረት እንደሚቀጥሉ የተጠቀሱ የሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች የውል ነክ ግዴታዎች እንደቀሩ አይቆጠርም፡፡

22.2 ውሉ ሲቋረጥ ወይም የውሉ ዘመን ሲጠናቀቅ ከምክር አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁሉንም መረጃዎች፣ ሰነዶች እና ማህደሮች (በኤሌክትሬኒክስ ወይም በሌላ መልኩ የተቀመጡ) ለግዢ ፈፃሚው መረከብ ይኖርበታል፡፡አማካሪው የእንደዚህ አይነቶቹን መረጃዎች ከምክር አገልግሎቱ ጋር የማይገናኝ ወይም ህግ በሚፈቅደው መልኩ ቅጂ የመያዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ በተጨማሪም አማካሪው ከግዢ ፈፃሚው ጋር ውሉ ሲቋረጥ እንደዚህ አይነቶቹ ተዛማጅ ዳታዎች፣ መረጃዎች እና ንብረቶች ርክክብ ሂደት ላይ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡ እንደዚህ አይነቶቹ ትብብሮች የዕለትተዕለት ተግባራት ሳይደናቀፉ የሚደረገው ሽግግር የተቃና ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሁሉንም ሰነዶች፣ ሪፖርቶች፣ ማጠቃለያዎች እና ሌሎች የሚያስፈልጉ የመረጃ ልውውጦች አቅርቦት ክፍት ማድረግን ይጨምራል፡፡

23. የመብቶችና ግዴታዎች መቋረጥ

23.1 ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች በስተቀር በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 21 መሰረት ውል ሲቋረጥ ወይም በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 28 መሰረት ውል ሲጠናቀቅ በዚህ ውል ስር ያሉ የሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች መብቶች እና ግዴታዎች ይቋረጣሉ፡፡

(ሀ) እነዚህ አይነቶቹ መብቶች እና ግዴታዎች ውሉ በሚቋረጥበት ወይም የውሉ ዘመን ሲጠናቀቅ ቢሆንም ተፈፃሚ የሚሆኑ ከሆነ

(ለ) በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 29 በተቀመጠው መሰረት ሚስጢር የመጠበቅ ግዴታ

(ሐ) አማካሪው ላሉት ሂሳቦች እና ማህደሮች በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 52 መሰረት ቁጥጥር፣ ቅጂ እና ኦዲት የማድረግ ፈቃድ መስጠት ግዴታ ሲኖርበት

(መ) ማንኛውም ወገን በገንዘው ሕግ ሊኖረው ስለሚችል መብት

24. የምክር አገልግሎትን ማቋረጥ

24.1 አንደኛው ወገን ለሌላኛው ወገን በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 21 በተጠቀሰው መሰረት ውሉ እንዲቋረጥ ማስታወቂያ በመስጠት ውሉን ሲያቋርጠው አማካሪው የማማከር አገልግሎቱን በተቻለ ፍጥነት ስርአት ባለው መንገድ ማቋረጥ አለበት። ለዚህ ጉዳይ የሚወጣውንም ወጪ አሳማኝ በሆነ መንገድ ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡ በአማካሪው የተዘጋጁ ሰነዶችን በሚመለከት እና በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተሰጡትን መሳሪያዎች እና እቃዎች በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ 50 ወይም 62 መሰረት እንደየቅደም ተከተላቸው መፈፀም አለበት፡፡

25. የአለመግባባቶች አፈታት

25.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አማካሪውን መቀጠል እንደሌለበት በጽሁፍ ካላሳወቀው በስተቀር የውሉ ህጋዊነትን ጨምሮ ማንኛውም አለመግባባት ሲከሰት አማካሪው በውሉ መሰረት የገባውን የውል ግዴታ ወይም ስራዎች እንዲቀጥል ሁለቱም ወገኖች በጋራ ተስማምተዋል።

25.2 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እና አማካሪው በመግባባት በቀጥታና መደበኛ ባልሆነ ድርድር በማድረግ በውሉ ወይም በውሉ ትርጓሜ የሚነሱ አለመግባባቶች፣ ግጭቶች ወይም ልዩነቶች መፍታት ይኖርባቸዋል፡፡

25.3 በተፈቀደለት የስራ ኃላፊ ወይም በአማካሪው የውል መሪ የማይፈቱ አለመግባባቶች ከተነሱ ጉዳዩ በአጠቃላይ የውል ሁኔታ ንዑስ አንቀጽ 25.4 ወደ ተጠቀሰው የአለመግባባት አፈታት ሥርዓት ሊመሩት ይችላሉ፡፡

25.4 ከላይ በንዑስ አንቀፅ 25.3 የተጠቀሰው ሁኔታ በድጋሚ ሲያጋጥም ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ና አማካሪው ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን ተወካዮች በመምረጥ ለብቻ ተገናኝተው አለመግባባቱ በውይይት እንዲፈታ ማድረግ አለባቸው፡፡ ወይይቱ የሚካሄደው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሰብሳቢነት ሲሆን የስብሰባው ውጤቶችም በቃለጉባኤ ይመዘገባሉ፡፡ ስብሰባዎቹ የሚካሄዱት ስብሳቢው በመረጣቸው ሁኔታዎችና ቦታዎች (በስልክ የሚካሄድ ስብሰባንም ይጨምራል) ሲሆን አላማቸው አለመግባባቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ነው፡፡

25.5 ተዋዋዮች አለመግባባትን ወይም ውዝግብን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከጀመሩበት ዕለት ጀምሮ በ28 ቀናት ውስጥ መፍታት ካልቻሉ በልዩ የውል ሁኔታው በሚገለጸው መሰረት አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን መጠቀም ይችላሉ፡፡ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን የሚጠቀሙ ከሆነ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በተቋቋሙ እና በተገቢው መ/ቤት ዕውቅና በተሰጣቸው አካላት በኩል ያለበት ሲሆን መ/ቤቱ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን የሚጠቀም ከሆነ በልዩ የውል ሁኔታዎች ላይ ማሳወቅ አለበት፡፡ ከላይ በተዘረዘሩት አማራጮች መፍታት ካልተቻለ አንደኛው ወገን የኢትዮጵያ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ጉዳዩን ወደ ፍ/ቤት ሊያቀርበው ይችላል፡፡

25.6 በሕግ የተፈቀደላቸው የግዥ ፈጻሚ አካላት ብቻ ወደ ግልግል ዳኝነት መ/ቤት መቅረብ ይችላሉ፡

26. የታወቁ ጉዳቶች ካሳ

26.1 በውሉ አጠቃላይ ሁኔታዎቹ አንቀጽ 18 ላይ ከተገለፀው በስተቀር አማካሪው የማማከር አገልግሎቱን መፈፀም ካልቻለ ግዢ ፈፃሚው መ/ቤት የሚከተሉትን የጉዳት ካሣ ክፍያዎችን ከውል ዋጋው ላይ ይቀንሳል፡፡

(ሀ) የማማከር አገልግሎት ሳይሰጥ ለቆየበት እያንዳንዱ ቀን የአገልግሎቱ ዋጋ 0.1 በመቶ ወይም 1/1000 ቅጣቱ አገልግሎቱ እስኪሰጥ ወይም እስኪፈፀም ድረስ ይቀጥላል፡፡

(ለ) የሚከፈለው አጠቃላይ ቅጣት የውሉን 10 በመቶ ዋጋ መብለጥ የለበትም፡፡

26.2 አማካሪው ውል በመፈጸም ረገድ በመዘግየቱ የውሉ ስራዎች ላይ ጉዳት የሚደርስ ሲሆን የግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ከፍተኛው የጉዳት ካሳ መጠን (10%) እስኪደርስ ድረስ መጠበቅ ሳያስፈልገው በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 20 መሰረት የቅድሚያ ማስታወቂያ በመስጠት ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል::

27. የማማከር አገልግሎት ሥራውን ስለመጀመር

27.1 ይህ ውል ተግባራዊ የሚሆነው ግዢ ፈፃሚው አማካሪውን ስራ እንዲጀምር ካዘዘበት ቀን ጀምሮ "ውል የሚፀናበት ቀን" ይሆናል፡፡ ይህ ትዕዛዝ የሚያረጋግጠው በውሉ ልዩ ሁኔታዎች የተዘረዘሩትን መሟላታቸውን ነው፡፡

27.2 አማካሪው የአገልግሎት ስራውን በውሉ ልዩ ሁኔታዎች ላይ በተገለፀው ጊዜ መሰረት ይጀምራል፡፡

27.3 ውሉ በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎቹ አንቀጽ 27.1 በተጠቀሰው ቀን ተግባራዊ ካልሆነ 1ኛው ወገን ከሀያ አንድ (21) ቀናት በማያንስ የጊዜ ሠሌዳ ለሌላኛው ወገን በጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ውሉ ውድቅ እንደሆነ ያሳውቃል፡፡ በማናቸው ወገን እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ እንዲታወቅ ከተደረገ ማንኛውም ወገን ምንም አይነት የይገባኛል ጥያቄ አያነሳም፡፡

28. የማጠናቀቂያ ቀን

28.1 በዚህ ስምምነት በአጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎቹ ክፍል 21 መሰረት ቀድሞ ካልተቋረጠ በስተቀር አቅራቢው በውሉ ልዩ ሁኔታዎች ተብሎ በተቀመጠው የመጨረሻ ማጠናቀቂያ ጊዜ ስራውን ማጠናቀቅ አለበት፡፡

29. ምስጢራዊነት

29.1 ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት እና አማካሪው በሌላኛው ወገን የተሰጠውን ማንኛውም በውል ጊዜ ወይም በኃላ የተሰጠ ሰነድ ማስረጃ ከውል መጠናቀቅ ወይም መቋረጥ በፊት ለሶስተኛ ወገን አሳልፈው መስጠት የለባቸውም፡፡ የሰነዶቹ መሰጠት ሕገወጥነት የሚያስፋፋ ሕግ አስከባሪዎችን የሚያደናቅፍ ወይም የሕዝብ ጥቅምን የሚጠብቁ ተዋዋይ ወገኖች የግብይት ፍላጎት የሚያበላሽና ነፃ ውድድርን የሚገታ ስለሚሆን ነው፡፡ ነገር ግን አማካሪው ለንዑስ አማካሪው እና ለውሉ መልካም አፈፃፀም የሚረዱትን ከግዥ ፈፃሚው የተረከባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ሚስጢራዊነቱን እንዲጠብቅ እና በዚህ አንቀፅ ውስጥ በአማካሪው ላይ የተጣለው ግዴታ እንደሚፈፅም ንዑስ አማካሪውን ቃል በማስገባት ሊሰጠው ይችላል፡፡

29.2 ግዥ ፈፃሚ ይህንን መስል ሰነዶች፣ መረጃ እንዲሁም ከአማካሪው የሚቀበሉ ሌሎች መረጃዎች ከዚህ ዓላማ ጋር ለማይዛመዱ ጉዳዮች ሊገለገልበት አይችልም፡፡ አማካሪውም ከግዥ ፈፃሚ የሚቀበላቸው መሰል ሰነዶች፣ መረጃዎች እና ሌሎች መረጃዎች በኮንትራት ስምምነት መስፈርት ከተቀመጠው የማማከር አገልግሎት ውጭ መጠቀም የለበትም፡፡

29.3 ነገን ግን በዚህ ክፍል ስር የተጣሉት የተዋዋይ ወገኖች ግዴታዎች በሚከተሉት ምስጢራዊ መረጃዎች ላይ ተግባራዊ አይደረጉም፡፡

(ሀ) የግዥ ፈፃሚ ወይም አማካሪው ውልን በገንዘብ ከሚደገፉተቋሞች ጋር መረጃ መለዋወጥ ይኖርባቸዋል

(ለ) የተዋዋዮች ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ባልሆነ ሁኔታ አሁንም ይሁን ወደፊት ህዝብ ዘንድ መረጃ ሲደርስ

(ሐ) መረጃውን ይፋ ለማድረግ ህጋዊ እውቅና በተሰጠው ሶስተኛ ወገን በኩል ለሶስተኛ ወገን ሲደርስ

(መ) መረጃው በሚቀርብበት ጊዜ ለተዋዋይ ወገን ከመድረሱ አስቀድሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሶስተኛ ወገን የተያዘ መሆኑ ሲረጋገጥ

(ሠ) ከሌላው ወገን በተደረገ የጽሁፍ ስምምነት መረጃው ይፋ መደረጉ ሲረጋገጥ፡፡

29.4 ተዋዋይ ወገኖች ጠቅላላ እውቀታቸውን ተሞክሮና ልምዳቸውን እንዳይጠቀሙም አያግድም፡፡

29.5 አማካሪው ግዥ ፈፀሚው መ/ቤት በየጊዜው በፅሁፍ ለሚያሳውቀው ግለሰብ ወይም ግለሰቦች ሚስጢራዊ መረጃዎችን ይፋ እንዲያደርግ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡ ይህም መረጃ የሚውለው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በውሉ መሠረት የሚቀርቡትን የማማከር አገልግሎቶች ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ለማጣራት በሚያደርገው ጥረት አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እስከተጠቀመበት ጊዜ ድረስ ማለትም ለንፅፅር

(Benchmarking) ተብሎ ለሚታወቀው አገልግሎት ብቻ ሲሆን ነው፡፡ ሚስጢራዊ መረጃዎች ይፋ ለሆኑበት አላማ አንጂ ለሌላ ተግባር እንዳይውሉና በሚስጢር እንዲያዙ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተቻለውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ግዢ ፈፃሚው መ/ቤት ተጨባጭ ምክንያት ሳይኖረው በገበያ ያለው ዝቅተኛ ዋጋ ትክክለኛ የሆነ ዝቅተኛ ዋጋ ነው ብሎ አይወስድም (አያምንም)፡፡

29.6 አማካሪው በሚከተሉት ሁኔታዎች ተስማምቷል

(ሀ) ከንኡስ ክፍል 29.6 (ለ) የተመዘገበ ሪኮርድ መረጃ ይፋ ላለማድረግ የሚቀርቡ ማናቸውም ጥያቄ ብቸኛ ውሳኔ ሰጪው ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት መሆኑን፤

(ለ) ግዢ ፈፃሚው መ/ቤት በንዑስ አንቀጽ 29.6 (ሀ) መሠረት የቀረበ መረጃ ይፋ የማድረግ ጥያቄን በሚመለከትበት ወቅት አማካሪው ከግዢ ፈፃሚው መ/ቤት ጋር ይተባበራል፡፡ እንዲሁም ግዢ ፈፃሚው ጋር መተባበር አለበት፡፡በዚሁም መሠረት አማካሪው ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚቀርብለትን የትብብር ጥያቄ ምላሽ በአምስት (5) ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ መስጠት እንዳለበት፤

29.7 አማካሪው በንኡስ አማካሪዎች ዕጅ ወይም ሥልጣን ስር የሚገኙ ሁሉም መረጃዎች ቅጂዎች ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መረጃውን በጠየቀ በ 5 የስራ ቀናት ወስጥ /ወይም ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚያመላክተው ጊዜ/ ማቅረብ አለበት፡፡

29.8 ግዥ ፈፃሚው የአማካሪው ሚስጥራዊ መረጃዎች ማያያዝ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ጥያቄ ተቀባይነት ባለው የመመሪያ መሰረት ቀርቦ የአማካሪው ምክር ይጠበቃል፡፡

29.9 ከላይ የተጠቀሱት የዚህ አንቀፅ ደንቦች ከውል በፊት በሁሉቱም ተዋዋይ ወገኖች የተደረጉትን ሚስጢራዊ ሰነዶችን ይፋ ያለማድረግ ስምምነቶችን ሊያሻሽሉ አይችሉም፡፡

29.10 ይህ አንቀፅ 29 የግል መረጃን የያዙ ሚስጥራዊ መረጃዎችን በተመለከተ በጊዜ ሳይገደቡ ተግባራዊ ሆነው ይቆያሉ፡፡ ከላይ እንደተገለፀው ካልሆነ ወይም በውሉ በግልፅ ካለተቀመጠ በስተቀር አንቀፅ 29 ውሉ ከተቋረጠ ወይም ውሉ ካበቃ በኋላ ለ3 አመታት ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

29.11 አቅራቢው በዚህ አንቀጽ 29 የተመለከቱትን ሁኔታዎች ሳይፈፀም ሲቀር የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወዲያውኑ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን የማቋረጥ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

30. ልዩ ልዩ

30.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በውሉ መሠረት የሚያስፈልገውን ወይም የተፈቀደለትን ማንኛውም ውሳኔ፣ ተግባር ወይም ጉዳይ በአጠቃላይ ይሁን በዝርዝር ማንኛውም ውሳኔ ወይም ተግባር ወይም ጉዳይ እንዲያከናውን በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተፈቀደለት ማንኛውም ሰው ሊፈፅመው ይችላል፡፡ ይህም የሚሆነው በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአማካሪው የተወከለውን ግለሰብ ሥም ሲያሳውቀው ነው፡፡

30.2 ከግዥ ፈፃሚ መ/ቤት በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት አማካሪው በየጊዜው ተጨማሪ ሰነዶችን ማዘጋጀት ወይም ሌሎች ማናቸውም ውሉን ለማስፈረም የሚያበዙ ተግባራት ወይም ጉዳዮችን ማከናወን ይችላል፡፡

30.3 በማንኛውም የስልጣን ክልል ተቀባይነት ወይም ተፈፃሚነት የሌለው ማንኛውም በዚህ ውል ውስጥ የተካተተ አንቀፅ ውድቅ ይደረጋል፡፡ ይህም የሚሆነው በዚህ ውል የሰፈሩትን ሌሎች አንቀፆችን ተቀባይነት ወይም ተፈፃሚነት የማይከለክልና በዚህ የስልጣን ክልል ተቀባይነት ወይም ተፈፃሚነት የሌላቸውን አንቀፆች በሌላ የስልጣን ክልል ተቀባይነት ወይም ተፈፃሚነት እንዳይኖራቸው የማይከለክል እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው፡፡

30.4 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ና አማካሪው በዚህ ውል የተጠቀሱትን ማናቸውም አንቀፆች ወይም ስምምነቶች ጥብቅ በሆነ መልኩ አለመፈፀም ወይም ውሉን ባለመፈፀማቸው ምክንያት ተከትለው የሚመጡ መብቶች አለመጠቀም ወይም ማስተካከያዎችን አለማድረግ እነዚህን አንቀፆችና ስምምነቶች አላማክበር ወይም አለመጣስ ተደርጎ ያለመቆጠርን አያመላክትም፡፡

30.5 ውሉን ለማዘጋጀት፣ ለመስራትና ለአፈፃፀም የሚውሉ ማናቸውም የህግና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎች በእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን ይሸፈናሉ፡፡

30.6 አማካሪው በማንኛውም ፍርድ ቤት ወይም የአስተዳደር መ/ቤት ውሳኔ ያላገኙ ወይም ገዳት ሊያደርሱ የሚችሉ በሂደት ላይ ያሉ የአማካሪውን የፋይናንስ አቅም ወይም እቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ ሊያውኩ የሚችሉ ሁኔታዎች ወይም ይህ ውል እንዳይፈፀም የሚከለክሉ ከሌላ ወገን ጋር የተደረጉ ሌሎች የኮንትራት ውሎች አለመኖራቸውን ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ዋስትና መስጠትና ይህንንም ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም አማካሪው ይህን ውል በመፈረሙ ሊከተሉ የሚችሉ አደጋዎችና ስጋቶች በውሉ መሠረት የገባቸውን ግዴታዎች ለመፈፀም የሚያስችሉትን ሁሉም መረጃዎች በሚያረካ መልኩ መሰብሰቡን እና በዚህ መሠረት ሊፈፅም የተስማማ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

30.7 በዚህ ውል የተሰጡ መብቶችና መፍትሄዎች አንዱ ባንዱ ላይ የሚጨመሩ (Cumulative) እና በሌላ ውል ወይም ሰነድ ውስጥ ከተሰጡ መብቶችና መፍትሄዎች ጋር የማይጋጩ ናቸው፡፡ በዚህ አንቀፅ መሠረት “መብት” ማለት ማንኛውም ስልጣን፣ ጥቅም መፍትሄ ወይም የንብረት ባለቤትነትና የዋስትና ባለመብትነትን ያጠቃልላል፡፡

ሐ. የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግዴታዎች

31. የድጋፍና የነፃ መብት ድንጋጌ

31.1 በውል ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚመለከተውን የመንግሥት መ/ቤት በመጠየቅ በታቻለ አቅም የሚከተሉት መፈፀማቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

(ሀ) አማካሪው፣ ንዑስ አማካሪዎቹ እና ሠራተኞች የማማከር አገልግሎትን እንዲሰጡ የሚያስፈልጓቸውን የሥራ ፈቃዶችና እና ሌሎች ሰነዶች ማቅረብ፡፡

(ለ) ሠራተኞች አስፈላጊም ሲሆን በስሩ ለሚተዳደሩ ቤተሰቦች በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለመቆየት የሚያስፈልጋቸውን የመግቢያና የመውጫ ግዢ፣ የመኖሪያ ፈቃድ፣ የሠራተኞች ልውውጥ ፈቃድ፣ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች እንዲያገኙ በወቅቱ ማቀላጠፍ

(ሐ) ለማማከር አገልግሎት፣ ለሠራተኞቹና ለቤተሰብ የግል መጠቀሚያ የሚገቡት ዕቃዎች ከግምሩክ የማስለቀቅ ሥራዎችን ማቀላጠፍ

(መ) ለማማከር አገልግሎቱ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ሁሉንም መመሪያዎች ለመንግሥት ሥራ ሀላፊዎች፣ ኤጀንቶች እና ተወካዮች መስጠት

(ሠ) አማካሪው፣ ሰራተኞች ወይም በአማካሪው የተቀጠሩ ንዑስ አማካሪዎች በሙያቸው ለመስራት ወይም ራሳቸውን በግለሰብም ይሁን በኩባንያ ደረጃ ለማደራጀት ከሚጠየቀው ምዝገባ ወይም ፈቃድ ነፃ ማድረግ

(ረ) አማካሪዎች ንዑስ አማካሪዎች ወይም ሁለቱም የቀጠሯቸው ሰራተኞች የክልሉ እና/ወይም ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህግ በሚፈቅደው መሠረት ለማማከር ወይም ለቤተሰቦቻቸው አገልግሎት የሚውል በቂ የውጭ ምንዛሪ እንዲያስገቡ እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ ሰርተው ያገኙትን ገንዘብም እንዲያወጡ መፍቀድ

(ሰ) በልዩ የውል ሁኔታዎች በተጠቀሰው መሰረት ለአማካሪው፣ ለንዑስ አማካሪዎች ወይም ለሠራተኞቹ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉም ድጋፍ ማድረግ

31.2 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለውሉ አፈፃፀም የሚረዱ በዕጁ የሚገኙ ማናቸውም መረጃዎችና ሰነዶች ለአማካሪው ማቅረብ አለበት፡፡ እነዚህ ሰነዶችም ውሉ ሲጠናቀቅ ለግዢ ፈፃሚው መ/ቤት መመለስ አለባቸው፡፡

31.3 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ቀልጣፋና ብቃት ላለው የማማከር አገልግሎት አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ ሁሉንም መመሪያዎች ለሠራተኞቹ ለኤጀንቶቹ እና ለተወካዮቹ መስጠት አለበት፡፡

31.4 ለማማከር አገልግሎት አፈፃፀም አስፈላጊ ሲሆን ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሥራ ቦታውን አማካሪው እንዲጠቀም መፍቀድ ይኖርበታል፡፡ በውሉ መሠረት የማማከር አገልግሎት ለሚሰጥበት አካባቢም ለአማካሪው የዋስትና ሰነዶች ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

32. የሚያስፈልገውን የሥራ ቦታ አቅርቦት

32.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አማካሪው የማማከር አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልገውን የሥራ ቦታ በሙሉ ከክፍያ ነፃና ካለምንም ገደብ ማቅረብ አለበት፡፡ በአማካሪው ወይም በንዑስ አማካሪዎች ወይም በሠራተኞቻቸው ስህተት ወይም ቸልተኝነት የተፈጠረ ካለሆነ በስተቀር በዚህ መሬት ወይም በውስጡ በሚገኙ ንብረቶች ለሚፈጠረው ጉዳት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ኃላፊነቱን ይወስዳል፡፡

33. አገልግሎቶችና መገልገያ ዕቃዎች (facilities)

33.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአማካሪውና ለቅጥር ሰራተኞች የማማከር አገልግሎት ከመስጠት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን የመገልገያ ዕቃዎችን ከክፍያ ነፃና በአባሪ "ሠ" (Appendix E) በተጠቀሰው ጊዜና ሁኔታ ማቅረብ አለበት፡፡

33.2 እነዚህ አገልግሎቶችና የመገልገያ ዕቃዎች በአባሪ "ሠ" በተገለፀው ሁኔታ ካልቀረቡ ተዋዋይ ወገኖች የሚከተሉትን ለማድረግ ይስማማሉ፤

i. አማካሪው የማማከር አገልግሎቱን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ጊዜ መስጠት
ii. አማካሪው አገልግሎቶቹንና መገልገያ ዕቃዎችን እንዲገዛ ማድረግ
iii. በዚህ ምክንያት የሚፈጠሩ ተጨማሪ ክፍያዎችን ከታች በተጠቀሰው የአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 38.3 መሠረት መፈፀም

34. ክፍያ

34.1 በዚህ ውል በአማካሪው በተከናወነው አገልግሎት መሠረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትበአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ምዕራፍ "መ" በተጠቀሰው ሁኔታ ክፍያውን ይፈፅምለታል፡፡

35. አቻ ሠራተኛ (የሰው ኃይል)

35.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትበአባሪ "ሠ" ከተጠቀሰው አማካሪው በሚያገኘው ምክር መሠረት አቻ ባለሙያና ድጋፍ ሰጪ የሰው ኃይል ሊመደብለት ይገባል፡፡

35.2 በአባሪ ‹ሠ› በተጠቀሰው ሁኔታ መሰረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአማካሪው አቻ የሰው ኃይል ካልመደበ ሁለቱም የሚከተሉትን ለማድረግ ይሰማማሉ፡፡

i. በዚህ ምክንያት የሚጎዳውን የሥራ ክፍል እንዴት መስራት እንደሚቻ
ii. በዚህ ምክንያት የሚፈጠሩ ተጨማሪ ክፍያዎችን በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 38.3 መሠረት መፈፀም

35.3 ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አገናኝ መኮንን (liason personnel) በስተቀር ሌሎች አቻ ባለሙያና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በአማካሪው አመራር ሥር ይሠራሉ፡፡ በዚህ መልክ የተመደበ ማንኛውም ሠራተኛ በተገቢው ሁኔታ ስራውን ማከናወን ካልቻለ አማካሪው ግዥ ፈፃሚን መ/ቤት ሌላ ሰራተኛ እንዲቀየረለት መጠየቅ ይችላል፡፡ ግዥ ፈፃሚውም መ/ቤት በቂ ምክንያት ከሌለው በስተቀር ጥያቄውን መቀበል አለበት፡፡

መ. ለአማካሪው የሚፈፀሙ ክፍያዎች

36. የውል ዋጋ የክፍያ ሁኔታ እና የገንዘብ አይነት

36.1 የውሉ ዋጋ በስምምነት የሚገለፀው በሚከተሉት ሁኔታዎች በመጠን ተለይቶ ነው፡፡
ሀ. ለጥቅል ዋጋ ውል የሚከፈለው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ወይም
ለ. ጊዜን መሰረት ለሚያደርግ ውል ግምታዊ የገንዘብ መጠን
ሐ. በልዩ ሁኔታ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም እየታየ ተመጣጣኝ ክፍያ መፈጸም
መ. የፕሮጀክት አፈጻጸምና የፕሮጀክት ጊዜን ታሳቢ ያደረገ ክፍያ መፈጸም

37. የውል አወሳሰድና እና የገንዘብ አይነት በተመለከተ ፡-

37.1 የውሉ ዋጋ በስምምነት የሚገለፀው በሚከተሉት ሁኔታዎች እና በመጠን ተለይቶ መሆን ይኖርበታል፡፡
ሀ. ለጥቅል ዋጋ ውል የሚከፈለው አጠቃላይ የውል የገንዘብ መጠን ወይም
ለ. በጊዜ (Time Base) እና ጥቅል ዋጋ (Lump Sum) በጥምረት (Mixed approach) ይሆናል፡፡

37.2 ለአማካሪው የሚፈፀሙ ሁሉም ክፍያዎች በልዩ የውል ሁኔታዎች በተጠቀሰው የገንዘብ አይነት (ምንዛሪ) ይሆናል፡፡

37.3 ግዥ ፈፃሚው አካል አማካሪው በውሉ መሠረት ያከናወናቸውን አገልግሎቶች በመረጃ በማረጋገጥ ክፍያዎችን በየወቅቱ መፈፀም አለበት፡፡

የአማካሪ ክፍያ ለመፈጸም በስራ ላይ የሚዉሉበት አግባብ፡-

38. በጥቅል ዋጋ ውል (Lump Sum) መሰረት የሚፈፀሙ ክፍያዎችን በተመለከተ

38.1 ለአማካሪው የሚከፈለው ክፍያ በውል በተጠቀሰው መሰረት የሚፈፀም ሆኖ የስራ አፈፃፀም ደረጃን መሰረት ተደርጎ ክፍያው በጥቅል የውል ዋጋው መሰረት ይፈፀማል፡፡

38.2 በጥቅል ውል (Lump Sum) የሚወሰዱ ክፍያዎችን ለመወሰን እንዲረዳ በጥቅል የውል ዋጋው የሚከናወኑ ተግባራትን በየምዕራፉ በገንዘብ ፤ በጊዜ እና በመቶኛ (ፐርሰንት) በመለየት ተከፋፍሎ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

የክፍያ አፈጻጸምን በተመለከተ

38.3 ለግንባታ የንድፍ ስራዎች ሙሉ በመሉ በጥቅል የዋጋ ውል (Lump Sum) መሰረት በማድረግ ክፍያው የሚፈፀም ሲሆን ለክፍያ አፈፃፀም እንዲያመች የሚከናወኑ ተግባራት በስራ ምዕራፍ ፤ በገንዘብ ፤ በጊዜ እና በስራ መጠኑ በፐርሰንት ተለይተው የውሉ አካል መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

38.4 የአፈር ምርመራ አማካሪዎች የሚሳተፉበት የምክር አገልግሎት ግዥ ሙሉ በሙሉ በጥቅል የዋጋ ውል (Lump Sum) የምርመራ ስራውን መሰረት በማድረግ ክፍያው የሚፈፀም ይሆናል፡፡

39. የጥቅል ዋጋ (Lump Sum) እና ጊዜን መሰረት (Time Base) ጥምረት (Mixed approach) በተመለከተ

39.1 የህንፃ አማካሪ ፣የአርክቲክቶች አማካሪ፣ የሃይዌይና የድልድይ አማካሪ ፣የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት አማካሪ የግንባታ የምህንድስና ግምት ዋጋቸው ከዚህ በተቻ በተመለከተው ሰንጠረዥ መሰረት የሆኑት የክፍያ አፈፃፀማቸው በጥምረት (Mixed approach) ሆኖ የግንባታ የአፈፃፀም ደረጀውን (Performance based) መሰረት በማድረግ የውል ክፍያ አፈፃፀሙን ተከትሎ የሚከናወን ይሆናል፡፡

ተ.ቁ	የምህንድስና የግንባታ ግምት ዋጋ በብር(Engineering Estimation)	የስሌት ድርሻ በመቶኛ(በፐርሰንት)	
		በጥቅል ዋጋ (Lump Sum)	ጊዜን መሰረት በማድረግ (Time Base)
1	ከ 10 ሚሊዮን በታች	80	20
1	ከ 10 ሚሊዮን በላይ - 100 ሚሊዮን	50	50
2	ከ 100 ሚሊዮን በላይ - 500 ሚሊዮን	40	60
3	ከ 500 ሚሊዮን በላይ - 1 ቢሊዮን	30	70
4	ከ1 ቢሊዮን በላይ	20	80

39.2 ከተጠቀሱት ወጪዎች በላይ ያልተጠበቀ ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ተጨማሪ ክፍያዎች በአገር ውስጥ እና/ወይም በውጪ ምንዛሪ እንዲከፈል ከተስማሙ በተከፈለው ተጨማሪ ክፍያ መጠን መሰረት የምክር አገልግሎቱንም በመጨመር ለአማካሪው ይከፈለዋል፡፡

39.3 በሥራ ወቅት የስራ ተሳትፎ ለሌላቸዉ ገና ላልተመደቡ ወደፊት ለሚመደቡ ሠራተኞች የሚከፈል ክፍያ ታሳቢ ያደረገና ለክለሳ ክፍት መሆን አለበት፡፡ ይህም ተፈጻሚ የሚሆነው መከፈል ያለበት ደመወዝና አበል ከታወቀ በኋላ በግዥ ፈፃሚው አካል የፅሑፍ ማረጋገጫ ሲሰጥበት የሚፈፀም ይሆናል ፡፡

40. የክፍያ ጊዜ ሰሌዳና ቅድሚያ ክፍያ

40.1 ሁሉም ክፍያዎች በልዩ የውል ሁኔታዎች በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ይፈፀማሉ፡፡

40.2 በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ ሲጠየቅ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአማካሪው በሚያቀርበው ጥያቄና በውሉ መሠረት በተረጋጋጠ ቼክ ወይም በሁኔታ ያልተገደበ የባንክ ዋስትና መልክ የቅድሚያ ክፍያ ይሰጠዋል፡፡ ነገር ግን አማካሪው በጠየቀው

የቅድሚያ ክፍያ መጠን አስቀድሞ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና ማቅረብ አለበት።

i. ይህ ዋስትና፤ ቅድሚያ ክፍያው ተጠናቆ እስከሚከፈል የፀና ይሆናል፡፡

ii. በውሉ በተገለፀው መልክ ወይም ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በፅሁፍ ባረጋገጠው መልክ ይሆናል

የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ቅድሚያ ክፍያውን የሚጀምረው በልዩ የውል ሁኔታዎች በተገለፁት አገልግሎት የሚሰጥባቸው ወራት ዝርዝር መሠረት ተከፋፍሎ ሲሆን ቅድሚያ ክፍያው ተጠናቆ እስኪከፈል ድረስ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

40.3 አማካሪው የቅድሚያ ክፍያ ጥያቄ ካቀረበ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚፈፅመው ክፍያ ከጠቅላላው የውል ዋጋ ከ 30% ያልበለጠውን ነው፡፡

40.4 የቅድሚያ ክፍያ ዋስትናው ዋጋ ሲያጠና አማካሪው ማሳደስ ሲያቅተው ግዥ ፈፃማ መ/ቤት ለፈፀመው የቅድሚያ ክፍያ እኩል መጠን ያለው ገንዘብ ወደፊት ለአማካሪው ከሚከፍለው ሂሳብ ተቀናሽ ያደርጋል፡፡

40.5 በሆነ ምክንያት ውሉ ከተቋረጠ ለአማካሪው የተከፈለውን ቅድሚያ ክፍያ ለማካካስ ሲባል የቅድሚያ ክፍያ ዋስትናው ይወረሳል፡፡

41. የደረሰኝ አቀራረብና የአከፋፈል ሁኔታ

41.1 በዚህ ውል የገባውን ግዴታ በአግባቡ መፈፀሙን ግምት ውስጥ በማስገባት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አማካረውን በዚህ አንቀፅ መሠረት ይከፈለዋል፡፡

41.2 በልዩ የውል ሁኔታዎች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የአንድ ወቅት አገልግሎቶች ከተጠናቀቁ በኃላ አማካሪው መከፈል ያለበትን ክፍያ የሚገልፅ ዝርዝር ዋጋ የያዙ ደረሰኞች እና ሻውቸርና ሌሎች ደጋፊ የሰነዶች ቅጂዎችን አብሮ በማያያዝ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማቅረብ አለበት፤

41.3 የሚቀርቡት ደረሰኞች በውጭ ምንዛሪ እና በሀገር ውስጥ ምንዛሪ የሚከፈለውን ለይቶ ማሳየት አለበት።

41.4 የአማካሪው ደረሰኞች በትክክል ቀረቡ የሚባለው፤

(ሀ) ደረሰኙ በውሉ ውስጥ ደረሰኝ እንዲቀበል ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለጠቀሰው የሥራ ኃላፊ አድራሻ ሲላክና የውሉን ቁጥር ሲጠቀስ

(ለ) ደረሰኙ የተሰጠበት ቀንና የደረሰኝ ቁጥር ሲኖረው

(ሐ) በደረሰኙ የተጠቀሰው ገንዘብ መከፈል ያለበት ሂሳብ ሲሆን

(መ) በደረሰኙ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በውሉ መሠረት የተሰላ ሲሆን

(ሠ) ደረሰኙ የተዘጋጀው ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት የትኛውን የማማከር አገልግሎት እንደሚሸፍን (ዝርዝር ብዛት እና መላኪያ) እና የእያንዳንዱ ዋጋ ወይም አገልግሎቱን በተመለከተ መከፈል ያለበትን ሂሳብ ማረጋገጥ የሚያስችለው ሲሆን

(ረ) ደረሰኙ ክፍያ የሚልክለትን አማካሪ ስምና አድራሻ የያዘ ሲሆን

(ሰ) ደረሰኙ የተበላሸ በሚሆንበት ጊዜ እንዲያውቀው የሚደረግ ግለሰብ ስም የሥራ ኃላፊነት እና የሥልክ ቁጥር የያዘ ሲሆን

(ሸ) ደረሰኙ የአማካሪው የባንክ ሂሳብ ቁጥር መረጃ የያዘ ሲሆን

(ቀ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደረሰኙ ከሽያጭ ታክስ ክፍያ ነፃ መሆኑን

ከላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች በወቅቱ ካልቀረቡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መረጃዎች እስኪቀርቡ ድረስ ክፍያውን ማዘግየት ይችላል፡፡

41.5 አማካሪው በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 41.4 መሠረትና እና በልዩ የውል ሁኔታዎች በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ደረሰኞችና ደጋፊ ሰነዶችን ሲያቀርብ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ክፍያውን መፈፀም ይኖርበታል። አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ደጋፊ ሰነዶች ያልቀረቡለት ደረሰኝ ብቻ ክፍያው ይቆያል፡፡

41.6 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በስህተት፣ በልዩነት፣ በግድፈት ወይም በሌላ ምክንያት ተቀባይነት የማያገኙ ክፍያዎችን ለአማካሪው ያሳውቀዋል፡፡ ሁለቱም ወገኖች የተፈጠሩ ስህተቶች እንዲታረሙና የተስተካከለው የክፍያ ጥያቄ እንዲፈፀም መስማማት ይኖርባቸዋል፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውዝግብ ያልተፈጠረባቸውን ክፍያዎች ከሚገባው ጊዜ በላይ ማቆየት የለበትም፡፡ በተከፈለው ክፍያና አማካሪው ባወጣቸው ወጪዎች መካከል ልዩነት ከተፈጠረ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተከታይ ለአማካሪው መከፈል ካለባቸው ክያዎች ተቀናሽ ያደርጋል፡፡

41.7 አማካሪው የሚያስረክባቸው ውጤቶች በሚኖሩበት ጊዜ በቢጋሩ መሠረት እነዚህን እስከሚረከብ ድረስ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የውል ዋጋ ክፍያውን ማቆየት ይችላል፡፡

41.8 በዚህ ውል መሠረት የመጨረሻ ክፍያ የሚፈፀመው የመጨረሻ ሪፖርትና ደረሰኝ በዚሁ መልክ በአማካሪው ሲቀርብና ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ም አጥጋቢ መሆኑ ሲያረጋግጥ ነው፡፡ የተሰጠው የማማከር አገልግሎቱ ተጠናቋል እንዲሁም በመጨረሻ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተቀባይነት አግኝቷል የሚባለው እንደየ ማማከር አገልግሎቱ ሁኔታ በልዩ የውል ሁኔታው ላይ የሚገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ለግንባታ ሥራዎች የማማከር አገልግሎት ግን ሪፖርቱና ደረሰኙ በቀረቡ በስድሳ (60) የሥራ ቀናት ውስጥ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተጠቀሱት ስድሳ ቀናት ውስጥ ለአማካሪው በአገልግሎቱ በሚቀርቡት ውጤቶችና ደረሰኞች ያሉትን ጉድለቶች በዝርዝር በፅሁፍ ካላሳወቀው በስተቀር ነው፡፡ በዚህ ጊዜ አማካሪው ተገቢውን ማስተካከያ ሲያቀርብ ቀጣይ ሂደቶች በተጠቀሰው መንገድ ይቀጥላሉ፡፡

41.9 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በዚህ ውል መሰረት መከፈል ካለባቸው ክፍያዎች በላይ ክፍያ ከፈፀመ አማካሪው ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማስታወቂያ ከደረሰው ከ30 ቀናት በኃላ ልዩነቱን ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡ እንዲህ አይነቱ የተመላሽ ጥያቄ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የመጨረሻ ሪፖርትና ደረሰኝ በደረሰው በአስራ ሁለት (12) የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

41.10 በዚህ ውል መሠረት የሚፈፀሙ ሁሉም ክፍያዎች በልዩ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 36.2 በተጠቀሰው የገንዘብ ዓይነት (ምንዛሪ) ወደ አማካሪው የባንክ ሂሳብ ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

41.11 የውል ዋጋ ወይም ተመላሽ (ተተኪ) ክፍያዎችን በተመለከተ በውሉ ከተጠቀሱት ዝርዝሮች ዋጋ የበለጠ ከሆነ ላልታሰቡ ወጪዎች በአገር ውስጥና በውጭ ምንዛሪ

ከተያዘው ገንዘብ ሊከፈሉ ይችላሉ። ነገር ግን ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አስቀድሞ ሊያፀድቀው ይገባል፡፡

41.12 ከላይ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 41.8 ውስጥ ከተጠቀሰው በስተቀር የክፍያዎች መፈፀም የተሰጡ አገልግሎቶችን መቀበል ወይም አማካሪው ከገባቸው ግዴታዎች ነፃ መሆኑን አያመለክትም።

42. የዋጋ ማስተካከያ

42.1 የውል ዋጋዎች አማካሪው በውሉ መሠረት ስራውን እስኪያጠናቅቅ ድረስ አንድ አይነት ናቸው፣ ምንም አይነት ማስተካከያም አይደረግባቸውም፡፡ ነገር ግን 24 ወራት እና ከዚህ በላይ ለሚቆዩ የማማከር አገልግሎት ግዥዎች፣ ከ12ኛው ወር ጀምሮ የዋጋ ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

42.2 በምክር አገልግሎት ግዥ የውል አፈጻጸም ወቅት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል መፈጸሚያ ጊዜው በመራዘሙ ለአማካሪው የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን መ/ቤቱ ሲያምንበት የዋጋ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፡፡

42.3 ለአማካሪዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ከሃያ ከመቶ (20%) ሊበልጥ አይችልም፡፡ ሆኖም መ/ቤቱ ለአማካሪዎች የሚያደርገውን የዋጋ ማስተካከያ በልዩ የውል ሁኔታዎች ላይ በግልጽ ማመላከት አለበት፡፡

42.4 የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ሁኔታዎች፣ የዋጋ ማስተካከያ ማሳወቂያ የመገናኛ ዘዴዎች፣ የማስረጃዎች አይነት እና መቅረብ ያለባቸው ደጋፊ ሰነዶች የቅጂዎች ቁጥር እና የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄዎች በልዩ የውል ሁኔታዎች ተገልፀዋል፡፡

42.5 በአማካሪው የተሰጠ የዋጋ ቅናሽ በውሉ ሂደት በማንኛውም ጊዜ ውስጥ ሊጨምር ይችላል፡፡ በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ሌላ ቀን እንዲሆን ካልተወሰነ በስተቀር ተጨማሪው የዋጋ ቅናሽ ተግባራዊ የሚሆነው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የዋጋ ቅናሽ ማስታወቂያው ከአማካሪው ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

42.6 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በፅሁፍ ስምምነቱን ካልገለፀ በስተቀር አማካሪው በዚህ ውል የሰጠውን የዋጋ ቅናሽ ሊቀንስ አይችልም፡፡

ሠ. የአማካሪው ግዴታዎች

43. የአማካሪው ኃላፊነቶች

43.1 አማካሪው የማማከር አገልግሎቱንና የገባቸውን ግዴታዎች በተገቢ ጥንቃቄ፣ በብቃት እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ማከናወን አለበት፡፡ ይህም ተቀባይነት ባላቸው ሙያዊ

ደረጃዎችና አሠራሮች መሠረት፣ ተገቢ የሆኑ የማኔጅመንት አሰራሮች በመከተል አግባብነት ያለው ቴክኖሎጂ እና ደህንነታቸውን የጠበቁ ብቃት ያላቸው መሣሪያዎች፣ ማሽነሪዎች፣ ዕቃዎችና ዘዴዎች በመጠቀም መሆን ይኖርበታል፡፡ አማካሪው ከዚህ ውል ጋር ወይም ከአገልግሎቶቹ ጋር በተያያዘ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ታማኝ አማካሪና በማንኛውም ወቅት ከንዑስ አማካሪዎች ወይም ሶስተኛ ወገን ጋር በሚያደርጋቸው ድርድሮች የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ሕጋዊ ጥቅም መደገፍና መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

43.2 አማካሪው ተፈፃሚነት ያላቸውን ሁሉም ህጎችና ደንቦችን ማክበር አለበት፡፡ አማካሪው በራሱ፣ በንዑስ አማካሪዎቹ ወይም በሠራተኞቻቸው የሕግ ጥሰት ምክንያት ከሚመጡ ክሶች ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት መጠበቅ አለበት፡፡

43.3 ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እርምጃዎች ከመውሰዱ በፊት አማካሪው አስቀድሞ የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት የፅሁፍ ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፡፡

(ሀ) የማማከር አገልግሎቱን ከፊል ስራ ለማከናወን ከንዑስ አማካሪዎች ጋር ሲዋዋል ንዑስ አማካሪውና ሠራተኞቹ ለሚያከናውኑት የማማከር አገልግሎት በአባሪ ‹ሐ› መሠረት ሙሉ በሙሉ ኃላፊነቱን ይወስዳል፡፡

(ለ) በልዩ የውል ሁኔታዎች የተዘረዘሩት ማናቸውም ተግባራት ያከናውናል፡፡

43.4 አማካሪው በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 31.3 መሠረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አስፈላጊ ሠነዶችን ማዘጋጀት እንዲችል የሰው ኃይል ዳታ ወይም መረጃ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መስጠት አለበት፡፡

43.5 አማካሪው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሥራ ውል መሪ የሚሠጡትን ስተዳደራዊ ትዕዛዞችን ማክበር ይኖርበታል፡፡ እነዚህ ትዕዛዞች ከስራ መሪው ስልጣን በላይ ወይም ከውሉ ወሰን በላይ ሆኖ ሲያገኘው ስራውን ሳያቋርጥ አማካሪው ትዕዛዙ በደረሰው በ 30 ቀን ውስጥ አስተያየቱን ለሥራ መሪው መግለፅ አለበት፡፡ አንድን ሰነድ ለማሳተም ወይም ይፋ ለማድረግ አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውሳኔ የፀና ይሆናል፡፡

43.6 አማካሪው የሚያዘጋጀው ዲዛይን፣ የሥራ መጠን እና የሥራ ዝርዝር (Design, Bill of quantity and specification) በግንባታ ወቅት በእያንዳንዱ የሥራ መጠን ከተቀመጠው ከ15 በመቶ በላይ ወይም በታች ከሆነ እንዲሁም የማይሰሩ የግንባታ ሥራዎችን ማካተቱ ከተረጋገጠ በመንግስት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሙሉ ኃላፊነት አለበት፡፡

44. ውል የመፈጸም ብቁነት ፣

44.1 አማካሪው እና ንዑስ አማካሪዎች የብቁ ሀገሮች ዜግነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አንድ አማካሪ ወይም ንዑስ አማካሪ የአንድ ብቁ ሀገር ዜግነት አለው የሚባለው ዜግነት ሲኖረው ወይም የዚያ ሀገር ሕግና ደንቦችን አክብሮና ተመዝግቦ እየተንቀሳቀሰ የሚገኝ ሲሆን ነው፡፡

44.2 አማካሪውና ንዑስ አማካሪዎች የብቁ ሀገሮች ዜጋ የሆነ የሰው ኃይልን ማቅረብና ከብቁ ሀገሮች የመጡ ዕቃዎችንም መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

45. የስነ ምግባር ደንቦች

45.1 አማካሪው ለሙያው ሕጎችና የስነ ምግባር ደንቦች በመገዛት እና በራሱ የግል ውሳኔ መሠረት ሁልጊዜ በታማኝነትና ካለአድልዎ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አማካሪ ሆኖ መሰራት አለበት፡፡ በተለይም አማካሪው የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ፈቃድ ሳያገኝ ስለሚሰጣቸው የማማከር አገልግሎቶች መግለጫ ከመስጠትና በውሉ መሠረት ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከገባቸው ግዴታዎች ጋር የሚቃረኑ (የሚፃረሩ) ተግባራትን ከመፈፀም መቆጠብ አለበት፡፡ አስቀድሞ የፅሁፍ ስምምነት ሳያገኝ ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ግዴታ ውስጥ ማስገባት የለበትም አስፈላጊ ሲሆንም ይህን ለሶስተኛ ወገኖች ማሳወቅ አለበት፡፡

45.2 አማካሪው ወይም ከንዑስ አማካሪዎቹ አንዱ ወይም ሠራተኛ ወይም ወኪል ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከገባው ከዚህ ወይም ከሌላ ውል ጋር በተያያዘ የሆነ ተግባር ለመፈፀም በማንኛውም ሰው ጉቦ፣ ስጦታ፣ ወይም ኮሚሽን ለመስጠት ቢሞክር ወይም ቢስማማ ወይም ሰጥቶ ቢገኝ ወይም ኮሚሽን ለመስጠት ቢሞክር ወይም ለመጥቀም ሲል አድልዎ ቢፈፅም በዚህ ውል የተሰጡት የአማካሪው መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል፡

45.3 አማካሪው የሚከፈለው ክፍያ ከዚህ ውል ጋር ተያያዥነት ባለው ሁኔታ የሚያገኘው ገቢ ወይም ጥቅም ብቻ መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ አማካሪውም ይሁን ሠራተኞቹ ምንም አይነት ኮሚሽን፣ ቅናሽ፣ አበል፣ በተዘዋዋሪ መንገድ ሌላ ክፍያ ወይም ከዚህ ውል ጋር የተያያዙ ግዴታዎቻቸውን በመፈፀማቸው ምክንያት የተለየ አስተያየት ሊደረግላቸው አይገባም፡፡

45.4 በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በፅሁፍ ካልተፈቀደለት በሰተቀር አማካሪው ለዚህ ውል ጥቅም የዋለ የባለቤትነት መብት ወይም የፈጠራ ጥበቃ ከተደረገለት ንብረት ወይም አሰራር ምንም አይነት ሮያልቲ ወይም ስጦታ ወይም በተዘዋዋሪም ይሁን በቀጥታ የተለየ ጥቅም ማግኘት የለበትም፡፡

45.5 አማካሪውና ሠራተኞቹ ውሉ እስከሚጠናቀቅበት ቀን ድረስ ሚስጢር መጠበቅ አለባቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፅሁፍ ፈቃድ ካላገኙ በስተቀር አማካሪው፣ ሰራተኞቹ ወይም ያሳተፏቸው አካላት በማንኛውም ጊዜ ለማንኛውም ሰው አገልግሎቱን ለማስፈፀም ሲባል የተሰጣቸውን ወይም የደረሱበትን ሚስጥራዊ መረጃ አሳልፎ መስጠት ወይም ለህዝብ ይፋ ማድረግ የለባቸውም፡፡በተጨማሪም ለዚህ አገልግሎት ሲባል የተሰጣቸውን የጥናት፣ የሙከራ እና በሂደት የተገኘ የምርምር ውጤት መረጃዎችን ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሳያውቀው ጥቅም ላይ ማዋል የለባቸውም፡፡

45.6 የውሉ ክንውን ላልተለመደ የግብይት (ንግድ) ወጪ መዳረግ የለበትም፡፡ እነዚህ ያልተለመዱ ወጪዎች ከተከሰቱ ውሉ ይቋረጣል፡፡ ወጪዎቹ በውል ውስጥ ያልተከታቱ ክፍያዎች ወይም በአግባቡ ካልተቋጨ ውል የሚመነጩ ክፍያዎች ወይም ተገቢና ህጋዊ ለሆኑ አገልግሎቶች ያልተከፈሉ ክፍያዎች ለታክስ እፎይታ የተላኩ ኮሚሽኖች፣ በግልፅ ላልታወቀ መ/ቤት የተከፈሉ ኮሚሽኖች ታዋቂ መስሎ ለሚቀርብ ኩባንያ የተከፈለ ኮሚሽንን ያጠቃልላል፡፡

45.7 ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት አማካሪው ውሉ በምን መልኩ እየተከናወነ እንደሆነ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡ ያልተለመዱ ወጪዎች አሉ ብሎ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጠረጠረ ጊዜ ማንኛውም የሰነድ ማስረጃ ማሰባሰብ ወይም በቦታው ተገኝቶ ድንገተኛ ፍተሻ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

46. የጥቅም ግጭት

46.1 አማካሪው የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ጥቅም ከምንም በላይ መጠበቅ አለበት፡፡ አማካሪው ይህን የሚያደርገው ወደፊት የሚፈጠረውን የሥራ ዕድል ግምት ውስጥ ባለማስገባት እና ከሌላ ወገን ከተሰጡት ኃላፊነቶች ወይም የራሱን ጥቅም ጋር የሚጋጩ ሁኔታዎችን በማስወገድ ነው፡፡

47. የሚጋጩ ተግባራትን ማስወገድ

47.1 አማካሪው ውሉን በተጨባጭ ወይም ከአድልዎ ነፃ በሆነ መንገድ ለማከናወን የሚያውኩ ሁኔታዎች ከገጠሙት ይህን ለመከላከል ወይም ለማቆም ማንኛውም እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ አማካሪው፤ ንዑስ አማካሪዎቹና ሠራተኞቻቸው በሙሉ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በዚህ ውል ከተሰጣቸው ኃላፊነቶች ጋር የሚጋጩ ሙያዊ ወይም የቢዝነስ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መግባት የለባቸውም፡፡ እነዚህ የጥቅም ግጭቶች የሚመነጩት በተለይ በኢኮኖሚያዊ ጥቅም፣ ቤተሰባዊ ወይም ስሜታዊ ግኑኝነት ወይም ሌላ አይነት አግባብነት ያለው ግኑኝነት ወይም የጋራ ፍላጎት ነው፡፡ በውሉ አፈፃፀም ሂደት የሚከሰት ማንኛውም የጥቅም ግጭት ሳይዘገይ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በፅሁፍ እንዲያወቀው መደረግ አለበት፡፡

47.2 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተወሰዱት እርምጃዎች በቂ መሆናቸውን ማረጋገጥና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተጨማሪ እርምጃ እንዲወስድ የመጠየቅ መብት አለው፡፡አማካሪው ሰራተኞቹንና ማኔጅመንቱን የጥቅም ግጭት ሊያስከትል በሚችል ሁኔታ ውስጥ አለመኖራቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡ በአንቀፅ 24 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ አማካሪው ለጥቅም ግጭት የተጋለጠ ሠራተኛን ከግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ማካካሻ ሳይጠይቅና ጊዜ ሳይወስድ መተካት አለበት፡፡

47.3 አማካሪው የራሱን የሰራተኞቹን ገለልተኝነት የሚገፉ ግኑኝነቶች ከማደረግ መታቀብ አለበት፡፡ አማካሪው ይህን ገለተኝነት መጠበቅ ካቃተው በዚህ ምክንያት የሚደርስ የጉዳት ካሣ እደተጠበቀ ሆኖ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ካለምንም ማስጠንቀቂያ ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡

አማካሪው ከኮሚሽን፣ ተቀናሽ ወዘተ ተጠቃሚ አለመሆን

47.4 አማካሪው በምዕራፍ ‹መ› መሠረት የሚያገኘው ክፍያ በዚህ ውል ማግኘት ያለበት ክፍያ ብቻ ሲሆን በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 46.7 መሠረት ከዚህ ውል ጋር በተያያዘና ግዴታውን ለመወጣት በሚያከናውናቸው ተግባራት ለራሱ ጥቅም ኮሚሽን፣ ቅናሽ ወይም ተመሳሳይ ክፍያ ማግኘት የለበትም፡፡ አማካሪው፤ ንዑስ አማካሪዎች

ሰራተኞቻቸውና ኤጀንቶቻቸው ጨምሮ በተመሳሳይ ሁኔታ ተጨማሪ ክፍያ እንዳያገኙ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

47.5 በተጨማሪም የሚሰጠው የማማከር አገልግሎት መ/ቤት ሆኖ አማካሪው ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ዕቃዎች፣ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶችን ለመግዛት የማማከር ኃላፊነት ከተሰጠው የኢ.ፌ.ድ.ሪ አግባብነት ያላቸው የግዥ ደንቦች ማክበርና ይህም የግዥ ፈፃሚ አካሉን ጥቅም በሚጠብቅ መንገድ መሆን ይገባዋል፡፡ አማካሪው ከዚህ የሚገኘው ቅናሽ ወይም ኮሚሽን የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሂሳብ መሆን አለበት ፡፡

አማካሪዎቹ እና ተባባሪዎቹ ማድረግ የሌለባቸው ተግባራት

47.6 አማካሪው በዚህ ውል ሂደት እና ውሉ ከተጠናቀቀም በኃላ የራሱና የንዑስ አማካሪዎቹ እንዲሁም ማናቸውም የሁለቱም ተባባሪዎች ከአማካሪው የማማከር አገልግሎት የሚመነጭ ፕሮጀክት ዝግጅት ወይም አፈፃፀም ጋር የተያያዙ ዕቃዎችን ሥራዎችንና አገልግሎቶችን (ከማማከር አገልግሎት ውጪ) ለማቅረብ የማይፈቀድለት መሆኑን መስማማት አለበት፡፡

48. የካሣ ክፍያና የተጠያቂነት ገደብ

48.1 አማካሪው የማማከር አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት በሚፈፀም ድርጊት ወይም ግድፈት ምክንያት በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እና ሠራተኞች ሊደርስባቸው ከሚችሉ ማናቸውም ድርጊቶች የይገባኛል ጥያቄዎች፣ ጥፋቶችና ጉዳዮች በራሱ ወጪ ሊጠብቃቸውና ሊከላከልላቸው ይገባል፡፡ ይህም ማንኛውም አይነት የሕግ እና የሶስተኛ ወገን የባለቤትነት፣ የንግድ ምልክት ወይም ሌሎች የእዕምሯዊ ንብረት መብቶች ጥሰትን ያጠቃልላል፡፡

48.2 ከታች የተጠቀሱት ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው አማካሪው የገባቸውን ግዴታዎችን ባለመፈፀሙ ምክንያት በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሠራተኞቹ እና በኤጀንቶቹ ላይ ሊደርሱ ከሚችሉ ማናቸውም ድርጊቶች፣ የይገባኛል ጥያቄዎች ጥፋቶችና ጉዳቶች በራሱ ወጪ ሊጠብቃቸው እና ሊከላከላቸው ይገባል፡፡

(ሀ) ስለነዚህ ድርጊቶች የይገባኛል ጥያቄዎች ጥፋቶችና ጉዳቶች ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ አማካሪው እንዲያውቀው ከተደረገ፡፡

(ለ) የአማካሪው የጉዳት ካሣ ክፍያ ጣሪያ በልዩ የውል ሁኔታዎች እንደተጠቀሰው ከአጠቃላይ ዋጋ መብለጥ የለበትም፡፡ ነገር ግን ይህ ጣሪያ አማካሪው ሆን ብሎ በሚያደርገው የስራ ምግባር ጥፋትና ጉዳት ተግባራዊ አይሆንም፡፡

(ሐ) የአማካሪው የጉዳት ካሣ ክፍያ የገባቸውን ግዴታዎች ባለመወጣቱ ምክንያት በቀጥታ ከሚከሰቱ የይግባኝ ጥያቄዎች ጥፋቶች እና ጉዳቶች ጋር ብቻ የተወሰነ መሆን አለበት ቢሆንም በዚህ ሰበብ የሚከሰቱ ያለተጠበቁ ድንገተኛ ሁኔታዎችን አይጨምርም፡፡

48.3 አማካሪው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚከፍለው የጉዳት ካሣ ክፍያ ጠቅላላ ድምር ከውል ዋጋው መብለጥ የለበትም።

48.4 ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያት ለሚከሰቱ ድርጊቶች የይገባኛል ጥያቄዎች፣ ጥፋቶችና ጉዳዮች አማካሪው ምንም አይነት ተጠያቂነት አይኖረውም።

ሀ. ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአማካሪው የተሰጠ የውሳኔ ሃሳብ ውድቅ ካደረገ፣ የአማካሪውን ተግባር፣ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሃሳብ ከሰረዘ፣ ወይም አማካሪው ያለተስማማበትን ወይም ተአቅቦ ያሳየበትን ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሃሳብ ተግባራዊ እንዲያደረግ ካስገደደ ወይም

ለ. የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ኤጀንቶች፣ ሰራተኞች ወይም ገለልተኛ አማካሪዎች ከአማካሪው የተሰጠውን መመሪያ በትክክል ተግባራዊ ካላደርጉ (ካልፈፀሙ)።

48.5 አማካሪው የማማከር አገልግሎት ስራውን ካጠናቀቀ በኃላ ውሉን በሚገዛው ሕግ በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ በውሉ የገባቸውን ግዴታዎች ካልፈፀመ ከተጠያቂነት ነፃ አይሆንም።

49. በአማካሪው ሊሟሉ የሚገባቸው የመድን ዋስትናዎች

49.1 ይህ ውል በሚፈፀምበት ወቅት ወይም በአገልግሎት ግዥ ማዘጋጀ ሥራ ከመጀመሩ በፊት አማካሪውና ንዑስ አማካሪዎቹ በራሳቸው ወጪ ከውሉ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ለሚደርስ አደጋ በውሉ ልዩ ሁኔታዎች በተጠቀሱት ሁኔታዎች መሠረት የመድን ሽፋን መግዛት ማደስና ተግባረዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል። እነዚህም

(ሀ) ለራሱና ለውሉ ስራ የተቀጠሩ ሰራተኞች የህክምና መድን ዋስትና ለአማካሪው የሚደረጉ የሕክምና ወጪዎች ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተጠያቂ አይሆንም።

(ለ) ከሠራተኞች ሕመምና የሥራ ቦታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የአማካሪው የጉዳት ካሣ ክፍያ።

(ሐ) የውሉን ሥራ በማከናወን ሂደት በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መሣሪያ ላይ የሚደርስ ጉዳት

(መ) በሶስተኛ ወገን ወይም በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ና በሠራተኞቹ በውል አፈፃፀም ሂደት ለሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎች የአማካሪው የፍትሐብሄር (civil) ተጠያቂነት

(ሠ) ከውል አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የሚደርስ ሞት ወይም በጉዳት ምክንያት የሚደርስ ቋሚ የመ/ቤት ጉዳት።

49.2 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ይህን የመድን ዋስትና በመጠየቁ ምክንያት በዚህ ውል አማካኝነት በአማካሪው ላይ ተግባራዊ የሚሆኑ ስጋቶች (አደጋዎች) ዳሰሳ እንዲያደረግ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተገቢ ጥንቃቄ ለመውሰድ እንዲያመቸው ወይም የመድን ሽፋን ለማስፋት አማካሪው ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶች (አደጋዎችን) በራሱ መንገድ ዳሰሳ ማድረግ ይጠበቅበታል።አማካሪው በመጠን፣ በአይነትና በጊዜ በቂ የሆኑ የመድን ሽፋን ባለማቅረብ ምክንያት ከሚመጣ ተጠያቂነትና ሌሎች ግዴታዎች ነፃ አይሆንም።

49.3 የመድን ዋስትና መቅረብ ያለበት በአማካሪው ወጪ ሆኖ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በቀጥታ እንዲከፍል መደረግ የለበትም፡፡

49.4 በዚህ አንቀፅ ተፈላጊ የሆኑ የመድን ፖሊሲዎች በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰራ ፈቃድ በተሰጠው የመድን ድርጅት መፃፍ አለበት፡፡

49.5 የመድን ዋስትና ሽፋን እስከ ውል ማጠናቀቂያ ድረስ መቆየት አለበት፡፡ አማካሪው ወይም የመድን ድርጅቱ ለውጥ ከመደረጉ ወይም የመድን ሽፋኑ ከመሰረዙ ከ30 ቀናት በፊት ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ማሳወቅ አለባቸው፡፡

49.6 ይህ ውል በሚፈፀምበት ወቅት ወይም በአገልግሎት ግዥ ማዘዣ መሠረት ሥራ ከመጀመሩ በፊት አማካሪው ወይም የመድን ድርጅቱ የመድን ሽፋን ፍላጎት መሟላቱን የሚያረጋግጥ የመድን ዋስትና ሰርተፍኬት (COI) ማቅረብ አለባቸው፡፡ የመድን ዋስትና ሰርተፍኬቱ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እንዲያየው እንዲያፀድቀው መቅረብ አለበት፡፡ ውሉ እስኪጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ አማካሪው ወይም የመድን ድርጅቱ እድሳት ወይም የኢንሹራንስ ፖሊሲ ወይም ሽፋን ለውጥ መደረጉን በሚያሳይ ሁኔታ አዲስ ሰርተፍኬት በየጊዜው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

49.7 አማካሪው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትበሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት የመድን ዋስትና ሽፋን የተገዛ እየታደሰና ወቅታዊ ክፍያ መፈፀሙን የሚያሳይ ማስረጃ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

50. ጤና እና ደህንነት

50.1 የማማከር አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት አማካሪው ሠራተኞቹ፤ የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤትፖሊሲዎችና አሠሪዎችን ጨምሮ በዚህ ውል ውስጥ የተቀመጡ ተገቢ የሆኑ የጤንነትና የደህንነት ህጎችና ደንቦች እንዲሁም የመልካም አሰራር ደንቦችን ማክበራቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

50.2 ከውሉ ጋር በተያያዘ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሥራ አካባቢ (ቦታ) ሰራተኞቹ በሚሰሩበት ጊዜ አማካሪው በስራ ቦታ የጤናና የደህንነት ፖሊሲ (Health and Safety policy at work) ምንጊዜም ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

50.3 አማካሪው የጤናና ደህንነት ጉዳይ ከሚመለከተው ባለስልጣን ጋር አገናኝ መኮንን ሆኖ የሚያገለግል አንድ የጤናና ደህንነት ተወካይ መምረጥ አለበት፡፡

50.4 የአማካሪው ሠራተኞች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ና የአማካሪው ራሱ የአደጋ አመዘጋገብ ስርአት መከተል አለባቸው፡፡

50.5 መታወቅ ያለባቸው ሁሉም አደጋዎች የጤናና የደህንነት ኃላፊው እንዲያውቀው መደረግ ይኖርበታል፡፡

50.6 የእሳት ወይም ሌላ አደጋዎችን ለመከላከል የተቀየሱ ሁሉም የመከላከያ ዘዴዎች አጠቃቀም ላይ አማካሪው ሁሉም ሠራተኞች እንዲተባበሩ ማድረግ አለበት እንዲሁም እነዚህን አደጋዎች ሊያባብሱ ወይም አዳዲስ አደጋዎች ሊፈጠሩ የሚችሉ የአማካሪው አሰራሮች ወይም ሌሎች ክስተቶች ካለ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

50.7 የአማካሪው ሰራተኞች የሚከተሉትን ጨምሮ የተከሰቱ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን መለየት የሚያስችላቸው ስልጠና መውሰድ አለባቸው፡፡

(ሀ) በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግቢ ውስጥ በማንኛውም ግለሰብ የሚደርስ የመ/ቤት ጉዳት አደጋ፣

i. በተቻለ መጠንና ራስን ለአደጋ ሳያጋልጡ ክስተቱን መቆጣጠር

ii. እንዲህ አይነቱን የአደጋ ክስተት ለባለስልጣን ሪፖርት ማቅረብ

(ለ) የእሳት አደጋና መከላከያ አሰራሮች፣ በግዥ ፈፃማው መ/ቤት ፖሊሲዎች መሠረት የእሳት አደጋ ትምህርት/ከእሳት አደጋ የማምለጥ ልምምድን (drill) ጨምሮ

(ሐ) ደህንነት

(መ) የአደጋ አያያዝ (management)

(ሠ) ዋና (አስከፊ) አደጋዎች

50.8 አማካሪው የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ መሳሪያዎችን ማቅረብና ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚፈልገው አኳኋን ሠራተኞቹ የመጀመሪያ ዕርዳታ አሰጣጥ መርሆችን ማክበራቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

50.9 አማካሪው በማንኛውም ጊዜ ጥቅም ላይ የዋሉት መሣሪያዎችና አሰራሮች ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የእሳት አደጋ ፖሊሲ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

50.10 አማካሪው ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የእሳት እና የደህንነትና አማካሪዎች ጋር መተባበርና የሚሰጣቸውን ተገቢ መመሪያዎች ማክበር አለበት፡፡

51. የአዕምሯዊና የኢንዱስትሪ ንብረት ባለቤትነት መብቶች

51.1 ለዚህ ውል ስራ አፈፃፀም እንዲረዱ በአማካሪው የተሰበሰቡ ወይም የተዘጋጁ ሁሉም ሪፖርቶችና ዳታዎች ማለትም ካርታዎች፣ ስዕሎች፣ ስዕላዊ፣ መግለጫዎች፣ ዝርዝሮች፣ ንድፎች፣ ስታትስቲክስ፣ ስሌቶች፣ ዳታ፣ ቤዞች፣ ሶፍትዌሮች እና ሌሎች አጋዥ፣ ማህደሮችና ዕቃዎች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ብቸኛ ንብረት ይሆናሉ፡፡ አማካሪው የሥራ ውሉ እንደተቋረጠ ወይም እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ከላይ የተገለፁትን መረጃዎችና ሰነዶች ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማስረከብ አለበት፡፡ አማካሪው የእነዚህ ሰነዶች ሶፍትዌሮችና ዳታዎችና ቅጂዎችን ማስቀረት የለበትም፡፡ ያለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፅሁፍ ፈቃድም ከውሉ ጋር ተያያዥነት ለሌላቸው ሌሎች አገልግሎቶች ሊጠቀምባቸው አይችልም፡፡

51.2 በአማካሪው እና በሶስተኛ ወገኖች መካከል የኮምፒውተር ፕሮግራም ለመስራት የፈቃድ ስምምነት ማድረግ አስፈላጊ ወይም ተገቢ ሆኖ ሲገኝ አማካሪው የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፅሁፍ ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ም ይህን ፕሮግራም(ሞች) በመሰረት የወጣውን ወጪ በራሱ ውሳኔ የማስመለስ መብት አለው፡፡ እነዚህን ሰነዶች ወይም ሶፍትዌሮችን ወደፊት መጠቀም የሚከለክል ሁኔታ ካለ ዝርዝሩ በልዩ የውል ሁኔታዎች ውስጥ ይገለፃል፡፡

51.3 አማካሪው ከማማከር አገልግሎቱ ጋር የተያያዙ ፅሁፎችን ማሳተም ወይም ለሌሎች በሚሰጠው የማማከር አገልግሎት እንደ ማጣቀሻነት ሊጠቀምበት አይችልም፡፡ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ያገኘውን ሚስጥራዊ መረጃም የፅሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ ይፋ ማድረግ አይችልም፡፡

51.4 ለውሉ አፈፃፀም የዋለ የቅጅ መብቶችና የአዕምሯዊ ወይም የኢንዱስትሪ ንብረት መብቶች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤትብቸኛ ንብረቶች ናቸው፡፡ ይህ አዕምሯዊ ወይም የኢንዱስትሪ ንብረት መብት ባለበት አገር ከልሆነ በስተቀር ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የጀአግራፊያዊም ሆነ የሌላ ገደብ ሳይኖርበት የመጠቀም፣ የማሳተም ሌላ አሳልፎ መስጠት ይችላል፡፡

51.5 በውል አፈፃፀም ሂደት በስራ ላይ በመዋላቸው የአንድ ግለሰብ የአዕምሯዊ ንብረት መብት ምክንያት በግዥ ፈፃሚው መ/ቤትለሚደርሱ ማናቸውም ወጪዎች፣ የይግባኝል ጥያቄዎች፣ክሶች አማካሪው ግዥ ፈፃሚው የጉዳት ካሣ ክፍያ እንዳይጠየቅ ጥበቃ ያደርግለታል፡፡

52. ሪፖርት የማቅረብ ግዴታዎች

52.1 አማካሪው በአባሪ “ለ” የተዘረዘሩትን ሪፖርቶች እና ሰነዶች በቢጋሩ መሠረት በሚፈለገው መልክ፣ ቁጥር፣ እና ጊዜ ውስጥ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማስረከብ አለበት፡፡ ከላይ በተጠቀሰው አባሪ በወረቀት መልክ ከቀረቡት ሰነዶች በተጨማሪ በሌሎች የኤሌክትሮኒክ አማራጮች ተቀድቶ መሰጠት አለበት፡፡

53. የሂሳብ አያያዝ፤ ኢንስፔክሽንና ኦዲት

53.1 አማካሪው እና ንዑስ አማካሪዎቹ ዓለም አቀፍ ደረጃ የጠበቁ የሂሳብ አያያዝ መርሆችን በመከተል በዚህ ውል አፈፃፃም በየጊዜው የተደረጉ ክፍያዎችንና ወጪዎችን በዝርዝርና በግልፅ በሚያሳይ መልኩ ትክክለኛ የሂሳብ መዝገቦችን መያዝ አለባቸው፡፡

53.2 የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ሂሳብ ለመመርመር እና ማረጋገጫ ለመስጠት ሲባል ወይም የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሀብቱን እንዴት ኢኮኖሚያዊ አግባብነትና ጥራት ባለው መንገድ እንደተጠቀመበት ለማየት ዋና ኦዲተርና በቢሮው ወይም በኦዲተሮቻቸው አማካኝነት ከውሉ አፈፃፀምና የማማካር አገልግሎት ለመስጠት ከቀረበው የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ ጋር የተያያዙ ሂሳቦችና መዝገቦችን ሊመረምሩ ይችላሉ፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አማካሪው የቃልና የፅሁፍ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል፡፡ አማካሪው ከማንኛውም የፀረ ሙስና ፖሊሲ ወይም ሥልጣን በተሰጠው መ/ቤት በሚደረጉ ምርመራዎች ሁሉ ሙሉ ትብብር ለማድረግ መስማማት ይኖርበታል፡፡

54. የመረጃ (ዳታ) አጠባበቅ

54.1 አማካሪው ማንኛውም አይነት ተፈፃሚ የመረጃ ጥበቃ ሕግን ማክበር አለበት በተለይ አማካሪው የሚከተሉት ለማድረግ ይስማማል።

(ሀ) ተገቢ የሆኑ ቴክኒካዊ ወይም ድርጅታዊ ደህንነት እርምጃዎችን ለመጠበቅ

(ለ) ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚሰጠው መመሪያና በውሉ የተቀመጡትን ግዴታዎች ለመወጣት በሚያስችል መልኩ የግል መረጃዎችን ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ና በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስም ብቻ ማዘጋጀት

54.2 አማካሪው ውሉን በሚያከናውንበት ወቅት ወይም ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ለፈፀሟቸው ሌሎች ስምምነቶች አገልግሎት እንደውል የተሰጠን የግል መረጃ የአማካሪው ሠራተኞች ወይም ተወካዮች ሳይፈቀድላቸው ሕገወጥ በሆነ መንገድ በመጠቀማቸው በማጥፋታቸው እና/ወይም ጉዳት በማድረሳቸው ምክንያት በማንኛው ግለሰብ ወይም ህጋዊ መ/ቤት በደረሰው ጥፋት ወይም የህሊና ጉዳት ምክንያት ለደርሱ የካሳ ክፍያ እና ወጪዎች አማካሪው ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ከተጠያቂነት ነፃ ያደርገዋል ወይም ተገቢውን ጥበቃ ያደርግለታል፡፡

55. ክለሳ (Review)

55.1 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በውሉ መሠረት የቀረቡት የማማከር አገልግሎት ምን ያክል አጥጋቢ (የሚያረካ) መሆኑን ለማየት እና ችግሮች ካሉ እንዴት እንደሚወገዱ ስምምነት ላይ ለመድረስ አማካሪው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚያዘጋጃቸው ተከታታይ ስብሰባዎች ላይ መገኘት አለበት (እያንዳንዱ ስብሰባ "ክለሳ" ነው)፡፡ አማካሪው ለዚህ አስፈላጊ ተግባር የተደረሱ ስምምነቶችን ማደናቀፍ ወይም ማዘግየት የለበትም፡፡ በዚህ የክለሳ ስብሰባ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ና ከአማካሪው ከፍተኛ ኃላፊነትና ልምድ ያላቸው እንዲሁም አግባብነት ያላቸው ሠራተኞች መገኘት አለባቸው፡፡ ሁለቱም ወገኖች ለዚህ ክለሳ የሚሆን አጀንዳ ለማዘጋጀት ስምምነት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

56. የውል ማስከበሪያ ዋስትና

56.1 አማካሪው ውሉን ከፈረመበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ለውሉ አፈፃፀም ዋስትና የሚውል መጠኑ በልዩ የውል ሁኔታዎች የተጠቀሰውን የገንዘብ ዋስትና ያቀርባል፡፡

56.2 የውሉ ማስከበሪያ ዋስትና ገንዘብ አማካሪው የገባውን ግዴታ በአግባቡ ሳይወጣ ሲቀር በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለሚደርሰው ማንኛውም ኪሳራ በካሳ መልክ ይከፈላል፡፡

56.3 የውል ማስከበሪያ ዋስትናው በልዩ የውል ሁኔታዎች በተጠቀሰው የገንዘብ አይነት (ምንዛሪ) ሆኖ ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የተረጋገጠ የክፍያ ማዘዣ፣ በባንክ የተረጋገጠ ሌተር ኦፍ ክሬዲት (letter of credit) ወይም በልዩ የውል ሁኔታዎች በተገለፀው መልክ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Gurantee) መቅረብ አለበት።

56.4 የተያዘው የውል ማስከበሪያ ዋስትና አማካሪው የማማከር አገልግሎት ለመስጠት የገባቸውን ግዴታዎች በልዩ የውል ሁኔታዎች በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር የዋስትና ግዴታዎችን ጨምሮ ካጠናቀቀ ከሀያ ስምንት (28) ቀናት በኋላ መለቀቅና ለአማካሪው መመለስ አለበት፡፡

56.5 ከላይ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች በንዑስ አንቀፅ 56.2. የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ አማካሪው ስምምነቱን አለማክበሩ ቢታወቅ እንኳን የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጥቅም የማይጎዳ ወይም ተጨማሪ ወጪ የማያስከትል ወይም የአማካሪው ጥፋት አለመሆኑ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ሲያረጋግጥ የአፈፃፀም ዋስትናው ለአማካሪው ተመላሽ ይሆናል፡፡

56.6 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትየአፈፃፀም ዋስትና እንዲመለስ የሚያስገድድ የአገልግሎት ግዢ ጋር የተያያዙ በፅጁ ያለ ማናቸውም ሰነዶች ለአማካሪው መመለስ ይጠበቅበታል፡፡ ያከናወነውንም ተግባር በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 56.5 መሠረት ለቢሮ ወይም ሌሎች ሕጋዊ አካላት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ረ. ውል ስለመፈፀም

57. የምክር አገልግሎቶች ተፈፃሚነት ወሰን

57.1 የሚሰጠው የምክር አገልግሎት በክፍል 9 አባሪ "ሀ" በተገለፀው ዝርዝር መሠረት ይሆናል።

57.2 የምክር አገልግሎቱ የሚከናወነው በአባሪ "ሀ" በቀረበው መመሪያ መሠረት በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግቢ (የሥራ ቦታ) ወይም ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በፅሁፍ በተሰማሙበት ቦታ ይሆናል፡፡

58. የሚጠበቁ ውጤቶች - deliverables

58.1 የምክር አገልግሎት አማካሪው የሚረከቡ ሰነዶችን ማቅረብ በሚኖርበት ጊዜ

(ሀ) የሚረከቡት ሰነዶች የሚቀርቡት በውሉ በተገለፀው ቅፅና በቢጋሩ መሠረት ነው፡፡ በቢጋሩ የተገለፀ ቅፅ ከሌለ መረከብ ያለባቸው ሰነዶች የግዥ ፈፃሚው የሥራ ኃላፊ በሚያስታውቀው መሠረት ለሙያው ተገቢ በሆነ ቅፅ ይሆናል፡፡

(ለ) ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚቀርቡት ሰነዶች (በሙሉ ወይም በከፊል) ተገቢ የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ ከሆነ ወይም በቢጋሩ መሠረት ወይም የግዥ ፈፃሚው የሥራ ኃላፊ ባሳወቀው መሠረት ካልቀረቡ ግዥ ፈፃሚው የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት አለው፡፡

(ሐ) ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የማይቀበልበትን ምክንያት ለአማካሪው በፅሁፍ ሳይገልፅ የቀረቡትን ሰነዶቹን (በሙሉ ይሁን በከፊል) ውድቅ አያደርግም፡፡

(መ) ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚረከቡትን ሰነዶች አግባብ ባለው መንገድ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በተመለከተ አለመግባባት ከተፈጠረ ጉዳዩ በአለመግባባት አፈታት ስርዓት ይፈታል፡፡

58.2 ማናቸውም ውድቅ የተደረጉ ሰነዶች ሥልጣን የተሰጠውን ኃላፊ በሚያረካ ሁኔታ በተስተካከሉ ሰነዶች (ግዥ ፈፃሚን መ/ቤት ለተጨማሪ ወጪ ሳይደርጉ) መተካት አለባቸው

59. የምክር አገልግሎት አፈፃፀም

59.1 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 62.1 መሠረት አማካሪው በራሱ ወጪ የውሉን ደረጃዎች በጠበቀ መልኩ የምክር አገልግሎቱን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ሰራተኞች፣ መሣሪያዎች፣ ዕቃዎችና መገልገያዎች ማቅረብ አለበት፡፡

59.2 አማካሪው በቢ.ጋሩ የተጠቀሱትን፤ ቀን፣ የምክር የአገልግሎት አሰጣጥ ይዘትና ዘዴ የሚረከቡት ሰነዶች እና/ወይም ተቀባይነት ያላቸው የአፈፃፀም መለኪያዎች በተወሰኑ ቀናት የሚከናወኑ የሥራ አፈፃፀሞች፣ ዝቅተኛ የአፈፃፀም ደረጃ እንዲሁም የአፈፃፀም መለኪያ ዘዴዎችን በሙሉ ማክበር ይጠበቅበታል፡፡

59.3 በዚህ ውል አማካሪው ከሚኖሩት ግዴታዎች ውስጥ "ጊዜ" የበላይነት ይኖረዋል፡፡

59.4 የምክር አገልግሎቱ በተለያዩ ደረጃዎች እንዲሰጥ በቢ.ጋሩ ከተገለፀ አማካሪው የምክር አገልግሎቱን በቢ.ጋሩ የተቀመጠው የደረጃዎቹ የጊዜ ሰሌዳ በጥብቅ በማክበር ስራውን ማከናወን አለበት፡፡

59.5 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከዚህ ውል በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ና አማካሪው በቅንነትና በትብብር መረጃዎችን እና መመሪያዎችን እየተለዋወጡ ተገቢ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ የምክር አገልግሎት በሚሰጥበት ወቅት አማካሪው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግቢ ተመድበው የምክር አገልግሎት ከሚሰጡ ሌሎች አማካሪዎች ጋር በትብብር መስራት ይኖርበታል፡፡

59.6 በውሉ ስምምነት ላይ ከተጠቀሱት ዝርዝር ሁኔታዎች በተጨማሪ አማካሪው ከሥራተኛ ምደባ፣ የአከፋፈል እና የቅጥር ሁኔታ ወይም የሥራ ሰዓታት ወይም ሌሎች የቴክኖሎጂ ለውጦች በተመለከተ ከፍተኛ ለውጥ ካለ ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ ይህም ማድረግ ያለበት ለውጦቹ ተግባራዊ መሆን ከመጀመራቸው ቢያንስ ከአንድ ወር በፊት ነው።

59.7 አማካሪው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጥያቄ ሲቀርብለት ከምክር አገልግሎቱ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በሚፈለገው መልክና የመገናኛ ዘዴ ወይም እንደሁኔታው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚቀርበው ዝርዝር መሠረት ማቅረብ አለበት፡፡

59.8 በማንኛውም ጊዜ በግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ወይም አባላት ወይም ኃላፊዎች አማካኝነት የአማካሪውን የምክር አገልግሎት አፈፃፀም ሂደት በውሉ መሠረት እንዳይከናወን የሚያደናቅፉ ድርጊቶች ወይም ግድፈቶች በሚፈጠሩበት ጊዜ አማካሪው ይህን ድርጊት ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሥራ ኃላፊ ማሳወቅ አለበት፡፡ ጥርጣሬን ለማስወገድ ሲባል የአማካሪው ይህን አንቀፅ ማክበር (መቀበል) በዚህ ውል መሠረት የገባቸውን ግዴታዎች ከመፈፀም ነፃ አያደርጉትም፡፡

59.9 አማካሪው በዚህ ውል መሠረት የገባቸውን ግዴታዎች እንዲያከብር ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትአማካሪውን የፖሊሲዎች ሕጎች፣አሠራሮችና የጥራት ደረጃዎች ሰነዶች ቅጂዎች (በሰነዶቹ የተደረጉ ለውጦች ካሉ አማካሪውን ማሳወቅ አለበት) መስጠት ይኖርበታል፡፡

59.10 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አማካሪው የምክር አገልግሎቱን ለማቅረብ የሚያደርገው የሰራተኞች ቅጥርን በተመለከተ አግባብነት ያላቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ አሠራሮችና የጥራት ደረጃዎችን እንዲቀረጽና እንዲጠብቅ ይፈለጋል፡፡ ይህም የዲስፕሊንና የቅሬታ አፈታት ስርዓትንም ይጨምራ፡፡ አማካሪው ከላይ የተጠቀሱ ሰነዶች ቅጂዎች (የተደረጉ ለውጦች ካለ ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ማሳወቅ ወይም ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

59.11 አማካሪው በራሱ አማካሪዎች የተፈጠሩ ወይም ሊፈጠሩ የሚችሉ የአማካሪው የምክር አገልግሎት እንዳይሰጥ እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮችን ወዲያውኑ ለግዥ ፈፃማው መ/ቤትማሳወቅ አለበት፡፡

59.12 አማካሪው በማንኛውም ጊዜ የውሉን ደረጃዎች ጠብቆ የምክር አገልግሎቱን የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡

59.13 አማካሪው የምክር አገልግሎት እንዳይከናወን ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በሠራተኞቹ ወይም በሌላ የተነሱ ወይ የታቀዱ የሥራ ማቆም አድማዎች ካሉ ወዲያውኑ ለግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ያሳውቃል፡፡

59.14 አማካሪው የኢንዱስትሪ አመፅ ቢኖርም በውሉ ደረጃዎች መሠረት የምክር አገልግሎቱን መስጠት መቀጠል አለበት፡፡ ለዚህም ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተጨማሪ ክፍያ አይጠይቅም፡፡ አማካሪው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፀደቀ አማራጭ እቅድና ዝግጅት ሊኖረው ይገባል፡፡

60. የአፈፃፀም መለኪያ

60.1 በውሉ ስምምነቶች ከተጠቀሱት ዝርዝር ግዴታዎች በተጨማሪ አማካሪው የውሉን ደረጃ በጠበቀ እና የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት የሥራ ኃላፊ በሚያረካ መልኩ የምክር አገልግሎቱን ማቅረብ አለበት፡፡

60.2 አማካሪው በቢጋሩ በተገለፀው መሠረት እና የግዥ ፈፃሚን መ/ቤት የሥራ ኃላፊ በሚያረካ መንገድ የጥራት ቁጥጥር ስርዓት መቅረፅና በአግባቡ መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

60.3 በውሉ መሰረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ካሉት መብቶች በተጨማሪ ከላይ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 59.2 መሠረት አማካሪው የዘረጋውን የጥራት ቁጥጥር ስርዓት ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ ፍተሻ ማካሄድ ይችላል፡፡

60.4 በውሉ አፈፃፀም ሂደት ምንም ሳያሳውቅ ሥልጣን የተሰጠው ኃላፊ የአማካሪውን የምክር አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ ሊፈትሽና ሊመረምር ይችላል፡፡ ለዚህ ኢንስፔክሽንና ምርመራ የሚያስፈልጉ መገልገያ ቁሳቁሶችን አማካሪው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

60.5 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስህተት ወይም ቸልተኝነት ባልሆነ መንገድ የተሰጠው የምክር አገልግሎት በቢጋሩ ከተገለፀው ውጪ ወይም የውሉን ደረጃ ያልጠበቀ ሆኖ ሲገኝ አማካሪው በራሱ ወጪ የምክር አገልግሎቱን በድጋሚ ማከናወን አለበት፡፡ ይህም

የሚሆነው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በወሰነው ጊዜ ሆኖ አማካሪው አገልግሎቱን ማስተካከል ካልቻለ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አገልግሎቱን ከሶስተኛ ወገን የመግዛት ወይም የተጠቀሰውን አገልግሎት ራሱ የማከናወን መብት አለው፡፡ ይህ ስራ ለማከናወን ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚያወጣው ወጪ ለአማካሪው መክፈል ከሚገባው የበለጠ ከሆነ ልዩነቱን አማካሪው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ይመልስለታል፡፡

60.6 የአማካሪው የምክር አሰጣጥ አገልግሎት በግዥ ፈፃሚው ስህተት ወይም የአማካሪው ኃላፊነት ባልሆነና ባልተጠበቀ ሌላ ምክንያት ከተጠበቀው ጊዜ በላይ ከዘገየ አማካሪው የምክር አገልግሎቱን ማጠናቀቅ የሚያስችለው በቂ ጊዜ ይጨመርለታል (ይራዘምበታል)፡፡

60.7 ለእያንዳንዱ አገልግሎት የአማካሪው የምክር አገልግሎት አሰጣጥ በቢጋሩ የተጠቀሰው የአፈፃፀም መስፈርት ሚሟላቱን ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማረጋገጥ አለበት፡፡ መስፈርቶቹ ካልተገለፁ ግን የአንድ የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ ደረጃን የጠበቀ መሆን አለበት፡፡ በውል ጊዜ ውስጥ ወር በገባ ከመጀመሪያዎቹ 15 ቀናት በፊት እና ውሉ ከተቋረጠ በኋላ በ14 ቀናት ጊዜ ውስጥ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ፤

(ሀ) በየወሩ የሚከናወኑ እያንዳንዱ የምክር አገልግሎትን በተመለከተ ለአማካሪው ማስታወቂያ መስጠት (እያንዳንዱ "የአፈፃፀም ማስታወቂያ" ተብሎ ይጠራል)፡፡ ይህም የሚገልፀው የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት በአማካሪው አፈፃፀም ብቃትና በተሰጠው የምክር አገልግሎት ያልረካ መሆኑን ነው፡፡

(ለ) በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አማካሪው የሚሰጠው የአፈፃፀም ማስታወቂያ በማስታወቂያው በሰፈረው የአማካሪው የአፈፃፀም ጉድለት መጠን ልክ የሚቀንሰውን የውል ዋጋ መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

(ሐ) በቀረበው የአፈፃፀም ማስታወቂያ እና/ወይም በቀረበው የውል ዋጋ ተቀናሽ አማካሪው የማይሰማማ ከሆነ ቅሬታውን ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡ በአምስት (5) የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩ መፍትሄ ካላገኘ ግን ወደ የአለመግባባት አፈታት ስርዓት ይመራል፡፡

(መ) አማካሪው በአፈፃፀም ማስታወቂያ ላይ ያለውን ተቃውሞ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ (ወይም ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በሚስማሙበት የጊዜ ገደብ) ካላቀረበ የአፈፃፀም ማስታወቂያውን እንደተቀበለ ተቆጥሮ ከላይ የቀረበው የውል ዋጋ ተቀናሽ ሀሳብ ወዲያውኑ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

60.8 በዚህ አንቀፅ የተጠቀሱት የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት መብቶች የሚኖሩት ሌሎች መብቶች ወይም መፍትሄዎችን አይፃረሩም፡፡

60.9 ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት አቅርበው በቢጋሩ በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ (ካለ) መሠረት ስራውን እያከናወነ መሆኑን በዝርዝርና ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ባፀደቀው ቅፅ መሰረት ሪፖርት ያቀርባል፡፡ የዚህ ሪፖርት መቅረብና

ተቀባይነት ማግኘት ሌሎች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በዚህ ውል ያሉትን መብቶችና መፍትሄዎችን አያስቀሩም፡፡

60.10 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሁለቱንም ወገኖች አፈፃፀም ለማቀላጠፍ ሲባል በመረጃ ልውውጥና የአፈፃፀም መለኪያ መስፈርቶችን በማውጣት መተባበር ይኖርባቸዋል፡፡ እንደነዚህ አይነት ስምምነቶች በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በፅሁፍ መመዝገብ አለባቸው፡፡

61. ቦታ (location)

61.1 የምክር አገልግሎቱ የሚከናወነው በክፍል 9 አባሪ "ሀ" በተጠቀሰው ቦታ ነው፡፡
61.2 በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በሚደርስ የዋጋ ስምምነት መሠረት ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በውሉ ሂደት በማንኛውም ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥባቸውን ቦታዎች ቁጥር የመጨመር ወይም የመቀነስ መብት አለው፡፡
61.3 የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማንኛውም ሌላ መብት ወይም መፍትሄ እንደተጠበቀ ሆኖ የቦታዎችን ቁጥር መጨመር ወይም መቀነስ በተመለከተ የተቻለውን ያክል ማስታወቂያ ይሰጣል፡፡ ሆኖም የመጨረሻ ትንሹ ጊዜ በዚህ ሁኔታ አልተወሰነም፡፡

62. የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ቦታዎችን (site) ስለመጠቀም

62.1 በውሉ ጊዜ ውስጥ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከምክር አገልግሎት መስጠት ጋር በተያያዘ በቢጋሩ በተቀመጠው መሰረት አማካሪው የተወሰኑ ቦታዎችን እንዲጠቀም መፍቀድ አለበት፡፡

62.2 አማካሪው ቦታዎቹን የምክር አገልግሎት ብቻ ለመስጠት መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ሠራተኞቹም ቦታውን ለዚህ አገልግሎት ብቻ እንደሚጠቀሙበት ማረጋገጥ አለበት፡፡

62.3 አማካሪው ቦታዎቹ ፅዱ፣ ምቹ እና ሙያዊ የሆነ ገፅታ እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርበታል፡፡

62.4 አማካሪው እንዲጠቀምበት የተፈቀደለት ቦታ ለራሱና ለሠራተኞቹ ብቻ ነው፡፡ የአማካሪው ሠራተኞችና ሌሎች ከምክር አገልግሎቱ ጋር የተያያዙ ዕቃዎችን ለአማካሪው የሚያቀርቡ ሰዎች ብቻ የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት የጽሁፍ ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው መግባትና ቦታውን መጠቀም ይችላሉ፡፡

62.5 ጥርጣሬን ለማስወገድ እዚህ ቦታ ውስጥ ለመግባትና ለመጠቀም ፍቃድ ማግኘት የቦታው ማንኛውንም ክፍል የይዞታ ማረጋገጫ አይደለም፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በማንኛውም ወቅት የዚህ ቦታ ሙሉ ባቤትነት ያለው ሲሆን አማካሪው ግን በቦታው ምንም አይነት ይዞታና ጥቅም አይኖረውም፡፡

62.6 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በማንኛውም ጊዜ ቦታዎቹን እንዲጠቀሙ ለሶስተኛ ወገን የመፍቀድ መብት አለው፡፡ ይህም ከውሉ ጋር በተያያዘ ለአማካሪው በተሰጠው መብት መሠረት ነው፡

62.7 አማካሪው ቦታዎችን ንፁህ ምቹ (የተስተካከለ) እና ደህንነታቸው የተጠበቀ አድርጎ መያዝ አለበት

62.8 ግዥ ፈፃማው መ/ቤትየምትክ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያገለግሉ መሣሪያዎች ለማንቀሳቀስ የሚጠቅም በቂ ውሃ ነዳጅና የኤሌክትሪክ ኃይል ያቀርባል

62.9 በተፈቀዱ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች ቆሻሻ ለማስወገድ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሁኔታዎችን ያመቻቻል::

62.10 መለወጥ ወይም ማስተካከል አማካሪው የሚሰጠው የምክር አገልግሎት መ/ቤት ካልሆነ በስተቀር አማካሪው የተፈቀደለትን ቦታ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፅሁፍ ፍቃድ ሳያገኝ መለወጥ ወይም ማሻሻል አይችልም።

63. መገልገያ መሳሪያዎችና ዕቃዎች

63.1 ለአማካሪው በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የቀረቡ ወይም ከግዥ ፈፃሚው በተገኘ ገንዘብ በአማካሪው የተገዙ መሣሪያዎች፣መኪኖች ወይም ዕቃዎች ንብረትነታቸው የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ነው፡፡ በዚሁም መሠረት ምልክት ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

63.2 መሣሪያዎችና ዕቃዎች በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሲቀርቡ የሰርቪስና የጥገና አገልግሎት በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ይከናወናል፡፡

63.3 የውሉ ኃላፊ በግዥ ፈፃሚ መ/ቤት መሣሪያዎች የተከሰተ ማናቸውም ብልሽት፣ ጉድለት ወይም ጉዳት ስልጣን ለተሰጠው ኃላፊ ማሳወቅ አለበት፡፡ በአማካሪው ሠራተኞች ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት በተፈጠረ ጉዳት ምክንያት የተቀየረ ዕቃ ዋጋ አማካሪው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

63.4 በቢ.ጋሩ በተቀመጠው መሠረት አማካሪው የምክር አገልግሎት ለመስጠት የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎችን በራሱ ወጪ ይተክላል፡፡

63.5 አማካሪው በውሉ ሥራ ጥቅም ላይ የዋሉ መሣሪያዎች በአምራቹ መመሪያና በወቅቱ ህግ መሠረት በጥሩ ሁኔታ ጥገና እየተደረገላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

63.6 አማካሪው የሚጠቀምባቸው ሁሉም መሣሪያዎችና ዕቃዎች ተገቢ የሆኑ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ወይም ተመሳሳይ አለም አቀፍ ደረጃዎችን የሚያሟሉ መሆናቸው ማረጋገጥና በተጠየቀ ጊዜ የዚህን ማስረጃ ስልጣን ለተሰጠው ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡

63.7 አማካሪው የሚከተሉት ይጠበቅበታል፤

(ሀ) ብቃት ያለው የጥገና ፕሮግራም ማዘጋጀት

(ለ) የምክር አገልግሎቱ ቀጣይነት እንዲኖረው የድንገተኛ መለስተኛ ጥገናዎችን በብዛት ማዘጋጀት፣

(ሐ) ሁሉም የመሣሪያ ግዥዎችን ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ጋር መስማማት፣

(መ) የምክር አገልግሎት በሚሰጥበት መሣሪያዎች ጋር በተያያዘ የሚኖሩ የኢንስፔክሽንና የምርምር ደንቦችና ማክበር፣ እና

(ሠ) ሪከርዶችን መያዝ፣በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለሚከናወን የጥገና ፍተሻ እና ማረጋገጫ ኢንስፔክሽን ክፍት ማድረግ፡፡

63.8 አማካሪው ከውሉ ጋር የሚጠቀምበት የመገናኛ ወይም የኤሌክትሪካል መሣሪያ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ከሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች ጋር ግጭት (መጠላለፍ) መፍጥር ወይም ጉዳት ማድረስ የለበትም፡፡

63.9 አማካሪው ከውሉ ጋር በተያያዘ ሊጠቀምበት ያቀደው የመገናኛ ወይም የኤሌክትሪክ መሣሪያ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግቢ ውስጥ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በግዥው መ/ቤት ውሳኔ መፈተሸና መፈቀድ አለበት፡፡

63.10 ከላይ የተጠቀሰው ንዑስ አንቀፅ 62.9 እንደተጠበቀ ሆኖ አማካሪው በውሉ አገልግሎት በሚጠቀምበት የመገናኛ ወይም የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ለሚደርስ ማንኛውም ጉዳት ኃላፊነቱን ይወስዳል፡፡

63.11 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትከምክር አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ አማካሪው የሚጠቀምባቸውን መሣሪያዎች በማንኛውም ጊዜ የመፈተሽ መብት አለው፡፡ ስለ መሣሪያዎች አጠቃቀም ስልጣን በተሰጠው ኃይል የሚሰጡትን መመሪያዎችንም ማክበር አለበት፡፡

63.12 በአማካሪው አማካኝነት ወይ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግቢ ለሚመጡ መሣሪያዎች ክፍያ አይፈፀምም ወይም እንዲከፍል አይደረግም፡፡

63.13 ውሉ ተግባራዊ መሆን በሚጀምርበት ወቅት ለአማካሪው የቀረቡለት መሣሪያዎች ግዥ ፈፃሚው መ/ቤትና አማካሪው በሚመድቡት ገለልተኛ ባለሙያ ዋጋቸው መተመን አለበት፡፡ መሣሪያዎቹ ወደ አማካሪው የሚተላለፉት ካለ ምንም አይነት ክፍያ ነው፡፡ አማካሪው መሣሪያዎችን፣ መኪኖችን እና ዕቃዎችን በእጁ ካስገባ በኃላ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ወጪ (ሂሳብ) እና በሚኖራቸው ዋጋ የመድን ሽፋን ሊገዛላቸው ይገባል፡፡

63.14 ውሉ በሚቋረጥበት ወይም በሚጠናቀቅበት ወቅት አማካሪው የወሰዳቸው መሳሪያዎች መኪኖች እና ዕቃዎች በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ቆጠራ እንዲካሄድ ያዘጋጃቸዋል፡፡ በቢጋሩ በተገለፀው መሰረት ሁሉም መሣሪያዎች በድጋሚ ዋጋቸው ከተገመተ በኃላ ወደ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ይመለሳሉ፡፡ በመሣሪያው ዋጋ ላይ ጭማሪ ወይም ቅናሽ ካለ ከአማካሪው የመጨረሻ ክፍያ ይቀነሳል፡፡ የዋጋ ለውጥ ከሌለ በስተቀር መሣሪያዎቹ ወደ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚተላለፉት ካለምንም ክፍያ ነው፡፡

63.15 ወደ አገር ውስጥ በአማካሪው ወይም በሰራተኞቹ ለፕሮጀክቱ ስራ ወይም ለግል መገልገያ የገቡ መሣሪያዎችና ዕቃዎች እንደየሁኔታው የአማካሪው ወይም የሠራተኞቹ ንብረት ይሆናሉ፡፡

64. ቁልፍ የሰው ኃይል

64.1 ማዕረግ፣ ስምምነት የተደረሰበትን የሥራ ዝርዝር፣ የሚፈልገው ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ እና የእያንዳንዱ ቁልፍ የሠው ኃይል የምክር አገልግሎት ስራ ለመስራት የሚሳተፍበት ግምታዊ ጊዜ በአባሪ ‹ሐ› ተገልፀዋል፡፡ በመዕረግ እና በስም የተዘረዘሩት የሰው ኃይልና ንዑስ አማካሪዎች በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ይፀድቃሉ፡፡

64.2 ተዋዋይ ወገኖች ውሉ በሚጀመርበት ጊዜ በቁልፍ ሠራተኞች ምደባ ላይ ተስማምተዋል፡፡ አማካሪው እና ንዑስ አማካሪዎቹ ቁልፍ ሰራተኞችን ከተመደቡት ቦታ ከማባረራቸው እና ከመተካታቸው በፊቱ የግዥ ፈፃሚው መ/ቤትን የፅሁፍ ስምምነት ማግኘት አለባቸው፡፡ ከተቻለ አማካሪው ቁልፍ ሰራተኞቹን ከተመደቡበት የሥራ ኃላፊነት አንፃር የመተካት ሀሳብ ካለው ሀሳቡን ቢያንስ ከአንድ ወር (30 ቀናት) በፊት ማሳወቅ አለበት፡፡

64.3 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአማካሪው ወይም በንዑስ አማካሪዎቹ የቀረበለትን የቁልፍ ሰራተኞች ተተኪ ምደባ ስምምነቱን ለመግለፅ ከሚገባው በላይ ማዘግየት ወይም መያዝ የለበትም፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በሆነ ቦታ የታጩትን ቁልፍ ሠራተኞች ቃለ መጠይቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

64.4 በአማካሪው የተመደቡት ቁልፍ ሠራተኞች ለማማከር አገልግሎት አስፈላጊ መሆናቸው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤትማሳወቅ አለበት፡፡ አማካሪው ማንኛውም የቁልፍ ሠራተኛ ስራ ከ10 (አስር) የሥራ ቀናት በላይ ክፍት ሆኖ መቆየት የለበትም፡፡ የሚተካው ቁልፍ ሠራኛ ከወጣው ሠራተኛ ጋር እኩል ወይም የበለጠ ብቃት እና ልምድ ያለውና የፊተኛው ሠራተኛ የሚጫወተውን ሚና ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን መሆን ይኖርበታል፡፡

64.5 አማካሪው የተመደበው ቁልፍ ሠራተኛ በምክር አገልግሎት አሰጣት ሂደት ውስጥ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲችል ከስራው ጋር ተመጣጣኝ ለሆነ ጊዜ በስራው ላይ የሚቆይ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ይህ የሚሆነው ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተቃራኒው የፅሁፍ አስተያየቱን ካልሰጠ ነው ሕጋዊ መብቱን በሚጋፋ መልኩ ካላደረገው በስተቀር አማካሪው የሁሉም የቁልፍ ሰራተኞችን የምክር አገልግሎት ይዞ ለመቆየት የተቻለውን ሁሉ እርምጃ ይወስዳል፡፡

64.6 በአባሪ ‹ሀ› ከተዘረዘረው የምክር አገልግሎት ወሰን በላይ ተጨማሪ ስራ የሚያስፈልግ ከሆነ በአባሪ ‹ሐ› የተጠቀሰው የቁልፍ ሠራተኞች የሥራ ቆይታ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤትና በአማካሪው በሚደረግ የፅሁፍ ስምምነት ሊራዘም ይችላል፡፡ ክፍያዎች በውሉ ስምምነቱ ስር በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 39.2 ከተቀመጠው ጣሪያ በላይ ከሆነ ይህ በውል ስምምነቱ በግልፅ መጠቀስ አለበት፡፡

64.7 ቁልፍ ሠረተኞች ሊሆኑ የሚችሉ ተጨማሪ ግለሰቦች መኖራቸው በሚታወቅበት ጊዜ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በአማካሪው ስራተኞች የሚከናወኑ ተጨማሪ የሥራ መደቦችን ሊመርጥ ይችላል፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተመረጡትን ቁልፍ ሠራተኞች ለማፅደቅ አማካሪው ከሚገባው በላይ ጊዜ መውሰድ ወይም መያዝ የለበትም፡፡ ሲፀድቅ ቁልፍ

ሰራተኞች በአማካሪው ዝርዝር ውስጥ መካተት ይኖርባቸዋል፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በበቂ ምክንያት አጥጋቢ ሆኖ ያላገኘውን ቁልፍ ሠራተኛ ተብሎ የተመደበ ሠራተኛ በመተካቱ ምክንያት ተጠያቂ አይሆንም፡፡ አማካሪው በሰራተኞቹ በዚህ ሁኔታ ከሚፈጠር የይገባኛል (የካሣ ክፍያ) ግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት ጥበቃ ያደርግለታል፡፡

65. የሰው ኃይል ስለማፀደቅ

65.1 በአባሪ ‹ሐ› በማዕረግና በስም የተዘረዘሩትን ቁልፍ ሠራኞች በግዥ ፈፃሚው ፀድቋል፡፡ የማማከር አገልግሎቱን ለማከናወን አማካሪው የሚያቀርባቸው ሌሎች ሠራተኞች በተመለከተ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አይቶ እንዲያፀድቀው ካሪኩለም ቪቴ (CV) አብሮ መያያዝ አለበት፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተቃውሞውን (ምክንያቶቹን ጠቅሶ) CV በቀረበ በሃያ አንድ (21) ቀናት ውስጥ ካላቀረበ ሠራተኞቹ ተቀባይነትን እንዳገኙ ይቆጠራል፡፡

66. የሰው ሃይል ቁጥጥር እና ኢንስፔክሽን (ክትትል)

66.1 ለውል የሥራ መሪ የተሰጠ ማንኛውም ማስታወቂያ፣ መረጃ፣ መመሪያ ወይም ሌላ የመረጃ ልውውጥ ለአማካሪው እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

66.2 በቀረበው ቢጋር መሠረት የውሉ የሥራ መሪ ተግቢ ብቃት ያለው መሆን አለበት፡፡ለቃለ መጠይቅ ከመቅረቡ በፊትም ስልጣን የተሰጠው ኃላፊ እንዲያፀድቀው ግለ ታሪኩና የስራ ልምዱ በተጨማሪነት መቅረብ አለበት፡፡

66.3 የውል አስተዳዳሪ ሆኖ የሚመደበው ሰው ወይም ሌሎች ተከታታይ የስራ ምደባዎችን በሚመለከት አማካሪው በጽሁፍ ስለሚመደበው ግለሰብ ማንነት ለግዥ ፈፃሚው የስራ ሀላፊ ያሳውቃል፡፡ እንደዚህ አይነቶቹ የጽሁፍ ማስታወቂያዎች በሌላ እስከሚለወጡ ድረስ ግዥ ፈፃሚው ቀድሞ የውል አስተዳደሪ ተብሎ የተሰጠውን ሰው አሁንም ውል አስተዳደሪ እንደሆነ ይቆጥረዋል፡፡

66.4 አማካሪው በውል ስራ አስኪያጅነት ወይም በምክትልነት ስልጣን የሰጠው ሰው በማናቸውም ጊዜ ማለትም በስራ ሰዓት በግዥ ፈፃሚ የስራ ቦታ መገኘት አለበት፡፡

66.5 አማካሪው ከዚህ ጋር አያይዞ የውል የሥራ መሪ ሆኖ የተመደበውን ግለሰብ ማንነትና ተከታታይ ምደባዎችንም ስልጣን ለተሰጠው ኃላፊ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ይህ ማስታወቂያ እስኪደርሰው ድረስ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሥልጣን ለተሰጠው ኃላፊ የውል ሥራ መሪ ተብሎ በመጨረሻ የተላከለትን ሰው በዚሁ መልክ እውቅና ይሰጣል፡፡

66.6 በውሉ መሠረት ብቃት ያለው የምክር አገልግሎት መስጠት እንዲችል የውሉ የሥራ መሪ እና ምክትሉ ስልጣን ከተሠጠው ኃላፊና ሌሎች የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ቁጥጥር ሠራተኞች ጋር መገናኘት እና መረጃ መለዋወጥ ይገባቸዋል፡፡

66.7 አማካሪው ከውል ሥራ መሪ በተጨማሪ ብቃት ያለው የቁጥጥር ሰራተኞችን ማቅረብ አለበት፡፡ ይህም በሥራ ቦታው የምክር አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉት ሠራተኞች ሁል ጊዜ የተመደቡበትን ሥራ በአግባቡ እንዲያከናውኑ በቂ የሆነ ቁጥጥር እንዲኖር ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

66.8 በቢጋሩ መሠረት ለሥራ አመራርና ለሱፐርቫይዘርነት የሚመደቡት ግለሰቦች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ ተቀባይነት ያገኙ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኃላፊው ብቃት የሌላቸውን ሰራተኞች ምደባ የመሻር መብት አለው፡፡

66.9 የማማከር አገልግሎት በመሥጠት ላይ የሚገኙ የአማካሪው ሰራተኞች በቅድሚያ በአማካሪው ሱፐርቫይዘር ቁጥጥርና መመሪያ ስር ናቸው፡፡ ነገር ግን በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግቢ (የሥራ ቦታ) እስከሆኑ ድረስ አግባብነት ካለው አገልግሎት ጋር በተያያዙ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሱፐርቫይዘሮች የሚሰጣቸውን መመሪያ ማክበር አለባቸው፡፡

66.10 አማካሪው ሠራተኞቹ ሥራቸውን በአግባቡ እየሠሩ መሆናቸውን ማረጋገጥና በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግቢ ውስጥ ሲሆን የሥራው ሁኔታ በሚፈቅደው መሠረት በስርዓትና በፀጥታ እንዲሰሩ ማድረግ አለበት የአማካሪው ሰራተኞች የግዥ ፈፃሚውን መ/ቤት የዕለት ተዕለት ተግባራት፣ ልምዶች፣ እና አሰራሮች ወይም የጎብኝዎችን ወይም የማንኛውም ሌላ አማካሪ ሠራተኞችን ስራ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ማስተጓጎል (ማወክ) የለባቸውም፡፡

67. የሠራተኛው የሥራ ሠዓት

67.1 የቁልፍ ሠራተኞች የሥራ ሠዓታትና የዕረፍት ቀናት በአባሪ ‹ሐ› ተቀምጧል። በጉዞ ላይ የሚጠፋውን ጊዜ ከግምት ውስጥ ለማስገባት ሲባል ከውጪ ሀገር አገልግሎቱን ለመስጠት የሚመጡ ሠራተኞች ስራ ጀመሩ ወይም አጠናቀቁ የሚባለው ኢትዮጵያ ውስጥ ለመግባት የወሰዱባቸው ቀናት እና ከኢትዮጵያ ከወጡ በኋላ እንደቅደም ተከተላቸው ታሳቢ በማድረግ ነው ይህም በአባሪ ‹ሐ› ውስጥ በዝርዝር ተገልጿል፡፡

67.2 በአባሪ ‹ሐ› በተለየ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር ቁልፍ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ ወይም የህክምና ወይም የእረፍት ጊዜ ክፍያ የማግኘት መብት የላቸውም፡፡እንዲሁም በዚሁ አባሪ ካልተገለፀ በስተቀር አማካሪው የሚከፍላቸው ደመወዝ ይህን ሁሉ ይሸፍናል ተብሎ ይገመታል፡፡ ለሰራተኞቹ የሚፈቅድላቸው ዕረፍት በአባሪ ‹ሐ› ውስጥ ሰራተኞቹ አገልግሎት በሚሠጡባቸው ወራት ዝርዝር ተቀምጧል፡፡ ማንኛውም በሠራተኞች

የሚወሰድ ዕረፍት የምክር አገልግሎቱን ስራ እንቅስቃሴና ቁጥጥር እንደማያጓትት ከአማካሪው ቅድሚያ ማረጋገጫ ያስፈልገዋል፡፡

68. ሰራተኛ ማሰናበትእና/ወይምመተካት

68.1 አማካሪው ስምምነት የተደረሰባቸውን ሰራተኞች ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፅሁፍ ማረጋገጫ ሳያገኝ መለወጥ የለበትም፡፡ ከቁጥጥሩ በላይ የሆነ ምክንያት ሲያጋጥመው አማካሪው በሚከተሉት ሁኔታዎች በራሱ ውሳኔ ሰራተኞችን መተካት ይችላል፡፡

(ሀ) በሞት፣ በጡረታ፣ መገለል፣ በሕመም ወይም የሠራተኛው አባል አደጋ በሚያጋጥምበት ወቅት

(ለ) ከአማካሪው ቁጥጥር ወጪ በሆነ ምክንያት (ለምሳሌ ስራ መልቀቅ) ሰራተኛ መተካት የግድ አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት

68.2 አማካሪው የሚተካው ሰራተኛ ከቀድሞ ሠራተኛው ተመሳሳይ ወይም የበለጠ ብቃት ልኖረው ይገባል፡፡

68.3 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ማንኛውም ሠራተኛ፤

i. ከፍተኛ የስራ ምግባር ግድፈት ከፈፀመ ወይም በወንጀል ክስ ከተመሠረተበት ወይም

ii. የሠራተኛው የሥራ አፈፃፀም አጥጋቢ አለመሆኑ በቂ ምክንያት ካለው ይህን ተከትሎ አማካሪው ምክንያቱን ተጠቅሶ ፈፃሚው መ/ቤት በሚቀርብለት የፅሁፍ ጥያቄ መሠረት በብቃቱና ልምዱ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተቀባይነት ያለው ሠራተኛ ተክቶ ማቅረብ አለበት፡፡

68.4 ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ምክንያቱን ጠቅሶ የሠራተኞቹ አባል የሆነን ግለሰብ እንዲሰናበቱ አማካሪውን ከጠየቀ አማካሪው ሠራተኛውን በሰባት (7) ቀናት ውስጥ እንዲሰናበቱ በቀጣይነት ከውሉ ሥራ ጋር ግንኙነት እንዳይኖረው ማድረግ አለበት፡፡

68.5 ከላይ በተጠቀሰው ንዑስ አንቀጽ መሠረት በሚከተል ማንኛውም ሰራተኛ እንዲሁም ተመላሽ የሚሆኑ ወጪዎች (አብረው የሚመጡ ሕጋዊ የቤተሰብ አባላት ወጪ ጨምሮ) ምክንያት አማካሪው የይገባኛል ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ አስቀድሞ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፅሁፍ ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፡፡ ለሚተካው ሰራተኛ የሚከፈለው ክፍያ ተመን የሚሰላው፤ ለተተካው ሰራተኛ የሚከፈል ወርሃዊ ደመወዝ ከመተካቱ በፊት ካሉት ስድስት(6) ወራት ውስጥ የተከፈለው አማካይ ደመወዝ ከተከፈለ በኃላ ይህ ክፍልፋይ (ratio) የሚተካው ሰራተኛ በሚከፈለው ደመወዝ ተባዝቶ ነው፡፡ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተለየ አኳኃን ካልተስማማ በስተቀር፤

i. አንድን ሰራተኛ ለማሰናበት እና/ወይም ለመተካት የሚደረግ የጉዞ እና ሌሎች ወጪዎች አማካሪው ይሸፍናል፡፡ እና

ii. ለተተኪው ሰራተኛ የሚከፈለው ደመወዝ (ክፍያ) ለተተካው ሠራተኛ ይከፈል ከነበረው መብለጥ የለበትም፡፡

68.6 አንድን ሰራተኛ በማሰናበት እና/ወይም በመተካት ምክንያት ለሚከሰቱ ተጨማሪ ወጪዎች አማካሪው የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ አይችልም፡፡

69. ጊዜን ስለማራዘም

69.1 በውሉ አፈፃፀም ሂደት በማንኛውም ጊዜ አማካሪው ወይም ንዑስ አማካሪዎቹ የምክር አገልግሎቱን በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀፅ 59 መሠረት እንዳያጠናቅቁ የሚያጓትቱ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ አማካሪው ስለ ስራው መዘግየት የሚያስፈልገው ጊዜና ምክንያቱን ጠቅሶ ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ከአማካሪው ማስታወቂያ ከደረሰው በኃላ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በተቻለ ፍጥነት ጉዳዩን መርምሮ በራሱ ውሳኔ የአማካሪው የማጠናቀቂያ ጊዜ ሊያራዝምበት ይችላል፡፡ ይህን የጊዜ ማራዘም ሁለቱም ወገኖች የውል ሰነዶች በማሻሻል ሊያፀድቁት ይገባል፡፡

69.2 በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀፅ 18 በተጠቀሰው መሠረት ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ካልሆነ በስተቀር እና በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች ንዑስ አንቀፅ 68.1 እንደተገለፀው ጊዜ እንዲራዘም ስምምነት ካልተደረሰ አማካሪው አገልግሎቱን በወቅቱ ካላስረከበና ግዴታዎቹን ካልፈፀመ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀፅ 26 መሠረት የታወቀ የጉዳት ካሣ እንዲከፈል ይገደዳል፡፡

ሰ. ፍትሃዊነትና ታማኝነት (Good Faith)

70. ቅን ልቦና (ታማኝነት)

70.1 ሁሉም ተዋዋይ ወገኖች የእያንዳንዳቸውን መብት በተመለከተ በታማኝነት ለመተግበር መሥራት አለባቸው፡፡ የዚህ ኘሮጀክት አላማዎች እንዲሳኩም ሁሉም አይነት አሳማኝና ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡

71. የውል አፈፃፀም

71.1 ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች በዚህ ውል አፈፃፀም ሂደት የሚያጋጥሙ ሁሉም ያልተጠበቁ ሁኔታዎችን መገመት የማይታሰብ እንደሆነ በመገንዘብ የሁለቱም ወገኖች ጥቅም በማይጎዳ መልኩ እና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ውሉን ለመፈፀም ተስማምተዋል፡፡ በውሉ አፈፃፀም ወቅት አንዱ ወገን ውሉ ፍትሃዊ በሆነ አኳኃን እየተከናወነ አይደለም ብሎ ካመነ ለዚህ ፍትሃዊ ያልሆነ አካሄድ መንስኤ የሆነውን ምክንያት ለማስወገድ መወሰድ ስላለበት እርምጃ ሁለቱም ይስማማሉ፡፡ በዚህ አንቀፅ የተጠቀሱት ተግባራት ለመፈፀም ስምምነት ካልተደረሰ ግን ጉዳዩ በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀፅ 25 መሠረት ባለመግባባቶች አፈታት ስርዓት የሚታይ ይሆናል፡፡

ክፍል 8: የውሉ ልዩ ሁኔታዎች

ማውጫ

ሀ. አጠቃላይ ድንጋጌዎች 1
ለ. ውል.....1
ሐ. የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግዴታዎች 4
መ. የአማካሪው ክፍያዎች 4
ሠ. የአማካሪው ግዴታዎች 5
ረ. ውል አፈፃፀም 5

ክፍል 8
ልዩ የውል ሁኔታ

የሚከተሉት ልዩ የውል ሁኔታዎች አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች መ/ቤት ይሆናሉ፡፡ አለመጣጣም በሚኖርበት ወቅት በውሉ አጠቃላይ ሁኔታዎች የተጠቀሱት በበላይነት ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

<table>
<tr><td>አጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች አንቀጽ መለያ</td><td>ልዩ የውል ሁኔታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">ሀ. አጠቃላይ ድንጋጌዎች</td></tr>
<tr><td></td><td>የግዥው መለያ ቁጥር፡ [የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]</td></tr>
<tr><td>አ.ው.ሁ. 1.2 (ነ)</td><td>የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ፡ [የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ሙሉ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td colspan="2">ለ. ውል</td></tr>
<tr><td>አ.ው.ሁ. 7.1 (መ)</td><td>በአጠቃላይ የውል ሁኔታዎች አንቀጽ 7.1 ከተጠቀሱት ሰነዶች በተጨማሪ የሚከተሉት ሰነዶች የውሉ አካል ይሆናሉ፡፡</td></tr>
<tr><td>አ.ው.ሁ. 8.1</td><td>ገዥው ሀግ _____ ይሆናል፡፡</td></tr>
<tr><td>አ.ው.ሁ. 9.1</td><td>የውሉ ቋንቋ _____ ይሆናል፡፡</td></tr>
<tr><td>አ.ው.ሁ. 10.2 እና 10.3</td><td>ለማስታወቂያ አላማ የግዥ ፈፃሚው የመንግስት መ/ቤት አድራሻ
<table>
<tr><td>ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስምና ሀላፊነት</td><td>[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስምና ሀላፊነት ይግባ]</td></tr>
<tr><td>[የመንገድ ስም ይግባ]</td><td>[የመንገድ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>[የከተማ ስም ይግባ]</td><td>[የከተማ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ኢትዮጵያ</td><td>ኢትዮጵያ</td></tr>
<tr><td>[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ]</td><td>[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ]</td></tr>
<tr><td>[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የፋክስ ቁጥር ይግባ]</td><td>[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የፋክስ ቁጥር ይግባ]</td></tr>
<tr><td>[ኢሜይል አድራሻ ይግባ]</td><td>[ኢሜይል አድራሻ ይግባ]</td></tr>
<tr><td>[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስምና ሀላፊነት ይግባ]</td><td>[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስምና ሀላፊነት ይግባ]</td></tr>
<tr><td></td><td></td></tr>
</table>
ለማስታወቂያ አላማ የአማካሪው አድራሻ
<table>
<tr><td colspan="2">አማካሪው</td></tr>
<tr><td>ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው</td><td>[ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ስምና ሀላፊነት ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ቢሮ ቁጥር</td><td>ቢሮ ቁጥር ይግባ</td></tr>
</table></td></tr>
</table>

<table>
<tr><td></td><td><table>
<tr><td></td><td></td></tr>
<tr><td>የመንገድ ስም</td><td>[የመንገድ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ከተማ</td><td>[የከተማ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>የፖስታ ኮድ</td><td>[ፓ.ሳ. ኮድ ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ]</td></tr>
<tr><td>ሀገር</td><td>ኢትዮጵያ</td></tr>
<tr><td>ስልክ</td><td>[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ]</td></tr>
<tr><td></td><td></td></tr>
<tr><td>ኢ-ሜይል አድራሻ</td><td>[ኢሜይል አድራሻ ይግባ]</td></tr>
</table></td></tr>
<tr><td>አው.ሁ. 11.1</td><td>ኃላፊነቱ የተሰጠው አባል (የአባሉን ስም ይግባ)</td></tr>
<tr><td>አው.ሁ. 12.1</td><td>ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ስልጣን የተሰጠው የስራ ኃላፊ ----ነው<table>
<tr><td>ስልጣኑ የተሰጠው የስራ መኮንን</td><td>የቢሮው ወኪል</td></tr>
<tr><td></td><td></td></tr>
<tr><td>የመንገድ ስም</td><td>[የመንገድ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ከተማ</td><td>[የከተማ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>የፖስታ ኮድ</td><td>[ፓ.ሳ. ኮድ ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ]</td></tr>
<tr><td>ሀገር</td><td>ኢትዮጵያ</td></tr>
<tr><td>ስልክ</td><td>[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ]</td></tr>
<tr><td></td><td></td></tr>
<tr><td>ኢ-ሜይል አድራሻ</td><td>[ኢሜይል አድራሻ ይግባ]</td></tr>
</table>
በአማካሪው ስልጣን የተሰጠው የስራ ኃላፊ<table>
<tr><td>ስልጣኑ የተሰጠው የስራ ኃላፊ</td><td>የቢሮው ወኪል</td></tr>
<tr><td></td><td></td></tr>
<tr><td>የመንገድ ስም</td><td>[የመንገድ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>ከተማ</td><td>[የከተማ ስም ይግባ]</td></tr>
<tr><td>የፖስታ ኮድ</td><td>[ፓ.ሳ. ኮድ ይግባ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ]</td></tr>
<tr><td>ሀገር</td><td>ኢትዮጵያ</td></tr>
<tr><td>ስልክ</td><td>[የሀገርና ከተማ ኮድ ጨምሮ የስልክ ቁጥር ይግባ]</td></tr>
<tr><td></td><td></td></tr>
<tr><td>ኢ-ሜይል አድራሻ</td><td>[ኢሜይል አድራሻ ይግባ]</td></tr>
</table></td></tr>
<tr><td>አው.ሁ. 16.1</td><td>የማንኛውም የህግ ወይም ደንብ ለውጥ በውሉ አገልግሎት ወይም ዋጋ ማጠናቀቂያ ወቅት የሚያስከትለው ለውጥ</td></tr>
</table>

አው.ሁ. 17.1	አማካሪው፣ንዑስ አማካሪ እና ሰራተኞቻቸው (i) ☐ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከሚጣሉት ቀረጦች እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብሮች ነፃ መሆን የለበትም፡፡ (ii) ☐ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከሚጣሉት ቀረጦች እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብሮች ነፃ መሆን አለባቸው፡፡ ☐ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚጣልበትን ማንኛውም ቀረጥ ቀጥተኛ ያልሆኑ ግብር ከከፈለ በግዥ ፈፃሚው ተመላሽ ይደረግለታል (ወይም ግዥ ፈፃሚው በአማካሪው እና ሰራተኞቹ ወክሎ ክፍያ ይፈጽማል) ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት አማካሪውን ንዑስ አማካሪዎችንና ሰራተኞቹን ከማንኛውም ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ፣ግብሮች፣ክፍያዎች እና አግባብነት ያለው ህግ ከጣለባቸው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሌሎች ክፍያዎች ነፃ እንዲሆኑ ዋስትና ይሰጣቸዋል (ወይም ግዥ ፈፃሚውን አማካሪውን ንዑስ አማካሪውን ወይም ሠራተኞቹን ወክሎ ክፍያ ይፈፀማል ወይም የከፈሉት እንዲመለስላቸው ያደርጋል) (ሀ) ለአማካሪው፣ንዑስ አማካሪው እና ሰራተኞች (ዜጎች ወይም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ካልሆነ በስተቀር) ከአገልግሎቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ማንኛቸውም ክፍያዎች (ለ) በአማካሪው ወይም ንዑስ አማካሪው ለሚሰጡት አገልግሎቶች እንዲውሉ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ እና ከአገልግሎት በኋላ ተመልሰው የሚያወጧቸው ማንኛውም መሳሪያዎች፣ እቃዎች እና አቅርቦቶች አካባቢው ከገቡ በኋላ፤ (ሐ) አገልግሎቱን ለማከናወን ከውጭ ሃገር ለገቡ መሳሪያዎች እና ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በጀት ክፍያ የተፈፀመባቸው እና የግዥ ፈፃሚው ንብረት ተደርገው የሚወሰዱ መሣሪያዎች (መ) በአማካሪው ንዑስ አማካሪዎችወይም በሰራተኞች (የኢትዮጵያ ዜግነት ወይም ቋሚ መኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ካልሆነ በስተቀር) ወይም የሠራተኞቹ ህጋዊ ጥገኞች ወደ አገር ያስገቧቸውና ሲወጡ ይዟቸው የሚመለሱ ንብረቶች፡፡ ይህም የሚፈፀመው የሚከተሉት ሲሟሉ ነው፡፡ አማካሪው፣ ንዑስ አማካሪው እና ሰራተኞቹ እንዲሁም ህጋዊ ጥገኞች የተለመደውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከውጭ ሃገር ንብረቶች የማስመጣት የጉምሩክ አሰራር ደንብ መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ አማካሪው፣ ንዑስ አማካሪው ወይም ሰራተኞቹ ወይም ጥገኞቻቸው ከቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ ያስገቧቸውን ዕቃዎች ይዘው ካልተመላሱ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቀሩ ካደረጉ እንደየአስፈላጊነቱ (i) ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ደንቦች መሠረት የጉምሩክ እና ቀረጥ ክፍያዎችን መፈፀም ይኖርባቸዋል፡፡ (ii) ንብረቱ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የተከፈለ ከሆነ ተመላሽ ይደረጋል፡፡
አ.ው.ሁ. 25.5	አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ፣ (i) ☐ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን የምንጠቀም ከሆነ አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሰረት በተቋቋሙ እና በተገቢው

	መ/ቤት ዕውቅና በተሰጣቸው የግልግል ዳኝነት አካላት በኩል መሆን አለበት፡፡ (ii) ☐ አለመግባባት ሲፈጥር.....አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴን በመጠቀም ይፈታል፡፡
አ.ው.ሁ. 27.1	የውሉ ተፈፃሚነት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ ሀ. ለ. ሐ.
አ.ው.ሁ. 27.2	አገልግሎት የሚጀመርበት ቀን _____ይሆናል፡፡
አ.ው.ሁ. 28.1	የማጠናቀቂያው ቀን _____ይሆናል፡፡
ሐ. የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ግዴታዎች	
አ.ው.ሁ. 31.1 (ሰ)	ግዥ ፈፃሚው የሚከተሉትን ተጨማሪ ድጋፎች ለአማካሪው ይሰጣል፡፡ ሀ. ለ. ሐ.
መ. የአማካሪው ክፍያዎች	
አ.ው.ሁ. 36.1	በዚህ ውል መሰረት በአማካሪው የሚሰጡ ክፍያዎች በሙሉ በ_____ ይሆናል፡፡
አ.ው.ሁ. 36.1	እንደ አስፈላጊነቱ የክፍያውን ከፍተኛ መጠን _____ መቶኛ ነው፡፡
አ.ው.ሁ. 37.1	ይህ ውል .....ውል ነው፡፡
አ.ው.ሁ. 39.1	የክፍያ የጊዜ ሰሌዳ የሚከተለው ይሆናል፡፡ ሀ. ለ.
አ.ው.ሁ. 39.2	የሚደረግ ቅድመ ክፍያ: ለሚደረጉ የቅድመ ክፍያ እና የቅድመ ክፍያ ዋስትና የሚከተሉት ደንቦች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ያስፈልጋል፡፡ ውሉ ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ቅድመ ክፍያ በውጭ ምንዛሪ ወይም በሀገር ውስጥ ገንዘብ ይፈፀማል፡፡ የሚፈፀመው ቅድመ ክፍያ ከአማካሪው ከእያንዳንዱ ወርሃዊ ክፍያዎች በግዥ ፈፃሚው ቅድመ ክፍያው ሙሉ ለሙሉ ተጠናቆ እስከሚከፈል ተቆራጭ እየተደረገ ይከፈላል፡፡ የቅድመ ክፍያ ዋስትና ለቅድመ ክፍያ ከተያዘው ውስጥ በተጠቀሰው መጠን እና የገንዘብ ምንዛሪ ይፈፀማል፡፡
አው.ሁ. 40.2	አማካሪው ለግዥ ፈፃሚው መ/ቤት በ------- ጊዜ ልዩነት የወጪ ዝርዝር የያዙ ደረሰኞች ያቀርባል፡፡
አው.ሁ. 40.5	ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአማካሪው የውሉ ዋጋ ደረሰኝ ከተረከበበት ቀን ጀምሮ በ_____ቀናት ውስጥ እንዲሁም ያመጨረሻ ክፍያን በተመለከተ በ_____ቀናት ውስጥ ይፈጽማል፡፡
አው.ሁ. 41.2	ለአማካሪዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ በሚከተሉት መልኩ ይሆናል፡፡ ሀ. ለ.
አው.ሁ. 41.4	የዋጋ ማስተካከያ፣ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄዎች በምን አይነት መንገድ መቅረብ እንዳለባቸው፤ እንዲሁም ለሚደረጉ የዋጋ ማስተካከያዎች ከዋጋ ማስተካከያ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ተገቢ ደጋፊ ሰነዶች እንዲሁም የቅጂ ብዛት የሚከተሉት ናቸው፡-

ሠ. የአማካሪው ግዴታዎች	
አው.ሁ. 42.3 (ለ)	የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የቅድሚያ ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸው፡- ሀ------- ለ------ ሐ------
አው.ሁ. 46.2 (ለ)	አጠቃላይ የተጠያቅነት መጠን_____ይሆናል፡፡
አው.ሁ. 47.1	አደጋዎች እና የመድን ሽፋን እንደሚከተለው ይሆናሉ፡- ሀ. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ በአማካሪ ወይም ሰራተኞቹ ስለሚነዱ ተሸከርካሪዎች ወይም ንዑስ አማካሪዎቹ ወይም ሰራተኞቹ የ3ኛ ወገን ተሸከርካሪ ሞተር የጉዳት ካሣ የመድን ዋስትና ተጠያቂነት ዝቅተኛ ሽፋን መጠን:- _____ ለ. የ3ኛ ወገን የመድን ዋስትና ዝቅተኛው የሽፋን መጠን፡- _____ ሐ. የሙያ የመድን ዋስትና ዝቅተኛ የተጠያቂነት የሽፋን መጠን _____ መ. የአማካሪው ሠራተኞች ወይም ማናቸውም ንዑስ አማካሪዎች በተመለከተ የአሰሪው ተጠያቂነት እና የሠራተኞቹ የጉዳት ካሣ መድን እንዲሁም አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት እነዚህን ሰራተኞች በተመለከተ የሕይወት፣የጤና፣ የአደጋ፣ የጉዞ ወይም እንደየአስፈላጊነቱ ሌሎች የመድን ዋስተናዎች እና ሠ. በሚከተሉት ላይ ለሚደርስ ጥፋት ወይም ውድመት የመድን ሽፋን፤ ይህም (i) በሙሉ ወይም በከፊል በዚህ ውል በተመደበ ገንዘብ የተገዙ እቃዎች (ii) አገልግሎቶቹን ለመስጠት አማካሪው ጥቅም ላይ ያዋላቸው ንብረቶች እና (iii) ለአገልግሎቱ አፈፃፀም አማካሪው ያዘጋጃቸው ማናቸውም ሰነዶች
አ.ው.ሁ. 49.2	የሰነዶች የወደፊት አጠቃቀም እንደሚከተለው ተገድቧል፡-የሰነዶች አጠቃቀም በሁለቱም ወገኖች ስምምነት መሰረት ይሆናል። ፈፃሚው መ/ቤትም ሆነ አማካሪው የአንዱን ወገን የቅድሚያ ስምምነት ሳያገኝ ሰነዱን ወይም ሶፍት ዌርን ከዚሁ ጋር ላልተያያዘ ጉዳይ መጠቀም አይችሉም።
አ.ው.ሁ. 54.1	የውል ማስከበሪያ ዋስትና መጠን _____ነው፡፡
አ.ው.ሁ. 54.3	ተቀባይነት ያላቸው የውል ማስከበሪያ ዋስትና አይነቶች _____ናቸው፡፡ የውጭ ምንዛሪ አይነት _____ይሆናል፡፡
አ.ው.ሁ. 54.4	የውል ማስከበሪያ ዋስትና የሚለቀቀው _____ይሆናሉ፡፡
ረ. ውል አፈፃፀም	

ክፍል 9: የውል ቅጾች

ማውጫ

ሀ. የውል ስምምነት.....1

1. ስምምነት.....1
2. የውሉ ስምምነት ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን.....2

ለ. አባሪዎች.....3

1. አባሪ ሀ - የአገልግሎት ዝርዝር (መግለጫ).....3
2. አባሪ ለ - የሪፖርት አደራረግ መስፈርቶች.....3
3. አባሪ ሐ - ቁልፍ ሰራተኞች እና ንዑስ አማካሪዎች.....3
4. አባሪ መ - የውል ዋጋ ዝርዝር/ የወጪ ግምት.....3
5. አባሪ ሠ - የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተግባራት.....3

ሐ የውል ማስከበሪያ ዋስትና.....4

መ. የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና.....5

ሀ. ለ_____ግዥ የተደረገ የውል ስምምነት

የግዥ መለያ ቁ፡

ይህ የውል ስምምነት በዛሬው ቀን / ወር _____ዓ. ም. በአንድ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት _____ዋና የስራ ቦታው_____ (ከዚህ በኋላ ‹‹ግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ›› እየተባለ የሚጠራው)

እና

በሌላ በኩል በ_____በ_____ህግ የተቋቋመው እንዲሁም ዋና የስራ ቦታው የሆነው (ከዚህ በኋላ “አማካሪ” ተብሎ የሚጠራው) መካከል ተፈርሟል፡፡

ሀ. ግዢ ፈፃሚው ለአንድ ለተወሰነ የምክር አገልግሎት ጨረታ በማውጣቱ (ከዚህ በኋላ “የምክር አገልግሎት” ተብሎ የሚጠራው) ይህንን ተከትሎ የምክር አገልግሎቱን የሚሰጡ ተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያ ሀሳብ የውሉ ዋጋ (ከዚህ በኋላ "የውል ዋጋ" ተብሎ የሚጠራው) ከዚህ በተገለፁት ሁኔታዎች መሠረት ስለተቀበለ፤

ለ. አማካሪው በጨረታው የውል ግዴታ መሠረት የምክር አገልግሎት ለመስጠት ተፈላጊ ክህሎት፣ ሰራተኞች እና የቴክኒክ ሀብት እንዳለው፤ እንዲሁም ስራዎቹን በተፈለገው መልኩ ማከናወን የሚያስችል የቴክኒክ ብቃት እንዳለው ለግዥ ፈፃሚ መ/ቤት በማረጋገጡ፤

1. **በሁለቱ ወገኖች መካከል የሚከተለው ስምምነት ተደርሷል፡-**
   ስምምነት

1.1 **በዚህ ስምምነት የተጠቀሱት ቃላት እና አገላለፆች በተጠቀሱት የውል ሁኔታዎች ውስጥ በቅደም ተከተል የተሰጣቸው ተመሳሳይ ትርጓሜ ይኖራቸዋል፡፡**

1.2 **የሚከተሉት ሰነዶች በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት እና በአማካሪው መካከል በተደረገው የውል ስምምነት ውስጥ የተካተቱና የውሉ መ/ቤት ሆነው የሚነበቡ/የሚቆጠሩ ናቸው፡፡**

1. **ይህ ውል ስምምነት እና ሁሉም አባሪዎች**
2. **ልዩ የውል ሁኔታዎች**
3. **አጠቃላይ የውል ሁኔታዎች**

1.3 **ይህ ውል በሁሉም የውል ሰነዶች ላይ የበላይነት ይኖረዋል፡፡ በውል ሰነዶቹ መካከል አለመግባባት ወይም ግጭት ከተነሳ ሰነዶቹ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ቅደም ተከተል መሠረት የበላይነት ይኖራቸዋል፡፡**

1.4 **በግዥ ፈፃሚው ለአማካሪው የሚፈፀምን ክፍያ ታሳቢ በማድረግ አማካሪው ለግዥ ፈፃሚው የምክር አገልግሎት ለመስጠት፤ እንዲሁም ችግሮች ሲያጋጥሙ በውሉ ድንጋጌዎች መሠረት ተገቢውን ማስተካከያ ለማድረግ ቃል ገብቷል፡፡**

1.5 አማካሪው ለሚሰጣቸው የምክር አገልግሎቶች እንዲሁም ለሚታዩ ጉድለቶች የሚደረግ ማስተካከያን ጨምሮ ግዥ ፈፃሚው የውሉን ዋጋ በውሉ ሁኔታ በተጠቀሱት ደንቦች እና የጊዜ ሰሌዳ ለአማካሪው ክፍያ ለመፈፀም ተስማምቷል፡፡

የውሉ ስምምነት ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን

1.6 ይህ ውል ግዥ ፈፃሚው ለአማካሪው አገልግሎቶቹን እንዲጀምር ትዕዛዝ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ይህ ማስታወቂያ በውሉ ልዩ ሁኔታዎች የተዘረዘሩ ሁኔታዎች ተፈፃሚ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

1.7 በማንኛውም ሁኔታ ውል ስምምነቱ ከመፈረሙ በፊት ተግባራዊ አይሆንም፡፡

1.8 ለማስረጃነት ይሆን ዘንድ ተዋዋይ ወገኖቹ ይህንን ውል በእያንዳንዱ ስማቸው ስር ከዚህ ከላይ በመጀመሪያው ገፅ ላይ በተጠቀሰው ቀን እና ሀላፊነት ፊርማቸውን ከዚህ በታች አስቀምጠዋል፡፡

ስለ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት	ስለ አማካሪው
ፊርማ _____	ፊርማ_____
ስም _____	ስም _____
የስራ ኃላፊነት _____	የስራ ኃላፊት _____
ቀን _____	ቀን _____

ምስክሮች

ከግዥ ፈፃሚው በኩል	ከአማካሪው በኩል
ፊርማ _____	ፊርማ _____
ስም _____	ስም _____
የስራ ኃላፊት _____	የስራ ኃላፊት _____
ቀን _____	ቀን _____

ለ. አባሪዎች

አባሪ ሀ - የአገልግሎት ዝርዝር (መግለጫ) (ይህ ክፍል በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ና በአማካሪው በቴክኒክ ድርድር ጊዜ የተቀረፁ የመጨረሻ የስምምነት ውሎች የተለያዩ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስፈልገው ጊዜ ስራው የሚከናወንበት ቦታ በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የሚፀድቁ ያጠቃልላል፡፡)

አባሪ ለ - የሪፖርት አደራረግ መስፈርቶች (የሪፖርቱ ቅርፅ፣ ብዛት፣ ይዘት፣ ሪፖርቱን የሚቀበሉ ግለሰቦች የሚቀርብላቸው ቀናቶች ዝርዝር)

አባሪ ሐ - ቁልፍ ሰራተኞች እና ንዑስ አማካሪዎች

ሐ-1	(በኢትዮጵያ ተመድበው የሚሰሩ የውጭ ሀገር ሰራተኞች የስራ ዝርዝርና ዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ ይግባ)
ሐ-2	(በ ሐ-1 እንደሰፈረው ለሀገር ውስጥ ሰራተኞም ይግባ)
ሐ-3	(በ ሐ-1 እንደሰፈረው ከኢትዮጵያ ውጭ በስራው ለሚሳተፉ ሰራተኞ ይግባ)
ሐ-4	ተቀባይ ያገኙ፣ ንዑስ አማካሪዎች ዝርዝ መረጃው እንደሁኔታው በ ሐ-1፣ በ ሐ-2 ወይም በሐ-3 መሠረት መሰጠት አለበት፡፡

(ለቁልፍ ሠራተኞች የስራ ሰዓት ብዛት ወደ ኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጪ የሚደረግ ጉዞ ወቅት (ለውጭ ሀገር ሠራተኞች) እና ጥቅማጥቅሞች ይዘርዘር)

አባሪ. መ

የውል ዋጋ ዝርዝር/ የወጪ ግምት (አጠቃላይ ድምር ውሎች በተመለከተ የክፍያ ደረጃዎች የሚተኩ ወጪዎች ዝርዝር አስቀምጥ)

አባሪ ሠ

የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ተግባራት

ሠ-1	በግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ለአማካሪው መቅረብ ያለባቸው አገልግሎቶች፣ መገልገያዎች እና ንብረቶች
ሠ-2	በግዥ ፈፃሚው ለአማካሪው መቅረብ ያለባቸው አቻ ሙያተኛ እና አጋዥ ሰራተኞች

ሐ. የውል ማስከበሪያ ዋስትና

(የባንክ ዋስትና)

ቀን:- [ጨረታው የቀረበበት ቀን (ቀን፣ወር እና አመተ ምህረት)ይግባ]
የግዥ መለያ ቁጥር:- [የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]

ለ:- [የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ሙሉ ስም ይግባ]

የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ (ከዘህ በኋላ "አማካሪ" እየተባለ የሚጠራ) በቀን___ ወር__ ዓ.ም.___ በተፈረመው ውል ቁጥር ___ (ካሁን በኋላ "ውል" እየተባለ የሚጠራው) መሠረት የአገልግሎቶች ዝርዝር ይገለጽ ለማቅረብ ግዴታ የገቡ ሲሆን፣

በተጠቀሰው ውል ውስጥ እርስዎ አማካሪው ለገቡበት የውል ግዴታ ይሆንዎ ዘንድ የዋስትና አይነት ይገለጽ ከታወቀ ዋስትና ሰጭ መጠኑ ለተጠቀሰው ገንዘብ የውል ማስከበሪያ ዋስትና እንዲያቀርቡ አጥብቀው የጠየቁ ስለሆነ፡፡

እኛ ከዘህ በታች ፊርማችንን ያኖርንና ህጋዊ አድራሻችን የዋሱ ሙሉ ስም ይግባ ሕጋዊ የመኖሪያ አድራሻው (ሙሉ የዋሱ አድራሻ ይግባ)፣ የሆንን (ካሁን በኋላ "ዋስ" እየተባለን የምንጠራው) ለአማካሪው ዋስትና ለመስጠት የተስማማን ስለሆነ፣

ስለዚህ እኛ አማካሪውን በመወከል እስከ የዋስትናው የገንዘብ ዓይነትና መጠኑ በአሀዝ እና በፊደል ይግባ ለሚደርስ ዋስትና ተጠያቂ መሆናችንንና አማካሪው ውሉን መጣሱን በመግለጽ የክፍያ ጥያቄ በጽሑፍ እንደቀረበልን ያላንዳች ማስረጃና ክርክር ክፍያ ለተጠየቀበት ምክንያት እስከ የዋስትናው መጠን በአሀዝና በፊደል ይግባ የሚደርስ ለመክፈል ግዴታ እንገባለን፡፡

ይህ ዋስትና የሚፀናው እስከ ቀን___ ወር___ ዓ.ም___ ድረስ ይሆናል፡፡

ይህ ዋስትና በዓለም አቀፍ የንግድ ምክር ቤት እትም ቁ. 458 መሰረት ለደንበኞች በጥያቄ የሚሰጥ አንድ ዓይነት ዋስትና ነው፡፡

ስም፡- [ዋስትናው የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስም ይግባ]
ኃላፊነት፡- [ዋስትናው የሚፈርመው ሰው ኃላፊነት ይግባ]
ፊርማ፡- [እላይ የተጠቀሰው ሀላፊነትና ስም ያለው ሰው ፊርማ ይግባ]
ዋስትናው ለመፈረም ሙሉ ውክልና የተሰጠው መ/ቤት [የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ]
ቀን:ፊርማው የተፈረመበት [ቀን ይግባ] [ወር ይግባ] [አ.ም. ይግባ]

መ. የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና
(የባንክ ዋስትና)

ቀን:- [ጨረታው የቀረበበት ቀን (ቀን፣ወር እና አመተ ምህረት)ይግባ]
የግዥ መለያ ቁጥር:- [የግዥ መለያ ቁጥር ይግባ]

ለ:- [የግዥ ፈፃሚ መ/ቤት ሙሉ ስም ይግባ]

በዚህ ውል ውስጥ በተጠቀሰው የአከፋፈል ድንጋጌ መሠረት ቅድሚያ ክፍያን በተመለከተ የአማካሪው ሙሉ ስም ይግባ (ካሁን በኋላ "አማካሪ" ተብሎ የሚጠራው) በውሉ አንቀጽ የተጣለበትን ግዴታ በአግባቡና በሃቀኝነት ለመፈጸም ግምቱ የዋስትናው ገንዘብ ዓይነትና መጠን በፊደልና በአሃዝ ይግባ የሆነ የዋስትናው ዓይነት ይግባ ከግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ዘንድ ማስቀመጥ አለበት፡፡

እኛ ፊርማችን ከታች የሚታየውና ሕጋዊ አድራሻችን የዋሱ ሙሉ አድራሻ ይግባ የሆነው የዋሱ የተሟላ ስም ይግባ (ካሁን በኋላ "ዋስ" እየተባለን የምንጠራው) አማካሪው እንዳዘዘን ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታና ቃላችንን ባለማጠፍ ተራ ዋስ ሳንሆን በማይሻር ዋስትና እንደ መጀመሪያ ተገዳጅ ገዥው በመጀመሪያ እንደጠየቀን ያለምንም ተቃውሞና ክርክር አማካሪው ሳይጠየቅ እስከ የዋስትናው ገንዘብ ዓይነትና መጠን በፊደልና በአሃዝ ይግባ የሚደርስ ለመክፈል ተስማምተናል፡፡

ይህ ዋስትና የሚጸናው በውሉ መሠረት የቅድሚያ ክፍያ ለአማካሪው ከተፈጸመበት እለት ጀምሮ እስከ ቀን___ ወር_____ ዓ.ም_____ነው፡፡

ስም፡- [ዋስትናው የሚፈርመው ሰው ሙሉ ስም ይግባ]

ኃላፊነት፡- [ዋስትናው የሚፈርመው ሰው ኃላፊነት ይግባ]

ፊርማ፡- [እላይ የተጠቀሰው ሀላፊነትና ስም ያለው ሰው ፊርማ ይግባ]
ጨረታው ለመፈረም ሙሉ ውክልና የተሰጠው መ/ቤት [የተጫራቹ ሙሉ ስም ይግባ]

ቀን: [ቀን ይግባ] [ወር ይግባ] [ፊርማው የተፈረመበት አመተ ምህረትይግባ]